

# ራስን ማግኘት

## ኦሾ

ትርጉም:- ዘላለም ንጉሴ

አሾ

# ራስን ማግኘት

# Creativity:

## Unleashing the forces within

# ማውጫ


አርዕስት ገጽ

መቅድም 5

የነጻነት መዓዛ

ሸራው ሲወጠር 7

ሶስቱ መርሆች

በተግባር ላይ ተዝናኑ

ከተፈጥሮ ጋር ተስማምተህ ተራመድ

አምስቱ መሰናክሎች 39

ግለ ንቅ-ሕሊናዊነት

ፍፁማዊነት

ሕሊና

እምነት

የዝና ገበጣ



ፎርቱና ዲጂታል ስቱዲዮ
Fortuna Digital Studio

አራቱ ቁልፎች 93

ዳግመኛ ሕጻን ሆንኩኝ

ለመማር ዝግጁ ሁን

ኒርቫናን በተራ ነገር ውስጥ አግኙ

ሕልመኞች ሁኑ

አራቱ ጥያቄዎች 106

ትውስታና ዐይነ ሕሊና

የማጠናቀቅ ድብርት

የገንዘብ ጥበብ

ፍጥረት 129

የፈጠራዎች ሁሉ ራስ-የሕይወት ትርጉም

# መቅድም

## የነፃነት መዓዛ

ፈጠራ በፍጥረት ሁሉ ተወዳዳሪ የሌለው አማፂ ነው፡፡ መፍጠር ከፈለግን፣ ማንነትን የመቅረፅ ኃይል ያላቸውን ነገሮች ሁሉ ማስወገድ አለብን፡፡ ይህ ካልሆነ፣ ፈጠራችን የሌሎችን ሥራ በቀጥታ ከመገልበጥ የተለየ ዐይነት ባህሪይ አይኖረውም፡፡ ፈጠራ ሊታደለን የሚችለው የራሳችን የሆነ ማንነት ሲኖረን ነው፣ የአጀቡ አንድ አካል ሆነን መፍጠር አንችልም፡፡ የአጀቡ ሥነ-ልቦና ፈጠራ አልታደለውም፣ የሚኖረው ወደኋላ ጎታች ሕይወት ነው፡፡ መቃኘት፣ መዘመር፣ ማሽብሸብ፣ መደሰት አያውቅም፤ ሕይወቱ አሰልቺ ነው፡፡

ፈጣሪ ሩፃ የበዛበትን መንገድ መከተል አይችልም፡፡ የራሱን መንገድ ፈልጎ ማግኘት በሕይወት ጥቅጥቅ ዱር ውስጥ በጥያቄ አሰሳ ማድረግ አለበት፡፡ ፈጣሪ መራመድ ያለበት ብቻውን ነው፡ ከአጀቡ አእምሮ እና ከወሉ ሥነ-ልቦና መገንጠል ይኖርበታል፡፡ በዓለም ላይ ዝቃጭ አስተሳሰብ ያነገበው ወይንም ከአእምሮ ዘገምተኞች እንኳን ከዚህ እንኳን ከዚህ የአጀብ ዘገምተኝነት በላይ ናቸው፡፡ አጀቡ ግን የራሱ የሆኑ መደለያዎች አሉት፣ ሰዎች የዚህን የአጀብ አእምሮ አካሄድ እንደብቸኛው ትክክለኛ መንገድ ቆጥረው ሲከተሉትና ሲደግፉት፣ ክብርንና ሞገስን ይሰጣቸዋል፡፡

ባለፉት ዘመናት በየትኛውም ዘርፍ ላይ ተሰማርተው የነበሩ የፈጠራ ማንነቶች፣ ማለትም፣ ሰዓሊያን፣ አሽብሻቢያን፣ አቀንቃኞች፣ ገጣሚዎች እና ቀራፂዎች፣ የመከበርን ፀጋ ለመጎናጸፍ ያደረሳቸው፣ የዚህ ክህደት አስፈላጊነት ብቻ ነበር፡፡ የተንጎላቆለ የዝቅጠት ሕይወት የመኖር ግዴታ ነበረባቸው፣ በፈጠራ ክህሎት ለመታደልና ለመቀደስ ያላቸው ብቸኛ አማራጭ ይህ ብቻ ነበር፡፡ በመጪው ጊዜ ይህ ሊቀጥል አይገባውም፡፡ ከተረዳችሁኝ እና፣ እየተናገርኩት ያለሁት ነገር እውነት

ማዘሉ ከተሰማችሁ፣ በመጪው ዘመን የሰው ፍጡር ሁሉ የራሱን ልዩ ሕይወት ለየግሉ የሚኖር ከሆነ፣ የተናቁ ሕይወትን የመግፋት አስፈላጊነት መቅረቱ ሊታያችሁ ይገባል፡፡ ይህ የወረደና የተናቀ ሕይወት፣ በስምምነት እውነት የተደረገ፣ የተከበረ ኑሮን ግትር እና ቀጥተኛ በሆነ መልኩ ከመደገፍ የመጣ ውጤት ነው፡፡

ጥረቱ የአጀቡን አስተሳሰብ መደምሰስና እያንዳንዱ ግለሰብ ራሱን ወይም ራሷን እንዲሆን / እንድትሆን ነፃ ለማድረግ ወይም አርነት ለማውጣት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ምንም ችግር አይኖርም፣ እናንተም ሕይወታችሁን ልክ ልትኖሩት እንደምትፈልጉት አድርጋችሁ መኖር ትችላላችሁ የሰው ልጅ በእውነተኛ ማንነቱ ሊወለድ የሚችለውና የሚወለደው ሁሉም ሰው በአመፃው በሚከበርበት ወቅት ብቻ ነው፡፡ የሰው ልጅ እስከ አሁን ገና አልተወለደም፡፡ አሁንም ማህፀን ውስጥ ነው፡፡ አሁን በሰብዓዊ ፍጡርነት ስም የምትመለከቱት ባህሪው ሁሉ ትርኪ- ምርኪነቱ የበዛ ማንነቱ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ግለሰብ ፍፁም ነፃነት ሰጥተን በራሱ መንገድ እንዲኖር ካልፈቀድን በስተቀር ይህ ትርኪ-ምርኪነት ማንነቱ ይቀጥላል፡፡ እርግጥ በተሰጠው ነፃነት የሌሎች ግለሰቦች ነፃነትን መጣስ የለበትም፡፡ የነፃነት አንዱ ክፍል ይህ ነው፡፡ ማንም በሌላው ሕይወት ጣልቃ የመግባት መብት አይኖረውም፡፡

ባለፉት ጊዜያት ሰዎች ምንም በማይመለከታቸው የሌሎች ሰው ሕይወት ውስጥ ጣልቃ እየገቡ ኖረዋል፡፡ ጭራሹኑ ከማህበረሰብ ጋር ምንም ትስስር በሌላቸው የግል ጉዳዮች ውስጥ ሳይቀር ጥልቅ ይላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት ጋር ፍቅር ይይዘዋል፡፡ ታዲያ ይህ ከማህበረሰብ ጋር ምን አገናኘው? ሙሉ ለሙሉ የግል የሚባል እንጂ የአደባባይ ጉዳይ አይደለም፡፡ ግን ማህበረሰቡ የራሱን ዘልማዳዊ እምነቶች እያጣቀሰ በቀጥታና በተዘዋዋሪ በፍቅረኞቹ መሀል ጣልቃ ይገባል፡፡ ሕግ አስከባሪው፣ ዳኛው ወ.ዘ.ተ በፍቅረኞቹ መሀል ጣልቃ ይገባሉ፡፡ ይህም አልበቃ ብሉ፣ ማህበረሰቦች እግዚአብሔር የሚባል ቀጪ ሕግ አስከባሪ ፈጥረው ጣልቃ እንዲገባ ያደርጋሉ፡፡

## ሽራው ሲጠጠር

ከበሽታው በዳነ ጊዜ ሰው ሁሉ ፈጣሪ ይሆናል። የጥፋት ባለሟሎች ሁሉ የጤና ችግር አለባቸው። ጤናሞች የፈጠራ ክህሎት አላቸው። ጥልቅ ግንዛቤን ማግኘት ያለበትም ይኸው ነው። ፈጠራ ከእውነተኛ ጤንነት የሚነሳ ጥሁም መዓዛ ነው። አንድ ሰው በእውነት ጤናማና ምሉዕ ሲሆን፣ ፈጠራ ያለምንም ጥረት ወደእሱ ትመጣለች፣ የፈጠራ ኃይልም ይቀሰቀሳል።

## ሦስቱ መርሆች

አሁን የሰው ልጅ መንታ መንገድ ላይ ደርሷል። እስከ አሁን፣ ባለ አንድ አውታራዊውን ሰው ሕይወት ስንኖር ቆይተን፣ ይህን የሕይወት ዘዬ አሰልችተነዋል። እንደማያዋጣም ተገንዝበናል። አሁን የሚያስፈልገን ከቀድሞው ይልቅ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ያለው ባለ ሦስት አውታራዊ ሰው ነው። እነዚህ ሦስት እውነታዎች ንቃተ-ሕሊና፣ ርህራሄና፣ ፈጠራ ናቸው።

ንቃተ-ሕሊና ህላዌ ነው፣ ርህራሄ ስሜት ነው፣ ፈጠራ ደግሞ የምንወስደው ርምጃ ወይም ተግባር ነው። አዲሱ የሰው ልጅ በተመሳሳይ ጊዜ ሦስቱንም የያዘ ነው፣ የሚል ራዕይ አለኝ። ከፈተናዎች ሁሉ የላቀ ፈተናን፣ ከተግባራት ሁሉ የከበደ ተግባርን እያቀረብኩላችሁ ነው። የቡድሀን ያህል እርምሞ፣ የክሪሽናን ያህል ፍቅር እና የሚኬያኤል አንጀሎን ያህል የፈጠራ ክህሎት ሊኖራችሁ ይገባል። በአንድ ጊዜ ሦስቱንም ሆናችሁ መገኘት ይኖርባችኋል። ምልዓት የሚኖራችሁ ያን ጊዜ ብቻ ነው። ካለዚያ ግን ከውስጣችሁ አንድ የሚጐድል ነገር ይኖራል። ይህ የሚጐድላችሁ ነገር ደግሞ እርካታን ያሳጣችኋል፣ ባዶነትን ሕይወት ያደርግባችኋል። አንድ አውታራዊ ብትሆኑ፣ የተወሰነ የከፍታ ጣሪያ ላይ መድረስ ትችሉ ይሆናል። ከዚህ ሌላ ግን ምንም አትሆኑምም፣ አታገኙምም። እኔ ግን አንድ ከፍታ እንዳለው አንድ ተራራ ብቻ ሳይሆን የብዙ ከፍታዎች ባለቤት እንደሆኑት እንደነሰንሰለታማዎቹ የሒማሊ ተራሮች እንድትሆኑ እሻለሁ።

ባለ አንድ አውታሩ የሰው ልጅ አልተሳካለትም። ውብ ምድርን መፍጠር አልቻለም። ምድረ - ገነትን መፍጠር አልተሳካለትም። በጭራሽ አልሆነለትም! የተወሰኑ ጥቂት ውብ ሰዎች ቢፈጥርም የሰው ልጅ ሙሉ በሙሉ መለወጥ አልቻለም። የሰብዓዊ ፍጡርን ሁሉ ንቃተ ሕሊና መለወጥ አልቻለም። ንዑዶትን (enlightenment) ያገኙ ጥቂት ብቻ ናቸው። ይህ ደግሞ ከአሁን በኋላ ጥቅም የለውም። ንዑዳን ሰብዓዊ ፍጡራን በበለጠ መጠን ያስፈልጉናል። ንዑድነታቸውም ሦስት አውታራዊ ሊሆን ይገባል።

ለእኔ አዲሱ ሰው ማለት ይህ ነው።

ቡድሀ ባለቅኔ አልነበረም፣ አዲስ ሰው እንጂ። አሁን የቡድሀነትን ማዕረግ የሚያገኙት ግን ባለቅኔዎች ይሆናሉ። ‹‹ባለቅኔዎች›› ስል፣ መቀኘት ወይንም መግጠም አለብህ ማለቴ ሳይሆን፣ ቅኔያዊ መሆን አለብህ ማለቴ ነው። ሕይወትህ እና ለማንኛውም ነገር የሚኖርህ እይታ ወይም አቀራረብ ቅኔያዊ መሆን አለበት።

ምክንያት (logic) ደረቅ ነው፣ ቅኔ ህያው ነው። ሎጂክ መደነስ ወይም መጨፈር አይችልም፣ ሎጂክ ጨፈረ ወይም ሎጂክ ሲደንስ አየነው ማለት ማህተመ ጋንዲ ሲጨፍሩ አየናቸው እንደማለት ይሆናል። የማይሆንና የማይታሰብ ነገር ነው። ቅኔ መደነስ ይችላል፣ ቅኔ የብልህ ጭፈራ ነው። ምክንያት ወይንም ሎጂክ ማፍቀር አይችልም። ስለ ፍቅር መናገር ይችላል፤ ግን ማፍቀር አይችልም፣ ፍቅር ምክንያታዊ ይመስላል። ማፍቀር የሚችለው ቅኔ ብቻ ነው፣ ግራ ወደሚያጋባው ፍቅር የተባለ ነገር ውስጥ የሚዘልና የሚገባው ቅኔ ብቻ ነው።

ምክንያታዊነት ቀዝቃዛ፣ በጣም ቀዝቃዛ ነው የመልካምነቱ መጨረሻ ማቲማቲክስ ላይ ይፈፀማል እንጂ፣ ሰብዓዊነት ደረጃ ድረስ መዝለቅ አይችልም። ሰብዓዊነት ምክንያታዊነትን ቢያበዛ መጨረሻው መጥፋት ይሆናል። ያን ጊዜ ሰብዓዊ ፍጡራኖች ሳይሆኑ ሕልውና የሚኖራቸው ቁጥሮች ብቻ ይሆናሉ። በሌሎች ቁጥሮች መተካት የሚችሉ ቁጥሮች ብቻ ይቀራሉ።

ቅኔ፣ ፍቅር፣ እና ስሜት ጥልቀትን እና ግለትን ያጎናጽፉናል። በበለጠ እየቀለጥን፣ እንደሚቀልጥ ብረት ቅዝቃዜያችንን እንጥላለን። በበለጠ ሰብዓዊ እየሆንን እንሄዳለን። ቡድሀ ልዩ-ሰው (superhuman) ለመሆኑ አያጠያይቅም፣ ቡድሀ ግን ከሰብዓዊነት አውታር ወጥቷል። ምድራዊ አልነበረም። በኢምድራዊ ሕላዌ ውበት ነበረው፣ ግን ግሪካዊው ዞርባ የነበረው ዐይነት ውበት የለውም። ዞርባ ዓላማዊ ነበር። እኔ ሁለቱንም - ዞርባንና ቡድሃን እንዲትሆኑ እሻለሁ። ቡድሃው ዞርባ። ሰው አርምሞአዊ ግን በስሜት የተሞላና በተትረፈረፈ ፍቅር የታደለ መሆን አለበት። በተጨማሪ ደግሞ ፈጣሪ መሆን አለበት። ፍቅራችን ግን በተግባር ያልታጀበ ስሜት ብቻ ከሆነ ሌላው የሰብዓዊ ፍጡር ላይ ተፅእኖ አይኖረውም። እውን ልናደርገው እና ወደ ተጨባጭ ነገር ልንለውጠው ይገባል።

ሦስቱ አውታሮች እነዚህ ናቸው፣ ሕላዌ፣ ስሜት እና ተግባር። ተግባር ፈጠራን አቅፎ ይዟል፤ ሙዚቃ፣ ቅኔ፣ ስዕል፣ ቀረፃ፣ ሥነ-ሕንፃ፣ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ በቃ ሁሉንም ዐይነት ፈጠራ። ስሜት ማራኪነት ያላቸውን ሁሉ አቅፎ ይዟል። ፍቅር እና ውበት በስሜት አውታር ውስጥ ናቸው። ሕላዌ ደግሞ ምስጠትን (አርምሞን)፣ ንቀተ-ሕሊናን ያካትታል።

## በተግባር ላይ ተዝናና

በመጀመሪያ የክንዋኔ (activity) ተፈጥሮንና ድብቅ ሞገዶቹን መረዳት አለብን። ካለዚያ ዘና ማለት አይቻልም። ዘና ማለት ብንፈልግ እንኳን የክንዋኔያችንን ተፈጥሮ እስተውለን እስካልተረዳነው ድረስ ዘና ማለት አንችልም። ምክንያቱም ክንዋኔ ቀላል ክስተት አይደለም። ብዙ ሰዎች ዘና ማለት ይፈልጉና ያቅታቸዋል። መዝናናት በራሱ የሚያብብ እንጂ በግድ ልናመጣው የምንችለው ነገር አይደለም። ክስተቱን ሙሉ በሙሉ መረዳት ይጠበቅብናል። ለምን ሕይወትህ በክንዋኔዎች እንደተሞላች፣ ለምን አርፈህ መቀመጥ እንደማትችል፣ ለምን የክንዋኔዎች ባሪያ እንደሆንክ መረዳት አለብህ።

ሁለት ቃላቶችን አስታውስ፦ የመጀመሪያው ተግባር (action) ሲሆን ሌላው ክንውን ነው። ተግባር ክንውን አይደለም፣ ክንውንም ተግባር አይደለም። ተፈጥሮዎቻቸው እጅግ ተጻራሪ ናቸው። ተግባር፣ በአንድ ሁኔታ ግፊት ወይንም ስለሚጠበቅብን የምንወስደው ርምጃ ነው፣ ለሁኔታው ምላሽ እንሰጣለን። ክንዋኔ፣ ከሚፈጠረው ሁኔታ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፣ ምላሽ አይደለም። ከውስጣችን ቅብጥብጥነት የተነሳ፣ ሁኔታው ወይም ክስተቱ ክንዋኔ ውስጥ የመግቢያ ሰበብ እንጂ ሌላ ፋይዳ የለውም።

ተግባር ከስክነ ሕሊና ይመነጫል - በዓለም ላይ በውበት ወደር የለውም። ክንውን ግን የሚመነጨው ከቅብጥብጥ አእምሮ ነው - በዓለም አለ የተባለ አስቀያሚ ነገር ነው። ተግባር (ድርጊት) ምክንያት አለው ከክስተቱ ጋር ተዛማጅም ነው። ክንውን ግን ተዛማጅነት የለውም። ድርጊት በየቅፅበቱ በራሱ ጊዜ ተቀጣጣይ ሲሆን፣ ክንውን ግን ባለፈው ጊዜ ትውስታ የታጨቀ ነው። ለዚህች ለምንገኝባት ቅጽበት የምንሰጠው ምላሽ አይደለም። ካለፈው ጊዜ ይዘነው የመጣነውን ቅብጥብጥነት የምናስወጣበት ነው። ድርጊት የፈጠራ ድባብ አለው። ክንውን ግን አጥፊነቱ የበረታ ነው! ሌሎችን ያጠፋል። ሊያሳስት የሚችል ዐይነት ልዩነታቸውን ለማየት ሞክር። ለምሳ ይርበንና እንመገባለን፣ ይህ ድርጊት ነው። ግን ሳይርበን፣ ምንም ረሀብ

ላይስማን መብላት መቀጠል ሲሆን፣ ይህ ክንውን ነው። የመብላት ነገር ከተነሳ ሌላ ነገር ልናገር ይህ የመብላት ክንዋኔ እንደ ጭካኔ ተግባር ነው፤ ምግብን ጥርሳችሁ መሀከል በማስገባት ታወድመዋለህ፣ ይህም ቅብጥብጥነትህን በጥቂቱ ያረግብልሃል። የምትመገበው ስለራበህ ሳይሆን ውስጥህ ብላ ስለሚልህ ነው። ይህ ባህሪይ ከማጥፋት ከማውደምና ከጭካኔ መንፈስ ይመነጫል።

በእንስሳቱ ዓለም፣ የጭካኔ ተግባር ከአፍና ከእጆች ጋር እንዲሁም ከጥፍሮችና፣ ከጥርሶች ጋር ተዛማጅነቱ የጎላ ነው። በእነሱ ዓለም አውዳሚ የሚባሉት ጥርሶችና ጥፍሮች ናቸው። በምትመገብ ጊዜ ከምግቡ ጋር ቁርኝት ትፈጥራለህ። በእጅህ ምግቡን ትወስድና በአፍህ ታላምጠዋለህ። በዚህ ሁናቴም በውስጥህ የታመቀው ጭካኔ ይረግባል። ረሀብ ሳይፈጠር የምትበላ ከሆነ ግን መብላትህ ድርጊት ሳይሆን በሽታ ነው። ይህ ክንዋኔ የከፋ ሱስ ይሆናል። በእርግጥ በዚህ ሁኔታ እየበላህ መቀጠል አትችልም፣ ምክንያቱም መጨረሻ ላይ ቁንጣን ይገድልሃል። ስለዚህ ሰዎች ብዙ ምትክ-ስልቶችን ፈጥረዋል ትንባሆ፣ ጫት፣ ማስቲካ ያላምጣሉ። ሲጋራ ያጨሳሉ። እነዚህ ሐሰተኛ ምግቦች ናቸው። በውስጣቸው ምንም ገንቢ ንጥረነገር የላቸውም፣ ግን ጭካኔንና ውድመትን ለማስወገድና ለማስወጣት ጥሩ መሳሪያዎች ናቸው።

ተቀምጦ ማስቲካ የሚያላምጥ ሰው፣ ምን እያደረገ ነው? አንድ ሰው እየገደለ!? በአእምሮው የተሸሸገ የመግደልና የማጥፋት ፍላጎት አለ። ስለዚህ በራሱ ምንም ስህተት የማይባል ነገር ያደርጋል፣ ማስቲካ ያላምጣል። ሌላ ሰውን እየጎዳህ አይደለም፣ ተግባሩ ግን ለአንተ በጣም አደገኛ ነው። ምክንያቱም የምታደርገውን አውቀህ እያደረግከው አይደለም። ሲጋራ የሚያጤስ ሰው ምን እያደረገ ነው? በትክክል ምን እያደረገ እንዳለ ሳያውቅ፣ ግን ጢሱን እያስገባ ያስወጣል። ተግባሩ ከሐሰተኛ የእርምጃ ተግባር ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። መንፈሳዊ ሰው መቁጠሪያ ይዞ ዶቃዎቹን ተራ በተራ በተመሳሳይ መልኩ እንደሚዳስሳቸው ሁሉ፣ አጫሹም ጢሱን እንዲሁ እያስገባ መልሶ በማስወጣት፣ ተደጋጋሚ ግን ተመሳሳይ ተግባር ይፈጽማል።

በማጤሱ ቅኝታዊ ተደጋጋሚነት ያለውና በዚህም ምስጠት ውስጥ የሚያስገባውን ድርጊት ያከናውናል፣ ይህም የውስጡን ቅብጥብጥነት ያበርድለታል።

አንድ ትክክለኛነቱ የማያጠያይቅ እውነታ አለ፣ ከአንድ ሰው ጋር እየተነጋገራችሁ ሳለ፣ ይህ ሰው ድንገት ሲጋራ ፍለጋ ኪሶቹን መዳበስ ከጀመረ የዚህ ድርጊቱ ትርጓሜ፣ ደብሮታል። ስለዚህ አሁን ብትተወው ይሻላል የሚል ይሆናል። እንስቶ ወደ ውጪ ቢወረውራችሁ ደስ ይለው ነበር፤ ይህ ግን የጨዋ ደንብ አይሆንም። ስለዚህ ሲጋራ ለማጤስ በመፈለጉ እየነገራችሁ ያለው ነው፣ «አሁንስ በቃህ! ሰለቸኸኝ!» የሚል ይሆናል። የተፈጠረው ከእንስሳ ቢሆን ኖሮ ዘሎ ጉብ ይልብህ ነበር፣ ግን ሰው ነው። ስለዚህ ዘሎ ሲጋራው ላይ ጉብ ይልና ማጤስ ይጀምራል። አሁን ስለአንተ አይጨነቅም፣ ሲጋራውን እያነበነበ ነው። ማጤሱ እንደፀሎት ነው። ያፅናናዋል።

ይህ ክንዋኔ ግን፣ የጤና ያልሆነ ፍቅር እንደያዘው ያሳያል። ራሱን ሆኖ መቆየት አይችልም፣ በዝምታ መቆየት አይችልም፣ ምንም ነገር ሳያደርግ መቆየት አይችልም ማለት ነው። በክንዋኔ በመጠመድ የአእምሮ ጤና ማጣቱን እና ቀውሱን ከውስጡ እያወጣ ይጥላል።

ድርጊት ውብ ነው፣ ድርጊት በራሱ ጊዜ ተቀጣጥሎ የሚነድ ነው። ሕይወት ምላሽን ትሻለች፣ በእያንዳንዷ ቅፅበት ድርጊት ይጠበቅብሃል፣ ክንዋኔ ግን ያለህበትን ይህችን ቅፅበት ተመርኩዞ ይመጣል። ሲርብህ ትበላለህ፣ ሲጠማህ ውሀ ትፈልጋለህ፡ ፡ እንቅልፍህ ሲመጣ ትተኛለህ። ድርጊት ውስጥ የምትገባው ነባራዊ ሁኔታውን ተመርኩዘህ ነው። ድርጊት በራሱ ጊዜ የሚፈጠርና ምሉዕ ነው።

ክንዋኔ በራሱ ጊዜ የተቀጣጣይነት ባህሪይ የለውም። የሚመጣው ካለፈው ጊዜ እንስቶ ነው። ለብዙ ዓመታት ስታከማቸው ኖረህ ሊሆን ይችላል። አሁን ድንገት ይገነፍላል፣ ግን ከአሁኑ ጊዜ ጋር ምንም ዝምድና የለውም። ያ ቦታው የተፈጠረ ነገር ነው። አእምሮ ግን ብልጥ በመሆኑ የዚህን ድንገተኛ ክንዋኔ ክስተት

ምክንያታዊ ያደርገዋል፡፡ አእምሮ ዘወትርም ቢሆን ይህ ተግባርህ በዚህ ጊዜ አስፈላጊ የሆነ ድርጊት እንጂ ክንዋኔ ያለመሆኑን ለማረጋገጥ ይሞክራል፡፡ ለምሳሌ፡- ደርሰህ በንዴት ትንገበገባለህ፣ አጠገብህ ያሉ ሌሎች ሰዎች ሁሉ ንዴትህ እንዳልሆነ በቀላሉ ለማብራራትም ከሁኔታው ጋር ምንም ዝምድና እንደሌለው ይታወቃቸዋል፡፡ ሰዎች፣ ‹‹ምን እያደረገ ነው? ምን የሚያስቆጣ ነገር አለ? አላስፈላጊ ነበር፡፡›› የሚል ሐሳብ ይፈጠርባቸዋል፡፡ አንተ ግን ማመካኛዎች ትፈልግለታለህ፣ ለንዴትህ አስፈላጊነት ምክንያቶች ታመቻችለታለህ፡፡

እነዚህ ማመካኛዎችም እብደትህን ሳታውቀው ተደብቆህ እንዲኖር ለማድረግ ይረዱሃል፡፡ ጆጅ ጎርጂፍ ‹‹ማርገቢዎች›› በማለት የሚጠራቸው እነዚህ ነው፡፡ የአንድ ሁኔታ ምንነት በውል እንዳታገናዝብ በዙሪያህ የማመካኛ ማርገቢዎችን ትፈጥራለህ፡፡ ማርገቢዎች (Buffers) በሁለት የባቡር ፉርጎዎች መካከል የሚገኙና፣ ድንገተኛ ግጭት ቢፈጠር መንገደኖች ላይ ከባድ ነውጥ እንዳይነሳ የርግብግቢቱን ኃይል ውጠው የሚያስቀሩ ናቸው፡፡ ክንዋኔህ ከሁኔታው ጋር ምንም ግንኙነት ሳይኖረው ይቀጥላል፣ የማመካኛ ማርገቢዎች ደግሞ ሁኔታውን እንዳትመለከት ይጋርዱሀል፡፡ በአርጋቢዎቹ ታውረህ ክንዋኔዎችህን ትቀጥላለህ፡፡

ይህ ክንዋኔ እስካለ ድረስ ዘና ማለት አትችልም፡፡ እንዴት ልትዝናና ትችላለህ? ምክንያቱም ምንም ይሁን ምን አንድ ነገር ማድረግ አለብህ፡፡ በቀላሉ የማይጠፋ አመል ነው፡፡ በዓለም ላይ ‹‹ያለ ምንም ነገር ስራ ፈቶ ቁጭ ከማለት አንድ ነገር ማድረግ ይሻላል፡፡›› እያሉ የሚለፍፉ ብዙ ቂሎች አሉ፡፡ ‹‹ባዶ አእምሮ የዲያብሎስ ቤት ነው›› የሚል ተረት የተረቱም ብዙ ቂሎች በዓለም ዙሪያ ሞልተዋል፡፡ ተረቱ ስህተት ነው! ባዶ አእምሮ የአምላክ ቤት ነው፡፡ በዓለም ላይ ከባዶ አእምሮ የበለጠ ውብ ነገር የለም፣ በንጽህናው ወደር የለውም፡፡ ታዲያ እንዴት ባዶ አእምሮ የዲያብሎስ ቤት ይሆናል፡፡ ዲያብሎስ ባዶ አእምሮ ውስጥ በፍፁም መግባት አይችልም! ዲያብሎስ መግባት የሚችለው በክንዋኔ በተጠመደ አእምሮ ብቻ ነው፡፡ ያን ጊዜ ሊቆጣጠረንና በበለጠ ክንዋኔ የምንጠመድባቸውን መንገዶች እና ዘዴዎች

ሊያሳየን ይችላል፡ ዲያብሎስ ‹‹ተዝናና!›› የሚል ቃል አይወጣውም ‹‹እረፍ!›› አይልም፡፡ የሚለው ‹‹ለምን ጊዜህን ታባክናለህ? የሆነ ነገር አድርግ - ተንቀሳቀስ! ሕይወት እያለፈችህ ነው፡፡ አንድ ነገር አድርግ!›› የዚህች ዓለም ታላላቅ አስተማሪዎች ሁሉ የሕይወትህን እውነት የተገነዘቡ ሁሉ፣ ባዶ አእምሮ መለኮታዊው ወደ ውስጣችን እንዲገባ ቦታ እንደሚሰጠው ተረድተዋል፡፡

ዳያብሎስ በክንዋኔ እንጂ በባዶ አእምሮ መጠቀም አይችልም፡፡ እንዴት ሊጠቀምበት ይችላል? አጠገቡ ለመድረስም አይደፍርም፣ ምክንያቱም ባዶነት ይገድለዋል፡፡ ዳሩ ግን በሆነ ነገር የመጠመድና ክንዋኔ ውስጥ የመግባት ትልቅ ፍላጎት ጠፍሮ ከያዘህ ያን ጊዜ ዳያብሎስ ይቆጣጠርሀል፡፡ ያን ጊዜ እሱ አንተን መምራት ይጀምራል - ከእሱ ሌላም መሪ አይኖርህም፡፡

ይህ ተረት ስህተቱ እጅግ የጐላ ከመሆኑ የተነሳ ሐሳቡን ያመነጨው ራሱ ዳያብሎስ ሊሆን እንደሚችል ልነግራችሁ እወዳለሁ፡፡

ይህ በክንወኔ የመጠመድ ፍላጎት ልንጠነቀቀው የሚገባ ነገር ነው፡፡ በራሳችሁ ሕይወት ውስጥም ልታስተውሉት ይገባል፡፡ ምክንያቱም በራሳችሁ ላይ ተመልክታችሁት ግብ የለሽነቱና አላስፈላጊነቱ ካልተገለጠላችሁ በስተቀር የምናገረው ሁሉ እምብዛ ትርጉም አይኖረውም፡፡ ለምንድን ነው የምታደርጉት?

በጉዞ ላይ ስሆን ሰዎች ያለማቋረጥ አንድን ነገር በተደጋጋሚ ሲያደርጉት ተመልክቼአለሁ፡፡ ለሀያ አራት ሰዓታት ሙሉ፣ በአንድ የባቡር ፉርጎ ውስጥ ከአንድ መንገደኛ ጋር በጉዞ ያሳለፍኩበት ጊዜ ነበር፡፡ ሌላ የሚያደርገው ነገር በማጣቱ የያዘውን ጋዜጣ ራሱን እያደጋገመ መቶ ጊዜ ያነበዋል፡፡ ፉርጎው ውስጥ ተገዶ በመቀመጡ ሌላ የሚያደርገው ነገር ጨንቆታል፡፡ እኔ ደግሞ ይሄ ሰውዬ ምን እያደረገ ነው? እያልኩ እመለከተዋለሁ፡፡

ጋዜጣ መፅሐፍ ቅዱስ ወይም ቁራን አይደለም፡፡ ቅዱሳን መፅሐፍትን ደጋግሞ ማንበብ ይቻላል፣ ደግመን ባነበብነው ቁጥር ያላስተዋልነው አዲስ ሐሳብ

ልናገኝ እንችላለን። ጋዜጣ ግን ቅዱስ መፅሐፍ አይደለም። እንዴ ከተነበበ በኋላ አበቃለት። እንደውም አንድ ጊዜ እንኳን የመነበብ ዕድል ማግኘት ያልነበረበት ጽሁፍ ነበር፣ ሰዎች ግን እንደ ዳዊት ይደግሙታል። ምንድን ነው ችግሩ? አሳሰፈላጊ ነው? አይደለም - በቃ ተጠናውቷቸው ነው ዝም ብለው ያለ ሥራ መቀመጥ አይችሉም። ይህ ለእነሱ የማይቻልና ሞት የሚመስላቸው ነገር ነው። የሆነ ነገር ማድረግ አለባቸው።

ብዙ ዓመታትን በጉዞ ማሳለፌ፣ ሰዎችን እነሱ ሳያውቁ የምመለከትበት ዕድል ሰጥቶኛል። ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ በፋርጎው ውስጥ ከእኔ ሌላ አንድ ሰው ብቻ የሚኖርበት ጊዜ አለ። እንዳነጋግረው ብዙ ጥረቶችን ሲያደርግ ይቆያል፣ እኔ ደግሞ አዎ ወይም አይደለም እያልኩ አጭር ምላሽ እየሰጠሁ ዝም ስለው ሐሳቡን ይተውዋል። ከዚያ በቃ ትኩር ብዬ ማየት ነው። ያለ ምንም ወጪ የማደርገው አስደሳች ሙከራዬ ነው! እኔ አየዋለሁ፣ እሱ ሻንጣውን ይከፍታል - ምንም እንዳልፈለገ አውቃለሁ - ከዚያ ሻንጣውን ይበረብርና መልሶ ይዘጋዋል። ከዚያ ደሞ መስኮቱን ይከፍተዋል፣ መልሶ ይዘጋዋል። ከዚያ ወደ ጋዜጣው ይመለሳል፣ ከዚያ ደግሞ ያጤሳል፣ ከዚያ እንደገና ሻንጣውን ይከፍተዋል፣ በአዲስ መልክ ያስናዳዋል፣ ተነስቶ መስኮቱን ይከፍታል፣ ወደ ውጪ ይመለከታል። ምን እያደረገ ነው? ለምን? ከውስጡ የሚጎተጉተው ነገር አለ የሚቅበጠበጥ አእምሮው አንድ ነገር ማድረግ አለበት። ካለዚያ አለቀለት። ሕይወቱ በክንዋኔ የተሞላ በሥራ የተጠመደ ሰው ይሆናል፣ አሁን የሚያርፍበት፣ ዘና የሚልበት ቅፅበት አገኘ። ግን አልቻለም፣ የድሮ ልማዱ ተመልሶ መጣ።

የሞጋሁል ንጉሠ ነገስት የነበሩት አውራንግዜብ፣ ወላጅ አባታቸውን በዚያ ዕድሜያቸው ወህኒ-ቤት ማስራቸው ይነገራል። ታጅ መሀል የተባለውን አፀብ ድንቅ የተሰኘ ሕንፃ ለሚያፈቅሯትና በሞት ለተለየቻቸው ባለቤታቸው ማስታወሻነት የገነቡት እኒሁ የአውራንግዜብ አባት ሻን ጀሀን ነበሩ። ልጃቸው ግን ወህኒ-ቤት ከተቷቸው ከዙፋናቸውም አወረዷቸው። እንደሚባለውና በአውራንግዜብ ግለ-ሕይወት

ታሪክ ላይ ሰፍሮ እንደሚገኘው ከሆነ ከጥቂት ቀናት በኋላ ኻን ጁሀን በመታሰራቸው ይሰማቸው የነበረው ጭንቀት ጠፋ፡፡ ምክንያቱም የሚፈልጉት ነገር ሁሉ አጠገባቸው ነገር፡፡ ከአንድ ነገር በስተቀር፣ ይህ ምንም ነገር ማድረግ ያለመቻላቸው ነበር፡፡ እናም ልጃቸውን አውራንግዜብን እንዲህ ሲሉ ጠየቁት፣ ‹‹መልካም ነው፣ ሁሉን ነገር አዘጋጅተህልኛል፣ ምንም የጎደለ ነገር የለም፡፡ አንድ ነገር ብቻ ላስቸግርህ፣ ይህን ካደረግክ ዘወትር ሳመሰግንህ እኖራለሁ፣ ሰላሳ ታዳጊዎችን ላክልኝ፡፡ ላስተምራቸው እፈልጋለሁ፡

አውራንግዜብ ማመን አልቻለም፡፡ ‹‹አባቴ ለምን ሰላሳ ልጆች ማስተማር ፈለገ?›› ከዚህ በፊት አስተማሪ የመሆን ፍላጎት አሳይቶ አያውቅም፣ በየትኛውም ዐይነት ትምህርት ላይ አትኩሮት ኖሮትም አያውቅም፣ ምን ነካው? ብሎ ቢያስብም የፍላጎታቸውን አደረገላቸው፡፡ ለሻን ጁሀን ሰላሳ ታዳጊ ወንዶች ተላኩላቸው፣ ደግሞም ንጉሠ ነገስት ሆኑ፡፡ እስቲ ወደ አንድ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ጎራ በሉ፣ የአስተማሪ ማዕረግ ከንጉሠ ነገስትነት አይተናነስም፡፡ ተቀመጡ ብሎ ሲያዛቸው ይቀመጣሉ፣ ተነሱ ሲላቸው ተነስተው ይቆማሉ፡፡ እሳቸው በዚያ ክፍል ውስጥ በሠላሳው ልጆች የቀድሞ ችሎታቸውን (ችሎት) ሙሉ ድባብ ፈጠሩ፡፡ የከረመ ልማድ ብቅ ማለቱ እንደማይቀር ሉስ አይደል፡፡

የሥነ-አእምሮ ጠበብት የአስተማሪዎች ትክክለኛ ባህሪይ ፖለቲከኝነት ሳይሆን እንደማይቀር ይጠረጥራሉ፡፡ እርግጥ ፖለቲካ ውስጥ የሚያስገባ በቂ በራስ የመተማመን መንፈስ ባይኖራቸውም ወደ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ሄደው፣ ፕሬዝዳንቶችና ጠቅላይ ሚኒስትሮች ይሆናሉ፣ ይነግሳሉ፡፡ ትንንሽ ልጆችን ያዝዛሉ ያስገድዳሉ፡፡ ከዚህም ሌላ እነዚሁ ጠበብት እንደሚጠረጥሩት ከሆነ፣ አስተማሪዎቻቸው የጨካኝነት አዝማሚያ አላቸው፣ ሌሎችን ማሰቃየት ይወዳሉ፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ከአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የተሻለ ስፍራ የለም፡፡ ምንም የማያውቁ ሕፃናትን ለራሳቸው ጥቅም ብለህ ማሰቃየት ትችላለህ፡፡ ሂድና ተመልከት! እኔ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ ተገኝቼ አስተማሪዎችን ተመልክቼያለሁ፡፡ የሥነ-

እእምሮ ጠበብቶቹ የጥበብ ውጤት የሚያሳየው ጥርጣሬን ብቻ ቢሆንም፤ እኔ ግን ሰዎችን የማስቀየት የጭካኔ ባህሪይ እንዳላቸው እርግጠኛ ነኝ! ደግሞስ፣ ምንም መከታ የሌለው የዋህ ሰለባዎች ሌላ የት ማግኘት ይቻላል? በእነሱ ክሳሳንትና ደካማነት ላይ የአስተማሪ ጭካኔ ሲጨመርበት፣ አስተማሪውን ንጉሠ ነገሥት አድርጎት ቁጭ ይላል።

አውራንግዜብ በግለ-ሕይወት ታሪካቸው ሲፅፉ፣ ‹‹አባቴ፣ ከድሮ ልማዶቹ የተነሳ፣ አሁንም ንጉሠ-ነገስት እንደሆነ ለማስመሰል ይፈልጋል። ታዲያ ምን አለበት፣ ራሱን በማስመሰል ቢያሞኝ ምን ችግር አለው? ሠላሳም ይሁን ሦስት መቶ፣ የፈለጋቸውን ያህል ታዳጊዎች እልክለታሁ። የራሱን አነስተኛ ትምህርት ቤት እያስተዳደረ ይደሰት።

አንድ ድርጊት ያለ ዓላማ ሲፈፀም ክንዋኔ ይሆናል። በራስህ ላይ አስተውለው። የኃይልህ ዘጠና በመቶ የሚባክነው በክንዋኔ ላይ ነው። በዚህ የተነሳም ድርጊትን የሚሻ አንድ ቅፅበት ሲመጣ፣ ለድርጊት የተረፈ ኃይል አይኖርህም። እረፍት ላይ ያለ ወይም ዘና ያለ ሰው ማለት፣ የተጠናወተው ምንም ልማድ የሌለው ነው። ይህ ደግሞ ኃይል በውስጡ መገንባት እንዲጀምር ያደርጋል። ኃይሉን ይቆጥባል፣ ኃይሉ ያለምንም ጥረት እየጨመረ ይሄዳል። ከዚያም ድርጊት መፈፀም የሚያሻበት ጊዜ ላይ ሁለንተናዊ ሀላዌው በድርጊቱ ላይ ያርፋል። ድርጊት ሁለንተናዊ ወይንም ምሉዕ የሆነበት ምክንያት ይኸው ነው። ክንዋኔ የሚከናወነው በግማሽ ልብ ነው፤ በእርግጠኝነትም ባይሆን ራሳችንን እያሞኘን መሆናችንን ይታወቀናል። እንደውም አንዳንዴ ምንም ፋይዳ እንደሌለው እየታወቀን እናከናውነዋለን። ግልጽ ካልሆኑልህና ምንነታቸውን በውል በማታውቃቸው ምክንያቶች የተነሳ እንደምታደርጋቸውም ይታወቅሀል።

የምትፈጽማቸውን ክንዋኔዎች መለወጥ ብትችልም፣ ወደ ድርጊት እስካልለወጥካቸው ድረስ ጥቅም የለውም። ሰዎች ወደ እኔ ይመጡና፣ ‹‹ማጨስ ማቆም እንፈልጋለን።›› ይሉኛል፤ እኔ ደግሞ፣ ‹‹ለምን? ይህ እኮ ጥሩ ጊዜ ማሳለፊያ

ነው፣ ቀጥሉበት እንጂ፡፡›› እላቸዋለሁ፡፡ ቢያቆሙትም ሌላ ክንዋኔ ይጀምራሉ፣ ምክንያቱም የበሽታውን ምልክቶች በመለወጥ በሽታን መለወጥ አይቻልም፡፡ ማጤስ ያቆሙና ጥፍራቸውን ወይ ማስቲካ ማላመጥ ይጀምራሉ፡፡ ከእነዚህም የከፋ ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህ የደጋግ ሰዎችን ማንነት የሚወክሉ ናቸው፣ ምክንያቱም ማስቲካ የምታኝክ ከሆንክ የምታኝከው ለራስህ ነው፡፡ ቂል ልትሆን ትችላለህ፣ ግን ጨካኝ አይደለህም፣ ሌሎች ሰዎችን እየጎዳህ አይደለም፡፡ ማስቲካ ማላመጥ፣ ማጤስ ወዘተ፣ ብትተው ሌላ ምን ታደርጋለህ? አፍህ ማከናወን ይፈልጋል፣ አፍህ ጨካኝ ነው፡፡ ይህን ጊዜ ደሞ ታወራለህ፡፡ ያለማቋረጥ ታወራለህ፣ የባሰ እለ አገርህን አትልቀቅ ማለት ይህ ነው፡፡

የሙላ ናስሩዲን ሚስት ባለፈው ጊዜ ወደ ቤቴ መጥታ ነበር፡፡ እኔን የመጠየቅ ልማድ እንብዛም ስለሌላት፣ ገና እንደመጣች አንድ ችግር ተፈጥሮ እንደሆነ ገባኝ፡፡ ‹‹ምን ችግር ተፈጠረ?›› አልኩና ጠየቅኋት፡፡ ‹‹ሙላ ናስሩዲን በእንቅልፍ ልቡ ያወራል፣ ምን እድርጊ ትለኛለህ? በጣም ስለሚለፈልፍ አብሬው መተኛት አልቻልኩም፡፡ እየጮኸ ፀያፍ ነገሮች ይናገራል፡፡›› ብላ ለመናገር ሠላሳ ደቂቃና ከአንድ ሺህ ቃላቶች በላይ አባከነች፡፡

እኔም ስመልሳት፣ ‹‹ምንም የሚደረግ ነገር የለም፡፡ አንቺ ግን ከእንቅልፍ ሰዓታችሁ ውጪ በነፃነት የሚያወራበት ዕድል ስጪው፡፡›› አልኳት፡፡

ሰዎች ያለማቋረጥ የማውራት ጥማቸውን ለማርካት ሲሉ፣ ሌሎችን የመናገር ዕድል ይነፍጋሉ፡፡ መናገር እንደማጤስ ነው፡፡ ሀያ አራት ሰዓት ሙሉ ካወራህ የሚፈጠረውን ገምት፣ ደጋግሞ ታወራለህ! በእውንህ ታወራለህ! ስታወራ ትውልና አካልህ ይደክማል፣ ትተኛለህ፡፡ ግን ወሬህ ተኝተህም ይቀጥላል፡፡ ሃያ-አራት ሰዓት ሙሉ ስታወራ፣ ስታወራ ትቆያለህ፡፡ ወሬ ልክ እንደማጤስ ነው፡፡ ምክንያቱም መንስኤያቸው አንድ ነው፣ አፍ እንቅስቃሴ ይፈልጋል፡፡ አፍ ደግሞ የክንዋኔ መሰረት ነው፣ በሕይወትህ መጀመሪያ ያከናወንከው ነገር አፍህን በመሳሪያነት ተጠቅመህ ነው፡፡

ሕፃን ልክ እንደተወለደ፣ የእናቱን ጡት መጥባት ይጀምራል። የመጀመሪያውና መሰረታዊው ክንዋኔ ይህ ነው። ማጤስም ጡት እንደመጥባት ነው፣ በጉሮሮአችን ወደ ውስጥ የሚፈስሰው ለብ ያለ ወተት መሆኑ ቀርቶ ለብ ያለ ጢስ ይሆናል። ከናፍርህ መሀል የለጎምከው ሲጋራ ከእናት ጡት ጫፍ ጋር ተመሳሳይ ስሜትን ይፈጥራል። ማጤስ ከተከለከልክ ወይ ራስህን ከከለከልክ፣ ማስቲካ ታላምጣለህ፣ መፋቂያ ትለጉማለህ፣ በመጨረሻ ወሬ ትጀምራለህ። ይህ ደግሞ ከማጤስም በላይ አደጋ አለው፤ ምክንያቱም ትርኪ ምርኪ ሐሳብህን በሰዎች ሕሊና ውስጥ እየጣልክ ነው።

ለረጅም ጊዜ በዝምታ መቆየት ትችላለህ? የሥነ-አእምሮ ጠበብት እንደሚሉን ከሆነ ለሦስት ሳምንታት ዝም ብለህ ከቆየህ፣ ከዚያ ከራስህ ጋር ማውራት ትጀምራለህ። ያን ጊዜ ሁለት ቦታ ትከፈላለህ ማለት ነው፣ ተናጋሪም አንተ አድማጩም አንተ ትሆናለህ። በዝምታህ ፀንተህ ሦስት ወር ከቆየህ ደግሞ፣ የእብዶች ሆስፒታል በር ወለል ብሎ ይከፈትልሃል። ምክንያቱማ፣ አሁን ሰው አጠገብህ ኖረ አልኖረ ግድ የለህም። ታወራለህ፣ ማውራት ብቻም አይደለም፣ መልስም ትሰጣለህ። አሁን ምሉዕ ሆነሃል፣ የሌላ ሰው ጥገኛ አይደለህም። እብድ ማለት ትርጉሙ በቀላሉ ይኸው ነው።

እብድ ማለት መላውን ዓለም በራሱ ውስጥ ማግኘት የሚችል ማለት ነው። ተናጋሪ እሱ ነው፣ አድማጩ እሱ ነው፣ ተዋናዩ እሱ ነው፣ ተመልካቹ እሱ ነው - ቦታ ሁሉም እሱ ነው፣ ዓለምን ሁሉ በውስጡ ያገኛታል። ራሱን ብዙ ቦታ ከፋፍሎታል። በዚህ የተነሳ ሁሉ ነገር ሽርፍራፊ ሆኗል። ሰዎች ዝምታን የሚፈሩት ለዚህ ነው - ሳያስቡት ሊለፈልፉ እንደሚችሉ ይታወቃቸዋል። ስለዚህ አንተም ዝምታ የሚያስፈራህ ከሆነ፣ ዘወትር ያለሚቋረጥ በክንዋኔ እንድትጠመድ የሚወተውትህ ቅብጥብጥና ጤነኛ ያልሆነ አእምሮ አለህ ማለት ነው።

ክንዋኔ ከራስህ ማምለጫ ነው። በድርጊት ውስጥ ስትሆን ራስህን ነህ፣ በክንዋኔ ውስጥ ግን ከራስህ አምልጠሃል - ልክ እንደ አደንዛዥ እፅ ነው። በክንዋኔ

ውስጥ ራስህን ትረሳለህ፣ ራስህን ከረሳህ ደግሞ ሐሳብና ጭንቀት ይጠፋሉ። በዚህ የተነሳ፣ አንድ የሆነ ነገር እያደረግክ ያለማቋረጥ ከንዋኔ ውስጥ ለመኖር ትገደዳለህ። ምንም ነገር ያለማድረግ አእምሯዊ ድባብ በውስጥህ አብቦ የሚንሰራበት ሁኔታ ውስጥ በፍጹም አትገባም።

ድርጊት መልካም ነገር ነው። ከንውን ግን ሕመም ነው። የሁለቱን ልዩነት በውስጥህ ፈልገው። የመጀመሪያው ተግባርህም ይህ ይሁን። ቀጣዩ ተግባርህ አብላጫው ኃይልህ ድርጊት ላይ እንዲውል ራስህን በበለጠ በድርጊት መጥመድ ነው። በተጨማሪም ከንውን / ባዶ ተግባር ላይ ስትሆን ለማወቅ የሚያስችል ሙሉ ንቃት ሊኖርህ ይገባል። ንቁ ከሆንክ ባዶ ተግባር ያከትማል። ኃይልህ ይቆጠብና ወደ ድርጊት ይለወጣል።

ድርጊት ቅፅበታዊ ወይም ድንገተኛ ነው። ቀደም ብሎ የተዘጋጀ ወይም የተጠነሰሰ አይደለም። ዝግጅት የማድረጊ ወይም የመለማመጃ ዕድል አይሰጥህም። ድርጊት ግን ዘወትር አዲስ እና እንደ ጠዋት ጤዛ አፍላ ነው። የድርጊት ሰውም ዘወትር ትኩስና አፍላ ነው። አካሉ ቢያረጅም አፍላነቱ ግን አይጠፋም፣ አካሉ ሊሞት ይችላል፣ ወጣጥነቱ ግን ይቀጥላል። አካሉ ቢጠፋም እሱ ግን ይቀራል፣ ምክንያቱም እምላክ አፍላነትን ይወዳል። እምላክ ሠርክ የአፍላዎችና የትኩሶች ወገን ነው።

ከዋኔን ቀስ በቀስ አስወግድ። እንዴት ታስወግደዋለህ? ማስወገዱን በራሱ ልማድ ማድረግ ትችላለህ። በየገዳሙ የሚገኙ ባህታዊያን ላይ የደረሰው ይህ ነው። ከዋኔን ማስወገድ በራሱ ሌላ ልማድ ሆነባቸው። ከዋኔን ለማስወገድ ያለማቋረጥ አንድ ነገር ማከናወን ተያይዘዋል - ፀሎት፣ አርምሞ፣ ምስጠት፣ ዮጋ ወዘተ። ይህም ከዋኔ መሆኑን ልብ እንበል። በዚህ ዘዴ ልታስወግደው አትችልም፣ በጓሮ በር ይመጣል።

ንቃት ይኑርህ። በድርጊትና በክዋኔ / በባዶ ተግባር መካከል ያለው ልዩነት ይሰማህ። ስለዚህ ክዋኔ በሚቆጣጠርህ ወይም በሚገዛህ ጊዜ፣ ሲያቁነጠንጥህና አድርግ አድርግ ሲልህ፣ ንቃበት / አስተውል። ልታደርገው የምትችለው ይህንን ብቻ ነው። አስተውለው። የግድ ማድረግ ካለብህ እንኳን እያስተዋልክ፣ ነቅተህ አድርገው። ሲጋራውን አጢስ፣ ግን ምን እያደረግክ እንደሆነ ለመረዳት እንድትችል በሙሉ ማስተዋል በጣም በዝግታ አጢሰው።

የማጤስ ክዋኔን ማስተዋል ከቻልክ፣ የኋላ ኋላ ትርጉም የለሽነቱ ሙሉ በሙሉ ይገለጥልህና አንድ ቀን ድንገት ሲጋራው ከጣቶችህ ሊወድቅ ይችላል። ፍፁም ምንም ትርጉም የሌለው ፋይዱቢስ ነገር ነው። ይህንን በተረዳህ ጊዜ በቃ፣ ጣቶችህ ላይ ቦታ ያጣና ይወድቃል። ልትወረውረው አትችልም፣ ምክንያቱም መወርወር በራሱ ክዋኔ ነው። ለዚህ ነው፣ ልክ የደረቀ ቅጠል ከዛፍ ላይ እንደሚወድቅ ሁሉ፣ ሲጋራውም ከአንተ ህልውና ጋር ተቆራኝቶ የነበረ ህልውናው አክትሞ፣ በቃ ይወድቃል ያልኩት። ወርውረኸው ወይም ራስህን አስገድደህ ትተኸው ቢሆን ኖሮ፣ ሌላ መልክና ቅርፅ ይዞ ዳግመኛ ታገኘውና ታነሳዋለህ።

ነገሮች ራሳቸው እንዲወድቁ ተዋቸው እንጂ አትጣላቸው። ክዋኔ ራሱ እንዲወገድ ፍቀድለት እንጂ አንተ ገፍተህ አታስወግደው። ምክንያቱም ክዋኔን ለማስወገድ የማስገደድ ጥረት በራሱ ሌላ መልክ ያለው ክዋኔ ነው። የምታስተውልና የምትነቃ ከሆንክ፣ ተዓምራዊ ክስተት ላይ ትደርሳለህ። አንድ ነገር በራሱ ጊዜ ሲወገድ ምንም ዐይነት ጠባሳ ወይም ቅሪት አንተ ላይ አይተውም። ገፍተህ ካስወገድከው ግን ጠባሳ ጥሎብህ ያልፋል። ያን ጊዜ ሠላሳ ዓመት አጭሰህ ማቆምህን በጉራ ስታወራ ትኖራለህ። ይህ የጉራ ወሬህም ያው ነው። ባታጤስም ማጤስ ስለማቆምህ ከመጠን የዘለለ ወሬ እያወራ ነው። ከናፍሮችህ አሁንም እያከናወኑ ነው፣ አፍህ ተግባር ላይ ነው፣ ስለዚህ ጭካኔህ አሁንም አለ።

አንድ ሰው ከልቡ ካስተዋለና ከተረዳ ነገሮች ይወገዳሉ። ከዚያ «አስወገድኩ!» ወይ «አቆምኩት!» እያለ ጉራውን መንዛት አይችልም። ነገርየው

ራሱን ነፃ ያስወገደው። በዚህም እኔነትህ መኩራሪያ ስለማያገኝ፣ ግብዝ አትሆንም። ያን ጊዜ ታዲያ ስበለጠ ድርጊት ትበረታለህ፡

ምሉዕ ድርጊት ውስጥ የምትገባበት አጋጣሚ ስታገኝ ታዲያ አታመንታ፣ አድርገው። በበለጠ በድርጊት እየተጠመድክ ስትሄድ ክዋኔዎች በራሳቸው ጊዜ ይወገዳሉ። ቀስ በቀስ ትሰወጣለህ። ማግበል ስለሚፈልግ ጊዜን ይጠይቃል፣ ስለዚህ የሚያስቸኩል ነገር የለም።

ቀጣዮቹን የታይሎፓ ቃላት አዳምጡ። ታይሎፓ፣ የቡድሃን ትምህርቶች ለሕንድ ወደ ቲቤት የወሰደ የ11ኛው ክፍለ-ዘመን መንፈሳዊ ሰው ነበር።

በአካላችሁ ምንም አታድርጉ ዘና ብላችሁ እረፉ፣ አፋችሁን ዝጉና በዝምታ ፅኑ፣ አእምሮአችሁን እራግፉና ባዶ አድርጋችሁ ስለ ምንም ነገር አታስቡ፡

የመጀመሪያው መስመር የእረፍትን ምንነት ለመረዳት ያስችላችኋል። በሌላ አባባል፣ በውስጣችሁ የክዋኔ ጉጉት ወይም ግፊት ያለመኖሩን ያሳያል። ዘና ማለትና ማረፍ ማለት እንደሞተ ሰው መዘርጋት ማለት አይደለም፣ ደግሞም እንደሞተ ሰው መዘርጋት አትችሉም፣ ምናልባት ታስመስሉ እንደሆን እንጂ። እንዴት እንደሞተ ሰው መጋደም ትችላላችሁ? ካላስመሰላችሁ በስተቀር ህያውያን ናችሁ። ዘና የምትሉት የሆነ ነገር ለማድረግ የሚያቅበጠብጥ ስሜት በማይኖራችሁ ጊዜ ነው። ኃይላችሁ ወደየትም ሳይሄድ ከእናንተ ጋር ነው። አንድ ሁኔታ ቢፈጠር ርምጃ ለመውሰድ ወደ ድርጊት ትገባላችሁ፣ እንጂ ወደ ድርጊት ለመግባት ሰበብ አትፈልጉም። ከራሳችሁ ጋር ተስማምታችኋል፣ ማንም ምንም ሊረብሻችሁ የማይችልበት ቦታ ላይ ናችሁ። ቤታችሁ እንደመገኘት ነው።

ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ መጽሐፍ አንብቤ ነበር። የመፅሐፉን ርዕስ ‹‹ዘና ማለት አለባችሁ›› (you must relax) የሚል ነው። ርዕሱ በራሱ ግራ ያጋባል፣ ዘና ማለትን ግዴታ ያደርገዋል። ግዴታና መዝናናት ደግሞ አይጣጣሙም። መሰል መፅሐፎች አሜሪካ ውስጥ ጥሩ ገበያ አላቸው። ግዴታ ከክዋኔ ጋር የተሳሰረና

ልማድን የሚጠቁም ነው። ‹‹must›› በተገኘበት ቦታ ሁሉ ከበስተጀርባው አንድ የተሸሸገ አጉል ልማድ አለ። በሕይወት ውስጥ ድርጊቶች መኖራቸው ግልፅ ቢሆንም፣ ግዴታ ግን የለም፤ ካለዚያ ግን ግዴታዎቹ አብደት ውስጥ ያስገባሉ። ‹‹መዝናናት አለባችሁ።›› ከተባለ ዘና ማለት ራሱ አጉል ልማድ ይሆናል። አካላችንን አስገድደን ዘና እንዲል ልናደርገው አንችልም።

ለምን ግዴታ ይደረጋል? ዘና ማለት የሚገኘው በሕይወታችሁ ውስጥ ግዴታ የሚባል ነገር ሲጠፋ ነው። ዘና ማለት አእምሯዊ ብቻ አይደለም፣ አካላዊ ብቻም አይደለም፣ የሁለንተናዊ ሕላዌያችን እንጂ።

ብዙዎቻችሁ ከኖኔ ውስጥ ስምጣችኋል፣ ስለዚህም ድካም፣ ስልቹነት፣ ድብርትና ምሬት የቅርብ ወዳጆቻችሁ ቢሆኑ አያስገርሙም።

ዘና ማለት የሚጠቅምህ ምንም ዐይነት መጽሐፍ የለም። ዘና ለማለት ማንበብ ያለብህ የራስህን ውስጠ ማንነት ወይንም ሕላዌ ነው። በዚያን ወቅት ያለጥረት ዘና ማለት ትችላለህ። መዝናናት ግዴታ አይደለም። የኮኖኔ ያለመኖር ነው። ከድርጊት ጋር ግንኙነት የለውም። ለመዝናናት መጠጥ ቤት መሄድ ወደ መዝናኛ ማምራት አያስፈልግም። ምን ወደ መዝናኛ መሄድ አስፈለገ? ድርጊት መቅረት የለበትም ምክንያቱም ከድርጊት ገሸሽ ማለት ከሕይወት ገሸሽ እንደማለት ነው። ያን ጊዜ ምትክ እንጂ ተዝናናህ አይባልም። በየገዳሙ የምናገኛቸው የሞቱ እንጂ የተዝናኑ ባህታዊያን አይደሉም። ከድርጊት፣ ብሎውም ከሕይወት ያመለጡ ባህታዊያን ናቸው።

ግንዛቤን ማግኘት ያለበት ጥንቃቄ የሚያሻው ነጥብ ይህ ነው። ከኖኔ እንጂ ድርጊት መቅረት የለበትም የሚለው። ሁለቱንም መተው ቀላል ነው። ሁለቱንም ትተህ ወደ ሰደራ መሄድ ወይንም ከናካቴው ገዳም መግባት ትችላለህ። ይህንን ማድረግ ቀላል ነው። ሌላ ቀላል መንገድም አለው። በከኖኔዎችህ ቀጥለህ በየማለዳው ወይም በየምሽቱ ራስህን በግድ ዘና ማድረግ ትችላለህ። የሰው ልጅ አእምሮ

ውስብስብነትና አሰራሩ አልገባህም፡፡ መዝናናት የአእምሮ ሁኔታ በመሆኑ ልታስገድደው አትችልም፡፡ በቃ አሉታዊ ሐሳቦችንና ገደቦችን በምታስወግድበት ጊዜ በራሱ ጊዜ ይከሰታል፡፡

ለሊት ተኝተህ ምን ታደርጋለህ? የምትሰራው ሥራ አለ? በቃ ትጋደምና እንቅልፍ ይዞህ ይሄዳል፡፡ የምትሰራው ሥራ ወይ የምታስበው ነገር ካለህ፣ ኢንሶምኒያ (Insomnia) የተባለው የእንቅልፍ እጦት የጤና ችግር ተጠቂ ነህ ማለት ነው፡፡ ለመተኛት ምንም «የሚደረግ» ነገር የለም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ እንቅልፍ እንዲወስደን የሚያደርገው ብቸኛው መንስኤ የአእምሮ ሥራ መቋረጡ ነው፡፡ የዕለቱ የክዋኔ ሂደት መቋረጥ አለበት፡፡ በቃ ይኸው ነው! ክንዋኔው ከአእምሮ ሲጠፋ፣ አእምሮ ይዝናናና እንቅልፍ ይወስደናል፡፡ ለመተኛት ብለን የምናደርገው ነገር ካለ እንቅልፍ የማይታሰብ ይሆናል፡፡

ማድረግ የሚባል ነገር ከናካቴው አስፈላጊ አይደለም፡፡ ታይሎፓ እንደነገረን፣ «ተዝናኑ እንጂ በአካላችሁ ምንም አታድርጉ» አዎ፣ ምንም አታድርጉ! የሚያስፈልገው የክዋኔ ያለመኖር ነው፡፡ ክዋኔ በምን ይጠፋል? ከመረዳትና ከመገንዘብ ሌላ ምንም ሥነ-ምግባር የለም። ክዋኔዎችህን እያስተዋልክና እየተረዳሀቸው አከናውናቸው፣ ያን ጊዜ ድንገት በክንዋኔህ መሀል ትነቃና፣ በራሱ ጊዜ ይጠፋል። ለምን እያደረግከው እንደሆነ ካስተዋልክ፣ አከተመለት ማለት ነው። ያን ጊዜ ትዝናናለህ።

መዝናናት ምንድን ነው? ኃይልህ ወደየትም የማይባዝንበትና የማይበታተንበት አእምሯዊ አካላዊ ሁናቴ ነው፡፡ ኃይልን ወደ አለፈውም ሆነ ወደ መጪ ጊዜ ሳይባዝን ከአንተ ጋር ይቆያል፡፡ በራስህ ኃይል የሰከነ ኩሬ ውስጥ አዝናኝን ለብቻው ተጎናፅፈህ የምትገኝበት ሁናቴ ነው፡፡ በዚህ ሁናቴ ውስጥ የምታልፈው እያንዳንዷ ቅፅበት እንጂ ሌላ ምንም ነገር የለም፡፡ ሌላ ቅፅበት ስለማይኖሩ ጊዜ ሂደቷን ታቆማለች፡፡ ያኔ መዝናናት አለ፡፡ ጊዜ ካለ ግን፣ ጊዜ ህልውናውን ሲያገኝ መዝናናት አይኖርም፡፡ ሰዓት ጉዞውን ያቋርጣል፣ ካለህዓት

ከዚያች ቅፅበት ሌላ ምንም ጊዜ የሚባል ነገር አይኖርም። የምትፈልገው ነገር አይኖርም። በቅፅበቱ ብቻ ሐሴት ውስጥ ትገባለህ። ተራ ነገሮች በውበታቸው ብቻ አስደሳች ይሆናሉ። እንደውም ተራ የሚባል ነገር አይኖርም፤ ነገሮች ሁሉ ልዩ አስደናቂነትና እፁብነት ይኖራቸዋል።

ሰዎች፣ «በፈጣሪ አምላክ ታምናለህ?» ብለው ይጠይቁኛል። እኔም፣ «አዎ፣ ምክንያቱም ተፈጥሮ ሁሉ እፁብ ድንቅ ነው፤ ታዲያ በውስጡ ትልቅ ንቃተ-ሕሊና ሳይኖረው እንዴት ሊሆን ይችላል?» በቃ ጥቃቅን ነገሮች እንኳን ይመሰክሩለታል . . . ገና ጤዛው ያልረገፈ መስክ ላይ ስንራመድ፣ በስፍራው ምሉዕ የመገኘት መንፈስ ካለን፣ ጠቅላላ ድባቡ፣ የመስኩ ሕያው ልስላሴ፣ የጤዛ እንክብሎቹ ቅዝቃዜ፣ የማለዳው ነፋስ እና የጀምበሯ መፈንጠቅ በአንድነት ይመሰክሩለታል። ታዲያ ለመደሰት ከዚህ በላይ ምን ትፈልጋላችሁ? በቃ ለሊት በአልጋችሁ ላይ በቀዘቀዙ አንሶላዎቻችሁ ቀስ በቀስ እየሞቁ ሲመጡ፣ በክበባችሁ ጭለማና በለሊቱ ፀጥታ ውስጥ የሚፈጠርባችሁ ስሜት . . . ዐይኖቻችሁን በመክደን ይህን ስሜት ማዳመጥ። በቃ ከዚህ በላይ ምን ትፈልጋላችሁ? ከመጠን በላይ ነው። ጥልቅ የሐሴት መንፈስን ይፈጥራል። መዝናናት ይህ ነው።

መዝናናት ማለት ይህቺ ቅፅበት ከምንም ነገር በላይ፣ ከበቂ በላይ፣ እንዲሁም ልንጠይቀውና ተስፋ ልናደርገው ከምንችለው ነገር ሁሉ በላይ ናት ማለት ነው። የምንጠይቀው ነገር የለም፣ ልንመኘውና ልንፈልገው ከምንችለው ከበቂ በላይ አግኝተናል። ይህን ጊዜ ኃይል ወደየትም አትሄድም፤ እንደለዘነ ኩሬ ትሆናለች። በራሳችን ኃይል ውስጥ እንሟሟለን። ይህች ቅፅበት ራሷ መዝናናት ናት።

መዝናናት የአካል ብቻ ወይ የአእምሮ ብቻ አይደለችም። መዝናናት ሁለንተናዊ ናት። በዚህ የተነሳ ነው! የቡድሃ ተከታዮች «መሻት-አልባ» ሁኑ እያሉ ያለመሰልቸት የሚናገሩት፣ ምክንያቱም ፍላጎት ካለ ዘና ማለት እንደማይቻል ያውቃሉ። ቀጥለው ደግሞ፣ «ሙታንን ቅበሩ!» ይላሉ፣ ምክንያቱም አትኩሮት ባለፈው ጊዜ ላይ ከመጠን በላይ ካነጣጠረና ስላለፈው ካሰላሰለ መዝናናት አንችልም።

ለጥቀው ደግሞ፣ ‹‹በዚህች በአሁኗ ቅፅበት ደስ ይበላችሁ፡፡›› ይላሉ፡፡ እየሱስም ‹‹የሜዳ አበቦችን ተመልከቱ - አይደክሙም፣ አይለፉም፣ ዳሩ ግን በውበት ወደር የላቸውም፣ ግርማቸው ከንጉስ ሰለሞን ይበልጣል፡፡››

ምን ማለቱ ነው? ዘና በሉ እያለ ነው፤ ለመዝናናት መልፋት አያስፈልጋችሁም - እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ሁሉ ነገር ተዘጋጅቶላችኋል፡፡ እየሱስ እንዲህ ይላል፣ ‹‹የሰማይ አእዋፍትን፣ የዱርና ለማዳ እንስሳትን ዛፎችና ቁጥቋጦዎችን የሚጠብቃቸው እሱ ከሆነ፣ እናንተ ለምን ትጨነቃላችሁ? እናንተንስ አይጠብቃችሁምን?›› መዝናናት ማለት ይህ ነው፡፡ ስለመጪው ጊዜ ይህን ያህል ለምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦችን፣ አደይ አበቦችን አስተውሏቸውና እናንተም አደይ አበቦች ሁኑ፡፡ ከዚያ ዘና በሉ፡፡ መዝናናት ከአቀማመጥና ከአረማመድ አኳኋን ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ መዝናናት የኃይላችሁ ሁለንተናዊ ለውጥ ነው፡፡

ኃይል ሁለት አውታሮች ሊኖሩት ይችላል፡፡ የመጀመሪያው በመንፈስ ተነሳሽነት ታጅቦ ወደሆነ አንድ ስፍራ ወይም ግብ የሚያመራ ነው፡፡ ይህች ቅፅበት የምታገለግለው በመንስኤነት ነው፣ የሚደረስበት ግብ ግን ሌላ ስፍራ ነው፡፡ የኃይልህ አንዱ አውታር ይህ ነው፡፡ ይህ አውታር የክዋኔ አውታር ነው፡፡ አውታሩ ግብ-ተኮር በመሆኑ፣ ሌላው ሁሉ ነገር ያንን ግን የሚያሳካ መንስኤ ይሆናል፡፡ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ፣ መድረግ አለበት፣ ግባችሁ ላይ መድረስ አለባችሁ፡፡ ከዚያ በኋላ መዝናናት ትችላላችሁ፡፡ ዳሩ ግን፣ የዚህን መሰል ኃይል ግን መቼም ይሁን መቼ አይላካም ወይም አይደረስበትም፡፡ ምክንያቱም ይህን ዓይነቱ ኃይል የአሁኗን እያንዳንዷን ቅፅበት ወደ ሌላ ግብ መንስኤነት ይለውጣታል፡፡ ወደመጪው ጊዜነት ይለውጣታል፡፡ የታሰበው ግብ ሠርክ በአድማስ ርቀት ላይ ተቀምጦ ይቀራል፡፡ ሩጫችሁን ትቀጥላላችሁ፣ ግን አትደርሱበትም፡፡

ከዚህ የተለየ የኃይል አውታር አለ፡፡ ይህኛው አውታር የመንፈስ ተነሳሽነት ያላጀበው ሐሴት ነው፡፡ ግቡ እዚሁ ነው፣ አሁን ነው፡፡ ግቡ ሌላ ስፍራ አይደለም፡፡ እውነቱን እንናገር ከተባለ ግቡ አንተ ራስህ / አንቺ ራስሽ / ነህ/ሽ፡፡ ከዚህች ቅፅበት

ሌላ ምንም አርባታ የለም - አደይ አበባችን አበቡ። ግቡ እናንተ አንጂ በመጪው ጊዜ ላይ የተቀመጠ ግብ ካልሆነ፣ የሚባካ ትልም ከፊታችሁ ካልተደቀነና እንደውም በጥቅምቱ እዚያው ግብ እየመታችሁ በስኬታችሁ ሐሴትን ስታደርጉ፣ መዝናናት ማለት ይህ ነው። የስሜት ተነሳሽነት ያልተበረበበት ኃይል።

በዚህ የተነሳ ለእኔ፣ ሁለት ዐይነት ሰዎች አሉ። ግብ አዳኞችና አመክጋኞች ወይም ስኬትን የሚሹና ሐሴተኞች። ግብ-መሮቹ እብዶች ናቸው። ቀስ በቀስ ወደ እብደት እየሄዱ ነው፡ እብደታቸውን የሚፈጥሩት ራሳቸው ናቸው። ይህንን የእብደት ትዕና እንደ ከተያያዙት እብደቱ በራሱ በፍጥነት እየተገዘ ቀስ በቀስ ጠልቀው ይገቡበታል፣ በመጨረሻ ፍፅም ይጠፋሉ። ሌላው ዐይነት ሰው ግብ-አዳኝ አይደለም፣ እንዲያውም ከናካቴው መሻት አልፈጠረበትም፣ ይህ ሰው ሐሴተኛው ሰው ነው።

ሐሴተኞቹን ሁሉ፣ ሐሴትን አድርጉ! የተትረፈረፈ ፀጋ አለ - አበቦቹ አብበዋል፣ አዕዋፋት እየዘመሩ ነው፣ ጀምበር ፈንጥቃለች፣ በዚህ ሁሉ ተደሰቱ! እስትንፋሳችሁ አለ፣ ህያው ናችሁ፣ ንቃተ ሕሊናም አላችሁ፣ በዚህ ሐሴት ይኑራችሁ! ያን ጊዜ ድንገት መዝናናትን ታገኛላችሁ፣ ውጥረትና ጭንቀት ይጠፋሉ። ወደ ጭንቀትነት ይለወጥ የነበረው ኃይል ምስጋና ይሆናል። ሙሉ ልባችሁ በጥልቅ ምስጋና መመታቷን ትቀጥላለች - ፀሎት ማለት ይህ ነው። የፀሎት ትርጉሙ ይኸው ነው፣ በጥልቅ ምስጋና ተሞልታ የምትመታ ልብ ማለት ነው።

በእካላችሁ ምንም ሳታደርጉ ተዝናኑ። ዘና ለማለት ምንም ማድረግ አያስፈልግም። የኃይሉን እንቅስቃሴ፣ የስሜት ተነሳሽነት ያልገባበትን ኃይላችሁን እንቅስቃሴ መረዳት ብቻ በቂ ነው። ይህ ኃይል ሐሴትን ሆኖ ይፈስሳል። የሚፈሰው ወደ አንድ ግብ አይደለም። እንቅስቃሴው ወደ አንድ ግብ አይደለም። የሚንቀሳቀሰው በራሱ ሞልቶ የተረፈ ኃይል መንስኤነት ነው።

አንድ ሕፃን ይቦርቃል፣ ይዘላል፣ ይሮጣል። «ወደየት እየሄድክ ነው?» ወደ አንድ ስፍራ መሄድ ለምን አስፈለገ? አንድ ሕፃን ይህንን ጥያቄያችሁን መመለስ

አይችልም፣ ምክንያቱም አግባብ የሌለው ጥያቄ ነው። የትም እየሄደ ስላልሆነ፣ ቡቃ ትከሻውን ወደላይ ይሰብቅና፣ «የትም!» ሲል ይመልሳል። ግራ መሩ አስምሮ መልስ፣ «ታዲያ ለምን ትሮጣለህ?» ብሎ ይጠይቀዋል። ምክንያቱም አንድ ክምኒ አግባብ የሚኖረው፣ ወደ አንድ ሥፍራ የሚመራ ሲሆን ብቻ ነው።

እኔም የምናገረው ይህንኑ ነው፣ የሚሄድበት ቦታ የለም። የትም መሄድ አትችሉም። ከአሁን በስተቀረ ምንም ቦታ የለም። ሁሉም አሁን ነው። ሕልውና ባጠቃላይ በዚህች ቅፅበት ላይ ተቋጭቷል፣ እዚህች ቅፅበት ላይ ተጠቃልሎ ተገኝቷል። ሕልውና በሙሉ፣ ቀድሞ ነገር ወደዚህች ቅጽበት እየጎረፈ ነው። ሕልውና ያለው ሁሉ እዚህና አሁን ነው። ሕፃኑ በዚህ ኃይል እየተደለተ ነው። ከመጠን በላይ አለው፤ የሚሮጠው አንድ ሥፍራ ለመድረስ ሳይሆን ከመጠን በላይ ኃይል ስላለው ነው። ስለዚህ መሮጥ አለበት።

*ወደ ድርጊት ለመግባት ያስብህ በስሜት ተነሳሽነት ሳይሆን ሞልቶ በተረፈ ኃይልህ አማካይነት መሆን አለበት። አካፍሉ ግን አትነግዱ፤ አትደራደሩ፣ ስጦታችሁ ስጡ እንጂ፤ መልሳችሁ ለመቀበል በማሰብ አትስጡ። ይህንን ካደረጋችሁ ሰቀቀን ውስጥ ትገባላችሁ። ነጋዴዎች ሁሉ ገሀነም ይገባሉ። ወደር የሌላቸው ተደራዳሪዎችና ነጋዴዎች ማግኘት ከፈለጋችሁ ወደ ገሀነም ሂዱ። መንግስተ-ሰማያት የነጋዴዎች ሳትሆን የሐሴተኞች ናት።*

በክርስትና ሥነ-መለኮት ውስጥ ለብዙ ምዕተ-ዓመታት በተደጋጋሚ የተጠየቀ ጥያቄ አለ፣ «መላዕክት ገነት ውስጥ ምን ይሰራሉ? የሚል ነው። ይህ ግብር መር ለሆኑ ሰዎች ተገቢ ጥያቄ ተደርጎ የሚታይ ጥያቄ ነው። «መላዕክት ገነት ውስጥ ምን ይሰራሉ?» የሚያደርጉና የሚሰሩ ነገር ያለ አይመስልም፣ የሚሰሩ ነገር የለም። አንድ ሰው ሜይስተር ኤክሀርትን ይህንኑ ጥያቄ ጠይቶት ነበር። «ምን ዐይነት ቂሎች ናችሁ? ገነት ሐሴትን የማድረጊያ፣ የመደሰቻ፣ የማመለከቻ ቦታ ናት። ምንም አያደርጉም። ቦታ ግርማውን፣ ዕፁብነቱን ያመለኩታሉ። በቅኔው እና በውዳሴ ሐሴትን ያደርጋሉ። ይዘምራሉ፣ ይፈነድቃሉ፣ ይደሰታሉ።» በማለት መልሶ ነበር። ይህ ሰው

ግን በሚይስተር ኢክሀርት ምላሽ አልረካም፣ ምክንያቱም ለእኛ፣ አንድ ተግባር ትርጉም የሚኖረው ወደ አንድ ግብ የሚወስድ ሲሆን ብቻ ነው። ክዋኔ እንጂ ድርጊት ግብ-መር ያለመሆኑን አስታውስ። ድርጊት፣ ሞልቶ የሚፈስ ኃይል ነው። ድርጊት ይህች ቅጽበት ማለት ነው። ያለ ቅድመ ልምምድና ያለ ዝግጅት የሚሰጥ ምላሽ ነው። በሕልውና በአጠቃላይ ጋር ትገናኝና፣ ፊት ለፊት ስትተያይ፣ በራሱ ጊዜ የሚቀሰቀስ ምላሽ ያወጣሀል። ወፎች እየዘመሩ ነው፣ አንተም መዘመር ጀመርክ። ይህ ክዋኔ አይደለም። ድንገት የሚፈጠር ነው። ሳታስበው እየሆነ ታገኘዋለህ። ትዘምራለህ፣ ይህ ድርጊት ነው።

*ስለዚህ ራስህን በዋጊዜው በድርጊት በበለጠ እየጠመድክና ከክዋኔ እያወጣህ ስትሄድ፣ ሕይወትህ ይለወጣል፣ ጥልቅ መዝናናትንም ታገኛለህ። ያን ጊዜ «ታደርጋለህ» ግን እንደተዝናናህ ትቀያለህ።*

*አንድ ቡድሂስት በፍፁም አይደክምም። ለምን፣ ምክንያቱም «አድራጊ» አይደለም። ምንም ይኑረው ምን፣ ሞልቶት እየተረፈው ይሰጣል።*

በአካልህ ምንም አታድርግበት፣ ተዝናና እንጂ፣ አፍህን ግጥም አድርገህ ከድነህ በዝምታ ፅና። አፍ እውነትም ትልቅ ሥፍራ ሊኖረው የሚገባ ነገር ነው። ምክንያቱም የመጀመሪያዋ ክዋኔ ያረፈችበት ሥፍራ ነው። የመጀመሪያዋን ክዋኔ የጀመሩት ከናፍሮችህ ናቸው። የክዋኔ ሁሉ ጅማሬ አፍ አካባቢ ነው። የመጀመሪያ አስትንፋስህን ያስገባኸው፣ ያለቀስከው እና የእናትህን ጡቶች የጠባህበት በዚሁ በአፍህ ነው። ከዚህ በኋላ ይህ አፍህ በተስገበገበ ክዋኔ ተጠምዶ ኖሯል። ለዚህ ነው ታይሎፓ «ክዋኔን ተረዳ፣ ድርጊትን ተረዳ፣ ዘና በል እና . . . አፍህን ግጥም አድርገህ ዝጋው። የሚል አስተያየት የሚሰነዝረው።

ለአርምሞ ወይም ለማሰላሰል በምትቀመጥበት፣ ወይም በዝምታ ለመቀመጥ በምትፈልግበት ጊዜ ሁሉ፣ ከሁሉ በፊት አፍህን ግጥም አድርገህ ዝጋው። አፍህን ሙሉ ለሙሉ ግጥም አድርገህ ከዘጋኸው፣ ምላስህን የላንቃህን ጣሪያ ይነካል። ሙሉ

በሙሉ ግጠመው። ይህ ግን እስካሁን የተናገርኩትን ሁሉ በውል ተከታትለህ ከተረዳኸው በኋላ እንጂ፤ ከዚያ በፊት ሊሆን የሚችል አይደለም። ልታደርገው ትችላለህ፤ አፍን መዝጋት ያን ያህል ከባድ ጥረት አይጠይቅም። አፍህን ጥርቅም አድርገህ ዘግተህ እንደ ሀውልት መቀመጥ ግን ክንዋኔን አያስቀረውም። ውስጥ ውስጥህን ሐሳብ ድሩን ማድራቱን ይቀጥላል። ሐሳብ እስካላቋረጠ ድረስ ደግሞ ከንፈሮችህ ላይ በሌሎች የማይታዩ ጥቃቅን መርገብገቦች ይኖራሉ። የከናፍሮችህ መንቀጥቀጥ የሚሰማህ ለአንተ ብቻ ሊሆን ይችላል።

እውን ተዝናንተህ፣ ይህ መንቀጥቀጥ ይጠፋል። እየተናገርክ አይደለም፤ በውስጥህ እየተካሄደ ያለ ክዋኔም መኖር የለበትም። አፍህን ግጠምና ፅና። ሐሳብህንም አጥፋው። ሐሳብ ሊጠፋ ይችላል?

ምን ማድረግ ይኖርብሀል? ሐሳቦች ዘወትር ይመጣሉ ይሄዳሉ። ተዋቸው እየመጡ ይመለሱ። ይህ ችግር የለውም። አንተ ግን በሐሳቦች ውስጥ ተሳትፎ አይኖርህም፣ ራስህን ከእነሱ ታነጣለህ። ሲመጡና ሲሄዱ ከመመልከት ውጪ ምንተ ጉዳይ አይደሉም። አፍህን ዘግተህ በዝምታህ ፅና። የኋላ ኋላ ሐሳቦች በራሳቸው ጊዜ ይቋረጣሉ። ምክንያቱም በሥፍራው ለመገኘት የአንተ ትብብር ያስፈልጋቸዋል። ካስተናገድካቸው አይሄዱም፤ ልትመልሳቸው ከታገልካቸውም አይመለሱም። ማስተናገድም ሆነ መታገል መተባበር ነው። የጥላቻና የፍቅር ትብብር ነው። ሁለቱም ዐይነት ትብብሮች ክዋኔዎች ናቸው። ስለዚህ አንተ ከመመልከት ሌላ ምንም አይጠበቅብህም።

ሆኖም አፍን መዝጋቱ በጣም ይረዳል። ስለዚህም ብዙ ሰዎችን ባስተዋልኩት መሰረት የምሰጣቸው ምክር አለ። መጀመሪያ ማዛጋት አስፈላጊ ነው። አፍን በተቻለ መጠን በሰፊው መክፈትና መወጠር፣ ጡንቻዎች ላይ ሕመም እስኪሰማ ድረስ ሙሉ ለሙሉ ማዛጋት። ይህንን ለሁለት ወይንም ለሦስት ጊዜ ማድረግ። ይህንን ማድረጉ፤ አፍ ለረጅም ጊዜ ተዘግቶ እንዲቆይ ለማድረግ ይጠቅማል። ከዚያ በኋላ ለአንድ ወይም ለሁለት ደቂቃ ድምፅን ከፍ በማድረግ

ትርጉም የሌለው ባይሆን እንኳን ያለማቋረጥ መናገር፡፡ የምትናገሩት በሐሳባችሁ የመጣውን ነገር ሁሉ ሲሆን፣ በዚህም ደስታ ታገኛላችሁ፡፡ ከዚያ አፍን ግጥም ማድረግ፡፡

ከተቃራኒው ጫፍ መጀመሩ የበለጠ ይቀልላል፡፡ እጆቻችሁን ማገዝናናት ብትፈልጉ፣ በመጀመሪያ በተቻላችሁ መጠን ጥብቅ አድርጋችሁ ቡጢያችሁን መጨበጡ የተሻለ ይሆናል፡፡ የመዝናናትን ተቃራኒ ማለትም ውጥረትን ከፈጠራችሁ በኋላ ዘና ማድረግ፡፡ ከዚህ በኋላ፣ የነርቭ ስርዓታችሁ የበለጠ መዝናናትን ያገኛል፡፡ የፊትና የአፍ ጡንቻዎቻችሁን ለጥቂት ጊዜ ያህል ካወጣጠራችሁ በኋላ፣ አፍን መዝጋት፡፡ ይህ ውጥረት ካለፈ በኋላ ከናፍሮችና አፍ የበለጠ መዝናናትን እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል፡፡ በዚህን ወቅት ፀጥታ ይነግስባችኋል፡፡

የፀጥታ ዐይነቱ ሁለት ነው፡፡ የመጀመሪያው ዐይነት በግድ ራሳችን ላይ የምንፈጥረው ፀጥታ ነው፡፡ እጅግም ተወዳሽ ነገር አይደለም፡፡ አእምሯችንን አስገድዶን ከመድፈር ያልተናነሰ የጭካኔ ተግባር ነው፡፡ ሌላው ልክ እንደ ጀንበር መፈንጠቅ ሁለንተናን የሚያደምቅ፣ ቀስ እያለ የሚያሰፍን ፀጥታ ነው፡፡ በራሱ ጊዜ ተከስቶ ይሸብብሀል፡፡ አንተ ይህ ፀጥታ እንዲሰፍንብህ ማድረግ የሚጠበቅብህ ነገር ቢኖር የሚከሰትበት ሁኔታ ማመቻቸት ብቻ ነው፡፡ ሲመጣ መቀበል፡፡ አፍህን ገጠምና አስተውል፡፡ ፀጥ ለማለት አትሞክር፡፡ ሙከራህ ከጥቂት ደቂቃዎች የበለጠ ፀጥታን አያመጣልህም፡፡ በውስጥህ መንተክተክህን ትቀጥላለህ፡፡ ስለዚህ ሙከራውን ተውና፣ ሁኔታውን ብቻ አመቻች፡፡ አፈሩን አዘጋጅተህ ዘሩን በመትከል ተጠባበቅ፡፡

አእምሮህን ባዶ አድርገህና ስለ ምንም ነገር አታስብ፡፡

አእምሮን ባዶ ለማድረግ ምን ይጠበቅብሀል? ሐሳቦች ዘወትር ይከሰታሉ፡፡ ሲመጡና ሲሄዱ ተመልከታቸው፡፡ ምልከታህ በጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ ተመልካች እንጂ ተሳታፊ እንዳትሆን ተጠንቀቅ፡፡ እነዚህ ስልቶች ከፍተኛ ጥንቃቄን ስለሚጠይቁ ሳትረዳ የቀረኸው ነገር መኖር የለበትም፡፡ ካለዚያ አንድ ቦታ ላይ ልትሳሳት ትችላለህ፡

፣ አለትዮኛ የሚባል ነገር ብትሰጥ እንኳን ነገሩ በሙሉ ትክክለኛ ባህሪውን ይለውጣል።

ስታስተውልና ስትመለከት ያለ ተሳትፎ ከውጪ ሆነህ ነው። ልዩነቱ ምንድን ነው? ለምሳሌ፣ የቤት ጓደኛህን እየጠበቅክ ከሆነ ጥበቃህ ወይንም እፎታህ አንተን ይለቀፈ ነው። በዚህ የተነሳ፣ አንድ ሰው በበርህ አቋርጦ ካለፈ እሷ የመጣች እየመሰለህ ዘለህ ትወጣለህ። ከዚያ ደግሞ፣ ንፋስ ቅጠሎችን ካንኳኳቸው፣ የመጣች እየመሰለህ ልብህ ይዘላል። አእምሮህ በጣም ጉጉ ሆኗል እሷን በመጠበቅ ተጠምደሀል። ይህ ምንም ፋይዳ የለውም። ከመጠን ያለፈ ጉጉትና ንቃት እኔ የምለውን ዐይነት ፀጥታን አያመጣልህም።

ስክነት ይኑርህ። አንድ ወንዝ ዳር ተቀምጠህ ውሀው እየተመመ ሲያልፍ እንደምትመለከተው ማለት ነው። ምንም ዐይነት ጉጉት፣ ችኮላና፣ ትዕግስት ማጣት አይኖርህም። ማንም እያስገደደህ አይደለም። ቢያመልጥህ እንኳን ያመለጠህ ምንም ነገር የለም፡ በቃ እንትና ተመልካች፣ አስተዋይ ነህ። ወንዙ ዳር ተቀምጠህ የሚወርደውን ውሀ እንደምትመለከት ወይም ወደ ሰማይ አንጋጠህ የሚያልፈውን ደመና እንደምትመለከት ዐይነት። ዋናው ነገር የስክነ የመገለል መንፈስ መያዝህ ነው። ይህንን መረዳት አለብህ። ምክንያቱም በዘዋኔ ለመጠመድ ያለን ተነሳሽነት ወደ ጉጉት ወይም ወደተንሰፈሰፈ ተስፋ ወይንም ጥበቃ ሊቀየር ይችላል። ያን ጊዜ መሰረታዊ ነጥቡን እንስተዋለን። ከዋኔም በጀርባ በኩል ዞሮ ያገኘናል። በስክነ የመገለል መንፈስ ተመልከት። አእምሮህን ባዶ አድርገህ፣ ስለምንም ነገር አታስብ።

መስከንህ ብቻውን አእምሮህን ባዶ ያደርገዋል። የዘዋኔ ሞገዶች የአእምሮ ኃይል ሞገዶች፣ የቅብጥብጥነት መንስኤዎች ሁሉ የጊዜ ጊዜ እየተወገዱ በመሄድ በአሊናህ ዙሪያ ገባ ባጠቃላይ ሞገድ-አልባ፣ ነውጥ-አልባ ይሆናል። እንደ ፀጥተኛ ማስታወት ረግቶ መንፀባረቅ ይጀምራል።

ታይሎፓ ሌላም የሚነግረን አለው፡-

ልክ እንደ ክፍት ሸንበቆ ከአካልህ ጋር ተስማማ:: ይህኛው፣ ታይሎፓ ከሚጠቀምባቸው ልዩ ስልቶች መካከል አንዱ ነው:: እያንዳንዱ የጥበብ መምህር ራሱ ብቃት ላይ የደረሰባቸውና ሌሎችንም ለመደገፍ የሚጠቀምባቸው የራሱ የሆኑ ልዩ ስልቶች አሉት:: ይህኛው የታይሎፓ የራሱ ብልሀት ነው:: ውስጡ ክፍት እንደሆነ መቃ ወይም ሸምበቆ ሁኑ በማለት በምሳሌ ይናገራል:: እረፍት ላይ ስትሆኑ፣ ልክ ውስጡ ባዶ እንደሆነ ሸምበቆ የሆናችሁ ያህል ሊሰማችሁ ይገባል:: እውነታውንም ብናየው ከዚህ የተለየ አይደለም፤ አካላችሁ ልክ እንደሸምበቆ ውስጡ ክፍት ነው:: ቆዳችሁ፣ አጥንትና ደማችሁ፣ ሁሉም የመቃው አካል ሲሆኑ፣ ሌላው ሁሉ ግን ባዶ፣ ወና ነው::

ያለ ወሬ ሙሉ ለሙሉ በዝምታ ተውጣችሁ፣ ከክዋኔ ሁሉ ተቆጥባችሁ፣ በሐሳቦች ሞገድ የማይርገበገቡ በተዘጉ ከናፍሮች ሆናችሁ - አእምሮአችሁን በስክን የመገለል መንፈስ ውስጥ ሆኖ ለምንም ነገር መጓጓት በተወ ጊዜ፣ ያን ጊዜ በባዶ መቃነት ስሜት ይሰማችሁ:: ያን ጊዜ ዳርቻ አልባ ኃይል ወደውስጣችሁ መፍሰስ ይጀምራል:: ያን ጊዜ በዚያ ከአእምሮ በላይ በሆነው፣ በህቡዑ፣ በመለኮታዊው ትሞላላችሁ:: ክፍቱ መቃ ወደ ዋሽንትነት ይለወጥና፣ መለኮታዊ በህቡዕ ቅኝት ይጫወተው ይጀምራል:: ክፍት ከሆናችሁ በኋላ፣ መለኮታዊው ወደውስጣችሁ እንዳይገባ የሚገድበው ምንም ነገር አይኖርም::

ከእርምጃ ስልቶቹ ሁሉ ውብ ከሚባሉት አንዱ የሆነውን ይህንን ባዶ ሸምበቆ የመሆን ማሰላሰያ ሞክሩት:: የምታደርጉት ምንም ነገር የለም:: እናንተ ብቻ የተባላችሁትን ሆናችሁ መገኘት ነው፣ ከዚያ ሌላው ሁሉ ይከሰታል:: ድንገት አንድ ነገር ባዶነታችንን ሲሞላው ይሰማችኋል:: እናንተ እንደመሀፀን ሆናችሁ፣ አዲስ ሕይወት ወደውስጣችሁ ዘር ሆኖ እየገባ ነው:: ከዚያም ይህ ባዶ ሸምበቆ ራሱ ሙሉ በሙሉ የሚጠፋበት ቅፅበት ይመጣል::

ልክ እንደወና መቃ ከአካልህ ጋር ተስማምተህ ዘና በል:: (like a hollow bamboo rest at ease with your body) በሌላ አገላለፅ፣ አካልህ ጋር ተስማምቶ ዘና

ማለት፣ መንፈሳዊ ነገሮችን፣ መንግስተ ሰማያትን እና ፈጣሪ አምላክንም ቢሆን ያለመሻትን የሚያመለክት ነው። ፈጣሪ አምላክ ሲፈለግ ወይም ሲሻት አይችልም፣ መሻት ሳያናራችሁ ሲቀር ግን ወደ እናንተ ይመጣል። ነፃነትም ሲሻት አይችልም፤ ምክንያቱም ባርነትን ያመጣው ራሱ መሻት ነው። መሻት በማይናራችሁ ጊዜ እርንት ትወጣላችሁ። መለኮታዊነት ሊሻት አይችልም፣ ከመለኮታዊነት የሚያግደን መሻታችን ነውና። ይህ ሊጋጅና ገዳቢ በተወገደ ጊዜ ግን፣ መለኮታዊነት ድንገት በውስጣችሁ ያብባል፣ ይጎመራል። ፍሬው አሁንም በውስጣችሁ አለ። ባዶ ስትሆኑ እና ቦታውን ሲያገኝ፣ ይህ ፍሬ ድንገት ያብባል።

ታይሉፓ እንዲህ ይላል፡-

ልክ እንደወና መቃ ከአካላችሁ ጋር በመስማማት ዘና በሉ። ሳትሰጡና ሳትቀበሉ፣ አእምሯችሁን አሳርፉት።

ምንም ምስጥር ነገር የለም፣ የሚገኝም ምንም ነገር የለም። ሁሉም ነገር እንደሆነና እንዳለው፣ ምንም ለውጥ ሳያሻው በራሱ መልካም ነው። መስጠትና መቀበል አያስፈልግም። እናንተም እንዳላችሁት ምንም ለውጥ ሳያሻችሁ፣ በራሳችሁ እንከን አልባ ናችሁ።

ይህ የምስራቅ ዓለም ትምህርት በምዕራባውያን ዘንድ እጅግ የተሳሳተ ግንዛቤ ሲሰጠው ይታያል። ምክንያቱም ምዕራባውያኑ ሲናገሩ፣ «ይህ ምን ዐይነት ትምህርት ነው? ይህንን በመከተል ሰዎች ለኑሮ መጣራቸውን ያቆማሉ፣ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ለመድረስ አይሞክሩም። ባህሪያቸውን ለመለወጥ ወይም የክፋት መንገድን ትተው መልካም መንገድን ለመከተል ምንም ጥረት አያደርጉም። ይህንን ትምህርት ስተከተሉ፣ የዲያብሎስ ሰለባ ሊሆኑ ይችላሉ።» በማለት ነው። በምዕራቡ ዓለም፣ ዋናው መሪሕር «ራስህን አሻሽል!» የሚለው ነው። የዚህች ዓለምም ይሁን የሆኖው ዓለም ሕይወታችንን ማሻሻል፣ ዋና እና ቀዳሚ ተግባር ተደርጎ ይወሰዳል። የተለያዩ የሕይወት ዘርፎችን እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ይሰበካል። እንዴት

በበለጠ ስኬታማ መሆን ወይም የተሻለ ነገር ማግኘት እንችላለን? የሚለውን ጥያቄ የሚመልሱ ትምህርቶች በስፋት ይሰጣሉ።

በምስራቁ ዓለም ደግሞ፣ ጥያቄውን በበለጠ ጥልቀት እንረዳዋለን። ይህ ለ...መሆን... የሚደረግ ጥረት በራሱ፣ ገዳቢ ወይንም አጋጅ መሆኑን ተረድተናል። ምክንያቱም ቀድሞ ነገር ሕልውናችሁ ከእናንተው ጋር ነው። በተፈጠራችሁ ጊዜ ሕልውና ይዟችኋል፣ ሆናችኋል። ሌላ ምንም ነገር መሆን አያስፈልጋችሁም። ማን እንደሆናችሁ ብቻ አስተውሉ፣ በቃ። በውስጣችሁ ተሸሽጎ ያለውን ማንነት ብቻ አስተውሉ።

ዳሩ ግን፣ የምታሻሽሉት ምንም ይሁን ምን፣ የማሻሻል ሕይወትን መኖራችሁ፣ ለቀቀንና ጭንቀት እንዳይለዩዋችሁ ያደርጋል። ምክንያቱማ፣ ለመሻሻል ወይም በልጦ ለመገኘት የምታደርጉት ጥረት በራሱ በተሳሳተ መንገድ እየወሰዳችሁ በመሆኑ ነው። መጪውን ጊዜ፣ ግቦችንና ዓላማዎችን እንዲሁም የሕይወት መርሆችን ጥልቅ ደረጃ ላይ የሚያስቀምጥ ነው። ሕሊናችሁ ለእነዚህ ነገሮች ትልቅ ቦታ ከሰጠ፣ ያለ ጥርጥር ከፍላጎት ጋር የሚኖር ይሆናል።

ፍላጎት እስካላችሁ ድረስ ታጣላችሁ። በማግኘትና በመሆን ፍላጎት ውስጥ ለሚገኝ፣ እውነት አትገለጥም። መሻታችሁ እየበረደ ሄዶ፣ የስክነ ያለመሻት ባህር ውስጥ በገባችሁ ጊዜ ግን፣ ድንገት ሳትጠብቁት ፈላጊዎች በእግር በፈረስ የሚያስሱትን ሁሉ እዚያው እናንተው ዘንድ ታገኙታላችሁ። ያን ጊዜ እንደ ቡድሃዲርማ፣ ሆዳችሁን እስኪያማችሁ ትስቃላችሁ። የቦድሂዳርማ ተከታዮች እንደሚሉት ከሆነ፣ ዳግመኛ በፀጥታ ውስጥ ስትሆኑ፣ እያምባረቀ የሚንከተከተውን የቦድሂዳርማን የሳቅ ድምፅ መስማት ትችላላችሁ። እስከአሁን እየሳቀ ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መሳቁን አላቋረጠም። መጀመሪያ የሳቀው እንዲህ እያለ ነበር፣ «ይህ ምን ዐይነት ቀልድ ነው? አሁን ልትሆኑት እየሞከራችሁት ያለውን፣ ቀድሞ ነገር የሆናችሁትን ነው። ታዲያ፣ ቀድሞ የሆናችሁትን ልትሆኑ በመሞከር እንዴት

ሕይወት ማግኘት ትችላላችሁ፤ ውድቀታችሁ ምንም አያጠራጥርም። የሆናችሁትንስ እንዴት መሆን ትችላላችሁ? እያለ በርናርድ ሻው ሳቀ፤ ከት እያለ ሆዱን ይዞ ሳቀ።

በርናርድ ሻው፣ ላኦትዙ በኖረበት ዘመን የነበረ ሰው ነው። ሁለቱ ይተዋወቁም ይሆን ይሆናል። በአካል ላይሆን ይችላል፤ ግን ሁለቱም ተመሳሳይ ሰላም ማግኘት ስለነበራቸው መተዋወቃቸው የግድ ነው።

ላኦትዙ እንዲህ ይላል፦

ሳትስሙና ሳትቀበሉ፣ ለእምነቶቻችሁን አሳርፉ። ማህሙድራ ከየትኛውም ነገር ጋር እንደማይቆራኝ ሕሊና ነው።

ስለዚህ ካልተቆራኛችሁ ወይም ምንምንት ከእናንተ ጋር ከሆነ ተሳክቶላችኋል።

ማህሙድራ ከየትኛውም ነገር ጋር እንደማይቆራኝ ሕሊና ነው።

በዚህ መሠረት ብትለማመዱ፣ ከዚያ በኋላ ቡድሀነት ላይ ትደርሳላችሁ። ታዲያ የምንለማመደው ምንድን ነው? በየጊዜው በበለጠ ዘና ማለትን። በዚህች ጊዜና ቅፅበት ላይ በበለጠ እየተገኘን መኖርን። በድርጊት ላይ በበለጠ እየተሳተፍን መምጣትን እና ከክዋኔ እየተላቀቅን መኖርን። የተሻለ ወናነት፣ ባዶነት እና ተሳትፎ አልባ አስተውሎት እያዳበርን መምጣትን። ያለ ምንም የመጓጓትና የቁጭት ስሜት፣ ምንም ነገር ይፈጠራል ወይም ይገኛል ብለን ሳንጠብቅ፣ ያለምንም ፍላጎት መኖርና መቀጠልን። በሆነውና በተሰጠን ማንነት መደሰትን መለማመድ አለብን።

ከዚህ በኋላ፣ ነገሮች ፍሬያማ ሆነው የሚያሸቱበት ትክክለኛው ወቅት ሲደርስ ባልተጠበቀች አንዲት ድንገተኛ ቅጽበት ላይ ወደ ቡድሀነት ትጎመራላችሁ።

# ከተፈጥሮ ጋር ተስማምተህ ተራመድ

የፈጠራ ክህሎት ለማንገቤ እጅግ አስቸጋሪ የሕልውና እና የንቃተ-ሕሊና ድባብ ነው። ያለ ድርጊት የሚወሰድ እርምጃ ነው። ላኦ ትዙ wei- wu-wei (ዌ - ው-ዌ) ብሎ ይጠራዋል። አንድ ነገር በአኛ መሳሪያነት እንዲፈጠር መፍቀድ ማለት ነው። የማድረግ ሳይሆን የመፈተድ ሂደት ነው። ባዶ መቃ መሆን ማለት ነው።

ይህን ጊዜ ከመቅፅበት አንድ ነገር መከሰት ይጀምራል። ምክንያቱም ከሰው በስተጀርባ ፈጣሪ ተሸሽጓል። ትንሽ መንገድ ብትሰጡት በእናንተ ውስጥ ሥራውን ይሰራል። የፈጠራ ክህሎት ማለትም ይኸው ነው። ፈጣሪ እንዲከሰት መፍቀድ ነው። የፈጠራ ክህሎት መንፈሳዊ ሁናቴ ነው።

ለዚህም ነው፣ አንድ ገጣሚ ከአንድ የሃይማኖት ሊቅ የበለጠ ለፈጣሪ አምላክ ይቀርባል የምለው። ከሁሉ ይልቅ ከፈጣሪ ርቆ የሚገኘው ፈላስፋው ነው፣ ምክንያቱም ሐሳብህ በጨመረ መጠን በራስህና በምሉዕ መካከል የምትገነባው ግድግዳ እያደገ ይሄዳል። ሐሳብህ በጨመረ መጠን እኔነትህ እያደገ ይሄዳል። እኔነትህ ባለፈው ጊዜ ያከማቸሃቸው አሳቤዎች ስብስብ ነው። አንተ ሆነህ በማትገኝበት ጊዜ ደግሞ፣ ፈጣሪ ሆኖ ይገኛል - የፈጠራ ክህሎት ይህ ነው።

የፈጠራ ክህሎት በቀላሉ ሲገለፅ፣ በሁለንተናዊ መዝናናት ውስጥ መሆን ማለት ነው። ያለ ድርጊት መቀመጥ ማለት ሳይሆን በመዝናናት መንፈስ ውስጥ መሆን ማለት ነው። ምክንያቱም ከመዝናናት ከፍተኛ የሆነ የድርጊት ድባብ ሊወለድ ይችላል። ይህ ድርጊት ግን የአንተ ድርጊት አይደለም። አንተ የአድራጊው መሳሪያ ነህ። አንተ ያልፈጠርከ፣ ከዚህች ዓለም ወዲያ የመጣ ዜማ በአንተ በኩል መቀኘት ይጀምራል። ይህ ዝማሬ የሚመጣው ከወዲኛው ዓለም ነው። የፈጠርከው አንተ ብትሆን ተራና የማይጥም ትንት ይኖረው ነበር። በአንተ በኩል ሲመጣ ግን ከህቡዑ ዓለም አንድ ነገር ይዞ ነው።

ታላቁ ባለቅኔ ኮሊሪጅ በሞት በተለየ ጊዜ በሺህ የሚቆጠሩ ግጥሞችን ሳያጠናቅቅ ነበር። በሕይወት ዘመኑ «እነዚህን ግጥሞች ለምን አታጠናቅቃቸውም?» እየተባለ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ነበር። ምክንያቱም አንድ ወይም ሁለት መስመር ብቻ የሚቀራቸው ብዙ ግጥሞች ነበሩ።

እሱም ሲመልስ፣ «ላጠናቅቃቸው አልችልም። ሞክሬ ነበር፣ ግን ሳጠናቅቃቸው አንድ ነገር ይጎድላቸዋል፣ አንድ ስህተት ይኖራቸዋል። ስንኝ፣ በእኔ በኩል ከሚመጣው ከዚያኛው ትንት ጋር አይጣጣምም። እንደመሰናከል ሆኖ የትንቱን ፍሰት ያስተጓጉለዋል። ስለዚህ እሱን መጠበቅ ግዴታ ይሆንብኛል። በውስጤ ሊፈስ የቆየው ያ ኃይል ዳግመኛ መፍሰስ ጀምሮ፣ ራሱ የጀመረውን ቅኔ በሚቋጨው ጊዜ ካልሆነ በስተቀር፣ ከዚያ በፊት ሊቋጭ አይችልም።» በማለት ነበር።

ያጠናቀቃቸው ቅኔዎች ጥቂት ብቻ ነበሩ። እነዚያ ቅኔዎች ግን እፁብ ውበት ነበራቸው። ታላቅ ሀቡዓዊ ድንቅነትን ያዘሉ ናቸው። በወትሮም ቢሆን ይህ ሁኔታ ሲስት ይታያል፡- ልክ ባለቅኔው ሲጠፋ የፈጠራ ክህሎት ትመጣለች። ይህን ጊዜ ባለቅኔው ሌላ መንፈስ ይሰፍንበታል፡ የፈጣሪ መንፈስ ሲሰፍንበት በፈጠራ ክህሎት ይሞላል።

ሳይመን ዲ ቧውቮ የሚከተለውን ተናግሮ ነበር፤ «ሕይወት ራሷን በማስቀጠል እና ከራሷ ተሻግራ በመገኘት ተግባር ተጠምዳ ትገኛለች፤ ራሷን ከማቆየት ሌላ ምንም ባይቻላት ኖሮ፤ መኖር ካለመሞት ያለፈ ትርጉም አይኖረውም ነበር።» እናዚህም የፈጠራ ክህሎት የሌለው ሰው የሚኖረው ላለመሞት ብቻ ነው፤ ቢቃ። ሕይወቱ ጥልቀት የለውም። ሕይወቱ ከመጠንሰስ ሌላ ገና አልተጀመረችም። መውለዱ እውን ቢሆንም፤ ግን ሕያው አይደለም።

የፈጠራ ክህሎት ሲኖረን፤ ማለትም ፈጠራ በእኛ ውስጥ እንድትከሰት ስንፈቅድላት፤ ያን ጊዜ የራሳችን ያልሆነ መዘመር መቀኘት እንጀምራለን። ይህንን መዘመር «የራሴን ነው» ብለን ፊርማችንን ልናሰፍር አንችልም። ይህን ስታገኝ ሕይወት ክንፎች አውጥታ፤ ከፍ ከፍ ትላለች። ይህ ከራስ በላይ የመሆን ሂደት የሚገኘው ፈጠራ ውስጥ ነው። ካለዚያ ግን ራሳችንን ከማስቀጠልና ሕይወታችንን ከማቆየት በላይ የምንደርስበት ነገር የለም። ልጆች እንወልዳለን፤ ልጅ መፍጠር ግን ከማቆየት በላይ የምንደርስበት ነገር የለም። ልጆች እንወልዳለን፤ ልጅ መፍጠር ግን የፈጠራ ክህሎት አያሻውም። እኛ ስንሞት ልጃችን ደግሞ ራሱን ለማቆየት ይኖራል። ዱሩ ግን ራሳችንን መብለጥ እስካልጀመርን ድረስ ራስን ማቆየት ብቻ በቂ አይደለም። ይህ ልህቀት የሚመጣው ደግሞ፤ ከዚህ ዓለም ወዲያ ከሚገኝ አንድ ነገር ጋር ግንኙነት ሲኖረን ነው።

የንጥቀት (transcendence) ዋነኛ ነጥብም ይኸው ከራስ ልቆ መገኘት ነው። በልህቀት ሂደት ውስጥም አንድ ተዓምር ይፈጠራል፡- አንተ አንተን አይደለህም፤ ግን ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ አንተ ትሆናለህ።

የጥበብ ውስጣዊ ፍሬ ነገር ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ መራመድ ነው። የሁሉም ታላላቅ መንፈሳዊያን ስምሳ፣ ላኦትዙ፤ ቡድሃ፤ ባሃውዲንን ሶሳን፤ ሳናይ . . . መልዕክት ከተፈጥሮ ጋር ህብር ፈጥረን እንድንራመድ ነው። እንስሶች እስበውበት ባይሆንም ከተፈጥሮ ጋር ተስማምተው ይኖራሉ። የሰው ልጅ ግን እስበውበት ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ መራመድ ይኖርበታል። ምክንያቱም ሰው ንቃተ ሕሊና አለው፤ ስለዚህ ከተፈጥሮ ጋር ሳያብር መራመድን የመምረጥ ነፃነት አለው። ታላቅ ኃላፊነቱም እዚህ ላይ ይሆናል።

የሰው ልጅ ኃላፊነት አለበት - ኃላፊነትን የታደለ የሰው ልጅ ብቻ ነው። የታላቅነቱ ምስጢርም ይኸው ነው። ሌላ የትኛውም እንስሳ ኃላፊነት የለውም። በቃ ከተፈጥሮ ጋር በአንድነት ይኖራል፣ ከተፈጥሮ የሚያፈነግጥበት ምንም መንገድ

የለውም። እንስሳ ልቡን ደስ እንዳለው መሆን አይችልም። ግና ንቃተ-ሕሊና ባለማግኘቱ የማማረጥ ነፃነትም ሆነ እንደልቡ የመሆን ስልጣንን አላገኘም። አሰራሩ እናንተ በእንቅልፍ ዓለም ውስጥ ካላችሁ አሰራር የተለየ አይደለም።

በተለየ እንቅልፍ ላይ ስትሆኑ እናንተም ብትሆኑ ከተፈጥሮ ጋር ሕብር ይኖራችኋል። በዚህ የተነሳም ነው፣ ጥልቅ እንቅልፍ ከፍተኛ መንፈስን አዳሽነትና አዝናኝ ኃይል ያለው። የጥቂት ደቂቃዎች ጥሩ እንቅልፍ ብቻ አፍላ መንፈስ ይዛችሁ ትነሳላችሁ። ስትሰበሰቡት የዋላችሁትን ጥቀርሻ ስሜት እና ድብርት ይተነናል። ከምንጩ ጋር ተገናኝታችሁ ተመልሳችኋልና።

ይህ ግን ምንጩን የመገናኛ እንስሳዊ ዘዴ ነው። እንስሶች የእግድሞሽ ሰው ደግሞ የቁም ነው። እናንተም ወደ እንቅልፍ ዓለም ለመግባት በአግድሞሽ መንጋለል አለባችሁ። በቆማችሁበት መተኛት አይቻልም ወይም በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። ይህንን ለማድረግ ወደ ኋላ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዓመታትን ሄዳችሁ እንደ እንስሳ መሆን አለባችሁ። እናንተ የመሬት ትይዩ አግድሞሽ ስትሆኑ ድንገት ንቃተ-ሕሊና ማጣት ትጀምራላችሁ፣ ከዚያ በኋላ ኃላፊነት የለባችሁም።

በዚህ የተነሳ ነበር ሲግመንድ ፍሮይድ አግዳሚ ሶፋ ወንበርን ለታካሚ መኝታነት የመረጠው። ለታካሚው ምቾት ሳይሆን ለዘዴ ነው። ታካሚ በአግድሞሽ ከሆነ በኋላ ኃላፊነት ማጣት ይጀምራል። እንዲሁም ነገሮችን ለመናገር ሙሉ ነፃነት እስካሳገኘ ደረስ ያላሰበባቸውን ነገሮች አይናገርም። በቁም ወይንም በቁመቱ ከሆነ ኃላፊነት ስለሚኖረው እንድን ነገር ልናገር አልናገር ብሎ ያለማቋረጥ ያስባል። ሳንሱር ያደርጋል። ሶፋ ወንበር ላይ በአግድሞሽ ሲተኛ ግን እንደ እንስሳ ይሆናል፣ አሁን ኃላፊነት የለበትም። በሥነ-ልቦና ባለሙያው ከዚህ በፊት ለማንም ተናግሯቸው የማያውቃቸውን ነገሮች መለፍለፍ ይጀምራል። በጥልቅና ድብቅ ሕሊናው ውስጥ ያሉት ነገሮች ሁሉ ወደላይ ይወጣሉ። ታካሚዎችን ልክ እንደ እንስሳ ወይንም እንደ ሕፃናት ረዳት አልባ የሚያደርገው የፍሮይድ የሕክምና ስልት ይህ ነበር።

ልክ ከኃላፊነት ነፃ ስንሆን ተፈጥሮአዊ እንሆናለን። ይህ የሳይኮቴራፒ መስክ ትልቅ እመርታ ነበር፣ ምክንያቱም መዝናናትን ይፈጥርብሃል። የደበቅከው እና ያደፈንከው ሁሉ ዳግመኛ ይወጣል፣ ከወጣ በኋላ ይተንናል። በሳይኮቴራፒው ሂደት ማለትም በሳይኮአናሊስስ ውስጥ ካለፍክ በኋላ ወደ ተፈጥሯዊ ማንነትህ እየቀረብክ ትሄዳለህ። የጤናማነት ትርጉሙ ይህ ነው።

# አምስቱ መሰናክሎች

ተፈጥሮ ለሁላችንም የተፈጠረ ክህሎትን የሚያላብስ ኃይል ትሰጣለች።

ይህ ኃይል አውዳሚ የሚሆነው በሚሰናከልበት ወይም ተፈጥሯዊ ሂደቱ በሚደናቀፍበት ጊዜ ብቻ ነው።

## 1. ግሉ-ንቅ-ሕሊናዊነት (Self-consciousness)

በተቀራራቢ ትርጉሙ ግሉ-ንቅ ሕሊናዊነት በማለት የፈታሁት ቃል በእንግሊዝኛው ስለራስ በተለይ በአሉታዊ መልኩ ማሰብንን፣ መስጋትን፣ ከሌሎች የተለየ ማንነት ወይም ከሌሎች የተለየና ያልተለመደ ሥፍራ ላይ ተገኝቻለሁ ብሎ ከማሰብ የሚመነጭ የይሉኝታ ፍራቻን የሚያመለክት ቃል ነው። ይህንን በልቦናችን ይዘን ወደ እሾ እንመለስ።

ግሉ-ንቅ-ሕሊናዊነት በሽታ ነው። ንቃተ-ሕሊናዊነት ጤና ሲሆን ግሉ-ንቅ-ሕሊናዊነት ግን አንድ ስህተት መኖሩን የሚያመለክት ችግር ወይም በሽታ ነው። በማንነት ላይ አንድ ቋጠሮ ወይም አንድ ያፈነገጠ ባህሪይ መፈጠሩን ያሳያል። የንቃተ-ሕሊና ፍልሰት ተፈጥሮአዊ ወይንም ትክክለኛ አይደለም ማለት ነው። በዚህ የንቃተ-ሕሊና ወራጅ ወንዝ ውስጥ የተቀላቀለ፣ ከወንዙ ጋር መጣጣም ያልቻለ፣ የወንዙ አካል መሆን የማይችል ባዕድ ነገር አለ።

ግሉ-ንቅ-ሕሊናዊነት፣ ጤናማ ያልሆኑ አስተሳሰቦችን እምነቶችን መያዝን ያሳያል። ግሉ-ንቅ-ሕሊናዊነት፣ የደነዘዘና የተደፈነ የአእምሮ ሁኔታ ነው። መንቀሳቀሻ አጥቶ በመርጋት፣ እየተነነና እየሞተ እንደሚገኝ ቆሻሻ ኩሬ ነው። እንጆታ ያለ ጥርጥር ይለማናል።

ስለዚህ ከሁሉ በፊት ግንዛቤን ማግኘት ያለበት በግሉ-ንቅ-ሕሊናዊነትና በንቃተ-ሕሊናዊነት መካከል ያለው ልዩነት ነው።

ንቃተ-ሕሊናዊነት «እኔ» የሚለው የኢጎ (የግላዊነት) መንፈስን አያውቀውም። የአንድ ሰው ከአካሉና ባሕሪያዊ የተገነጠለ ማንነት አይገባውም። ምንም ዐይነት ዝላ አያውቅም። ዳርቻዎች የሉትም። ከአካሉ ጋር አብሮ፣ በጥልቅ የአሃዳዊነት

ጊዜና ቦታ ላይ ይገኛል። በዐሐዱና በምልዑ መካከል ምንም ዐይነት ግጭት የለም። እሃዱ ወደምሉዑ፣ ምሉዑ ደግሞ ወደአሃዱ በፍሰሰት ላይ ይገኛሉ። ልክ እንደ እስትንፋስ ነው። ትንፋሽ ስታስገባ፣ ምልዓተ ወደ አንተ ይገባል፣ ትንፋሽ ስታስወጣ ደግሞ አንተ ወደ ምሉዑ ትገባለህ። የማያቋርጥ ፍሰሰት፣ የማያቋርጥ ማጋራት ነው። ምልዓ ሳያሰልስ ይሰጥሃል። አንተም ሳታሰልስ ለምልዓ ትሰጣለህ። ይህ ሚዛን ዝንተ-ዓለም ሳይዛባ ይኖራል።

ዳሩ ግን በግለ-ንቅ-ሕሊናዊው ሰው ዘንድ የተበላሸ አንድ ነገር አለ። ያስገባል ግን መቼም አውጥቶ አይሰጥም። መሰብሰቡንና ማከማቸቱን በመቀጠሉ የተነሳ ማጋራት የተሳነው ሆኗል። ማንም ጥሶ እንዳይገባበት በሚል ዘወትር በዙሪያው ግንብ መገንባቱን ተያይዞታል። በማንነቱ ዙሪያ፣ «መግባት ክልክል ነው።» የሚሉ ምልክቶችን መለጠፉን ቀጥሏል። የኋላ ኋላም እንደ መቃብር ይሆናል፣ የሞተ ማንነት / ሕላዌ ይኖረዋል። ምክንያቱም ሕያውነት እና ማጋራት የማይነጠሉ ናቸው።

ማንነት በስም ብቻ ሕያው የሆነ፣ የሞተ ነገር ነው። ንቃተ-ሕሊና ዳርቻ-አልባ ሕይወት፣ በረከት የሞላበት ሕይወት ነው። ገደቦች የሉትም። ዳሩ ግን ማንኛውም ሰው በተለምዶ ግለ-ንቅ-ህሊናዊ ሆኖ እናገኘዋለን።

ግለ-ንቅ-ሕሊናዊ መሆን ህሊና መሳት እንደማለት ነው። ይህ አደናጋሪ ሐሳብ ግንዛቤን ማግኘት አለበት፣ ግለ-ንቅ-ሕሊናዊ መሆን ህሊና መሳት ሲሆን፣ የዚህ ተቃራኒ ግን፣ ማለትም «ኢ-ግለ-ንቅ-ሕሊናዊ መሆን ደግሞ ንቃተ-ሕሊናዊ መሆን ነው። ስለዚህም ይህ ግለ-ማንነት፣ ይህ እዚህ ግባ የማይባል አናሳ ማንነት በሚጠፋበት ጊዜ እውነተኛና የተከበረውን ማንነትን እንቀዳጃለን። ይህንን ማንነት ታላቁ ማንነት ወይም የማንነቶች ሁሉ ማንነት ብለን መጥራት እንችላለን።

በዚህ የተነሳ፣ ታላቁ ማንነት ሁለት ባህሪያት ይኖሩታል። የራሳችን ብቻ የሆነ ማንነት ስላይደለ፣ ከዚህ አኳያ «ያልሆነ-ማንነት» ወይም «የሌለ-ማንነት» ወይም «ባዶ-ማንነት» (no-self) ሆኖ እናገኘዋለን። ምክንያቱም ታላቁ ማንነት የሕልውና ሁሉ ማንነት ነው። የራሳችሁን ደቂቅ ማንነት ወዲያ በመጣል፣ ከሕልውና ሁሉ

ማንነት ጋር ትዋሃዳላችሁ:: ይህንን ጊዜ ድንገት አፅናፍ-የለሽ ትሆናላችሁ፣ ድንገት ከገደብ ነፃ ትሆናላችሁ፣ በሕልውናችሁ ዙሪያ የከበባችሁ አጥር ይናድና አፅናፍ-የለሽ ኃይል በውስጣችሁ መመላለስ ይጀምራል:: ምንም እገዳዎች የማይከልሉት፣ የአፅናፍ የለሹ መሳሪያ ትሆናላችሁ:: ዘለዓለማዊው ኃይል የሚዘምርባችሁ ዋሽንት ትሆናላችሁ:: የራስ የሆነ ምንም ነገር የሌላችሁ፣ ከመተሳሰሬያነት በስተቀር የባዶነት ሕልውና ብቻ ያላችሁ ትሆናላችሁ:: መንበርከክ ብዬ የምጠራው ይህንን ነው::

ግሉ-ንቅ-ሕሊናዊነት የማይንበረከክ ወይንም እጅ የማይሰጥ አቋምን ይወክላል:: ይህ አቋም የግጭት፣ የፍልሚያ፣ የትግል አቋም ነው:: ከሕልውና ጋር ከተዋጋችሁ ግሉ-ንቅ-ሕሊናዊ ትሆናላችሁ:: በተደጋጋሚ ሽንፈትን መቅመሳችሁ አይቀሬ ይሆናል:: እያንዳንዷ ርምጃችሁ ተጨማሪ ሽንፈቶችን ይዛ ትመጣለች:: የተስፋችሁ መጨጨጥ የማያጠያይቅ ይሆናል፣ ምክንያቱም በዚህ ማንነታችሁ ከሕልውና ሁሉ ጋር እየታገላችሁ መቆየት አትችሉም:: ይህ በፍፁም የማይቻል ነው፣ ተነጥላችሁ ብቻችሁን ሕልውና ሊኖራችሁ አይችልም:: ባህታዊ መሆን አትችሉም::

ይህ ባህታዊ የሚለው ቃል «monk» ጥሩ ቃል ነው:: የእንግሊዝኛው ፍቺ ተመሳይ ሥርው-ቃል ያላቸውን፣ ለምሳሌ monopoly («የግል ንብረቴ ይዞታ) monologue «የብቻ መነባንብ» ወዘተ ይመሰርታል:: ባህታዊ ማለት ገደቦችን ለመወሰን፣ የብቃቱን ጫፍ ለመለካት የሚሞክር፣ ከምሉዑ ሕልውናው ተነጥሎ ለመኖር የሚጥር ግለሰብ ነው:: ጥሩ ባጠቃላይ ወይራሱ ብቻ የተነጣጠረ ነው:: ውድቀቱ አሌ የማይባል በመሆኑ የተነሳ መቼም ቢሆን ሊሳካለት የሚችል ባህታዊ አይኖርም::

ከፈጣሪ አምላክ ጋር ሆነህ ብቻ፣ እንጂ ከእሱ ተጣልተህ ሊሳካልህ አይችልም:: ከምሉዑ ጋር ሆነህ ብቻ፣ እንጂ ከምሉዑ ከአሃዱ ተነጥለህ ሊሳካልህ አይችልም:: ስለዚህ በተስፋ ማጣትና በጥልቅ ጭንቀት ውስጥ ስትገባ አንድ ነገር አስታውስ:: ጭንቀትህን የፈጠርከው አንተ ራስህ መሆንህን:: የምትፈጥረውም፣ ከአሃዱ ጋር የምትጋጭበት ወቅት ነው::

በአንድ የክረምት ወቅት ነው። በሚጥለው ኃይለኛ ዝናብ የተነሳ መንደራችን በውሃ ይጥለቀለቃል። የመንደሩ ሰዎች እየሮጡ ወደ ሙላ ናስሩዲን ይመጡና እንዲህ ይሉታል፣ «ሚስትህ ወንዝ ገብታ ጎርፍ እየወሰዳት ነው። ቶሎ ብለህ ሄደህ አድናት!»

ናስሩዲን እየተክለፈለፈ ሄዶ ከሉ ወንዙ ውስጥ ከዘለ በኋላ ከጎርፉ አቅጣጫ በተቃራኒ መዋኘት ይጀምራል። ሰዉሬ የተሰበሰበው ሰፈርተኛም፣ «አንተ ናስሩዲን ምን እየሰራህ ነው? ሚስትህ ወደ ላይ መሄድ አትችልም፣ ጎርፉ ወደታች ነው የወሰዳት!»

እያለ ይጮህበት ጀመር።

ናስሩዲንም ሲመልስ፣ «ምንድነው የምታወሩት? እኔ ሚስቴን አውቃታለሁ፣ በተቃራኒው አቅጣጫ እንጂ በሌላ አቅጣጫ መሄድ አትችልም» ብሎ አሳያቸው።

እኔነት፣ በውትርም ቢሆን በተቃራኒው አቅጣጫ ለመሄድ ጥረት ያደርጋል። ሰዎች ቀላል ነገሮችን ማድረግ አይወዱም። ነገሮችን ማድረግ ከመቻላቸው በፊት ፈታኝ እንዲሆኑ ቅርፅ ሊሰጧቸው ይፈልጋሉ። ሰዎች ፈታኝ ነገሮችን ማሸነፍ ያስደስታቸዋል። ለምን? ምክንያቱም ከባድና ፈታኝ ነገር ሲገጥመን፣ እኔነታችን (ego) ማንነቱን የሚያስመሰክርበት ፈተና በማግኘቱ ይደሰታል።

የኤቨረስትን ተራራ ለመውጣት መጀመሪያ የሞከረው ሰውዬ ተራራው ጫፍ ከደረሰ በኋላ አንድ ሰው የሆነን እለት ከወረደ መልስ አድመጋቹን ሲጠይቀው፣ «ይህን የመሰለ አደገኛ ነገር ለማድረግ ምን አነሳሳህ? ከአንተ ቀደም ብለው የሞከሩት ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል።» በማለት ጠይቆት ነበር። ሰውየው፣ ሰዎች ለምን ኤቨረስትን ለመውጣት በመሞከር ሕይወታቸውን የሚያጠፉበትን ምክንያት መረዳት ባለመቻሉ ነበር መጠየቁ። ምንድን ነው ትርጉሙ? ምን የሚገኝ ነገር አለ?

አድመጋቹ ሲመልሱ፣ «ይህ ኤቨረስት ድል እስካላደረግ ድረስ እረፍት ለማግኘት አልችልም። ኤቨረስትን ድል መንሳት አለብኝ» ብሎ መለሰለት ይባላል። ድል

በመንሳቱ የሚያስገኘው ምንም ነገር የለም፣ ግን ድል ያልተደረገ አሸረሰት የሚባል ተራራ መኖሩ ብቻ ፈተና ነው። ፈተናውስ የማነው? የኢጎ/የእኔነት ነው።

የየራሳችሁን ሕይወት ብታስተውሉ፣ በኢጎ የተነሳ ብቻ የምታደርጓቸው ብዙ ነገሮች መኖራቸውን ትመለከታላችሁ። ትልቅ ቤት መስራት ትፈልጉ ይሆናል። በአሁኑ ቤታችሁ ውስጥ ምንም የጎደለባችሁ ምቾት ባይኖርም፣ በቃ ትልቅ ቤተ-መንግስት ልታደርጉት ትፈልጋላችሁ። ይህ ግዙፍ ቤተ-መንግስት ግን ለእናንተ ሳይሆን ለኢጎዎች ነው። የምታገኙትና ባላችሁ ገንዘብ እንደልባችሁ መኖር እየቻላችሁ፣ ግን ተጨማሪ ገንዘብ ማጠራቀማችሁን ትቀጥላላችሁ። ይህ ገንዘብ ታዲያ የእናንተ ሳይሆን የኢጎዎች ነው። በዓለም ላይ ተወዳዳሪ የሌላችሁ ሀብታሞች እስከልሆናችሁ ድረስ እፎይ ብላችሁ መቀመጥ አትችሉማ!

ግን በዓለም ወደር የሌለው ሀብታም በመሆንህ ምን ታተርፋለህ? ስቀትህ እየጨመረ ይመጣል፣ ምክንያቱም ከግጭት ስቀትን እንጂ ሌላ ምንም አይገኝም። ስቀትንና ጭንቀት ግጭት ውስጥ የመገኘት ምልክቶች ናቸው። ስለዚህ ኃላፊነትህን በሌላ ነገር አታባክነው። ሰዎች ሰበብና ምክንያት በመፍጠር የሚችላቸው የለም። መከፋት ከተሰማቸው፣ «ምን ማድረግ እንችላለን? የሚያስከፋን ያለፈ ሕይወታችን ካርማ ነው።» ይላሉ። ትርጉም የሌለው ባዶ ምክንያት። ያለፈ ሕይወት ካርማ ምናልባት ባለፈው ሕይወታችሁ አስከፍቷችሁ ይሆናል! እስከ አሁን ምን አስጠበቃችሁ! የሚያስከፋችሁ የአሁኑ ሕይወታችሁ ካርማዎች ናቸው። ባለፈ ሕይወታችን ላይ ማሳበቡ ስለሚቀል ነው። ታዲያ ምን ማድረግ ትችላላችሁ? እንደሆናችሁት መሆን ብቻ! ምንም የሚደረግ ነገር የለም። ያለፈውን ጊዜ መለወጥ አይቻልም። ሂድልኝ ብላችሁ እጃችሁን በማወናጨፍ ብቻ ልታስወግዱት አትችሉም። ያለፈውን ለመሻር የሚጠቅም ምንም ዐይነት ምትሃት የለም። ተፈጥሯል፣ የተፈጠረው ላይሻር ነው። አሁንም ፀንቶ ይቆያል እንጂ ልትለውጡት የምትችሉበት ዕድል የለም። ይህ እውነታ፣ ከሸክሙ ነፃ ያወጣችኋል፣ «በቃ ይሁን፣ የተከፋሁት ያለፈው ካርማ በሚፈጥርብኝ ስቀትን የተነሳ ነው።» በማለት እንድታስቡ ያደርጋችኋል።

ኃላፊነቱን ለዲያብሎስ አሸከማችሁ፤ እንደ ክርስቲያኖች ማድረጋችሁን ትቀጥላላችሁ። ሒንዱዎች፤ ኃላፊነቱን ለካርማዎች ክርስቲያኖችም ኃላፊነቱን ለዲያብሎስ ማሸከማቸው ይቀጥላሉ። ወጥመድ የሚጠምድባችሁ እሱ ይሆናል። እናንተ አይደላችሁም። እያጠመደ ወደ ሰቀቀን የሚያስገባችሁና ወደ ገሃነም የሚጎትታችሁ እሱ መሆን አለበት።

ማነው እናንተን ስራዬ ብሎ የሚከታተል? ታድዬ ይሄ ሰይጣን የሚባል ነገርስ፣ ለምን ይረብሻችኋል?

ማርክሲስቶች፤ ሶሻሊስቶች፤ ኮሚውኒስቶች ይመጡና፦ በሰዎች ላይ ሀዘንና ሰቀቀን የሚፈጥሩት ማህበራዊ መዋቅሩና ኢኮኖሚያዊ ስርዓቱ ናቸው ይላሉ። ከዚያ ደግሞ ፍሮይዳዊያንና የሥነ-ልቦና ተንታኞች ይመጡና መከፋቱን የሚፈጥረው እናትና ልጅ መሀል ያለው ግንኙነት መሆኑን ይነግሩናል። ግን እነሱ የሚሉት ባይሆን እንኳን አንድ ከራሳችሁ ውጭ የሆነ ምክንያት ይኖረዋል። እናንተ የዚህ ምክንያት አይደለንም ብላችሁ ትገምታላችሁ። በጭራሽ።

እኔ ግን የመከፋታችሁ መንስኤ እናንተ መሆናችሁን ልነግራችሁ እወዳለሁ። ከተከፋችሁ የመከፋታችሁን ኃላፊነት የምትወስዱት ራሳችሁ ብቻ ናችሁ። ባለፈው ጊዜ በማህበራዊ መዋቅሩ ወይም በኢኮኖሚያዊ ስርዓቱ ላይ ማሳበቡ አይጠቅማችሁም። እናንተ በእናንተነታችሁ፣ አንተ በአንተነትህ፣ አንቺ በአንቺነትሽ፣ እሳቸው በእርስዎነታቸው እስከፀናችሁበት ጊዜ ድረስ፣ የትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ብትሆኑ መከፋታችሁ አይቀርም። በእኔነታችን እስከፀናን ድረስ በየትኛው ኢኮኖሚስት ስርዓት ውስጥም ሆናችሁ በየትኛውም ዓለም እንደተከፋችሁ ትኖራላችሁ።

ታዲያ ከህልውና ጋር የተያያዛችሁትን ይህንን ግብግብ ሙተው ስትጀምሩ፣ የመጀመሪያው መሰረታዊ ለውጥ መከሰት ይጀምራል። ታላላቅ የተባሉ ሃይማኖተኞች ሁሉ፣ «እኔነትን አስወግዱ» ወይም «ዓለምን ካዱ» በማለት የሚሰብኩት ቃል [illegible]ኛው ትርጓሜ ይኸው ነው። «ግብግቡን አቁሙ» ለማለት ነው። «እኔነትን ወይንም ኢጎን አስወግድ» የሚለው አባባል፤ ምስጢር አዘልነቱ ያየለ ፍልስፍና

ቀመስ ስለሚመስል፣ በማስተዋል እንድታስታውሱት እሻለሁ። እኔ ግለኝነትን እኔነት? እኔ የሚገኘው የት ነው? እኔ ምንድን ነው? ቃሉን ሁላችንም እናውቀዋለን ግን በቀላሉ የማይፈታ እና በቀላሉ የማይጨበጥ ትርጉም ያለው ይመስለኛል። እኔ ከቃሉ ይልቅ የበለጠ ተጨባጭነት ለመስጠት በመፈለጌ ነው፣ «ግለኝነትን እቀመጣለሁ» ያልኩት ምክንያቱም እኔ (ግለኝነት / ግለ-ማንነት) የራሳችን የአቋም ግጭቶች ውጤት ነው።

ሰዎች ተፈጥሮን ወይንም አንድ ሌላ ነገርን ድል በመንሳት ሲናገሩ ትሰማላችሁ - ተፈጥሮን እንዴት ድል ማድረግ ይቻላል? እናንተ / አንተ የተፈጥሮ አንዱ አካል አይደላችሁ እንዴ? ታዲያ የምትሉት ወይም የአሃዱው አንደኛው አካል ምትሉትን እንዴት ድል ሊነሳ ይችላል? የድርጊቱን ቂልነት አያችሁ? ከአሃዱ ጋር ሁለርን መፍጠር ትችላላችሁ። ከለዚያ ደግሞ ከአሃዱ ጋር በመጋጨት በውዥንብር መኖር ትችላላችሁ። ተቃርኖና ውዥንብር ውጤታቸው ስቃይና ስቀቀን ሲሆን፣ የሕብረቂትነት ውጤት ግን ሐሴትና በረከት ነው። ሕብረቂትነት የጥልቅ ፀጥታ፣ የሐሴት እና የደስታ ውጤት ማምጣቱ አይቀሬ ነው። ተቃርኖ ግን ፍጻሜው ጭንቀት፣ ውጥረትና ስቀቀን ነው።

ታዲያ እኔ ማለትም በሁሬያችሁ የፈጠራችሁት ውጥረትና ጭንቀት እንጂ ሌላ ነገር አይደለም። የሚገርመው ነገር መጀመሪያውኑ ኢጎን መፍጠር አስፈላጊ አልነበረም ግን የሰው ልጅ ኢጎን መፍጠሩን መቀጠሉ ለምንድን ነው? አንድ ምክንያት መኖር አለበት። ሰዎች ኢጎ ወይም ግለ-ማንነትን መፍጠራቸውን ያላቋረጡት ለምንድን ነው? ምክንያቱም ገና ራሳቸውን ያለማወቃቸው ነው። ያለ እንድ ማንነት መኖር በጣም አስቸጋሪ ነው፤ በዚህ የተነሳ ሐሰተኛ ማንነት እንፈጥራለን። ይህ ማንነት ምትክ ማንነት ነው። ትክክለኛው ማንነት አይታወቅም።

እንደ እውነቱ ከሆነ ትክክለኛውን ማንነት በፍጹም! በጭራሽ ሙሉ በሙሉ ማወቅ አይቻልም። ሕልውና፣ ምክንያታዊና ፍቺ-አልባ ሆኖ ይኖራል። እውነትና ትክክለኛው ማንነት ሁለቱ ወሰን-አልባ በመሆኑ ትርጉም ለመስጠት አንችልም። ይህ ማንነት ከምንፈጥር አለመኖሩ ልቀት የተነሳ እስኪሉ ወይንም ውስጣዊ ፍራቻ ላይ

መድረስ አይቻልም። ትክክለኛው ማንነት የምሰው ወይንም የአሃዱ ማንነት ነው። የሰው ልጆች ልቦና ሊመረምረውና ጠልቶ ሊፈትሸው አይችልም።

ታላቁ አሌክሳንደር ዘንድ ተጠርቶ የሄደ አንድ ጠቢብ ታሪክ ላጫውታችሁ። አሌክሳንደር እንዲህ ሲል ይጠይቀዋል፣ «የፈጣሪ አምላክህን ምንነት ልታውቅ መቻልህን ሰምቻለሁ፣ ስለዚህ እጠክህ ያወቅከውን ንገረኝ። እኔ እሱን ለማወቅ እፈልጋለሁ፣ አንተ ደግሞ የበቃህ ነህ እየተባለ ይነገራል፣ እናም ስለ ፈጣሪ ግለፅልኝ፣ የአምላክን ምንነት አስረዳኝ።» በማለት።

ጠቢቡ ሰውም ሲመልስ፣ «የማስብበት ቢያንስ የሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ስጠኝ» ይለዋል።

ሃያ አራት ሰዓቱ አልፎ፣ አሌክሳንደር በጣም በጉጉት ሲጠብቀው ጠቢቡ ሰው ይመጣና፣ «ሌላ ሰባት ቀናት ያስፈልገኛል።» ይለዋል።

ሰባት ቀን ከሞላ በኋላ አሌክሳንደር ትዕግስት እያጣ በጉጉት ሲጠብቀው ጠቢቡ ሰው አሁንም ይመጣና፣ «አንድ አመት ጨምርልኝ» ብሎ እርፍ።

ይህን ጊዜ አሌክሳንደር፣ «አንድ ዓመት ያስፈልጋል ስትል ምን ማለትህ ነው? ታውቃለህ ወይስ አታውቅም? ካወክ ንገረኝ። ጊዜ ማባከኑ ምን አስፈለገ?» ይለዋል። ጠቢቡ ሰው ሳቀና፣ «ባሰላሰልኩ ቁጥር አይታወቄነቱም ያን ያህል እየገዘፈ ይመጣል፡፡ ባወቅኩ መጠን ያወቅኩትን በቃላት ለመናገር የዚያን ያህል እየከበደ ይሄድብኛል። ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ ይህንን ለማድረግ ደግሜ ደጋግሜ ስሞክር ያወቅኩት ሁሉ ይምታታብኝ ጀመረ። ልክ እንደ ሜርኩሪ የማይጨበጥ ነገር ነው። ያን ጊዜ ሰባት ቀን እንዲሰጠኝ ብጠይቅም፣ ምንም አልጠቀመኝም። አሁንም ቢያንስ አንድ አመት ቢያስፈልገኝም፣ አንድ የማያጠያይቅ ጥርት ያለ የፈጣሪ አምላክን ትርጓሜ ይዤ መመለስ ስለመቻሌ እርግጠኛ አይደለሁም።» በማለት መለሰለት ይላችኋሉ።

ጠቢቡ ሰው ያደረገው መልካም ነበር። ምክንያቱም የትክክለኛውን ማንነት፣ ምንነት፣ በምንም ዐይነት ማወቅ ወይም ፍቺ መስጠት አይቻልም። የሰው ልጅ ግን ያለ አንድ ማንነት መኖር አይችልም። ማንነቱን ካጣ፣ ባዶነት ይሰማዋል። ስለዚ፣

‹‹እኔ ይህንን ነኝ::›› ‹‹እኔ ማለት እንደዚህ ነኝ::›› በማለት በስራሳቸው ማንነት መግለፅ ካልቻሉ መኖር ይከብዳቸዋል::

ትክክለኛውን ማንነት ማወቅ አድካሚ ፈተና ነው:: እዚህ ላይ ለመድረስ ረጅም መንገድ መጓዝን ይጠይቃል:: ወደ ትክክለኛው ሥፍራ ከመድረሱም በፊት ሌሎች ብዙ ቦታዎች ላይ በማረፍ የእውነተኛው ማንነት መገኛ ሥፍራ መሆን ያለመሆናቸውን ማጣራትንም ይጠይቃል:: ቀላሉ ከዚህ የምታመልጡበትዘዴ፣ ሐሰተኛ ማንነት መፍጠር ነው:: *እውነተኛ ፅጌረዳዎችን ማብቀል አስቸጋሪ ከሆነባችሁ፣ የፕላስቲክ ስሪት ፅጌረዳዎችን መግዛት ትችላላችሁ::* ራሳችሁን ማሞኘት ባይችሉም፣ ጎረቤቶቻችሁን ግን ማሞኘት ይችላሉ:: ልክ ነኝ? የሐሰተኛው ማንነት - የኢጎ ተግባርም እንደዚሁ ነው:: እናንተን ሊያሞኝ አይችልም:: እናንተ ራሳችሁን እንኳን እኑማ እንደሆናችሁ እንደማታውቁ ጠንቅቃችሁ ብትገነዘቡም፣ ግን ቢያንስ ለሚመለከታችሁና ለሚያውቃችሁ ሌላው ዓለም፣ ተለይታችሁ የምትታወቁበት አንበለውና ‹‹ታርጋ›› ይኖራችኋል። ይህም የማንነት ጥያቄዎችን ይመልስላችኋል::

አስባችሁበት ታውቃላችሁ? አንድ ሰው፣ ‹‹አንተ ማነህ?›› ወይ ‹‹አንቺ ማነሽ?›› ብሎ ቢጠይቃችሁ ምን ብላችሁ ትመልሳላችሁ? ስማችሁን ትነግሩታላችሁ:: ወደዚህች ዓለም ስትመጡ ስም አልነበራችሁም፣ ስለዚህ ይህ ስም የእናንተ አይደለም:: ተሰጥቷችሁ፣ ‹‹አንትና›› ትብላችሁ ተሰይማችሁ ነው እንጂ፣ ይህ ስም ንብረታችሁ አይደለም:: የተፈጠራችሁት ያለ ስም ነው:: ስማችሁ፣ በነሲብ የሰጣችሁ በመሆኑ፣ አሁን ከምትጠሩበት ስም ሌላ ሊሆን ይችል ነበር:: በጭራሽ ምንም ዐይነት ፋይዳና ፍሬ ነገር የለበትም:: ስምሽ ‹‹ሐና›› ከሆነ ጥሩ ይሁን፣ ስምህ ‹‹አሸናፊ›› ከሆነ፣ ጥሩ ነው ይሁን፣ ግን ምንም የተለየ ፋይዳ የለውም:: በቃ ልክ እንደተሽከርካሪ ታርጋ ነው:: ስያሜ ‹‹ማን ብዬ ልጥራህ / ልጥራሽ›› የሚለውን ጥያቄ ከመመለሱ ሌላ፣ ከማንነታችሁ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ነው::

ወይንም ደግሞ፣ ‹‹እኔ ዶክተር ነኝ›› አለዚያም ‹‹እኔ መሀንዲስ ነኝ›› ወይም ‹‹ነጋዴ ነኝ›› ወይም ‹‹ሰዓሊ›› እያልን ራሳችንን መሰየማችን፣ ስለራሳችንና

ስለማንነታችን የሚናገረው ምንም ነገር የለም። የተናገረው፣ ኑሮውን እንዴት እንደሚገፋ ነው። እንጂ ስለ ሕይወት የተናገረው ነገር የለም። ኑሮአችንን በምህንድስና፣ በዶክትሬት፣ ወይም በውትድርና መግፋታችን ስለማንነታችን የሚገልፀው ነገር አይኖርም።

ወይንም ደግሞ የአባት የእናታችሁን ስም ስትጠሩ፣ የዘር ሀረጋችሁን ቆጥራችሁ እንጂ፣ ስለማንነታችሁ የተናገራችሁት ነገር የለም። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ በሕልውና መወለዳችሁ የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ነው እንጂ ማን ያውቃል? በሌላ ቤተሰብ ውስጥ ተወልዳችሁ ሊሆን ይችል ነበር። ይህ ቢሆን ኖሮ ልዩነቱን እንኳን ማስተዋል ባልተቻላችሁ። እነዚህ ሁሉ ከኑሮ ሥርዓት ጋር ተያይዘው የሚመጡ አታላይ ነገሮች የሰው ልጅ አንድ ‹‹ማንነት›› ይሰጡታል። ይህ ማንነት ተመሳስሎ የተሰራ፣ የተፈጠረ ሐሰተኛ ማንነት ነው። የራሳችሁ ማንነት ግን በጭጋግና በምስጢራዊነት እንደተሸፈነ በጥልቅ ርቀት ተደብቆ ይኖራል።

*ካነበብኩት እነሆ፡ -*

እንድ ፈረንሳዊ፣ ከሌላ የአረብ መንገድ መሪ ጋር በረሃውን ያቋርጣል።

በየእለቱ አረቡ በጋለው አሸዋ ላይ ተንበርክኮ ፈጣሪውን ሳይማፀን አይውልም።

*በመጨረሻ ግን አንድ ምሽት ኢ-አማኒው ፈረንሳዩ ለአረቡ እንዲህ ይለዋል፣ ‹‹ፈጣሪ አምላክ መኖሩን እንዴት አወቅክ?››*

*መንገድ መሪውም አጠያየቁ የሹፈት መሆኑ ስለገባው ፈረንሳዊውን ትክ ብሎ እየተመለከተ ሲመልስለት፣ ‹‹ፈጣሪ አምላክ መኖሩን እንዴት አወቅክ ነው ያልከኝ? ትናንት ለሊት እኛ ተኝተን ሳለን በአጠገባችን አልፎ የሄደው ግመል እንጂ ሰው ያለመሆኑንስ እንዴት አወቅኩ? አሸዋው ላይ አሳርፎት ባለፈው ዱካው አልነበረምን?›› ካለው በኋላ፣ ከአድማሱ ወዲያ ማዶ ልትጠልቅ የመጨረሻ ጨረሮቿን እየፈነጠቀች ወደነበረችው ፀሀይ በጣቱ እያመለከተው፣ ቀጠለና፣ ‹‹ይህ የምትመለከተውም የሰው ዱካ አይደለም።›› ሲል ድንቅ ምላሽ ሰጠው።*

ማንነታችሁ በእናንተ ሊፈጠር አይችልም፣ ሰው ሰራሽ ማንነት ሊኖር አይችልም። ማንነትህን ይዘኸው መጥተሃል፣ ይዘኸው ተፈጥረሃል እንጂ አንተ አትፈጥረውም። የሆንከውን እንዴት ልትፈጥረው ትችላለህ? ፈጥረኸው ቢሆን ኖር ከመፍጠርህ በፊት ሕልውና ይኖርህ ነበር። ማንነትህ ለመፍጠር በፍጥረት መጀመሪያ ላይ መገኘት ነበረብህ። ክርስትና፣ እስልምና፣ ወይም ባጠቃላይ ሃይማኖተኞች ሁሉ የሰው ልጅ «ፍጡር» ነው የሚለው ስብከታቸው ትርጓሜም ይኸው ነው። ይህ ማለት፣ በቃ የሰው ልጅ ራሱን አልፈጠረም ማለት ነው። ከግንዛቤ በላይ በሆነውና በማይታወቀው አንድ ሥፍራ ላይ የተሸሸገ ህቡዕ ፈጣሪ አለ። እኛም የመጣነው ከአንድ ሕቡዕ የሕይወት ምንጭ ውስጥ ነው። ማንነታችሁ የራሳችሁ አይደለም! ይህ አሁን የያዛችሁት ሐሰተኛ ማንነት ራሳችሁ የፈጠራችሁት በመሆኑ የእናንተ አይደለም። እውነተኛው ማንነታችሁም ስርወ-መሠረቱ ፈጣሪ አምላክ ዘንድ የሚገኝ ከመሆኑ የተነሳ የራሳችሁ አይደለም። አሁንም ቢሆን ስርወ-መሰረታችሁና ምንጫችሁ ፈጣሪ አምላክ ነው።

በሕይወታችን የያዝነው የምንኖረው ዘወትር የመጥፋት አደጋ ያንዣበበበት የማንነት አርማ ይህ ነው። እጅግ ደካማና ተሰባሪ ነው። ሰው ሰራሽ እንደመሆኑ መጠንም ተሰባሪ ቢሆን አይገርምም። የሰው ልጅ አንድን ነገር እንዴት ዘለዓለማዊና ሞት የማይደርስበት አድርጎ ሊሰራው ይችላል? የሰው ልጅ ራሱ በብዙ ሞቶች ውስጥ ማለፍ አለበት። ስለዚህ እሱ የሚፈጥረው ማንኛውም ነገር ሟች ነው። በዚህ የተነሳ ነው፣ «ልጠፋ እችላለሁ። ማንነቴ ሊንኮታኮት ይችላል።» በሚል ፍራቻ ተሸብቦ የሚኖረው። ይህ ሐሰተኛ ማንነታችሁ ስለሚያጠራጥራችሁ፣ ሐሰተኛ መሆኑንም ስለምታውቁ፣ ሕልውናችሁ በማያቋርጥ ፍርሃት ተውጦ ቀኑን ይቆጥራል። ሐቁን ገሸሽ ልታደርጉ ትችሉ ይሆናል፣ ግን ሐሰት መሆኑን ጠንቅቃችሁ ታውቁታላችሁ። አንድ ላይ የተሰበሰበ የውሸት ፈጠራ በመሆኑ ህያው አይደለም። መቆቅረ-ሥርዓታዊ (mechanical) ነው እንጂ ሕያው-ሥርዓታዊ (organic) አይደለም።

በመቆቅረ-ሥርዓታዊ (mechanical) አንድነት እና በሕያው-ሥርዓታዊ (organic) አንድነት መካከል ያለውን ልዩነት አስተውላችኋል? የአንድ መኪና ሞተር

መስራት ከፈለጋችሁ፣ የሞተሩን ልዩ ልዩ ክፍሎች ከመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች መደብር ገዝታችሁ፣ ከዚያ እነዚህን ክፍሎች መገጣጠም ትችላላችሁ። ይህን ጊዜ ሞተሩ፣ ሞተር ሆኖ እንደ አንድ አካል ብቻውን መስራት ይጀምራል። እንዲሁም ይሁን ብቻ አንድ ማንነት ማግኘት ችሏል። አንድ የራዲዮ አካል ብቻውን መስራት አይችልም። ሁሉም አካላት አንድ ላይ ሆነው ግን ሬድዮ የሚለውን ማንነት ይሰጡታል። ይህ ማንነት ይኑረው እንጂ የሞተሩ ወይንም የራዲዮኑ ማንነት መዋቅረ-ሥርዓታዊ ነው። ከበስተ-ውጪ የተጫነበት ነው።

ዳሩ ግን ምድር አፈር ላይ ዘር ሲበተን፣ እነዚህ ዘሮች አፈር ውስጥ ገብተው ይሞቱና፣ በምትካቸው ተክል ይበቅላል። ይህ በዘሩ፣ በአፈሩና፣ በተክሉ መካከል ያለው አንድነት ሕያው-ሥርዓታዊነትን የተከተለ ነው። ከበስተ-ውጪ የተጫነ አንድነት ሳይሆን በዘር ፍሬው ውስጥ የነበረ አንድነት ነው። ፍሬው ከምድር አፈር ብዙ ሺህ ንጥረ-ነገሮችን እየወሰደ፣ ከፀሐይ ብርሃንን እየወሰደ፣ አየር እየወሰደ፣ ያለማቋረጥ ማፍራቱን ይቀጥላል። አንድነቱ ግን ከበስተ-ውስጡ የሚመነጭ ነው። ከፍሬው ወይም ከእስኳሉ ወይም ከመሃሉ ተነስቶ ወደ ውጪ እየሰፋና እያደገ የሚሄድ ማንነት ይኖረዋል። በመዋቅረ-ሥርዓታዊ አንድነት ላይ ግን ከዳር ተነስቶ ወደ መሃል ወይም ወደ እስኳሉ የሚሄድ አንድነት ይታያል።

የሰው ልጅ ሕያው-ሥርዓታዊ አንድነት ነው። መጀመሪያ ፍሬ ነበር፣ ከዚያም ከተክል ባልተለየ ሁኔታ በእናቱ መሃፀን አፈር ውስጥ ማደግ ይጀምራል። ቀድሞ የመጣው እስኳሉ በኋላ ነው። አሁን ታዲያ እስኳሉ ከፍካቴው ተዘንግቶናል። ዳር ዳሩን ስለምትኖሩ ሕይወታችሁ በአጠቃላይ ይህ ብቻ ይመስላችኋል። በዚህ የዳር ዳርታ ኑሮ ለረጅም ጊዜ መቆየት በራሱ አንድ የማንነት አምሳልን ያላብሳል። ይህ ሐሳዊ-ማንነትም ተለይተን መታወቅ የምንችል ሰው እንደሆንን የሚያሳስብ ስሜት ይፈጥርብናል። ይህ ሐሳዊ-ማንነት ግን በውስጡ ምንም ዐይነት ሕያው-ሥርዓታዊ አንድነት ባለመሆኑ ዘወትር በሥጋት ይኖራል።

ሞትን የምንፈራውም በዚህ የተነሳ ነው። እውነተኛ ማንነታችሁን ብታውቁ ኖሮ፣ ሞትን በጭራሽ ባልፈራችሁት ነበር። ምክንያቱም ሕያው ሥርዓታዊ አንድነት

መቼም እንደማይጠፉና እንደማይሞት ያለ ጥርጣሬ ስለምታውቁ፣ ሞት የሚባል ነገር አያስበረግጋችሁም። ሕያው-ሥርዓታዊ አንድነት ዘለዓለማዊ ነው። ተቀናብረውና ተገጣጥመው ሥራቸውን ሲጨርሱ የሚሞቱት መዋቅረ-ሥርዓታዊ አንድነቶች ብቻ ናቸው። የተገጣጠመ ነገር አንድ ቀን መፍረሱ አይቀርም። ሕያው-ሥርዓታዊው አንድነት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘለዓለማዊ ሂደት ነው።

ታዲያ እናንተስ እስኳላችሁን ታውቁታላችሁ? የማታውቁት ከሆነ በማያቋርጥ ፍርሃት ውስጥ ትሆናላችሁ። በዚህ የተነሳ ግሉንቃተ ሕሊና ዘወትር እንደሰጋና እንደተንቀጠቀጠ ይኖራል። እናንተም ዘወትር የሌሎችን እርዳታ ትፈልጋላችሁ። የሚያደንቃችሁ፣ የሚያጨበጭብላችሁ፣ ወይም ስለውበታችሁና ስለ አስተሳሰብ ብቃታችሁ የሚያወድሳችሁ ሰው ያስፈልጋችኋል። አዎ፣ እኔኮ ውብ ነኝ፣ አዎ፣ እኔኮ አስተዋይ ነኝ፣ አዎ፣ እኔኮ ኅበዝ ነኝ ብላችሁ እንድታምኑ የሌሎችን ሰዎችን ማረጋገጫ የግድ ትፈልጋላችሁ። ዋናው ነጥብ ምንድን ነው? አዎ፣ እናንተ የሌሎች ሰዎች ጥገኞች ናችሁ።

አንድ ምንም ፊደል ያልቆጠረ ሰው መጥቶ በጣም አስተዋይና ምሁር መሆንህን ቢነግርህ አንተን ከዚህ ሰው ፊት ምሁር ያስመሰለህን ያንን ትንሽ ዕውቀት ሚዛን ላይ ማወዳደር አይከብድህም። ማለትም እሱ ከአንተ በላይ አዋቂና ምሁር ቢሆን ኖሮ፣ .አንተ ምሁር መስለህ ባልታየኸው ነበር። ግን ይህ የትምህርት ዕድል ያላገኘ ሰው መጥቶ ምሁርነትህን ሲያረጋግጥልህ በጣም ደስ ትሰኛለህ። በሌላ አባባል መልከ-መልካም መስለህ ልትታይ የምትችለው በመልከ-ጥፉ ሰው ብቻ ነው። እሱ ከአንተ የበለጠ መልከ-መልካምነት ቢኖረው አስቀያሚ መስለህ በታየኸው ነበር። ምክንያቱም ሁሉም ነገር አንጻራዊ ነው። ታድያ መልከ ጥፉ ሰዎች መልኩ መልካምነትህ ሲያረጋግጡልህ ዘደስታ ጮቤ ትረግጣለህ።

ዱሩ - ግን ይህ በመሀይማን እውቅናና ማረጋገጫ የሚሰጠው ምሁርነት ምን ዐይነት ምሁርነት ነው? የመልከ-ጥፉ ሰዎችን ማረጋገጫ የሚፈልግ መልኩ-ሸጋነት ምን ዐይነት ውበት ነው? ፍጹም ሐሰት ነው። ቂልነት ነው! እኛ ግን ፍለጋችንን እንቀጥላለን። በውጪያዊው ዓለም ለግለሰባዊ ማንነታችን (ለኢጎ) የሚሆን ድጋፍ

ስንፈልግ ትንሽ እድናቆት ስንፈልግ እንኖራለን። ካለዚያ ግሉ-ማንነታችን ድጋፍ ነጣ ሊንኮታኮት የሚችልበት አደጋ ውስጥ ይገባል። በዚህ የተነሳ ከዚህና ከዚያ ጉትጎ መደገፍ ሲኖርብን፣ በማያቋርጥ ሐሳብና ጭንቀት ውስጥ እንገባለን።

ለብቻችሁ በምትሆኑ ጊዜ የበለጠ ግርማ ሞገስ የሚኖራችሁ ለዚያ ነው፣ ምክንያቱም አትጨነቁም። የሚከለክላችሁ ሰው የለም። ብቻችሁን ስትሆኑ ከሌላው ጊዜ ይልቅ የሞና ብፁእ ትሆናላችሁ። ልክ እንደ ሕፃን ልጅ። መስታወት ፊት ቆማችሁ ገፃችሁን እንዳሻችሁ እያጨማደዳችሁ፣ ዐይናችሁን እያፈጠጣችሁ፣ ምላሳችሁን እያወጣችሁ እንደቀውስ ብትሆኑ ደስ ይላችኋል። ግን ትንሹ ልጃችሁ በበሩ ቀዳዳ እያያችሁ መሆኑ ቢታወቃችሁ ወዲያው የተለየ ሰው ትሆናላችሁ። አሁን ኢጎ አደጋ ላይ ነቀ! ለዚህ ነው ሰዎች ሌሎችን በጣም የሚፈሩት።

አንድ ዝነኛ የዜን ቡድሂስቶች ተረት ልንገራችሁ፡-

አንድ የዜን ማስተር (መምህር) ስዕል እየሳለ ነው። ቀዳሚ ደቀ-መዝሙሩ ደግሞ ስዕሉ እንከን አልባ ሲሆን ጠብቆ ሊነግረው አጠገቡ ተቀምጦ ይመለከታል። ደቀ-መዝሙሩ መምህሩ እንዲህ ዐይነት አስቀያሚ ነገር ሲሰራ አይቶት ስለማያውቅ ለመናገር ጨንቆታል። መምህሩም የሚሠራውን ለማሳመር በጣረ መጠን እየተበላሸበት ተጨንቋል።

በጃፓን ወይም በቻይና ውስጥ የሥነ-ጹሁፍና የሥነ-ስዕል ጥበባት በአጠቃላይ የሚሰሩት ከሩዝ ዱቄት በተዘጋጀ በጣም ለስላሳና በቀላሉ የሚፈረካከስ ወረቀት ላይ ነው። አንድ ፀሀፊ ሥራ ላይ ሆኖ ትንሽ ካመነታ ፀሀፊው ያመነታበት ሥፍራ ለብዙ ክፍለ-ዘመናት እየታየ ሊኖር ይችላል። ምክንያቱም ያመነታበት ቦታ ላይ ብዙ ቀለም ይሰርገና፣ የሩዝ ወረቀቱ ላይ ማህተም ሆኖ አበላሽቶት ይቀራል። በሩዝ ወረቀት ላይ ማጭበርበር በጣም ይከብዳል። ያለማመንታት ፀሀፊው የፍሰት ሂደቱን ሳያቋርጥ መፃፍ ይኖርበታል። ከሰከንድ ሳነሰች አፍታ ምን ላድርግ? ብሎ አስቦ ካመነታ፣ በቃ በዚያች አፍታ ብላሽ ሆኗል። ስለዚህ አስተዋይ ዐይን ያለው ሰው አንድን ስዕል / ጹሁፍ ተመልክቶ ይህ የዜን ስዕል አይደለም ወይ ነው ማለት

ይችላል። ምክንያቱም የዜን ስዕል ያለግፊት በራሱ ጊዜ የሚፈስ አጣጣልን ይጠይቃል።

ወደ ታሪኩ ስንመለስ መምህሩ ተማሪውን ለማሳመር በጣረ መጠን አልሳካ ሲለው ላብ ያሰምጠው ጀመር። ደቀ-መዝሙሩ ደግሞ አጠገቡ ተቀምጦ አሁንም አሁንም አንገቱን በአሉታ እየወዘወዘ «አይደለም ይህ እንከን አልባ ስዕል አይደለም።» ሲለው የመምህሩ ስህተቶች እየበዙ መጡ።

ጥቂት እንደቆዩ ቀለም እያለቀበት ስለነበር መምህሩ ደቀ-መዝሙሩን ሄዶ ቀለም እንዲያዘጋጅ ይነግረዋል። እሱ ቀለም ሊቀይጥ ወጥቶ ሳለ መምህሩ ዕፁብ ድንቅ የሚባል እንከን የሌለው ስዕል ሰርቶ ጠበቀው። ደቀ-መዝሙሩ ተመልሶ ሲመጣ፣ «መምህር፣ ግን ይህኛው እኮ ምርጥ ነው! ምን ተፈጠረ?» ብሎ ይጠይቀዋል።

መምህሩም ሳቀና «አንድ ነገር አስተዋልኩ - ይህም የአንተን እዚህ መገኘት፣ ማለቴ የሚያደንቅህ ወይም የሚኮንንህ ሰው የመገኘቱ ሐሳብ በራሱ የውስጤን ሰላም አደፍርሶት እንደነበር አስተዋልኩ። ከአሁን በኋላ ግን በጭራሽ አልረበሽም። እንከን አልባ ሳደርገው ስሞክር እንደነበር ተረዳሁ። እንከን አልባ ከመሆን ያገደው ብቸኛው ምክንያትም ይኸው ሙከራዬ ነበር።

*አንድን ነገር እንከን-የለሽ ልታደርጉት ብትሞክሩ እንከን እንደያዘ ይኖራል። በተፈጥሮአዊ ደንብ ብታደርጉት ግን እንከን-የለሽ መሆኑ የግድ ነው። ተፈጥሮ እንከን-አልባ ነች፤ ጥረት ግን ጎደሎ ነው። ስለዚህ ማንኛውም ነገር ከመጠን በላይ በምታደርጉበት ጊዜ ሁሉ ጥፋት እየፈፀማችሁ ነው።*

ሌላው ከዚሁ ጋር የተያያዘ አስገራሚ ነገር በሕዝብ ፊት ንግግር የማድረግ ፍራቻ ነው። ማንኛውም አንደበት ያለው ሰው ያወራል። ሕይወቱን ሙሉ አስደሳች ጨዋታዎችን ከሰዎች ጋር ሲያወጋ እናውቀዋለን የምንለውን አንድ ሰው ግን ሕዝብ ፊት አቁመን ተናገር ብንለው፣ ደርሶ ዲዳ ይሆናል፣ የሚናገረው ይጠፋበታል፣ አንዲት ቃል መተንፈስ ያቅተውም ይሆናል። ወይም ርቱዕነቱ እጅግ ይቀንሳል። ምን ተፈጥሮ ይሆን? ይህን ሰው ስታውቁት ከጓደኞቹ፣ ከባለቤቱ፣ እና ከልጆቹ ጋር በውሀ

ስለዛ ሲነጋገር ነው። እነዚህ አሁን ከፊቱ ያሉትም ሰዎች ናቸው እንደዚህም እዚያው የሚያውቃቸው ሰዎች ሲሆኑ ይችላሉ። ታዲያ ምን አስፈራው? መልሱ፣ ሕሊናው ስለራሱ መገመቱ ወይንም ገሉንቅ-ሕሊናው ሆኖ ነው የሚል ይሆናል። ይሆን ጊዜ ገሉማገነት አደጋ ላይ ነው ምክንያቱም በሌሎች ፊት ቆቃቱን አሳይቶ ሲመጣ ነው።

ልዩ በሉ፣ አንድ ነገርን ለማክናወን በምትሞክሩበት ጊዜ ሁሉ ስለጎ ማንሌያ የሚሆን የሚሆለው ነገር እየፈለጋችሁበት ነው። እንደውትሮችሁ ሆናችሁ ነገሮች እንዲከሰቱ በምታደርጉበት ወቅት እንከን አልባ ውጤት ይኖራችኋል። ይህ ከሆነ ምንም ችግር አይኖርም። ተፈጥሯዊ በሆነው ማንነታችሁ ነገሮችን ስታከናውኑ ወይም እንዲከናወኑ ስትፈቅዱላቸው ያን ጊዜ ፈጣሪ ከጎኣ እየተከተላችሁ ነው። በስጋትና በፍራቻ አንድን ነገር ለማከመከር በምትሞክሩበት ጊዜ ግን ከፈጣሪ ጋር ትለያያላችሁ። በፍርሃታችሁ የተነሳ ረስታችሁታል። የተፈጠራችሁበትን የሕይወት ምንጭና ማዕከል ረስታችሁ ልባችሁን ለምኞ በገድ ወስዳችሁታል።

ገሉንቅ-ሕሊና ደከመት ይሆናል። ገሉንቅ-ህሊና የሌለው ሰው ጠንካራ ነው፣ ጥንካሬው የሚመነጨው ግን ከራሱ ሳይሆን ከእሱ ወደያ ከሚገኝ ሌላ ኃይል ነው።

ገሉንቅ-ሕሊና ካላችሁ ችግር ውስጥ ናችሁ። ገሉንቅ-ሕሊናዊ ስትሆኑ ግን እንደሆናችሁ ያለማወቃችሁን በትክክል የሚያመለክቱ የበሽታ ምልክቶች እያሳያችሁ ነው። ገሉንቅ-ሕሊናዊነታችሁ በራሱ ወደ እውነተኛ ማንነታችሁ ያለመመለሳችሁን ያሳያል።

እንዲህም ሆነ-

አንዲት ወጣት ልጃገረድ በነፋናው አልፋ ስትሄድ፣ መላ ክቡሩዲን ዞር ተመለከታት። ይሆን ጊዜ ሚስቱ በንዴት «ቆንጆ ሴት ባየህ ቁጥር ትዳር እንዳለህ ትረሳዋለህ።» ትለዋለች።

ክቡሩዲንም ሲመልስ፣ «ስህተትሽ እዚህ ላይ ነው።» ይላታል

ቀጥሎም፣ «እዚህ በተሳለ ይሆንን ሐቅ እንዳስተውል የሚያደርገኝ ምንም ነገር የለም።»

በተመሳሳይ ሁኔታም ግሉ-ንቅ-ሕሊና በሚኖራችሁ ጊዜ ሁሉ፣ ስለማንነታችሁ ፍፁም እንደዘነጋችሁና፣ ማስተዋሉ እንደራቃችሁ እያሳያችሁ ነው። ማን እንደሆናችሁ አላወቃችሁም፣ አታውቁም። ብታውቁ ኖሮማ ምንም ችግር አልነበረውም። ራሳችሁን ብታውቁ ኖሮ የሌሎችን አስተያየቶች ባልፈለጋችሁ ነበር። ማንነታችሁ ቢገለጥላችሁ ኖሮ ሌሎች ስለእናንተ ለሚሉት ሁሉ ግድ ባልኖራችሁ፣ ባልተጨነቃችሁም። እንዴ! ከናካቴው አግባብ የለውም! እንደ እውነቱ ከሆነ ካልተወሻሸን ማንም ሰው መቼም ይሄን መቼ ስለ እናንተ ምንም ተናገር አያውቅም። እንዴት? ምክንያቱም ሰዎች ስለሌላ ሰው አንድ ነገር ሲናገሩ የተናገሩት ስለራሳቸው እንጂ ስለዚያ ሰው አይደለም።

አንድ ቀን እንዲህ ሆነ፡- ጂፑር ከተማ ውስጥ እያለሁ፣ አንድ ሰው ማለዳ ወደ ቤቴ መጥቶ እንዲህ አለኝ፣ ‹‹አንተኮ መለኮታዊና ፃድቅ ሰው ነህ።››

እኔም፣ ‹‹ልክ ነህ!›› በማለት መለስኩለት።

እሱ እንደተቀመጠ ሌላ ሰውዬ ወደቤቴ መጣ እሱ ደሞ፣ ‹‹አንተኮ ከዲያብሉስ የማትተናነስ እርኩስስ ነህ።›› አለኝ።

እኔም፣ ‹‹ልክ ነህ!›› በማለት መለስኩለት።

የመጀመሪያው ሰው ጭንቅ ቢጤ ስለገባው፣ ‹‹ምን ማለትህ ነው? ለእኔም ልክ ነህ›› ነበር ያልከኝ አሁን ደግሞ ለዚህ ሰውዬም ‹‹ልክ ነህ›› አልከው፣ ሁለታችንም ልክ ልንሆን አንችልም።

እኔም ስመልስለት፣ ‹‹ሁለት ሰዎች ይቅሩና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ስለእኔ ልክ ሊናገሩ ይችላሉ ምክንያቱም ስለእኔ የሚናገሩት የትኛውም ነገር የተናገሩት ስለራሳቸው ነው። እነሱ እኔን እንዴት ማወቅ ይችላሉ? ሊሆን የማይችል ነገር ነው። ገና ራሳቸውን እንኳን አላወቁም። የሚናገሩት ሁሉ በራሳቸው ግምት የሚሰጡትን ትርጓሜ ነው።

እናም ሰውየው ግራ በመጋባት፣ ‹‹ታዲያ አንተ ማነህ? ፃድቅነትህ የእኔ ግምታዊ ትርጓሜ ከሆነ፣ እርኩስነትህ ደግሞ የዚህ ሰውዬ ግምታዊ ትርጓሜ ከሆነ ታዲያ አንተ ማነህ?›› ሲል ጠየቀኝ።

እኔም፣ ‹‹እኔማ፣ በቃ እኔ ነኝ›› ስለራሴ ምንም ዐይነት ትርጓሜ የለኝም፣ ቢኖረኝም አስፈላጊ አይሆንም። ማንነቴ ምንም ዐይነት ፍቺ ቢኖረውም ባይኖረውም ራሴን በመሆኔ ግን ደስተኛ ነኝ፣ በቃ በማለት መለስኩለት።

ስለ እናንተም ቢሆን ማንም ሰው ምንም መናገር አይችልም። ሰዎች የሚናገሩት ማንኛውም ነገር ስለራሳቸው ብቻ ነው። ዳሩ ግን እናንተ፣ ሐሳዊ ማንነታችሁ ላይ የሙጥኝ ብላችሁ ስለተጣበቃችሁ፣ በማንነታችሁ ላይ የተሰነዘረ አድርጋችሁ ትገምቱታላችሁ። ይህ ሐሳዊ ማንነት በሌሎች ሰዎች ላይ ጥገኛ ከመሆኑ የተነሳ፣ ዘወትርም ሰዎች ስለ እናንተ የሚናገሩትን ለማወቅ ትጥራላችሁ። ሡርክ ዘወትር ሌሎችን በመከተል እነሱን ለማስደሰት ስትጥሩ ትኖራላችሁ። ክብራችሁን ጠብቃችሁ ለመገኘት እና ኢጎአችሁን (ግለ-ማንነታችሁን) ለማሽብረቅ ስትሞክሩ ትኖራላችሁ። ይህ ግን ራስን ከማጥፋት ያልተናነሰ ጉዳት አለው።

ሌሎች ስለእናንተ በሚናገሩት በመረበሽ ፈንታ ውስጣችሁን መፈተሽ ልትጀምሩ ይገባል፡ እውነተኛ ማንነትን ማወቅ ቀላል ዋጋ የለውም። ሰዎች ርካሽ ለሆኑ ነገሮች ሲጥሩ ይታያሉ።

እንዲህም ሆነ፦

ሙላ ነስሩዲን፣ የጀርባ ሕመሙ ሲጠናበት ሳይወድ በግዱ ሐኪም ዘንድ ያመራል። ዶክተሩም ምርመራ ካደረገለት በኋላ፣ ‹‹ቀዶ ጥገና አድርገህ፣ ሁለት ሳምንት ሆስፒታል፣ ስድስት ወር ደግሞ ቤትህ ሳትነሳ ተኝተህ የምታርፍ ከሆነ ችግርህ ሊድን ይችላል።›› ይለዋል።

ነስሩዲንም፣ ‹‹እንዴ ዶክተር የዚህን ሁሉ ወጪና ኪሳራ መሸፈን አልችልም!›› ሲል በድንጋጤ እየጮኸ ይመልሳል። ‹‹እንደዚያ ከሆነማ፣ ሃያ-አምስት ዶላር ብቻ ብትከፍል ኤክስ-ሬይ ደግሜ ላነሳህ እችላለሁ።›› የሚል ሐሳብ አቀረበለት።

ይህ ርካሽ ነው! ድጋሚ ኤክስ-ሬይ መነሳት ዋጋው ቀላል ቢሆንም ግን ጤናን አይመልስም። እኛም የምናደርገው ከዚህ የተለየ ነገር አይደለም። ደግመን ደጋግመን ኤክስ-ሬይ እየተነሳን አንድ ተዓምር ተፈጥሮ ችግራችን እስኪወገድ

እየጠበቅን ነው። ግሉ-ማንነታችሁን በምታሳምሩና በምታሽበርቁበት ጊዜ ዳግመኛ ኢክሱ-ሬይ እየተነሳችሁ ነው። ይህ በየትኛውም መልኩ በሥነ ጥቅም የለውም። ጤናችሁን አይመልስላችሁም። ዋጋው ቀላል በመሆኑ ቀዶ-ጥገና አያስፈልጋም፣ ወጪ አይኖርባችሁም። ግን ትርጉሙ ምንድን ነው? ሰቃያችሁ አልተወገደም።

የተከበራችሁ ብትሆኑም ሰቃይና ሰቀቀናችሁ እንዳለ ይኖራል። ማህበረሰቡ ያስረግድላችኋል፣ ያሞግሳችኋል እናንተ ግን ስቃይ ላይ ናችሁ። በወርቅና ማዳለያዎችና በማዕረጎች አሸብርቃችኋል ግን ከስቃይ አልዳናችሁም። ማዳለያዎቻችሁ ዳግመኛ ኢክሱ-ሬይ ከመነሳታችሁ ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ለእኔ የምታበረክቷቸው እነዚህ ሁሉ ስጦታዎች ራሳችሁን ከማታለል የተለየ ሌላ ምንም ትርጉም የላቸውም። ኢጎ (ግሉ-ማንነት) እለት እለት እየተዳከመ የሚሄድ ከመሆኑ የተነሳ እናንተም ቀስ በቀስ እየተዳከማችሁ ትሄዳላችሁ። አካላችሁና አእምሯችሁ እየተዳከመ ይመጣል፣ አካልንና አእምሮን በማጣመር የፈጠራችሁት ማንነትም ይዳከማል። ኢጎ ይዳከማል። ፍርሃታችሁ እየናረ ይሄድና አንድ ቀን ድንገት ሊፈነዳ የሚችል እሳተ-ጎመራ ላይ እንደተቀመጣችሁ ዐይነት ትሆናላችሁ። እረፍት መዝናናትና የቅዕበት ሰላም እንኳን ይነፍጋችኋል።

ይህንን ከተረዳችሁ በኋላ ግን ኃይላችሁ በጠቅላላ ወደሌላ አቅጣጫ ያነጣጥራል። ሰው ራሱን ማወቅ እንዳለበት ይገባችኋል። ሌሎች ስለ እናንተ ስለሚናገሩት ማሰብና መጨነቅ እንደማይኖርባችሁ ታውቃላችሁ።

9 አንድ ወዳጄ የላከልኝን በጣም አስደሳች ቀልድ ላስነብባችሁ ማንም ከመኖሩ እንኳን የማያውቅ፣ ምንም ጓደኛ የሌለው አንድ ሰውዬ ነበር። በአንድ ወቅት ማያሚ ውስጥ በተደረገ የነጋዴዎች ጉባዔ ላይ ተገኝቶ ሳለ አንድ ነገር ያስተውላል። ሰዎች ሁሉ ይስቃሉ፣ ይጫወታሉ፣ ይደሰታሉ፣ ግን እሱን እንኳን ሊያጫውቱትና ሊያስቁት ይቅርና መኖሩንም ያወቁ አይመስሉም።

ከጉባዔው በአንዱ ቀን እንዲሁ ተደብሮ እንደተቀመጠ ሳለ ከተሳታፊ ነጋዴዎች ከአንዱ ጋር የመነጋገር ዕድል ያገኛል። በጨዋታቸው ላይ ይህንን ችግሩን ይነግረዋል። «ወይ፣ ይህ ችግርማ እንዴት እንደሚወገድ አውቃለሁ።» ይለዋል

ሌላው ነጋዴ። «ግመል ፈልግና ከተማ መሀል እየጋለብከው ተዘዋወር! ያን ጊዜ ወዲያው ሰው ሁሉ ስለአንተ ማውራትና መጠቋቆም ይጀምራል፣ ከዚያ የምትፈልገውን ያህል ወዳጅና ጓደኛ ማፍራት ትችላለህ።» ብሎ ምክሩን ይለግሰዋል።

ዕድሉ ሆኖ እየከሰረ የነበረ አንድ የሰርከስ ቡድን ግመል መሸጥ መፈለጉን ይሰማል። ብቸኛው ሰውዬም ግመሉን ይገዛና ከተማ ውስጥ ከወዲህ ወዲያ ሲጋልበው ይውላል። ይህን ጊዜ ሰው ሁሉ ይጠቋቆምበት ጀመር። በዚህ ዝናው ተደስቶ ዓለምን የገዛ ያህል ተሰማው። ግን ከሳምንት በኋላ ግመሉ የደረሰበት ጠፋ።

ሰውዬው በጣም በማዘኑ በጋዜጣ የአፋልጉኝ ማስታወቂያ ለማስወጣት በከተማው ለሚታተም አንድ ጋዜጣ አዘጋጅ ይደውላል።

ስልኩን የተቀበለው ሰው፣ «ግመሉ ወንድ ነው ሴት ናት?» ሲል ይጠይቀዋል።

«እኔ እንዴት አውቃለሁ?» ብሎ ከደነፋ በኋላ መለስ ብሎ አሰበና፣ «አዎ! እም ወንድ ነው።» ሲል ይመልሳል።

«እንዴት አወቅክ?» ሲል የማስታወቂያ ሰራተኛው ይጠይቃል።

«ያወቅኩትማ!» ይመልሳል ዝነኛው ሰው፣ «በየጎዳናው እየጋለብኩት ኢያለሁ ሰዎች ግመሉ ላይ ያለውን ያንን ሽመክት ተመልከቱ!» እያሉ ሲጮሁ እሰማ ነበር ነው።» በማለት መለሰለት ይባላል።

ሽመክት የሚለው ቃል የይዲሽ ቃል ሲሆን ሁለት ትርጓሜ አለው። የመጀመሪያው የማይረባ ወይም ቂል ማለት ሲሆን ሌላው ደግሞ የወንድ ብልት ማለት ነው።

ገለ-ማንነት (ego) በጣም አታላይ ነው። የሚያዳምጠው ሁሉ ማዳመጥ የሚፈልገውን ብቻ ነው። የሚያገናዝበውና የሚተረጉመው መተርጎም የሚፈልገውን ብቻ ነው። በፍፁም ሐቁን አይመለከትም። ሐቁ ምንነቱን እንዲገልፅልን በፍፁም አይፈቅድልንም። ከኢጎ በስተጀርባ በመጋረጃ ተከልለው የሚኖሩ ብዙ ሰዎ አሉ። እነዚህ መጋረጃዎች ተለዋዋጭ ናቸው፣ በዚህ የተነሳ በመጋረጃው አልፎ የሚሄድ የትኛውም ነገር መልኩን ይለውጣል።

ሰዎች እለት እለት የሚኖሩት ራሳቸው በፈጠሩት የሀሳብ ዓለም ውስጥ ነው። የዚህ ዓለማቸው ማዕከል ግለ-ማንነታቸው ነው። ይህ ዓለም የሕልም ዓለም ነው፡ ሐሰተኛ የፈጠራ ዓለም ነው። በግለ-ማንነት ዙሪያም የማንም ዓለም ያልሆነ ዓለም መፍጠራቸውን ይቀጥላሉ። እዚያ ዓለም ውስጥ የሚኖሩት እነሱ ብቻ ናቸው።

ግለ-ማንነትን ስታስወግዱ፣ በእሱ ዙሪያ የፈጠራችሁት ዓለም በሙሉም ይወገዳል። ይህን ጊዜ የነገሮችን ትክክለኛ ምንነት በትክክል መመልከት ትችላላችሁ፡ እንዲ እናንተ ደሰናችሁትን መልክ ስትሰጧቸውም። የሕይወትን ሐቆችና እውነት የማወቅ ብቃት በሚኖራችሁ ጊዜም ታላቁን እውነት የመረዳት ብቃት ይኖራችኋል።

አሁን አንድ የዜን ወግ ላጫውታችሁ፡-

በነፃ-ትግል ስፖርት ከፍተኛ ጥበብንና ችሎታን ያተረፈ፣ ኦ-ናሚ የተባለ በጣም ጠንካራ ነፃ-ትግል ተጫዋች ነበር። ብቻቸውን ከሆኑ የራሱን አስተማሪ እንኳን ድል የሚነሳ ቢሆንም የሚያሳዝነው ሕዝብ ፊት የራሱ ታዳጊ ተማሪዎች እንኳን እያነሱ ያፈርጡታል፣ ያሸንፉታል።

በዚህ ችግሩ የተነሳ በአጋጣሚ በአቅራቢያው በሚገኝ ቤተ-መቅደስ ወደተገኘ አንድ የዜን ቡድሂስት የበቃ መምህር ዘንድ ሄዶ ምክር ጠየቀ። በነገራችን ላይ ይህ የነፃ-ትግል ስፖርተኛ «ግዙፍ ማዕበል» የሚል የቅፅል ስም ነበረው። ታዲያ ይህን ምክር የጠየቀው ባህታዊ እንዲህ ይለዋል፣ «ስምህ ግዙፉ ማዕበል አይደለም?» አለና ቀጠል አድርጎ፣ «ስለዚህ ዛሬ ምሽት ቤተ-መቅደሱ ውስጥ ሆነህ የማዕበሉን ድምፅ እያዳመጥክ እደር።» ይለዋል፣ ቤተ-መቅደሱ የሚገኘው በባህር ዳርቻ ላይ ነበር። «በምናብህ፣ ከፊቱ ያገኘውን ሁሉ እየጠራረገ የሚሄደውን ማዕበል እንደሆንክ አስብ፤ ራስህን እርሳው። የነፃ-ትግል ስፖርተኛ መሆንህን እርሳውና እዚሁ ግዙፍ ማዕበሎች ሁን» አለው።

ኦ-ናሚ በቤተ-መቅደሱ አደረ። ስለማዕበሎቹ ብቻ ለማሰብ ቢሞክርም ብዙ የተለያዩ ሌሎች ሐሳቦች ጠመዱት። ከዚያ ግን ቀስ በቀስ ስለማዕበሎቹ ብቻ ማሰብ ጀመረ። ምሽቱ እየገፋ ሲሄድ ማዕበሎቹም እያደጉ መጡ። ከመቅደሱ ፊት

የተቀመጡትን አበቦች ጠርገው ወሰዷቸው። በነሃስ የተሰራውን የቡድሃ ቅርፅ ሳይቀር ጠርገው ወሰዱት። ንጋት ላይ ቤተ-መቅደሱ በውሀ ተጥለቀለቀ። ኡናሚም ገፅታው ላይ ጥቂት ፈገግታ እየታየበት እንደተቀመጠ ነበር።

የዚያን ዕለት በሕዝብ ፊት በሚደረግ የነፃ-ትግል ግጥሚያ ላይ ተሳተፈ። ያደረገውን ግጥሚያ ሁሉ በድል አጠናቀቀ። ከዚያን እለት ጀምሮ ጃፓን ውስጥ እሱን የሚጥል ሰው ጠፋ።

ይህ ታሪክ ስለ ግሉ-ንቅ-ሕሊናዊነት እና እንዴት እንደምናስወግደው የሚናገር ነው። እንዴት እናስወግደዋለን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ቀስ በቀስ እንገባበታለን።

ልክ እንደሰማነው ታሪክ ባለታሪክ፣ ኡናሚ ሁሉ ማንኛውም ሰው በከፍተኛ ጥንካሬና ኃይል የተሞላ ነው። ሁላችንም በከፍተኛ ኃይል የተሞላን ነን። ይህ የግድ ነው። ምክንያቱም የሁላችንም ስርው-መሠረት ፈጣሪ አምላክ ነው። የሁላችንም መነሻ መሳው ፍጥረተ-ዓለም (universe) ነው። የትኛውንም ያህል ትንሽና ደቃቃ ብንመስል፣ ትንሽ አይደለንም፣ የነገሮች ተፈጥሮ ራሱ ይህን አይፈቅድልንም።

የፊዚክስ ሳይንስ ባለሞያዎች ሲናገሩ በአንዲት ደቂቃ አቶም ውስጥ ታምቆ የሚገኝ ከፍተኛ ኃይል አለ። ሒሮሺማና ናጋሳኪ የወደሙት በአቶማዊ ኃይል ነው። የሚገርመው ይህቺ አቶም የተባለች የቁስ መሰረት፣ ከደቃቃነቷ የተነሳ እስከዛሬ ተመልክቷት የሚያውቅ ሰው ያለመኖሩ ነው። (እሾ election microscope) ላይ አልደረሰም ወይም አያውቀው ይሆናል ብለን እንገምት። የአቶም ሀልውና የታወቀው ነገሮችን በማስተዋል በተደረሰባቸው ድምዳሜዎች ነው። አንድ ቅንጣት አቶም ውስጥ ግን ከግምት በላይ የታጨቀ ኃይል ይገኛል።

ታዲያ አንዲት አተም ይህን ያህል ኃይል ካላት፤ የሰው ልጅስ ምን ያህል ኃይል ይኖረዋል? በሰው ልጅ ውስጥ ያለችው ይህች ትንሽ የንቃተ-ሕሊና ነበልባልስ? አንድ ቀን ይህች ትንሽ ነበልባል ቦታ አግኝታ መንደድ ስትጀምር የወሰን የለሽ ኃይልና ብርሃን ምንጭ መሆኗ አይቀርም። በቡድሃና በክርስቶስ ላይ ተከስቶ ያየነው ይህንኑ ነው።

የሰው ልጅ ሁሉ እጅግ ከፍተኛ ኃይል አለው፤ ምክንያቱም የሰው ልጅ ሁሉ የከፍተኛ መለኮታዊነት ባለቤት ነው። ሕልውናችን የተመሰረተው ወሰን የለሽን የሕልውና ምንጭ ማዕበል አድርጎ ከመሆኑ የተነሳ ሁላችንም እጅግ ከፍተኛ ጥንካሬ አለን። ይህንን ዘወትር ማስታወስ ይኖርብናል።

የሰው ልጅ ሕሊና ይህ ጥንካሬ እንዳለው የመዘንጋት አዝማሚያ ይታይበታል። ይህንን ስትዘነጉ ደካማ ትሆናላችሁ። ደካማ ስትሆኑ ደግሞ ጠንካራ ሆናችሁ ለመገኘት የሚያስችሏችሁ ሰው ሰራሽ ስልቶችን ለመፈለግና ለመፍጠር መጣር ትጀምራላችሁ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ይህንኑ እያደረጉ ይገኛሉ። እውነት፣ ምን እየፈለጋችሁ ነው? የምትፈልጉት ኃይልንና ጥንካሬን ነው። ታዋቂነትን፣ ፖለቲካዊ ሥልጣንን፣ ወይንስ ምን? የምትፈልጉት ኃይልንና ጥንካሬ ነው። ጥንካሬ ደግሞ ዘወትር ከጎናችሁ ተቀምጦ ይጠብቃችኋል። የምትፈልጉት ግን በተሳሳቱ ሥፍራዎች መሆኑ ፍለጋችሁን መና ያደርገዋል።

ኡናሚ (ግዙፉ ማዕበል) የተባለው የነዌ-ትግል ተጋጣሚ ብዙ ያስተምረናል።

ይህንን የኡናሚን ኃይል ማግኘት የሚቻለው ግን ማዕበሉ የታላቅና ወሰን የሌለው ውቅያኖስ ማዕበል መሆኑን ሲያውቅ ብቻ ነው። ማዕበሉ ይህንን ከዘነጋ በጣም ደካማ ማዕበል ይሆናል። «ዝንጋታችን» ደግሞ ከፍተኛ፣ ትውስታችን አናሳ፣ በጣም ትንሽ ነው። በመዘንጋታችን እንቀጥላለን እንደውም በቀላሉ የምንዘነጋው በጣም ግልፅ የሆኑ ነገሮችን ነው። በጣም የሚቀርበንን ነገር በቀላሉ እንዘነጋዋለን። ዘወትር በእጃችን ያለ ነገርን በቀላሉ እንረሳዋለን።

እስኪ እስቡት እተነፋፈሳችሁን ታስታውሳላችሁ? የምታስታውሱት አንድ ችግር ሲፈጠርባችሁ ነው - ትንፋን ሲይዛችሁ ወይም አስም ካለባችሁና ትንፋሽ ሲያጥራችሁ ብቻ እንጂ ትንፋሽን ማን ያስታውሰዋል? ለዚህም ነው ሰዎች በችግራቸው ጊዜ ብቻ አምላክን የሚያስታውሱት። ካለዚያ ማን ያስታውሰዋል? ፈጣሪ አምላክ ግን ከትንፋሻችሁም በላይ ቅርባችሁ ነው። ሰው የቀረበውን የመርሳት አዝማሚያ አለው፤ አስተውላችኋል? አንድ ነገር ሳይኖራችሁ ሲቀር

ታስታውሱታላችሁ። እጃችሁ ከገባ በኋላ ግን ትረሱታላችሁ። ፈጣሪን ደግሞ ከእጠገባችሁ ማጣት በጣም ከባድ በመሆኑ የማያስታውሱት ጥቂቶች ናቸው።

ውቅያኖስ ውስጥ ያለ ዓሳ ውቅያኖሱን አያስታውስም። ዓሳውን ከውሀ አውጥታችሁ ምድር ላይ ብትጥሉት ግን ያን ጊዜ ውሀው ትዝ ይለዋል። ከእናንተን ግን ከፈጣሪ ውቅያኖስ ውስጥ አውጥቶ መጣል አይቻልም። ፈጣሪ ዳርቻ አልባ ውቅያኖስ ነው። እናንተም እንደ ዓሶች ሳትሆኑ እንደ ግዙፍ ማዕበሎች ናችሁ። አምሳያችሁ ከፈጣሪ ጋር አንድ ነው የእናንተና የፈጣሪ ተፈጥሮ አንድ ዐይነት ነው።

ለዚህ መፅሐፍ የመረጥኩት ርዕሰ ምሳሌነቱም ይኸው ነው - ‹‹ፈጠራ››።

ኡናሚ የነፃ-ትግል ጥበብ ችሎታው ከፍተኛ ነበር። እንደውም የራሱን መምህር እንኳን ድል ይነሳል. . .

ግን ይህ ችሎታውና ድል አድራጊነቱ ሰው በሌለበት ነው፣ ምክንያቱም ሰው ከሌለ ማንነቱን መርሳት ይችላል።

ይህንን ነጥብ አትርሱ። ራሳችሁን ስታስታውሱ ፈጣሪን ትዘነጋላችሁ፣ ራሳችሁን ስትረሱ ደግሞ አምላክን ታስታውሳላችሁ፣ በአንድ ላይ ሁለቱንም ማስታወስ ግን አትችሉም። ማዕበሏ ራሷን እንደማዕበል ማሰብ ስትጀምር ውቅያኖስ መሆኗን ትረሳዋለች። ማዕበሏ ውቅያኖስ መሆኗን ብቻ የምታውቅ ከሆነ ግን አሁን ድንገት ራሷን እንዴት ማዕበል አድርጋ ልታስታውስ ትችላለች? ማሰብ ወይም ማስታወስ የምትችለው አንዱን ብቻ ነው፤ ማዕበሏን ወይ ራሷን ማዕበል ወይም ውቅያኖስ ማድረግ ብቻ ነው የምትችለው።

ኡናሚም ቢሆን ሰው በሌለበት አስተማሪውን እንኳን ድል ይነሳ የነበረው በዚያን ወቅት ማንነቱን፣ ኢጎውን ሙሉ ለሙሉ ስለሚረሳ ነበር። ይህንን ጊዜ በከፍተኛ ኃይል ይመላል። ሕዝብ ፊት ሲሆን ግን ግለ-ንቃ-ሕሊናዊነቱ ወይንም ስለራሱ ማሰቡ ይበረታበታል። ያን ጊዜ ደካማ ነው። ግለ-ንቃ-ሕሊናዊነት ደካማነት ነው። ራስን መርሳት ግን ጥንካሬ ነው።

ኡ-ናሚ በባህር ዳርቻ ላይ በሚገኝ ቤተ-መቅደስ እርፎ ወደነበረው የዜን መምህር ሄዶ ምክር ሲጠይቅ፣ ዛሬ ምሽት በቤተ-መቅደሱ አድሮ የባህሩን ማዕበል ድምፅ ሲያዳምጥ እንዲያድር ነገረው፡፡

መምህር ማለት ለሰዎች ሁሉ መፍትሄን የሚፈልግ ማለት ነው፡፡ መምሁሩ የኡ-ናሚን የቅፅል ስም ማለትም ግዙፏ ማዕበል የሚል ስሙን ብቻ በመጠቀም የመፍትሄ ሀሳብ ሰጠው፡፡

ማዳመጥ ወደ ፈጣሪ ቤተ-መቅደስ የመግቢያ መሰረታዊ ምስጢራት አንዱ ነው፡፡ ማዳመጥ ማለት መስከን ማለት ነው፡፡ ማዳመጥ ማለት ራስን ሙሉ ለሙሉ መርሳት ማለት ነው፤ ማዳመጥ የሚቻለው ይህን ጊዜ ብቻ ነው፡፡ አንድን ሰው በፅሞና ስታዳምጡት ያን ጊዜ ራሳችሁን ረስታችኋል ማለት ነው፡፡ ራሳችሁን መርሳት ካልቻላችሁ፣ በፍፁም ማዳመጥ አትችሉም፡፡ ስለራሳችሁ እያሰባችሁ ከሆነ ማሰመሰል እንጂ ማዳመጥ አትችሉም፡፡ ራሳችሁን ልታወዛውዙና አንዳንዴም አዎ ወይ አይደለም ማለት ትችሉ ይሆናል ግን እያዳመጣችሁ አይደለም፡፡

በምታዳምጡበት ጊዜ እንደመተላለፊያ ትሆናላችሁ፣ ትቀበላላችሁ፣ መሀፀን ትሆናላችሁ፡፡ እንስታዊ ትሆናላችሁ፡፡ ማዳመጥ ላይ መድረስ የፈለገ እንስታዊ መሆንን መረዳት አለበት፡፡ ቁጡ ወራሪ ሆናችሁ ፈጣሪ ዘንድ መድረስ አትችሉም፡፡ ፈጣሪ ዘንድ መድረስ የምትችሉት . . . ወይም ደግሞ ፈጣሪ ሊደርስባችሁ የሚችለው በእንስታዊ ተቀባይነት ስትጠብቁት ብቻ ነው፡፡ ያን ጊዜ በራችሁ ክፍት ነው፣ ሊጎበኛችሁ ቢመጣ እንኳን መግባት ይችላል፡፡

ማዳመጥ የተቀባይነት ጥበብ ነው፡፡ ቡድሃ ማዳመጥ በአንክሮ ሲናገር ኖሯል፡፡ ማህበር እና ክሪሽና ሙርቲም እንደዚያው፡፡ ጆሮ የራሱ ተምሳሌት አለው፡፡ ይህን አስተውላችኋል? ጆሮዎቻችሁ ከዓይኖቻችሁ ይልቅ እንስታዊ ናቸው፡፡ ዓይኖቻችሁ ተባዕታዊነታቸው ያይላል፡፡ አንድን ሰው በዓይኖቻችሁ በምትመለከቱበት ጊዜ ቁጡነታችሁ ይጨምራል፡፡ አንድን ሰው በምታዳምጡበት ጊዜ ግን እየተቀበላችሁት፣ ሀሳባችሁን ከሀሳቡ እያስማማችሁ ነው፡፡

በዚህ የተነሳ ነው፣ አንድን ሰው ለረጅም ጊዜ ያለ ምክንያት ትክ ብሎ ማየት ብልግና ወይም ጨዋነት የሌለው የሚሆነው። የሥነ-ልቦና ባለሙያዎች የአይታን ቆይታ ገደብ ሦስት ሰከንዶች ያደርጉታል። ለሦስት ሰከንድ አንድን ሰው ትክ ብሎ ማየት ለክፋት አይባልም። ከዚያ ካለፈ ግን እያያችሁት ሳይሆን እያፈጠጣችሁበት በመሆኑ ገደብ ጥሳችሁ እዚያ ሰውላይ እየደረሳችሁ ነው። ዳሩ ግን አንድን ሰው ማዳመጥ ገደብ የለውም ጆሮ ድንበር መጣስ አይችልም። እንደነበሩ ሳይለወጡ ይቆያሉ።

ዓይኖች እረፍት ይሻሉ። ካስተዋላችሁ ለሊት ዓይኖች ማረፍ አለባቸው። ጆሮዎች ግን ከዓመት ዓመት ሌት ተቅ ተከፍተው ይኖራሉ። ዓይኖች ግን ለደቂቆች እንኳን ተከፍተው መቆየት ስለማይችሉ ያለማቋረጥ እረፍት ያስፈልጋቸዋል፣ ስለዚህ ይርገበገባሉ። ቁጣ ያደክማል ምክንያቱም ቁጣ ኃይላችሁን ይወስድባችኋል፣ ስለዚህ ዓይኖች እፎይታ ያለናቸዋል። ጆሮዎች ግን ዘወትር እረፍት ላይ ናቸው።

በዚህ ምክንያ ነው ሙዚቃ ወይም ዜማ እንደፀሎት እድራሻ ተደርጎ በብዙ ኃይማኖቶች ዘንድ ጥቅም ላይ የሚውለው። ሙዚቃ ጆሮዎችን በበለጠ ተቀባይ ያደርጋቸዋል።

«ሁለመናህ ጆሮ ይሁን» ነበር መምህሩ ያለው። «አንተ ብቻ አዳምጥ። ምንም ነገር ማድረግ የለብህም - ያለ ምንም ምክንያት ምን እየጠፈጠረ እንደሆነ ሳታስብ ማዳመጥህን ቀጥል። የምታዳምጠው ፍቺ ሳትሰጥ በአንተ በኩል ምንም ምላሽ ሳይኖር አዳምጥ።» ያን ጊዜ፣ «እነዚያ ማዕበሎች አንተን እንደሆኑ በምናብህ ገምት።»

መጀመሪያ አዳምጥና ከማዕበሎች ቅኝት ጋር ተስተካክል ከዚያ ፍፁም የስክነት እና የተቀባይነት መንፈስ ላይ ስትደርስ አንተ እነዚያን ማዕበሎች መሆንህ አስብ። ማዕበሎቹን መሆን ሁለተኛው ደረጃ ነው። መጀመሪያ ቁጣህን አጥፋው ተቀባይ ሁን፣ ተቀባይ ከሆንክ በኋላ እነዚያ ማዕበሎች ውስጥ ራስህን ቀላቅለህ እነሱን ሁን።

መምህሩ ይህንን ምክር የሰጠው ራሱን እንዲረሳ ነው። ግላዊ-ማንነቱን (ኢጎውን) እንዲረሳ። የመጀመሪያው ደረጃ ተቀባይነት ነው፤ ምክንያቱም ተቀባይነትና ኢጎ አብረው መኖር አይቻላቸውም። ግሉ-ማንነት ህልውና የሚኖረው በግጭት ውስጥ ብቻ ነው። ተቀባይ በምትሆኑ ጊዜ ግን ምናባዊ ኃይላችሁ እጅግ ይበረታል።

ተቀባይና ስሜት-ስስ የሆኑ ሰዎች ምናባቸው ከፍተኛ ነው። የዛፎችን ልምላሜ ያለምንም ቁጣና ግልፍተኛ ስሜት ማየት የሚችሉ ሰዎች እነሱ ስፖንጅ የሆኑ ያህል ልምላሜን ወደራሳቸው የሚመጥጡ ሰዎች በፈጠራ ክህሎት ይወደሳሉ፤ የምናብ ኃይላቸው ይሰፋል። *ባለቅኔዎች፣ ሰዓሊያን፣ ዘፋኞች እነዚህ ናቸው። በጥልቅ የተቀባይነት መንፈስ ፍጥረተ-ዓለምን ወደውስጣቸው ይመጥጣሉ፣ የመጠጡትን ሁሉም ወደ ምናባቸው ያንቆረቁሩታል።*

ለፈጣሪ የቀረበ ብቸኛው ‹‹የስሜት ህዋሳችሁ›› ምናባችሁ ነው። የፈጣሪ ምናብ የረቀቀና የመጠቀ መሆን አለበት፤ አይመስላችሁም? እስኪ ፍጥረተ-ዓለሙን ተመልከቱት ይህ ሁሉ አበባ፣ ይህ ሁሉ ቢራቢሮ፣ እና ይህ ሁሉ ዛፍ፣ ይህ ሁሉ ወንዝ፣ አቤት! ይህ ሁሉ ሰው። እስኪ የእሱን ምናብ አስቡት! እነዚህ ሁሉ ክዋክብትና እነዚህ ሁሉ ሌሎች ዓለማት፣ . . . ፈጣሪ በባለ-ራዕይነት የሚደርስበት አይኖርም።

በምስራቁ ዓለም ሒንዱዎች እንደሚሉት ዓለም የፈጣሪ ህልም ናት፤ የምናብ ውጤት። ዓለም ምትሃቱ፣ ምናቡ ነች። እሱ እያለማት ነው፣ እኛ ደግሞ ህልሙ ውስጥ ነን።

መምህሩ ለኡ-ናሚ ‹‹በምናብህ እነዚህን ማዕበሎች ሁን›› ብሎ ሲነግረው፣ ‹‹አንተም ፈጠራ ይኑርህ። መጀመሪያ ተቀባይ ሁንና ከዚያ ፍጠር።›› እያለው ነበር። ግሉ-ማንነትህን ካስወገድህ በኋላ ግን እጅግ ተጣጣፊ ወይም በራስህ ዓለም ኗሪ ስለምትሆን በምናብህ የሳልከው ነገር ሁሉ እውን መሆን ይጀምራል። ያን ጊዜ ህልምህ ሁሉ እውን ይሆናል።

‹‹የነፃ-ትግል ተጋጣሚ መሆንህን እርሳውና፣ ከፊታቸው ያገኙትን ሁሉ እየደረማመሱ እንደሚያልፉ ማዕበሎች ሁን።››

መጀመሪያ አስቸግሮት ነበር ስለማዕበሎቹ ብቻ ለማሰብ ቢሞክርም ብዙ ሌሎች ሀሳቦች እየመጡ ሀሳቡን አባዘኑት፡፡ እሱ ግን ፀና፡፡ በጣም ታጋሽ መሆን አለበት፡፡ ቀስ በቀስ ግን ስለማዕበሎቹ ብቻ ማሰብ ጀመረ፡፡ ከዚያ ያቺ ቅፅበት መጣች፡፡ ከፀናንና ከታገስን ለብዙ ምዕተ-ዓመታት ስንመኘው የነበረው ነገር እውን የምትሆንባት አንዲት ቅፅበት ትመጣለች፡፡ ግን ትዕግስት ያሻል፡፡

ቀስ በቀስ ስለማዕበሎቹ ብቻ ማሰብ ሲጀምር፣ ለሊቱ እየገፋ ሲሄድ ማዕበሎቹ እያደጉ እየገዘፉ መጡ፡፡

እነዚህ ማዕበሎች የውቅያኖሱ ትክክለኛ ማዕበሎች አይደሉም፡፡ እንግዲህ ማስተዋል ነው፡፡ በሱ-ናሚ የምናብ ማዕበሎችና በውቅያኖሱ ማዕበሎች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም፡፡ ይህ ልዩነት ቢኖር እንኳን አክትሞለታል፡፡ የትኛው ማዕበል የእሱ የትኛው የውቅያኖሱ እንደሆነ አያውቅም፡፡ ዳግመኛ ወደ ሕፃንነቱ ተመልሷል፡፡ ይህን የማለም ብቃት ያላቸው ትንንሽ ልጆች ብቻ ናቸው፡፡

ማለዳ ጠዋት፣ አንድ ሕፃን ልጅ በሕልሙ ላየው አሻንጉሊት ሲያለቅስ ታገኙታላችሁ፡፡ የሚያለቅሰው ጠፍቶበት ነው፡፡ ‹‹አሻንጉሊቴን አምጡ!›› ይላል፡፡ ‹‹እናንተ ግን በህልምህ ነው ትሉታላችሁ፡፡ አያምናችሁም፡፡››

በሕልምና በእውን ዓለም መካከል ለእሱ ምንም ልዩነት የለም፡፡ እውነታ ለእሱ አንድ ነች፡፡

ተቀባይነት (receptivity) ሲኖራችሁ እንደ ሕፃን ልጅ ትሆናላችሁ፡፡

ወደማዕበሎቹ እንመለስ፡-

ምሽቱ ሲገፋ እያደጉና እየገዘፉ መጡ፡፡ በመቅደሱ ፊት የተቀመጡትን አበቦች ጠራርገው ወሰዷቸው፡፡ በነሃስ የተሰራውን የቡድሃ ቅርፅ ሳይቀር ጠራርገው ወሰዱት፡፡

ይህ ውብ ነገር ነው! ለአንድ የቡድሃ ተከታይ የቡድሃ ቅርፅ በጎርፍ ሲወሰድ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ ከኃይማኖቱ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው ከሆነ በምናቡ እዚያ ነጥብ ላይ ሲደርስ በተረታ ነበር፡፡ ‹‹ይብቃኝ! ቡድሃን እንኳን ጎርፍ ሲወስደው? ምን እያደረግኩ ነው? በቃ ከአሁን በኋላ ማዕበል አይደለሁም፡፡›› ብሎ በተወው ነበር፡፡

ማዕበሉ የቡድሃ እግር ስር ደርሶ፣ እግሩን ነክቶ ይመለሳል እንጂ ከዚህ በላይ የትም አይደርስም፡፡ ዳሩ ግን በመንገዱ ላይ የመሩት እነዚያ እግሮች እንኳን መወገዳቸው ግዴታ መሆኑን ማስተዋል አለበት፡፡ ምክንያቱም መግቢያ በሩን የሙጥኝ ብለን ከያዝነው በሩ ሳይቀር ገደብ ይሆንብናል፡፡

የአበባ ማስቀመጫዎቹና የቡድሃ በጎርፍ መወሰድ የመቅደሱ በማዕበሉች መጥለቅለቅና የማዕበሉቹ ግዝፈት እያደገ መምጣት እውን የሆነ ነገር መሆኑን እናስተውል፡፡ ለኡ-ናሚ እውን ሆኖ ነበር፡፡ በወቅቱ በቤተ-መቅደሱ ውስጥ የነበረ ሰው መቅደሱ በውኃ ሲጥለቀለቅ ይመለከት ነበር ማለት አይደለም - ለኡ-ናሚ ግን ነው፡፡ በኡ-ናሚ ሕሳዌ ፍፁም የተለየ አውታር ላይ እየተፈጠረ ያለ ነገር ነበር፡፡ ይህ አውታር የቅኔ፣ የምናብና የሕልም አውታር ነው፡፡ የልቦናዊ-ግንዛቤ የእንስታዊነት፣ የሕፃንነት እና የየዋህነት አውታር ነው፡፡ የምናባዊ ስሜት-ህዋሱን መግቢያ በሮች ከፍቷቸው ነበር፣ ምናባዊ ሆነ፡፡ ምናቡ እንደ ባለ አንድ ሺህ አንድ ቅጠል አበባ ፈክቶ አበበ፡፡

ንጋት ላይ ቤተ-መቅደሱ በውኃ ተጥለቀለቀ፣ ኡ-ናሚም በተቀመጠበት ፊቱ በፈገግታ ሞልቶ ታየ፡፡

ቡድሃን ሆነ! አንድ ዕለት ቡድሃ ዛፍ ስር ተቀምጦ የታየበት ያ ለስላሳ ፈገግታ እሱም ፊት ላይ ሳይታይ አልቀረም፡፡ ድንገት እሱነቱ አበቃ - የፈገግታው ምክንያትም ይህ ነው! ወደ ቤቱ፣ ወደ እውነተኛ ቦታው፣ ወደ ትክክለኛ ማንነቱ የመመለሱ ደስታ የፈጠረው ፈገግታ ነበር። የመድረስ ፈገግታ፣ ከዚህ በኋላ የሚሄድበት ቦታ ያለመኖሩን በማወቁ የሚፈጠር የእፎይታ ፈገግታ፡፡ መነሻ ምንጩ ላይ የመድረሱ ምስጢር፣ ሞቶ ዳግመኛ የመወለዱ ወይም የትንሳኤው ደስታ ያመጣው ፈገግታ፡፡

ኡ-ናሚም በተቀመጠበት ፊቱ በፈገግታ ሞልቶ ታየ፡፡
የዚያን እለት በህዝብ ፊት የነፃ-ትግል ግጥሚያ
አድርጎ ረታ፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላም በጃፓን ምድር
እሱን የሚጥል፣ እሱን የሚረታ ሰው አልተገኘም፡፡

ምክንያቱም አሁን ይህን ኃይል የራሱ ኃይል አይደለም። ከዚህ በኋላ ኢጎሚንም ማዕበሎቹንም ሳይሆን ራሱን ውቅያኖሱን ነው። ታድያ ውቅያኖሱን የትኛው ሰው ነው የሚረታው? ማሸነፍና መርታት የሚቻለው ማዕበሎቹን ብቻ ነው።

ልክ ግለ-ማንነትን (ኢጉን) ስታስወግዱ መረታትን ሁሉ፣ ተስፋ ማጣትን ሁሉ፣ ድል መንሳትን ሁሉ ታስወግዳላችሁ። ኢጉን ይዛችሁ ብትቀጥሉ ሽንፈታችሁ አይቀሬ ይሆናል። ግለ-ማንነትን ብታስወግዱ ወሰን-አልባው ኃይል በውስጣችሁ መመላለስ ይጀምራል። ኢጉን ስታስወግዱ ከራሳችሁ በረዶ ቀልጣችሁ፣ መፍሰስና መንሸራሸር ትጀምራላችሁ። ሕያውነት የእናንተ ትሆናለች።

ሕይወት ሁሉ የምሉዑ (የአሃዱው) ነው። ለብቻ በራሳችሁ ለመኖር እየሞከራችሁ ከሆነ ፋይዳ የለውም። በዛፍ ላይ ያለ ቅጠል የራሱን ሕይወት ለመኖር እየሞከረ ነው፤ ከማለት የተለየ አይደለም። ይህ ብቻም አይደለም፣ ከዛፉ ጋር፣ ከሌሎቹ ቅጠሎችና ከቅርንጫፎቹ እንዲሁም ከሥሮቹ ጋር እየተፋለመም ነው እንደማለትም ይሆናል። እነዚህ ሌሎች የዛፉ አካላት ከእሱ ጋር ምንም ዝምድና እንደሌላቸው ማሰቡ ብቻውን ግድየለሽነቱ ብቻውን ተቃርኖውን ይናገራል። እኛ ብንሆን፣ ሁላችንም የአንድ ትልቅ ዛፍ - ፈጣሪ ወይም አሃዱ በሉት - ቅጠሎች ነን። የፈለጋችሁትን ብላችሁ ጥሩት ግን ሁላችንም በአፅናፍ የለሹ የሕይወት ዛፍ ላይ የምንገኝ ትንንሽ ቅጠሎች ነን። ስለዚህ መጠላት አስፈላጊ አይደለም። ወደቤታችን የምንመለስበት ብቸኛው መንገድ ለዚህ አንድነት በመንበርከክ ብቻ ነው።

## ፍፁማዊነት

አንድ ውብ ታሪክ ሰምቼያለሁ። ከእለታት አንድ ጊዜ በቀተታ፣ በስዕ በሥነ-ጥበብ ወደር የሌለው የፈጠራ ሰው ይኖር ነበር። ከሥራው ፍፁማዊነ የተነሳ፣ ከድንጋይ አንድ ሰው ምስል ከቀረፀ፣ ሰው ይሁን ድንጋይ መለየት በጣ ያስቸግራል። ሥራዎቹ ሕይወትን የተሞሉ ሕያውነትን የተላበሱ ስለነበሩ እው መስለው ይታያሉ።

ታዲያ አንድ ሰብዓ-ሰገል (አስትሮሎጀር) ጊዜ ሞቱ እየተቃረበ መሆ ይነግረዋል። እንደማንኛውም ሰው ይህ የፈጠራ ሰውም ሞትን ይፈራ ስለነበ

ከመጣበት ሞት ማምለጥ ፈለገ። አሰበበትና አብሰለሰለበት ሲያበቃ አንድ መፍትሔ አገኘ። የራሱን አምሳል ከድንጋይ እየቀረፀ አስራ አንዱን ካዘጋጀ በኋላ የተቆረጠለት እለት መልዓከ ሞት በሩን አንኳኩቶ ቤቱ ሲገባ፣ ትንፋሹን ውጦ ከድንጋይ አምሳያዎቹ መሃል ገብቶ ተመሳስሎ ቆመ።

መልዓከ-ሞት ግራ ገባው፣ ዓይኑን ማመን ተሳነው። እንዲህ ዓይነት ነገር ገጥሞት አያውቅም፤ ፈጣሪ ሁለት ተመሳሳይ ሰዎችን ፈጥሮ አያውቅም የሚፈጥረው አየለያየ ነው። ፈጣሪ እንደ ጠርሙስ መፈብረኪያ ማሽን አይደለም። የአንድን ፍጡር አምሳያ ደግሞ አይፈጥርም። ታዲያ ምን አዲስ ነገር መጣ? አስራ ሁለት ተመሳሳይ ሰዎች፣ እሺ ማንም ይውሰድ፣ ከአንድ በላይ ይዞ መሄድ አይችልም . . .

መልዓከ-ሞት መወሰን አቃተው። ግራ ተጋብቶ፣ ተጨንቆና፣ በስጋት ተውጦ ተመልሶ ሄደ። ፈጣሪ አምላክ ዘንድ ሲደርስም፣ ‹‹ምንድን ነው ያደረግከው፣ እኔ ማምጣት የምችለው አንድ ሰው ብቻ ነው፣ ሄጄ ያገኘሁት ግን አስራ ሁለት አንድ ዓይነት ነው። እንዴት ነው መምረጥ ያለብኝ?›› ሲል ይጠይቀዋል።

ፈጣሪ አምላክም ሳቀና መልዓከ-ሞትን ከጠራው በኋላ፣ ከሐሰዊያን መሃል እውነተኛውን የማግኛውን ቁልፍ ቀመር በጆሮ ሹክ አለው። ይህንን የምስጢር ቃል ከሰጠው በኋላም፣ ‹‹አሁን ብቻ ያ የፈጠራ ሰው ራሱን በመሰሎቹ ድንጋዮች መሀል በደበቀበት ቤት ውስጥ ትገባና ይህንን የነገርኩህን የምስጢር ቃል መናገር ብቻ ነው። ›› ይለዋል።

መልዓከ-ሞትም፣ ‹‹እንዴት ነው የሚሰራው?›› ይጠይቀዋል።

ፈጣሪም፣ ‹‹ስለሱ አትጨነቅ፣ አንተ ብቻ ሂድና የነገርኩህን ሞክር።›› ብሎ ያሰናብተዋል።

መልዓከ-ሞትም የተነገረው ውጤት ይኖረዋል ብሎ ባያምንም የፈጣሪን ቃል አክብሮ ይሄዳል። የፈጠራ ሰውዬው መኖሪያ ቤት ከገባ በኋላ ዙሪያውን ተመልክቶ ሲያበቃ እንዲህ አለ፣ ‹‹ጌታዬ፣ ሁሉ ነገር ፍፁም እንከን የለሽ ነው። ግን አንድ ቅር የሚያሰኝ ነገር አለ። ጥሩ ሰርተሃል ግን አንድ ስህተት አለው።›› ይላል፣ በይፋናው ለአስራ ሁለቱም እየተናገረ።

ይህን ጊዜ አርቲስቱ መደበቁን ከናካቴው ዘንግቶት

‹‹ስህተት፣ የታለ ስህተት፣ የቱጋ?›› እያለ ዘሎ ወጣ።

መልዓከ-ሞት ከት ብሎ ሳቀ! ‹‹ተይዘሃል! ብቸኛው ስህተትህ ይህ ነው። ራስህን መርሳት አትችልም። በል ና፣ ተከተለኝ።›› አለው እላችኋለሁ።

አርቲስት በዓለም ላይ ካሉ ሰዎች ሁሉ የጠነከረ ኢጎ አለው፡፡ ቢያንስ አብዛኛውን ጊዜ፡፡ ይህ ካልሆነ ግን አርቲስቱ ትክክለኛ አርቲስት አይደለም፡፡ ዘወትር ስለራሳቸው ጉራቸውን የሚነዙና ዘወትር እርስ በእርስ የሚናከሱ፤ ኢጎዎቻቸው የበረታባቸው ፍጡራን ናቸው፡፡ ሁሉም ከራሳቸው በላይ ሌላ አርቲስት ያለ የማይመስላቸው ናቸው፡፡ ይህ እውነተኛ ጥበብ አይደለም፡፡

እውነተኛ አርቲስት ፍጹም የተሰወረ ነው፡፡ እነዚህ የተቀሩት ግን ከቴክኒክ ሙያተኞች ያለፈ ብቃት የላቸውም፡፡ እኔ ቴክኒሽያኖች እንጂ አርቲስት ብዬ አልጠራቸውም፡፡ ፈጣሪዎች ሳይሆኑ አቀናባሪዎች ናቸው፡፡ አንድን ቅኔ አቀናብሮ ማዘጋጀት አንድ ነገር ነው፤ አዲስ ቅኔ መፍጠር ደግሞ ሌላ ነገር ነው፡፡ ቅኔን ለማቀናበር የቋንቋ ሰዋሰው እና የቅኔ ደንቦችን ማወቅ ይጠበቅብናል፡፡ የቃላት ጨዋታ ነው፡፡ ጨዋታውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ቅኔ ወይም ግጥም ማቀናበር ይችላል: : ግጥሙ ግን ለዛ የለውም የማይጥም የቃላት ኳኳታ ይሆናል፡፡ ከቴክኒክ አንጻር እንከን አይወጣለት ይሆናል፤ ግን ነፍስ አይኖረውም፡፡ በድን አካል ብቻ እንጂ፡፡

ነፍስያው የምንታስራራው አርቲስቱ ከጥበቡ ሳይለይ፤ ውስጧ ገብቶ ሲጠፋ ነው፡፡ ጥበብ ውስጥ ገብቶ ሲሰወር ነው፡፡ ሰዓሊው ማንነቱን ረስቶ የሚስልበትና፤ እርሱ እንዳልሳለው ስለሚያውቅም በስዕሉ ላይ ፊርማውን ማኖር በሚያሳፍረው ጊዜ፤ ያኔ ስዕሉ ነፍስ ዘርቶበታል፡፡ ሰዓሊው እርሱ ሳይሆን አንድ ያልታወቀ ኃይል እሱን ተጠቅሞበት መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ በክፍለ-ዘመናችን ሲወደሱ የምናውቃቸው ታላላቅ አርቲስቶች የሕይወት ልምድም ይህንኑ ያስረግጥልናል፡፡ በሌላ ኃይል የመያዝን ስሜት፡፡ ይህ ስሜት በጨመረ መጠን የአርቲስቱ ታላቅነትም ይጨምራል፡፡

ሞዛርቱ፤ ቤትሆቨኑ፤ ካሊዳሱ፤ ጊብራት፤ ፒካሶው፤ አንጀሎው፤ ዳቪንቺው ምን አለፋችሁ ሁሉም ታላላቅ የጥበብ ማንነቶች ባዶ መቃዎች ሆነው ሕልውና እነሱን ዋሽንት አድርጋ ስትቀኝባቸው እንደኖረች ፍፁም እርግጠኞች ናቸው፡፡ እነሱ ዋሽንት ነበሩ እንጂ ቅኝቱና ዜማውም የእነሱ አልነበረም፡፡ በእነሱ በኩል የተንቆረቆረ እንጂ መምጫው አንድ ያልታወቀ ምንጭ ነው፡፡ ያደረጉት ነገር ቢኖር ፍሰቱን ያለመገደብ፤ ወይም በነጻነት እንዲንቆረቆር መፍቀድ ብቻ ነበር፡፡ እንጂ እነሱ አልፈጠሩትም፡፡

እንቆቅልሹ ይህ ነው፡፡ እውነተኛ ፈጣሪ ምንም ነገር እንዳልፈጠረ የሚያውቅ ነው፡፡ ሕልውና በእሱ በኩል ስራዋን ሰራች፡፡ ሰፈረችበትም በእጆቹ በማንነቱ በሕልውናው ባጠቃላይ ሰፈረችበት፡፡ እናም ታዲያ በእሱ መሳሪያነት አንድ ነገር ፈጠረች፡፡ እውነተኛ ኪን-ጥበብ ይህ ነው፡፡ ከያኒው የሚሰወርበት ኪን-ጥበብ፡፡ ይህን ጊዜ የኢጎው ጥያቄ አይነሳም፡፡ እናም ኪን-ጥበብ በመንፈሳዊነት ትባረካለች፡፡ ያን ጊዜ ከያኒው ህቡዕ (mystic) ይሆናል፡፡ ቴክኒካዊ ትክክለኛነትና ያልተበረዘ ሕልውና ይኖረዋል፡፡

ከያኒው ከኪነ-ጥበብ ሥራው ውስጥ እየጠፋ ሲሄድ ፍፅምናው እያየለ ይመጣል:: ከያኒው ፍፅም ሲጠፋና ሲሰወር የፈጠራ ሥራው ደግሞ ፍፅም እንከን አልባ ይሆናል:: ከያኒው ሥራ ላይ በተገለጠ መጠን ደግሞ የሥራው እቅለሸለሽነት እያየለ ይመጣል:: ጥርት ብሎ የሚታየው ኢጎው እንጂ ሥራው አይሆንም::

ኢጎ የነርቭ ችግር (ኒውሮሲስ) ነው:: ከዚህም በላይ መታወስ ያለበት ነገር ኢጎ ፍፅምናን መሻቱ ነው:: ኢጎ ፍፅምናን ናፋቂ ነው:: ኢጎ ሰርክ . . . ከሌሎች ተሽሎ መገኘትን ከሌሎች በልጦ መገኘትን ይሻል:: ዳሩ ግን ኢጎ መቼም ይሁን መቼ ፍፅምና ላይ አይደርስም፣ ስለዚህ ጥረቱ ሁሉ ከንቱ ነው:: ፍፅምና ላይ መድረስ የሚቻለው ኢጎ ራሱን ሳይሆን ሲቀር ብቻ ነው:: ያን ጊዜ ግን ስለ ፍፅምና አይታሰብም::

በዚህ የተነሳ እውነተኛና ትክክለኛው አርቲስት ስለፍፅምና በጭራሽ አያስብም:: ራሱን ለፈጣሪው ኃይል ያንበረክካል፣ አሳልፎ ይሰጣል እንጂ ምንም ይሁን ምን ፍፅምናን አያስባትም፣ አያውቃትምም:: ትክክለኛው ከያኒ ስለሁለንተናዊነት ማሰቡ እርግጥ ቢሆንም፣ ስለፍፅምና ግን ሲያልፍም አይነካው:: በቃ በሁለንተናዊ ሥራው ውስጥ መገኘት ይፈልጋል፣ በቃ ይኸው ነው:: ሲደገስ ዳንሱ ውስጥ ገብቶ መጥፋት ይፈልጋል:: እሱ እዚያ መገኘት አይፈልግም፣ ምክንያቱም የዳንሰኛው መገኘት ዳንሱን ይረብሸዋል:: የዳንሱ፣ የእስክስታው ግርማ ሞገስና ፍሰት ይረበሻል:: ዳንሰኛው ዳንሱ ውስጥ ጠፍቶብን ካላገኘነው ዳንሱ በለዛና በቅኝት የጣፈጠ ይሆናል::

ትክክለኛው አርቲስት የሚያስበው ስለ ሁለንተናዊነት እንዴት በሁለንተና መከወን ይቻላል? የሚለውን ብቻ ነው:: እንጂ ስለፍፅምና አያስብም:: ውበቱ ያለው ሁለንተናዊ የሆኑ ከያኒያን ፍፁምና ወደር-የለሽ መሆናቸው ላይ ነው:: ስለፍፅምና የሚያስቡ ግን መቼም ፍፁም አይደሉም፣ መቼም ሁለንተናዊ አይደሉም:: እንደውም በተቃራኒው ስለፍፅምና ባሰቡ ቁጥር ኒውሮቲክነታቸው (መርበድበዳቸው) እያደገ ይመጣል:: መሆን የሚፈልጓቸው ነገሮች አሉ:: ስለዚህ ራሳቸውን ከእነዚያ ነገሮች ወይም ሰዎች ጋር ማነፃፀራቸውን ይቀጥላሉ፣ ሊደርሱባቸው ግን አይችሉም::

መሆን የምትፈልጓቸው ነገሮች እስካሉና እናንተም እነዚህን ነገሮች ሆናችሁ እስካልተገኛችሁ ጊዜ ድረስ፣ ፍፅምና ላይ የደረሳችሁ አይመስላችሁም፣ ታዲያ በተግባራችሁ እንዴት ሁለንተናዊ መሆን ትችላላችሁ? ለምሳሌ፡- እንደ ጥላሁን ገሰሰ መዝፈን አለብኝ ብላችሁ የምታስቡ ከሆነ እንዴት በሁለንተናችሁ ማንጎራጎር ይቻላችኋል? ከአሁን አሁን እንዳይበላሽባችሁ በመስጋት፣ ለማሻሻል እየሞከራችሁ ራሳችሁን ያለማቋረጥ እየተቆጣጠራችሁ ነው:: ልባችሁ ሁለት ቦታ ተከፍሏል አንደኛው እያንጎራጎረ ነው፣ ሌላው ደግሞ ከፊታችሁ ቆሞ እየመዘናችሁ፣ እያሳያችሁና እየነቀፋችሁ ነው:: በሁለንተናችሁ አይደላችሁም::

ጥሩ ዘፋኝ ፍፅምና ያገኘው ሁለንተናዊ ስለነበር ነው፡፡ ዝነኛው ዳንሰኛ ኒጀስኪም እንዲሁ ነበር፡፡ ኒጂስኪ በሚደንስበት ወቅት ሰዐይን በማይታመን ሁኔታ አየር ላይ እንጣጥ ብሎ ይዘላል፡፡ ድርጊቱ ከስበት ሕግ ውጪ በመሆኑ፣ ለሳይንስ ጠበብት እንኳን እንቆቅልሽ ሆኖ ነበር፡፡ ከዘለለ በኋላ ደግሞ ወደ ምድር የሚመለሰው እንደላባ ቀስ ብሎ እየተንሳፈፈ መሆኑ የበለጠ ያስደንቃል፡፡

ታድያ ስለችሎታው የማይጠይቀው ሰው አልነበረም፡፡ የሰዎች ጥያቄ እየበዛበት ሲመጣና እሱም በበለጠ ሲያስብበት ግን ችሎታው እየከሰመ መጣ፡፡ እንደውም ከናካቴው ጠፋ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ስለችሎታው ማሰቡና መንቃቱ ሁለንተናዊነቱን ስላሳጣው ነው፡፡ ከዚያ ግን ለምን እንደከሰመ ተገነዘበ፡፡ ከዚህ ቀደም ይከሰት የነበረው፣ ኒጂስኪን በዳንሱ ድባብ ውስጥ ይሰምጥና ሙሉ በሙሉ ይጠፋ ስለነበር ነው፡፡ በዚህ ፍፁም መዝናናት ውስጥ ያለ ሰው የሚኖረው ሙሉ በሙሉ በተለየና ለሌሎች ሕግጋት በሚታዘዝ ዓለም ውስጥ ነው፡፡

ፈጠንም ዘገየ ሳይንስ ይደርስበታል ብዬ ስለማምንበት አንድ ሕግ ልንገራችሁ፡፡ የግርማ ሞገስ ወይም የፀጋ ሕግ ብዬ ስይሜዋለሁ፡፡ የስበት ሕግ ከዛሬ 300 ዓመታት በፊት አይታወቅ የነበረው፣ ሕልውና ስላልነበረው አይደለም፡፡ እንድ ሕግ ስላልታወቀ ብቻ ተግባሩን አይወጣም ማለት አይደለም፡፡ ከፍጥረታት ጋር ተፈጥሮ የኖረ ሕግ ነው፡፡ ከአይዛክ ኒውተንና ከፖም ፍሬው መውደቅ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡ ኒውተን ሕጉስ ስለደረሰበት አይደለም ፍሬዎቹ መውደት የጀመሩት፡፡ ሕጉ ያለና የሚኖር ነው፡፡

ልክ እንደዚሁ ሁሉ ወደ ፍፅምና ወይም ወደላይ የሚያነሳ የግርማ ሞገስ ሕግ አለ፡፡ (The Law of Grace) የስበት ሕግ ወደታች የሚገፋ ሲሆን የግርማ ሞገስ ወይም የፀጋ ሕግ ደግሞ ነገሮችን ወደላይ ያስነሳል፡፡ በዮጋ ጥበብ (levitation) ብለው ይጠሩታል፡፡ በአንድ የመሰየት ድባብ ውስጥ፣ በፍፁም የመማረክና የመንበርከክ፣ ኢጐ የሌለበት ድባብ ውስጥ፣ ይህ ሕግ ስራውን መሥራት ይጀምራል፡፡ ክብደት ይጠፋና፡፡ የመንሳፈፍ ብቃት ላይ ይደርሳል፡፡

ኒጂንስኪም ቢሆን የገጠመው ይኸው ነበር፡፡ ዳሩ ግን እናንተ ልትከስቱት አትችሉም፣ ምክንያቱም እናንተ ከተገኛችሁ አይከሰትም!

ኢጐ በእንገታችሁ ላይ እንደታሰረ ገመድ ነው፡፡ ኢጐው ከሌለ ክብደት አይኖራችሁም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ይህ ተሰምቷችሁ አያውቅም? ክብደት የማይኖራችሁ ጊዜያት አሉ፡፡ *ትራመዳላችሁ ግን እግራችሁ ምድር አይረግጥም። በደስታችሁ፣ በፀሎታችሁ፣ በምስጠታችሁ፣ በፈንጠዝያችሁና በፍቅራችሁ ቅፅበታት ክብደት አልባ ሆናችሁ ትንሳፈፋላችሁ።*

ፈጠንም ዘገየ ሳይንስ ይደርስበታል ያልኳችሁም፤ ሳይንስ በተቃራኒ ነገሮች ሕልውና ስለሚያምን ነው። ብቸኛ ሕግ የለም፤ ሕግጋት ሁሉ ተቃራኒ ሕግጋት አሏቸው። የኤሌክትሪክ ኃይል ያለሁለቱ ኔጋቲቭና ፓዘቲቭ ዋልታዎች ግንኙነት ሊፈጠር አይችልም። ስለዚህ የስበት ኃይልም ተፃራሪ ኃይል ይኖረዋል። ይህንን ሕግ ነው፤ የፀጋ ሕግ ያልኩት። ምናልባት ወደፊት ሳይንስ ጠበብት ፈልገው ሲደርሱበት የፀጋ ሕግ ብለው አይሰይሙት ይሆናል። ግን ይህ ስያሜ ይመጥነዋል ብዬ አገምታለሁ።

## 2. ሕሊና (intellect)

"Contemporary Mind" (ያለንበት ጊዜ አእምሮ ወይንም ዘመናዊ አእምሮ) የሚለው አገላለፅ ከያዛቸው ቃላቶች መቃረን የተነሳ የተጣረሰ ነው። አእምሮ በፍፁም ዘመናይ ሆኖ አያውቅም፤ ሠርክ አሮጌ ነው፤ አእምሮ ካለፈው ጊዜ ጋር ብቻ ካልሆነ ከሌላ ነገር ጋር ተያያዥነት የለውም። አእምሮ ማለት ትውስታ ማለት በመሆኑ፤ ያለንበት ጊዜ አእምሮ ሊኖር አይችልም። ከጊዜው ጋር መሄድ ማለት ያለ አእምሮ መሆን ማለት ነው።

በዚህች ቅፅበት እዚህ ከተገኛችሁ፤ ያኔ ኮንቴምፓራሪ ናችሁ። ግን ደግሞ ይህን ጊዜ አእምሯችሁ ይጠፋል! የሚንቀሳቀስ ሐሳብ፤ የሚያንሰራራ ፍላጎት አይኖርም። ስለዚህ ካለፈውና ከመጪው ጊዜ ጋር ትለያያላችሁ።

አእምሮ በጭራሽ አዲስ ሆኖ አያውቅም፤ ሊሆንም አይችልም። ትኩስ፤ አፍላ፤ ወጣት የሆነ አእምሮ የለም። አእምሮ ሠርክ አሮጌ፤ ሠርክ የበሰበሰና ያደረ ነው።

የጠቀስናቸው ቃላት ግን ጥቅም ላይ ይውላሉ። ጥቅም ላይ የሚውሉትም ሙሉ በሙሉ በተለየ ትርጉሜ ነው። ከሚሰጡት ከዚህ ስሜትና ትርጉሜ አኳያ ቃላቶቹ ተጨባጭ ፍቺ እንደሚኖራቸው አይካድም። የአስራ ዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን አእምሮ የተለየ አእምሮ ነው፤ የዚያ ዘመን ሕዝቦች ይጠይቋቸው የነበሩትን ጥያቄዎች እናንተ አትጠይቁም። በአስራ ስምንተኛው ክፍለ-ዘመን ከፍተኛ ቦታ የነበራቸው ጥያቄዎች አሁን የሞኝ ጥያቄዎች ናቸው። ‹‹በአንዲት ስፒል አናት ላይ ስንት መላዕክት መደነስ ይችላሉ? የሚለው ጥያቄ ከመካከለኛው ዘመን የሥነ-ኃይማኖት ጥያቄዎች መካከል እጅግ ከፍተኛ ሥፍራ ነበረው። ዛሬ ግን ይህ ጥያቄ ቦታ ይኖረዋል ብሎ የሚያስብ ቂል ፈልጋችሁ ማግኘት ትችላላችሁ? የሚገርመው ይህ ርዕስ በጊዜው ታላላቅ የሚባሉ የሥነ-ሃይማኖት ሊቃውንት መወያያ መሆኑ ነው። ተራ ሰዎች ሳይሆኑ፤ የተከበሩ ፕሮፌሰሮች ጥናታዊ ፁሁፍ ይፅፉበት የነበረ ነው። እወደ ጥናቶች ይዘጋጁሉ ‹‹ስንት መልእክት በስፒል አናት ላይ እስከስታ መውረድ ይችላሉ?›› የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ! አሁን፤ ለዚህ ጉዳይ ማንም ግድ የለውም። ከዘመኑ ሰው ሕይወት ጋር ተዛማጅ አይደለም።

ቡድሀ በኖረበት ዘመን ትልቅ ቦታ የነበረው ጥያቄ፣ ‹‹ዓለምን ማን ፈጠራት?›› የሚለው ነበር። ጥያቄው ለብዙ ዘመናት ሲያነጋግር የቆየ ቢሆንም፣ አሁን ግን ዓለምን ማን ፈጠራት? ብሎ የሚጨነቅ ሰው ከስንት አንድ ነው። እርግጥ አንዳንድ ዘመኑ ሲለወጥ ያልተለወጡ ሰዎች አሉ፣ ዱሮ ግን እንዲህን መሰል ጥያቄዎች የሚጠይቁ ጥቂቶች ናቸው። ቡድሀ ግን በእየለቱ ይህ ጥያቄ ይሰነዘርላት ነበር፣ አንድ ሰው ‹‹ዓለምን የፈጠራት ማነው?›› ብሎ ሳይጠይቀው የሚያሳልፈው ቀን አልነበረም። ቡድሀ፣ ዓለምን ማንም እንዳልፈጠራት እና ቀድሞውኑ እዚሁ እንደነበረች ደግሞ ደጋግሞ ለማስረዳት ይሞክራል፣ ሰዎች ግን በምላሹ አይረኩም። አሁን ግን ግድ የሚሰጠው ሰውም የለ። ከዚህ ትርጓሜው አኳያ፣ አእምሮ ከማያቋርጠው የጊዜ ለውጥ ጋር አንድ ላይ አብሮ ይለወጣል። ከዚያ አኳያ፣ አሁን ያለንበት ጊዜ አእምሮ ማለት ይቻላል።

ባል ለሚስቱ እንዲህ ይላታል፣ ‹‹ዛሬ ማታ ወጥተን እንዝናናም አልኩሽ እንዝናናም፣ ይህ የሩብ ፍፃሜ ውሳኔዬ ነው።›› ባል ሆኖ የዘመኑ የኳስ ጨዋታ አፍቃሪ ነው። እንግዲህ የዚህን ባል አእምሮ፣ የዘመኑ አእምሮ ልንለው እንችላለን። የድሮ ባል ቢሆን ይህንን አይልም። የድሮ ባል ውሳኔ ሁልጊዜም የመጨረሻ ነው፣ የዋንጫ።

ሁለት የከበርቴ ዘር እንግሊዛዊ ወይዛዝርት፣ ለንደን ውስጥ ለገበያ ወጥተው ሳሉ በአጋጣሚ ይገናኛሉ። አንደኛዋ ሌላዋ ነፍሰ-ጡር መሆኗን ታስተውልና፣ ‹‹ውይ፣ ውድዬ እንዴት ይገርማል! መጨረሻ ከተገናኘን በኋላ ትዳር ይዘሽ ማለት ነው?›› በማለት ትጠይቃታለች ሁለተኛ ወይዘሮዋ፣ ‹‹አዎ። ግሩም ሰው አግብቻለሁ፣ የጉርካ (የሕንድ ግዛት) ጦር መምሪያ ውስጥ መኮንን ነው።›› ትመልሳለች።

ጠያቂዋ በጣም ትደነግጥና፣ ጉርካዊ! ውድዬ፣ እዚህ ቦታ ያሉት ሁሉም ቁጥሮች አይደሉም እንዴ? ‹‹ውይ አይደሉምም›› መለሰች ‹‹ተራ ወታደሮች ብቻ ናቸው።››

ጠያቂዋው በአሽሙር፣ ‹‹ውድዬ ይህስ ዘመኑ ያመጣው ቢሆን ነዋ!›› አለቻት ይባላል።

ከዚህ አንጻር ከሆነ ዘመን አመጣሽ (contemporary) አእምሮ አለ። ካለዚያ ግን ዘመን አመጣሽ ወይም የዘንድሮ አእምሮ የሚባል ነገር አይኖርም። ፋሽኖች ይመጣሉ ይሄዳሉ። ስለፋሽን ካሰብን ለውጥ መኖሩ ግድ ነው። በመሰረታዊነት ግን አእምሮ የተባለ ሁሉ አሮጌ ነው። አእምሮ በተፈጥሮው አዛውንት በመሆኑ ዘመናዊ አእምሮ ሊኖር አይችልም። በዘመናዊነቱ ወደር የሌለው የሚባለው አእምሮ እንኳን ያለው ባለፈው ጊዜ ውስጥ ነው።

በትክክል ህያው የሚባለው እዚህ አሁን የሚኖረው ሰው ነው። የሚኖረው ባለፈው ጊዜ ላይ እየቀጠለ ወይንም ለመጪው ጊዜ ሲል ሳይሆን፣ በዚህች በሚገኝበት ቅጽበት ውስጥ ብቻ ነው። የመኖር ምክንያቱ ወይንም ተስፋውም ይህቺው ቅጽበት ናት። ከዚህች ቅፅበት ውጪ ሌላ ምንም ነገር የለም። ሁሉም የእሷ ናት። ይህ ሰው በራሱ ጊዜ ተቀጣጣይ ወይንም ሰበብን የማይሻ አድራጊ ነው።

ለድርጊት ምክንያት ያለመሻት (spontaneity) ደግሞ፣ የየትኛውም ባሀሪይ አይደለም፡ ፡ አእምሮ የድጋጋሚነት ባህርይ አለው፣ አድቱን እየዞረ ይደጋግማል፡፡ አእምሮ የሚሰራው የተሰጠውን መርህ ተከትሎ ነው፡፡ አንድን ዕውቀት እንመገበዋለን፣ ያንኑ ዕውቀት ሲደጋግም ይኖራል፡፡ ያንኑ ዕውቀት እያላመጠ ይኖራል፡፡

የግልፅነት፣ የንፁህነት፣ የየዋህነት መገለጫ ባህሪያት ከአልቦ-አእምሮ (no mind) ይፈልቃሉ፡፡ እውነተኛው የመኖሪያ መንገድ እውነተኛው የማወቅ መንገድ፣ እውነተኛው የመሆኛ መንገድ፣ አልቦ-አእምሮ ነው፡፡ No-mind is the real way to live, the real way to know, the real way to be.

ማስተዋል የኀሊና ብቃት (intellect) ሐሰተኛ ነገር ነው አስተውሎት (intelligent) ተክቶ ጥቅም ላይ ውሎ እናየዋለን፡፡ አስተውሎት ግን ፍፁም ከዚህ የተለየ ክስተት ነው፡፡ እውን ህልውና ያለውም ማስተዋል ነው፡፡ ማስተዋል ከፍተኛ ድፍረትንና በጀብዱ የተሞላ ሕይወትን ይፈልጋል፡፡ ማስተዋል ሥርክ ወዳልታወቁና ወዳልተዳሰሱ ዓለማት መሄድን ይጠይቃል፡፡ የሚያድገውና የሚጎለብተው ከእያንዳንዱ የማትታወቅ፣ ያልተዳሰሰች ቅፅበት ጋር ፊት ለፊት ሲገናኝ ብቻ ነው፡፡ ሰዎች ያልታወቀውን ይፈራሉ፣ ያልታወቀ ነገር ደህንነታቸውን ሥጋት ላይ ይጥለዋል፡፡ ‹‹ከማያውቁት መልዓክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል›› የሚል መርህ አንግበው ይኖራሉ፡፡ ከሚታወቀው ነገር አልፈው፣ ባሻገር ወደባይተዋር አይሄዱም፡፡ በዚህ የተነሳ ለ‹‹አስተውሎት›› (intelligence) ሐሰተኛና ራሳቸው የፈጠሩት ምትክ ፈጠሩና፣ ‹‹ኀሊና›› (intellect) ብለው ሰየሙት፡፡

ኀሊና ወደ ሐሳብ ከእንጉል ጨዋነት የዘለለ ፋይዳ የለውም፡፡ ስለዚህ ፈጠራ በውስጡ ሊኖር አይችልም፡፡

ወደ ዩኒቨርስቲዎች ጎራ ብላችሁ፣ ምን ዐይነት የፈጠራ ሥራ እንደሚሰራ ማየት ትችላላችሁ፡፡ በሺህ የሚቆጠሩ ጥናታዊ ጽሁፎች ይጻፋሉ፣ ፒኤችዲዎችና ሌሎችም የክብር ዲግሪዎች በሰዎች ላይ ይጫናሉ፡፡ የፒ.ኤች.ዲ ጥናታዊ ጽሁፍ መጨረሻ ምን እንደሚሆን ለማየት ግድ ያለው ተመራቂ የለም፡፡ አዎ፣ እነዚህ ጥናታዊ ጽሁፎች በየመፅሀፍት ቤቱ ከቆሻሻ ክምርነት ያለፈ ቦታ የላቸውም፡፡ የሚያነብባቸውም፣ አንብቧቸው መንፈሱን የሚያነሳሱለትም ማንም የለም፡፡ በእርግጥ ጥቂቶቹ ያነበቧቸው እነዚህ ሰዎች ግን ሌላ ቴሲስ (ጥናታዊ ፁሁፍ) ሊያዘጋጁባቸው እንጂ ስበዋቸው አያነብቧቸውም፡፡

ዩኒቨርስቲዎቻችሁ ሼክስፒሮችን፣ ሚልተኖችን፣ ዶስቶውስኪዎችን፣ ካህሊል ጆብራኖች አይፈጥሩም፡፡ የሚፈጥሩ ፍጹም ጥቅም የለሽ የሆነ ቅራቅንቦ ነው፡፡ ማስተዋል (intelligence) ግን እነ ፒካሶን፣ ጋን ጎግን፣ ሞዛርትን እና ቤትሆቨንን የመሳሰሉ ሊቃውንት ትፈጥራለች፡፡ ማስተዋል ሙሉ በሙሉ የተለየ እውታር ላይ ይገኛል፡፡ ዝምድናው ከጭንቅላት ጋር ሳይሆን ከልብ ጋር ነው፡፡ ኀሊና እንጎል ውስጥ ሲሆን፣ አስተውሎት ግን ልበ-ብርሃናዊነት የልብ ንቃት ነው፡፡ ልባችሁ ሲነቃ ልባችሁ ከህልውና ጋር ሲገጥምና በአንድነት ሲዘምር ልባችሁ በጥልቅ ምስጋና በተሞላ ጊዜ ከሚፈጠረው ህብር የፈጠራ ክህሎት ይመነጫል፡፡

ምሁራዊ የፈጠራ ክህሎት ለክለት የመቻል ዕድልም ያለው። ትርኢ ምርኢ ውጤት ሊኖረው ይችላል፣ ምርታማ ነው፣ መፈብረክ ይችላል፣ ዳሩ ግን መፍጠር አይችልም። ታዲያ በማምረትና በመፍጠር መሀከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ማምረት ስልታዊ እንቅስቃሴ ያለው ሂደት (mechanical activity) ነው። ኮምፒውተሮችም ቢሆኑ ያውም ከሰው በበለጠ ብቃት እያመረቱ ነው። ማምረት ማለት

እስተውሎት (ልቦና) ግን ይፈጥራል እንጂ አያመርትም። ማምረት ማለት ተደጋጋሚ ክንዋኔ ነው። ቀደም ብሎ የተሰራ ነገርን እየደጋገሙ ማድረግ ማለት ነው። ፈጠራ ማለት ለአዲሱ ሕልውና መስጠት ያልታወቀው የታወቀውን ግለ የሚወጣበትን መንገድ መጥረግ፣ ሰማይ ወደ ምድር እንዲመጣ መንገድ መቀየስ ማለት ነው።

አንድ ቬትሆቨን ወይ አንድ ሚካኤለ አንጀሎ በሚኖር ጊዜ ሰማያት ይከፈታሉ፣ ከዓለም ባሻገር ያለ ዓለም አበቦች ይዘንባሉ። ስለ ቡድሀ፣ ስለ ኢየሱስ፣ ስለ ክሪሽና ስለማህቪራ ስለዛራቱስትራ ወይ ስለሙሀመድ የማላነሳላችሁ ምክንያት ስላለኝ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ነፍሳት የሚፈጥሩት እጅግ ረቂቅ ከመሆኑ የተነሳ ከግንዛቤ በላይ ስለሚሆንባችሁ ነው። ሚካኤል አንጀሎ የፈጠረው ተጨባጭ ነገር ነው፣ ጋሽን ጉን የፈጠረውም በግለፅ ሊታይ ይችላል። ቡድሀ የሚፈጥረው ግን ፍጹም ከእይታ የተሰወረ ነው። ይህንን ለመረዳት ሙሉ በሙሉ ልዩ የሆነ አቀባበልን ይጠይቃል። አንድን ቡድሀ ለመረዳት ልቡናዊነት ወይም እስተውሎት ያሻል። ምክንያቱም በቡድሀ ፍጥረት ላይ ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ እስተውሎት መኖሩ ብቻ ሳይሆን፣ ከፍጥረቱ ዕፁብነትና ከአእምሮ በላይ ባህሪዩ የተነሳ ሌላው ይቅርና ለመረዳት ብቻ እንኳን እስተውሎ ወይም ልቡና ያስፈልገናል ነው። ኀሊና ግን ይህንን ለመረዳት እንኳን ጥቅም የለውም።

የሚፈጥሩ ሁለት ዐይነት ሰዎች አሉ - ተቃኚያን እና ኀቡእት (poets and mystics)። ባለቅኔዎቹ በተጨባጩ ዓለም ውስጥ ሲፈጥሩ፣ ኀቡእት ደግሞ በረቂቁ ዓለም ውስጥ ይፈጥራሉ። ተቃኚያን በስተ-ውጪው ዓለም ውስጥ አንድ ስዕል፣ ግጥም፣ ዜማ ወይንም ቅኔ ሲፈጥሩ፣ ኀቡእት ደግሞ በበስተ-ውስጡ ዓለም ውስጥ ይፈጥራሉ። የተቃኚው ፈጠራ እማሬያዊ (objective) የኀቡኡ ፈጠራ ደግሞ ፍካሬያዊ (subjective) እና ፍፁም ስውር ነው። ከሁሉ በፊት ባለ-ቅኔውን ወይም ተቃኚን መረዳት ይኖርባችኋል። ያን ጊዜ ብቻ ነው፣ ያውም አንድ ቀን ምናልባት፣ ኀቡኡን ልትረዱት የምትችሉት። ኀቡኡ፣ የፈጠራ ክህሎት የመጨረሻው ከፍተኛ እንቁ ነው። ዳሩ ግን ኀቡኡ እያደረገ ያለው ላይታያችሁ ይችላል።

ቡድሀ አንድ ስዕል ስሎ ወይም ብሩሽ አንስቶ እንኳን አያውቅም። ቅኔ ተቀኝቶም ሆነ ዜማ አዚሞም አያውቅም። ሲደንስ ወይም ሲጨፍር ተመልክቶት የሚያውቅ ሰውም የለም። እናንተም ተመልክታችሁ ቢሆን፣ በፀጥታ እንደተቀመጠ፣ ኀላዌው ሙሉ በሙሉ ፀጥታ መሆኑን ትመሰክሩ ነበር። አዎ፣ የከበበውና የሰፈነበት ፀጋ ነበር፣ ወሰን-የለሽ የውበት ፀጋ፣ የነጠረ ልዩ ውበት። ይሁን እንጂ፣ ይህንን ፀጋ ለመረዳት እጅግ የዋህ መሆን ይኖርባችኋል። ክፍት ተቀባይነት እንጂ ተሟጋች ባህሪይ ይዛችሁ መቅረብ አይኖርባችሁም። ከአንድ ቡድሀ ጋር በተመልካችነት መገኘት

አይችልም፣ ተሳታፊነት ያስፈልጋል። ምክንያቱም ተሳታፊነትን የሚሻ ምስጥር ነው። ሁሉ ጊዜ እየፈጠረ ያለውን ትመለከታላችሁ። የሚፈጥረው ንቃተ-ሕሊናን ነው። ንቃተ-ሕሊና ከትርፎች ሁሉ የላቀ ንጽህና ያለው ወይንም ምንም ያልተቀላቀለበት ጽርጽ ነው። ማለትም ከንቃተ-ሕሊና በላይ፣ ገዛዱን ዓለም ወይንም መቅረፅ የሚችል ለላ ምንም ዐይነት ቅኔ የለም።

አንድ ዝማሬ ወይንም ሽብሸባ ጥዑምና ውብ የሚሆነው፣ ከመለኮት የተወሰነ እንጥብጣቢ ይዞ ሲገኝ ነው። በአንድ ቡድሀ ውስጥ ግን የፈጣሪ አምሳክ ሙሉ መለኮት ይገኛል፡

የኅሊና ብቃት አንዳንድ እውቀትን የሚሹ ነገሮች ላይ ጠቃሚና ውጤታማ ተግባራትን እንድታከናውኑ ያስችላችኋል። ዳሩ ግን ኅሊና መዳበስ ያህል ነው። ኅሊና ወይም ሐሳብ ገና ምስጢትን ስለማያውቁት፣ ዐይን የሌለው ዐይነ ስውር ነው። ኅሊና በብድር የመጣ እንጂ የራሱ አመለካከት የለውም።

*ርዕሰ ጉዳዩ የፍቅር ጨዋታ ነበር። አርተር የተባለ ሰው በአንድ የቴሌቪዥን ጥያቄና መልስ ውድድር ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችን ሁሉ በትክክል መለሰ። ባገኘው ደረጃ መሰረትም አንድ መቶ ሺህ ዶላር ስለሚያስገኘው የጃክ ፖት ጥያቄ ተዘጋጀ። በዚህኛው ጥያቄ ብቻ በርዕሱ ላይ ዕውቀት ወዳለው ባለሙያ መደወል ይፈቀድለታል። አርተር የዋዛ ባለመሆኑ፣ በዓለም ዝነኛ ወደሆኑ ፈረንሳዊ የሥነ-ፆታ ፕሮፌሰር ይደውላል።*

*አሸላሚው ጥያቄም፣ ‹‹በአሶር አገዛዝ ዘመነ-መንግስት የመጀመሪያዎቹ ሃምሳ ዓመታት ነግሰህ ቢሆን ኖሮ በሰርግህ እለት ምሽት ልትስማቸው የሚጠበቅብህ ሦስቱ የአዲሷ ሙሽራህ የሰውነት ክፍሎች ምንድን ናቸው?››የሚል ነበር።*

*የመጀመሪያዎቹ ሁለቱን መልሶች አርተር እራሱ ወዲያው በማግኘት ‹‹ከናፍሮቿንና አንገቷን።›› ብሎ መለሰ።*

*ሦስተኛው መልስ ሲመጣለት ስላልቻለ፣ እገዛ ፍለጋ ለፈረንሳዩ ባለሙያ ጥያቄውን አቀረበ። ፕሮፌሰሩ ግን እኔ ምን አውቄ በሚል ዐይነት እየጋገር፣ ‹‹alors, nonami፣ እኔን ባትጠይቀኝ ይሻላል። እስካሁን እንኳን ሁለት ጊዜ ተሳስቻለሁ። ሲሉ መለሱለት እላችኋለሁ።*

ይታያችሁ ባለሞያው፣ ምሁሩና፣ ጠበብቱ የራስ የሆነ አመለካከት የላቸውም። የውስት ዕውቀት፣ የባህልና የደንብ ጥገኛ ናቸው። በጭንቅላታቸው ትልቅ ቤተ-መፀሐፍት ተሸክመው ይዞራሉ፣ ግን ራዕይ የላቸውም። የምንም ነገር ዕውቀት ሳይኖራቸው ብዙ ነገር ያውቃሉ ይባላሉ።

ሕይወት ከአፍታ አፍታ ዘወትር ስለምትቀያየር፣ ባለሞያው ዘወትር ኋላ ይቀራል፣ የሚሰጠው ምላሽም በቂ አይሆንም። በራሱ ጊዜ ወደ ድርጊት መግባት ስለማይችል ምላሽ ከመስጠት ሌላ ነገር አያውቅም። ቀድሞ ነገር መደምደሚያዎች ላይ ደርሷል። ቀደም ብለው የተመለሱ ‹‹ሬዲ ሜድ›› መልሶችን ይዞ ይዞራል። ሕይወት የምታነሳቸው ጥያቄዎች ደግሞ ዘወትርም አዳዲስ ናቸው።

ከዚህም በላይ ሕይወት ምክንያትን የምትከተል ክስተት አይደለችም። ኀሊና-መሩ ምሁር ግን ሎጂክን ተከትሎ ይኖራል። በዚህ የተነሳም እሱም ከሕይወት ሕይወትም ከእሱ ተጣጥመው አይዛለቁም። ይህ የሆነው ሕይወት ችግር ስላለባት ሳይሆን ምሁሩ ችግር ስላለበት ነው። ሠርክ ከመገለል ስሜት ጋር ይኖራል። ሕይወት ስላገለለችው ሳይሆን፣ እሱ ከሕይወት ራሱን በማግለሉ የሚፈጠርበት ስሜት ነው። *ሎጂክን የሙጥኝ ብላችሁ ከያዛችሁ ደስንበት ህሳዋ ይዞት የሚኖረው የሕይወት ሂደት እንደ አካል ልትሆኑ አትችሉም። ሕይወት ከሎጂክ በላይ ናት። ሕይወት እንቅቅልሽና ምስጥር ናት።*

*ጋናዊይ እና አኬይሲ የተባሉ ሁለት ጠበኞች፣ ጠባቸው በመክረሩ ይለይልን ተባብለው ለሽጉጥ ሽኩቻ ቀን ቆረጡ። (በቀድሞ አውሮፓውያንና አሜሪካውያን ባህል መሰረት ሁለት ሰዎች ለሽጉጥ ሽኩቻ ቀን ከቆረጡ በኋላ በእለቱ በተወሰነ ሰፊ ሜዳ ላይ ተገናኝተው በአስር ሜትር ርቀት ፊት ለፊት ይቆማሉ። ከዚያም የሽኩቻቸው ዳኛ ምልክት ሲሰጥ ሁለቱም የታጠቁትን ሽጉጥ አውጥተው በፍጥነት ወደ ባላጋራቸው መተኮስ ነው። ሽጉጦቻቸው ውስጥ ከአንድ በላይ ጥይት ማጉረስ አይፈቀድላቸውም። ኢላማውን በትክክል ያገኘ አሸናፊ ይሆናል። በዚህ ሽኩቻ ታዲያ፣ ጋናዊይ ፊት ለፊቱ የቆመ ጠላቱን ከሲታነት ያስተውልና አቤቱታውን ያሰማል። ጋናዊይ ከመጠን በላይ ወፍራም በመሆኑ ለኢላማ ከተቀናቃኙ ይልቅ የተመቸ ሰውነት አለው።*

*‹‹ይህን አልቀበልም፣›› ይላል ጋናዊይ። ‹‹እኔ የእሱን ሁለት እጥፍ በመሆኔ ፍልሚያው ላይም እሱ እኔ ካለሁበት ርቆ ከቆመበት ርቀት ሁለት እጥፍ ርቀት ላይ መቆም ይኖርብኛል።›› የሚል ነበር፣ አቤቱታው።*

*ያቀረበው የመከራከሪያ ሙሉ በሙሉ ምክንያታዊ ወይም ሎጂክን የተከተለ ነበር። ግን የጠየቀውን እንዴት መፈፀም ይችላል?*

> ባለጋራውም ሲመልስ፣ ‹‹ረጋ በል፣ ይህንን ችግር እኔ እፈታዋለሁ፡፡›› ብሎ ከኪሱ ትንሽ ጠመኔ በማውጣት በጠብደሉ ጋናዊይ ደረት ላይ ሁለት በመካከላቸው ክፍተት ያላቸው መስመሮች ቁልቁል ያሰምራል፡፡
>
> ‹‹አሁን መተኳኮስ እንችላለን፣ ግን ከእነዚህ መስመሮች ግራና ቀኝ ያረፈ ጥይት ነጥብ አያስገኝም፡፡›› አለው አላችኋለሁ፡፡

ሽኩቻው ላይ፣ ፍፁም እንከን የማይወጣለት ሎጂካዊ ጥያቄና ሎጂካዊ ምላሽ ተመልክተናል! ሕይወት ግን ይህን ያህል ሎጂካዊ አይደለችም፡፡ በሒሳብ የስሌት ሕግጋት አትመራም፡፡ ሰዎች ግን ሎጂክን ብቻ እየተከተሉ መኖራቸውን ቀጥለዋል፡፡ ምክንያታዊነት መከተላቸው ምሁርነታቸውን ወይም የእውት ባለቤትነታቸውን ያረጋግጥላቸዋል፡፡ ዳሩ ግን የ‹ቢሆንስ› ባህሪው ስለሚያመዝን ሰዎች ምክንያታዊነትን ይዘው መዝለቅ አይችሉም፡፡ በኅሊናችን አማካይነት ስናደርገው የኖርነው ሁሉ፣ ምክንያት ተመርኩዘን የደረስንበት መደምደሚያ ነው፡፡ ድርጊቶቻችን ሁሉ የእውነት ነፀብራቅ ሳይሆኑ፣ በስምምነት የተቀረፁ ደንቦችና ሕጎችን የተመረኮዙ ውሳኔዎቻችን ናቸው፡፡ ይህም፣ ሎጂካችሁ የራሳችሁ ፈጠራ እንጂ የራሱ ህልውና የሌለው መሆኑ ግልፅ ያደርገዋል፡፡

> ኩዳሂ የተባለ ሰው የቅዱስ ፓትሪክ በዓልን ለማክበር የሚደረገውን የሰልፍ ሥነ-ስርዓት ለማየት አደባባይ ይወጣል፡፡ ሳያውቀው፣ እያጤሰው የነበረውን ሲጋራ ለክብረ በዓሉ በተነጠፈ ምንጣፍ ላይ ጥሎታል፡፡
>
> ልክ ያን ጊዜ፣ የሴት ወታደር ነርሶች የሰልፍ ቡድን በሰልፍ ሆነው መሬቱን በጫማቸው እየደለቁ ማለፍ ይጀምራሉ፡፡ በተመሳሳይ ወቅት እሳት የገባው ምንጣፍ ከባድ ሽታ ያለው ጢስ ይለቅቃል፡፡
>
> ኩዳሂ ጠረኑን አንድ ሁለት ጊዜ በአፍንጫው ማግ ማግ ያደርግና፣ ቅርብ ወደተመለከተው አንድ መኮንን በመሄድ፣ ‹‹ጌታዬ፣ እነዚያን ነርሶች በጣም እያጣደፏቸው ነው!›› አለው ይባላል፡፡

ኅሊና በተወሰኑ ምክንያታዊ መደምደሚያዎች ላይ ሊደርስ ይችል ይሆናል፤ ኅሊና ወይም ሐሳብ ግን ማስተዋል የራቀው ክስተት ነው። በእንቅልፍ ልብ እንደ መራመድ ይቆጠራል።

አስተውሎት (intelligence) ግን መንቃት ነው። ስለዚህ ሙሉ በሙሉ ወይም በደንብ እስካልነቃችሁ ድረስ፣ የምትደርሱበት ውሳኔ ሁሉ በአንድ ወይ በሌላ መልኩ ስህተት ውስጥ መግባቱ አይቀሬ ይሆናል። መሳሳቱ አይቀሬ የሚሆነውም ባንቀላፋ አእምሯችሁ የደረሳችሁበት መደምደሚያ በመሆኑ ነው።

*አስተውሎትን / ልቡናን / ተግባር ላይ በማዋል ልቦናዊ ሕይወትን መኖር የሚያስፈልጋችሁ ተጨማሪ መረጃ ሳይሆን ተጨማሪ አርምሞ / ፀጥታ ነው። የበለጠ ዝምታና ስክነት፣ የበለጠ ሐሳብ-የለሽ ወና አእምሮ ያስፈልጋል ነው። ከአእምሯችሁ ይልቅ ወደልባችሁ ማድላት አለባችሁ። የነበባችሁት ምትሃት ማስተዋል ይጠብቅባችኋል።*

የሕይወትን ምትሃት፣ የፈጣሪ እምላክን ምትሃት፣ በለምለም ዛፎችና በቀለም ባሸበረቁ አበቦች ውስጥ ያለውን ምትሃት፣ በሰዎች ዐይኖች ውስጥ ያለውን ምትሃት . . . ምትሃትን በማንኛውም ሥፍራ ታገኙታላችሁ፤ ምትሃታዊና ተዓምራታዊ ያልሆነ ምንም የለም፤ ዳሩ ግን በኀሊናችሁ የተነሳ ማለትም በምክንያታዊ ሐሳቦቻችሁ የተነሳ ከራሳችሁ ሳትላቀቁ፤ በራሳችሁ ታስራችሁ፤ እውስጣችሁ ተቆልፎባችሁ ትኖራላችሁ። በእንቅልፍ ልባችሁ የደረሳችሁባቸው መደምደሚያዎችን፤ ወይም ከሌሎች ልክ እንደ እናንተው በእንቅልፍ ልባቸው ከሚመለሱ ሰዎች የተላለፉላችሁን የውሳኔ ሐሳቦች የሙጥኝ ብላችሁ ትኖራላችሁ።

ልቦና ግን ፈጠራን አጎናፃፊ መሆኑ አያጠራጥርም ምክንያቱም ልቦና፤ አእምሮአችሁን ወይም ሌላ ክፋያችሁን ብቻ ሳይሆን ሁለንተናችሁን ሥራ ላይ ያወጣዋል። ልቦና፤ ምሉዕ ኃላዊያችሁን ያናውፀዋል፤ ያርገበግበዋል። ማስተዋል ለእያንዳንዷ የማንነት ሕዋሳችሁ፣ እያንዳንዷን የሕይወታችሁን ድርና ማግ ቀስቅሶ፣ እየቃኘ በማንቀሳቀስ ከሁለንተናዊው ኀልውና ጋር ኅቡዕ-ኀብራዊነትን ያጎናፅፏል።

ፈጠራ ማለት ይህ ነው፤ ከሁለንተናዊው ሕልውና ጋር በፍፁም ኅብራዊነት መቃኘትና መዘመር ነው። ነገሮች በራሳቸው ጊዜ መፈጠር ይጀምራሉ። ልባችሁ የሐሴት መዝሙሮችን ማሰማት ይጀምራል። እጆቻችሁ ነገሮችን መለወጥ ይጀምራሉ። የምትዳስሱት ሁሉ እናንተ ወደምትፈልጉት ይቀየራል። ብረትን ወደ ወርቅ የመለወጥ ኃይልን ታገኛላችሁ። ይህን መሆን የሚቻለው ግን በታላቁ የአስተውሎት ንቃት፣ በታላቁ የልቡና ንቃት ውስጥ በማለፍ ብቻ ነው።

## 3. እምነት

አንድ ፈጣሪ ብዙ እምነቶች አይኖሩትም፤ እንደ እውነት ከሆነ ምንም እምነት አይኖረውም። ከራሱ ልምዶች በስተቀር የሚያምንበት ነገር የለውም። የሕይወት ልምድ ብዙ ገፅታ፣ ልምዱ ተጨማሪ ምርምርን የሚጋብዝ ክፍት መሆኑ ነው። እምነት ግን ስርክ ዝግ ነው፤ ምክንያቱም ሙሉ መደምደሚያ ላይ ደርሷል።

እምነት ያለቀለት የተጠናቀቀ ነው፡፡ ልምድ ግን ፈፅሞ አይበቃም፡፡ እየኖራችሁ ሳላችሁ የሕይወት ልምዳችሁ እንዴት ሊያበቃ ይችላል? ልምዳችሁ እያደገና እየተለወጠ ዘወትር እንቅስቃሴ ላይ ነው፡፡

ያለማቋረጥ፣ ከታወቀው ወዳልታወቀው፣ ካልታወቀው ሊታወቅ ወደማይችለው ሲመላለስ ይኖራል፡፡ ውበቱ አለማብቃቱ መሆኑን ደግማችሁ አስታውሱ፡፡ ከተቀመሩ ዜማዎች ሁሉ ወደር የለሽ የተባሉት ገና ሰርተው ያልተጠናቀቁት ነበሩ፡፡ ታላቅ ከተባሉት መፅሐፍት ጥቂቶቹም መቋጫ ያላገኙ ነበሩ፡፡ በዓለማችን በታላቅነት ተርታ የተሰለፉ ሌሎችም የኪነ-ጥበብ ሥራዎች አሉ፡፡ ያልተቋጨ ውብ ነው፡፡

የሰማሁት አንድ የዜን ተረት አለ፡-

አንድ ንጉሥ የአትክልት ሥፍራ አያያዝ ትምህርት ለመቅሰም ወደ አንድ የዜን መምህር ይሄዳል፡፡ መምህሩ ለሦስት ዓመት ባሰለጠነው ጊዜ ውስጥ ንጉሡ ያገኘውን ዕውቀት ሁሉ በራሱ ትልቅና ውብ መናፈሻ ውስጥ ይሞክረው ነበር፡፡ ከሦስቱ ዓመታት በኋላ የንጉሱ መናፈሻ እንከን በሌለው መልክ ዝግጁ ስለሆነ መጥቶ እንዲጎበኝለት መምህሩን ይጋብዘዋል፡፡ መምህሩ በጣም ጥብቅ በመሆኑ ንጉሡ፣ «ያደንቅልኝ ይሆን?» በሚል ተጠብቧል፡፡ ጉብኝቱ እንደፈተና በመሆኑ «እም» ትምህርቱ ገብቶሐል፣ ብሎ ያሞግሰኝ ይሆን?» በሚል ሐሳብ ገብቶታል፡፡

ከትልቅ እስከ ትንሽ ጉዳዮች በጥንቃቄ ተስተካክለዋል፡፡ መናፈሻው በውብ ሁናቴ በመጠናቀቁ የቀረ ነገር አልነበረም፡፡ ያን ጊዜ ነበር ንጉሡ መምህሩን የጋበዘው፡፡ መምህሩን ግን ከመግቢያ ጊዜ አንስቶ ሃዘን እጥልቶበታል፡፡ መናፈሻው ውስጥ ከወዲ ወዲህ እየተዘዋወረ ይቃኛል፡፡ ቀስ በቀስ ማምረር ጀመረ፡፡ ንጉሡ ተደናገጠ፡፡ ይህ ያህል ሲመረር አይቶት አያውቅም፡፡ «ምን እንከን አግኝቶበት ነው እንዲህ ያዘነብን?» ብሎ አሰበ፡፡

መምህሩ ራሱን ግራ ቀኝ እየወዘወዘ «አይሆንም» ይላል፣ አሁንም አሁንም እየደጋገመ፡፡

ንጉሡም፣ «ምንድነው ችግሩ መምህር? ለምን አትነግረኝም? ሲሰው ያሳዘነህ ትመስለለህ፡ ለምንድን ነው? እኔ የታየኝ ምንም እንከን የለም፣ የሰራሁት አንተ ያስተማርከኝን ነው፡፡ ይለዋል፡፡

መምህሩም፣ «ከመጠን አልፎ ከመጠናቀቁ የተነሳ ሙት ሆኗል፡፡ ሥራው ከመጠን በላይ ተቋጭቷል፣ ለዚያ ነው የማዝነውና «አይሆንም» የምለው፡፡ የሞቱና የደረቁ ቅጠል የደረቁ ቅጠሎች የታሉ? የረገፉ ቅጠሎችስ የታሉ? አንድም የደረቀ ቅጠል

አላየሁም፣›› የደረቁ ቅጠሎች ሁሉ ተነስተዋል፣ መተላለፊያዎቹ ላይ የቅጠል ዱር የለም። ዛፎቹ ላይ የጠወለጉ ቢጫ ቅጠሎች አይገኙም። ‹‹እነዚያ ቅጠሎች የታሉ..

ንጉሡ መለሰ፣ ‹‹አትክልተኞቼን ሁሉን ነገር አንስተው በማፅዳት አንዳች እንዳይኖረው አድርጉት፣ ብያቸው ነው።›› በማለት።

መምህሩም፣ ‹‹ለዚያ ነዋ ደብዛዛና ሰው ሰራሽ የመሰለው። የፈጣሪ አምላክ ስራዎች ግን መቼም ቢሆን መቋጫ የላቸውም።›› ብሉት ቅጠሎቹ ተጠርገው ወደተከመሩበት ሄደ፣ ከዚያም ከክምሩ በባልዲ ሞልቶ ደረቅ ቅጠሎችን ይዞ ተመለሰና፣ ሽቅብ ለነፋሱ በተናቸው። ነፋሱም እያንሳፈፈ ያስደንሳቸው ጀመር። ይሄኔ ተደስቶ፣ ‹‹አሁን ምን ያህል ህያው እንደሆነ ተመልከት፣ አለው። የነፋሱና የቅጠሎቹ ጨዋታ የሙዚቃ ያህል ጣፋጭ የሹክሹክታ ድምፅ ፈጥሯል። አሁን መናፈሻው በሹክሹክታ መናገር ጀምሯል። ካለዚያ ግን የመቃብር ሥፍራን ያህል ሙት በሆነ ነበር። የቀድሞው ፀጥታ ህያው አልነበረም። ይህንን ታሪክ እወደዋለሁ። መምህሩ እንዳሉት፣ ‹‹ከመጠን አልፎ መጠናቀቁ ነው ችግሩ።

ባለፈው አንድ ምሽት አንዲት ሴት ወደ እኔ መጥታ ነበር። ልብወለድ በመፃፍ ላይ በመሆኗና፣ ማድረግ ያለባትን ባለማወቋ ግን ግራ መጋባቷን ገለፀችልኝ። መጠናቀቅ የሚችልበት ነጥብ ላይ ብትደርስም፣ ከዚያ በላይ መስፋት እንደሚችልም ስለታያት፣ ገና አልተጠናቀቀም የሚል ሥጋት እንዳስጨነቃት ተነተነችልኝ። እኔም፣ ‹‹አጠናቅቂው። ያላለቀ ስመስለሽ ቋጪው። ያን ጊዜ ምስጢራዊ ድባብን ይጎናፀፋል። በአንጥልጥል መቅረቱ በራሱ ውበት ይሰጠዋል።›› አልኩና ነገርኳት።

ማንኛውም ድርሰት ወይም ታሪክ ቢሆን ፍፅም ከተጠናቀቀ ውበት አይኖረውም። እንደውም ፍፅም ሙት ይሆናል። የሕይወት ልምድም ዘወትር ያለመቋጫ ክፍት ሆኖ ይኖራል። እምነት ሁሉ የተቋጨና ያለቀለት ነው። የመጀመሪያው ወይንም ቀዳሚው የሰው ልጆች ባህሪይ ለሕይወት ልምድ ክፍት የሆነ አቋምን መያዝ ነው።

*አእምሮ የእምነቶቻችሁ ሁሉ ድምር ውጤት ነው። ክፍትነት ማለት አልቦ-አእምሮ (no mind) ማለት ነው። ክፍትነት ማለት አእምሮን ተውት በማድረግ ሕይወትን ባረጁ ሳይሆን በአዳዲስ ዐይኖች ደግሞ ደጋግሞ ስመመልከት ፈቃደኛ ዝግጁ መሆን ማለት ነው። አእምሮ ሕይወትን የሚያሳያችሁ ባረጁ ዐይኖች ነው፣ ማለቴ ጥገኛው እስከሆናችሁ ድረስ ‹‹በዚህ መንገድ ተመልከቱ›› እያለ ሐሳቦችን እየሰጣችሁ ባሪያው ያደርጋችኋል ለማለት ነው። ግን ደግመው የአእምሮን መንገድ ስትከተሉ፣ የምትመለከቱት ነገር በቀለም ይብረቀረቃል፣ ይህን ጊዜ ነገርየውን መመልከት በሙተው የአንድ ሐሳባችሁ ነፀብራቅ ታደርጉታላችሁ። ስለዚህ የምትመለከቱት ሐሳቦችን እንጂ ነገርየውን አይሆንም። በዚህ የተነሳ*

ለእናንተ እውነት ማለት ያስማቆረጥ ሐሳባችሁን የምታንፀባርቁበት ባዶ ሰሌን ይሆናል።

በአልቡ-አእምሮ መነፅር ተመልከቱ፣ በምንምነት መነፅር ተመልከቱ። በአልቡ እእምሮ መነፅር ስትመለከቱ ግንዛቤያችሁ ብቃት ይኖረዋል ምክንያቱም ይህን ጊዜ እውነት ጥርት ብላ ትታያችኋለች። እውነትም ነፃ ታወጣለች። ሌላው ሁሉ ባርነትን ፈጣሪ ነው፣ ነፃ የምታወጣው እውነት ብቻ ናት።

በእነዚህ የአልቡ-አእምሮ ቅፅበታት ውስጥ እውነት እንደብርሃን ወደ እናንተ እየዘለቀች መግባት ትጀምራለች። በዚህ ብርሃን እና በዚህ እውነት የበለጠ ሐሴትን እያደረጋችሁ ስትመጡ አእምሯችሁን ወደ ጎን ለመተው የሚያስችላችሁን ብቃትና ወኔ ጎን ለጎን ታገኙታላቹ። ፈጠነም ዘገየ ተመልከታችሁ የአእምሯችሁን ያለመኖር የምታስተውሉበት አንድ ቀን መምጣቱ አይቀርም። ከመመልከት በስተቀር ዐይኖቻችሁ የሚያርፉበት ምንም የተለየ ነገር የለም። ምልከታችሁ ንፁህ ነው። ልክ በዚያች ቅፅበት አቫሎኪታ ‹‹avaloxita›› ከቡድሃ ስያሜዎች መካከል አንዱ ነው። እሱ ይመለከተው ያለምንም ሐሳቦች፣ በንፁህ ዐይኖቹ ነው።

ፈጠራ በተለይ የሚዛመደው ምንም ዐይነት ክንዋኔ የለም። ማለትም ይህ ነው ተብሎ ከተቀመጠ ክህሎትን ከሚጠይቅ ስራ፣ ለምሳሌ፣ ከሥነ-ስዕል፣ ከውዝዋዜ፣ ከማቀንቀን ወዘተ. ጋር ምንም የተለየ ግንኙነት የለውም። ማንኛውም ነገር ፈጠራን አዘል ሊሆን ይችላል። ክንዋኔው ላይ ይህንን ባህሪይ ማላበስ የምትችሉት እናንተ ናችሁ። ክንዋኔ ራሱም ቢሆን ፈጠራን የተላበሰ ወይንም ያልተላበሰ ሊሆን ይችላል። ፈጠራ ያልታከለበት ስዕል ልትስሉ ፈጠራ ሊያልፍም የማይነካውን ዜማ ልታቀነቅኑ ትችላላችሁ። በሌላ መልኩ ደግሞ ወለላችሁን ፈጠራ በታከለበት መልክ ልታፀዱት ምግባችሁን በፈጠራ ልታበስሉ ትችላላችሁ። ፈጠራ ማለት በምታካሂዱት ክንዋኔ የምታክሉት ልዩ ባህሪ ነው። ነገሮችን የምትመለከቱበት አቋምና ውስጣዊ አቀራረብ ነው።

በዚህ የተነሳ ከሁሉ አስቀድመን ማስታወስ የሚኖርብን ፈጠራን ከተለየ አንድ ዘርፍ ጋር ማቆራኘት እንደሌለብን ነው። ፈጣሪነት የዚያ የፈጠራው ባለቤት ባህሪ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ሰው ፈጣሪ ከሆነ ወይም የፈጠራ ክህሎት ካለው፣ የሚያደርገው ማንኛውም ነገር በፈጠራ የታጀበ ይሆናል። ቢራመድ እንኳን በአረማመዱና አካሄዱ ላይ ፈጠራ ይታይበታል። ሌላው ቀርቶ ምንም ነገር ሳያደርግ በዝምታ ቢቀመጥ እንኳን ምን ባለማድረጉ ብቻ የማስተዋል የፈጠራ መንፈስ ይኖረዋል። ያለምንም ሥራ በቡድሂ ዛፍ ሥር የተቀመጠው ቡድሀ ዓለም ላይ ከተከሰቱ ጥቂት ታላላቅ ፈጣሪዎች መሃል አንዱ ነው።

የፈጠራ ክህሎት ወይም ፈጠራ የጎለለቡ መሆኑን ከተረዳችሁ፣ የፈጠራ ክህሎት ባለቤት አይደላሁም የሚለው ስሜት ይጠፋል።

ሁላችንም ሰዓሊ መሆን አንችልም፤ አስፈላጊም አይደለም። ሁሉም ሰው ሰዓሊ ቢሆን ኖሮ ዓለም አስቀያሚ በሆነችና መኖርም አስቸጋሪ በሆነ ነበር። ሁላችንም ዜመኞች መሆን አንችልም፤ አስፈላጊም አይደለም። ዳሩ ግን ሁላችንም የፈጠራ ክህሎት ሊኖረንና ፈጣሪ ልንሆን እንችላለን።

ምንም አድርጉ ምን በደስታና በፍቅር መንፈስ ካደረጋችሁትና ልታደርጉት የተነሳሳችሁበት ምክንያቱ የገንዘብ ፍቅር ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ብቻ እስካልሆነ ድረስ ድርጊታችሁ ፈጠራ ነው። ሥራችሁ በውስጣችሁ አዲስ ነገር እንዲበቅል ምክንያት ከሆነ ዕድገትን ካመጣላችሁና መንፈሳዊ ከሆነ የሰራችሁትን ፈጠራ ነው። ሥራችሁ መለኮታዊ ነው። የፈጠራ ክህሎታችሁ እያደገ ከመጣ መለኮታዊነታችሁም እያደገ ይሄዳል። የዓለማችን ሃይማኖቶች ሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው ብለዋል። እኔ ፈጣሪያችን እሱ ይሁን አይሁን ባላውቅም የፈጠራ ክህሎታችሁ እያደገ ሲሄድ መለኮታዊነታችሁም (Godlyess) እየጨመረ እንደሚሄድ ግን አውቃለሁ። የፈጠራ ችሎታችሁ የመጨረሻው ደረጃ ላይ ሲደርስና ጣሪያውን ሲነካ በእግዚአብሄር ውስጥ ወይም በፈጣሪ አምላክ ዓለም ውስጥ መኖር ትጀምራላችሁ። አሁን የእኔ ጥያቄም መልስ ያገኛል፤ የፈጠራ ክህሎትን ከታደሉ ሰዎች በላይ በፈጣሪ አምላክ የቀረበ ሌላ ማንም ከሌለ ፍጥረተ-ዓለም የፈጣሪ አምላክ ውጤት ናት ማለት ይሆናል።

የምታደርጉትን ውደዱ። የምትሰሩት ምንም ይሁን ምን በእርምጃ ሆናችሁ አክናውኑት። ያን ጊዜ ፅዳት እንኳን ፈጠራ ሊሆን እንደሚችል ይገለፅላችኋል። በምን ፍቅር? መልሱ ውስጣችሁ በሚዘምርና በሚፈነድቅ ፍቅር ነው። ወለሉን ይህን በመሰለ ፍቅር ብታፀዱት ለዐይን የማይታይ ስዕል የሰራችሁ ያህል ነው። ያቺን ቅፅበት የኖራችኋት ይህ ነው በማይባል ሐሴት ተሞልታችሁ ከመሆኑም የተነሳ በተወሰነ ደረጃ ውስጣዊ ዕድገትን ያመጣላችኋል። ከአንድ የፈጠራ ተግባር በኋላ ማንነታችሁ ይለወጣል። ከቀድሞው ከፍ ያለ ማንነት ይኖራችኋል።

ፈጠራ ማለት በምትሰሩት የትኛውም ሥራ መደሰት፣ ሐሴትን ማድረግ ማለት ነው። የሰራችሁትን ማንም ላያውቅ ይችላል። ደግሞስ የቤታችሁን ወለል ስላጸዳችኑ ማን ሊያመሰግናችሁ ነው። ታሪክ በመዝገቡ አይፅፋችሁ፣ ስምና ፎቶግራፋችሁ ጋዜጣ ላይ አይወጣም። ይህ ግን ከሥራችሁ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ተደስታችሁበታል። የዋጋው ውድነት ለእናንተ ብቻ ነው።

ስለዚህ ዝናን ለማግኘት ብላችሁ፣ ፈጣሪ ነኝ የሚል ሐሳብ ከመጣባቹ ግን አለቀላችሁ። ያን ጊዜ ከነአካቴው ፈጠራ «ሲያልፍም የማይነካችሁ» ፖለቲከኞች ትሆናላችሁ። ዝና በራሱ ጊዜ ከመጣ ጥሩ። ባይመጣም መልካም ነው። ግን እንደ ዓላማ መያዝ አይኖርበትም። ዓላማችሁ በሥራው መደሰታችሁና ከስራው ጋር ድብቅ ፍቅር ውስጥ መገኘታችሁ ነው።

ሥራችሁ እንደ ስርቆሽ ፍቅር ጣፋጭ ካደረጋችሁት የፈጠራ ሥራ ይሆናል፡ ፡ ፍቅርና ደስታ የዳሰሳቸው ሥራዎች ታላቅ ይሆናሉ።

ይሁን እንጂ የፈጠራ ክህሎትን አልታደልኩም ብላችሁ ካመናችሁ ክህሎቱ የእናንተ አይሆንም። ምክንያቱም እምነት ቃል ብቻ ሳይሆን የማድረግና ያለማድረግ፣ የመከፈትና የመዝጋት ታላቅ ኃይል ያለው ነገር ነው። የተሳሳተ እምነት ካላችሁ፣ ይህ እምነት እንደተዘጋ በር ሆኖ ሲከተላችሁ ይኖራል። የፈጠራ ክህሎት የለኝም ብላችሁ ካመናችሁም እምነታችሁ የፈጠራ ኃይላችሁን ፍሰሰት በመቃረንና በመቀናቀን ክህሎቱ እንዳይኖራችሁ ያደርጋል። ዘወትር «እኔ የፈጠራ ክህሎት የለኝም» በማለት ሳይታወቃችሁ ለራሳችሁ ስለምትነግሩት የኃይል ፍሰሰቱን ይገታዋል።

ይህን ሁሉ ያልተማረ የለም። ዳሩ ግን በፈጣሪነታቸው ተቀባይነት ያገኙ ጥቂቶች ብቻ ናቸው። ከሚሊዮን አንድ ሰዓሊ ወይ ገጣሚ፣ በቃ። ይህ የማይመስል ነገር ነው! እያንዳንዱ የሰው ልጅ የተወለደው ፈጣሪ ሆኖ ነው። ልጆችን ተመልከቱና ይህንን ትረዳላችሁ። ልጆች ሁሉ ፈጠራን የታደሉ ናቸው። ቀስ በቀስ ግን የፈጠራ ስጦታቸውን እናጠፋባቸዋለን። ቀስ በቀስ የተሳሳቱ እምነቶችን እንጭንባቸዋለን። እናዘጋጃቸዋለን። በመጨረሻም፣ ከኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊው የሩጫ መስመር ላይ እናሰልፋቸዋለን።

ለሥልጣንና ለሀብት መቋመጥ ሲጀመር ፈጠራ ትጠፋለች፣ ምክንያቱም ለሥልጣንና ለሀብት የሚቋምጥ ሰው እንድን ክንዋኔ ወይም ተግባር ለማከናወን ብቻ ብሎ ሊወደው አይችልም። ስዕል ሲስል፣ «መቼ ነው በሥራዬ ዓለም አድንቆ የሚሸልመኝ?» ብሎ ስለመጪው ጊዜ ቀድሞ ያስባል። መፅሐፍ እየደረሰ ከሆነም መፅሐፉ ሲታተም ስለሚመጣለት ዝና ወይንም የተትረፈረፈ ሀብት ያስባል። ስለዚህ ይህ ሰው ሥራውን የሚያከናውነው በመጪው ጊዜ ላይ ሆኖ ነው። በፈጠራ የተካነ ሰው ግን ዘወትርም በዚህች ቅፅበት ላይ ይኖራል።

ፈጠራን የምናጠፋት እኛ ራሳችን ነን። ያለ ፈጠራ ክህሎት የተወለደ ማንም የለም፣ ግን ከማህበረሰባችን ዘጠና ዘጠኝ ከመቶውን የፈጠራ ክህሎት እናሳጣዋለን። ይህንን ኃላፊነት በማህበረሰብ ላይ መጣል ብቻውን ምንም ፋይዳ አይኖረውም። እያንዳንዳችን ሕይወታችንን ራሳችን መምራት ይኖርብናል። ከቤተሰብና ከአስተዳደግ የወረስናቸውን የተሳሳቱ ወጎችና ልማዶች መተው ይኖርብናል። በልጅነታችሁ በተለያየ መልክ የተቀረፀባችሁን የተሳሳቱ እምነቶች ማስወገድ ይገባችኋል! ራሳችሁን ከእነዚህ ሁሉ አጉልና የተሳሳቱ እምነቶች ስታፀዱ ድንገት የፈጠራ ብቃታችሁ በግልፅ ታገኙታላችሁ።

መሆን (to be) እና ፈጣሪ መሆን (to be creative) ተመሳሳይ ናቸው። ከሆናችሁ የግድ የፈጠራ ክህሎትም ይኖራችኋል። ይሁን እንጂ፣ ሳትሆኑ ቀርታችሁ

የፈጠራ ክህሎታችሁ ሁሉ ተሰልቧል፣ ተገድቧል፣ ከነአነቱው ወድሟል። ኃይላችሁም ተጠቃልሎ ማህበረሰቡ ያተርፋል፣ ያከብራል ብሎ በፈረጀው ተግባር ላይ ተንጣጥፏል። እናም አስከፊውና አስቀያሚ ያለመሆን ክስተት ተፈጥሯል።

ለሕይወት ያለን አመለካከት ሙሉ በሙሉ ገንዘብን የተመረኮዘ ነው። ገንዘብ ደግሞ የአንድን ሰው አትኩሮት ከሚገዙ ከፈጠራ እጅግ ርቀው ከሚገኙ ነገሮች ሁሉ የከፋው ነው። ለሕይወት ያለን አቀራረብ ባጠቃላይ ኃይልን መሠረት ያደረገ ነው። ኃይል ደግሞ ብቻውን አውዳሚ እንጂ ፈጠራን አዘል አይደለም። ገንዘብን የሚያሳድድ ሰው አጥፊ መሆኑ አይቀርም፣ ምክንያቱም ገንዘብ መመዝበርና መዝረፍ ይኖርበታል። ከብዙ ሰዎች ላይ ካልተነጠቀ በስተቀር የራስ ሊሆን አይችልም። በቀላሉ ኃይል ማለት ብዙ ሰዎችን ማሽመድመድና ኃይላቸውን ማሳጣት ማለት ነው። ኃይል የሚገኘው ሌሎችን በማሳጣትና በማጥፋት ብቻ ነው። እነዚህ ድርጊቶች ግን እሉታዊና አውዳሚ መሆናቸውን አስታውሱ።

የፈጠራ ተግባር የዓለምን ውበት የበለጠ ያሳምራል። በዓለም አንድ አዲስ ነገርን ያበረክታል እንጂ፣ ያላትን አይወስድም። በፈጠራ የበቃ ሰውም የዚህችን ዓለም ውበት ያሳምራል፣ እዚህ ጋር ይቀኝላታል፣ እዚያ ጋር ይስልላታል። ዓለም በተሻለና በበለጠ እንድትደሰት፣ በበለጠ ፍቅር እንድትሞላ፣ በበለጠ ምስጠት ከኃያሉ ፈጣሪዋ ጋር እንድትተሳሰር ያደርጋል። ከዚህች ዓለም የሚለየው ከኗላው የተሻለች ዓለምን ትቶ ማለፍ ነው። የሚያውቀው ሰው ሊኖር ይችላል፣ ወይም ማንም እያውቀው ይሆናል፣ ዋናው ነገር ይህ አይደለም። የእሱ ሕይወት ልዩ ዋጋ ያለው ከመሆኑ የተነሳ ለዓለም ዋጋ ያለው አንድ ነገር ትቶ ያልፋል።

ገንዘብ፣ ኃይልና፣ ዝና ፈጠራ-አልባ ናቸው። ፈጠራ ያልፈጠረባቸው መሆናቸው ብቻም አይደለም፣ አውዳሚ ተግባራት ናቸው። ተጠንቀቋቸው! ከእነዚህ ከተጠነቀቃችሁ፣ በቀላሉ የፈጠራ ብቃት ልታዳብሩ ትችላላችሁ። የፈጠራ ክህሎታችሁ ኃይል፣ ገንዘብና ዝና ላያመጣም እያልኩ አይደለም። ችግር ሊያመጣባችሁ ይችላል። የድሃ ሰው ሕይወትን እንድትኖሩ ሊያስገድዳችሁ ይችላል። ቃል ልገባላችሁ የምችለው ነገር ቢኖር ጥልቁ ውስጣችሁ የናጠጠ ባለፀጋ እንደሚሆን ነው። ውስጣችሁ ምሉዕ፣ በደስታ የሚፈነድቅ ይሆናል። ያለማቋረጥ በተለያዩ በረከቶች ትታደላላችሁ፣ ሕይወታችሁ የተቀደሰ ሕይወት ይሆናል።

ከውጭ ሲመለከቷችሁ ዝና እና ገንዘብ የሌላችሁ ልትመስሉ ትችላላችሁ። በዚህ ዓለም ላይም ላይሳካላችሁ ይችላል። ዱሩ ግን ሌሎች ዓለም ብለው በሚጠሯት በዚህች ዓለም ላይ ስኬታማ መሆን ከመውደቅ ይቆጠራል። ታድያስ፣ ዓለም ሁሉ ከእግራችሁ ሥር ቢሰግድላችሁ የራሳችሁን ማንነት ካጣችሁ ምን ታተርፉላችሁ? የፈጠራ ብቃት ያለው ሰው ግን ማንነቱ የራሱ ነው፣ ስለዚህ እሱ እለቃ ነው። የኔ ቢጤ ነዳያኖች አለቆች ሆነው ያውቃሉ። የምናውቃቸው ነገስታት በእንዛዛቸው እና በግዛታቸው ፍፃሜ ላይ ነዳያን ሆነው አግኝተናቸዋል። ገንዘብን፣ ኃይልንና ዝናን

የሚያሳድድ ሰውም ለማኝ ነው፣ ዘወትር እንደለመነ በመሆኑ ለዚህች ዓለም የሚያበረክተው ምንም ነገር የለም። በሩቅ ምስራቃውያን ዘንድ ጥበብን የሚፈልጉ ሰዎችን፣ «ስዋሚዎች» (swamis) በማለት የሚጠሩዋቸው ለዚህ ነው። «ስዋሚ» ማለት አለቃ ማለት ነው። ሰዎችን በፍቅር ዐይን ተመልከቱ። በፍቅር ዐይን መመልከት ብቻ የአንድን ሰው ዓለም ሙሉ በሙሉ ሊለውጠው ይችላል።

ውጪ ሁኑ። ያላችሁን ማንኛውም ነገርን ለማካፈል ሞክሩ። ነገሮች ትልቅና ትንሽ ብዬ እየለያየሁ ያለመሆኔን አስታውሱ። ከልብ የመነጨ ፈገግታ ማሳየት የምትችሉ ከሆነ፣ የአንድን ሰው እጁን ይዛችሁ ይህን ፈገግታ ብትለግሱት፣ ድርጊታችሁ ታላቅ የፈጠራ ተግባር ነው። አንድ ሰው ወደ ልባችሁ በማስጠጋት ብታቅፉት፣ ታላቅ የፈጠራ ተግባር አደረጋችሁ ማለት ነው።

ፈጠራ ይኑራችሁ። እያደረጋችሁ ስላላችሁት ነገር አትጨነቁ። ብዙ ነገሮችን ማድረግ ይጠበቅብናል። ግን እያንዳንዱን ነገር በፈጠራ መንፈስ በታጀበ ፍቅር አድርጉት። ያን ጊዜ ስራችሁ አምልኮ ይሆናል። ያን ጊዜ የምታደርጉት ሁሉ ከፀሎት እና ከቅዱስ መስዋዕት ይቆጠራል።

የፈጠራ ብቃት የለኝም የሚል እምነታችሁን አስወግዱ። እነዚህ እምነቶች እንዴት እንደሚፈጠሩ አውቃለሁ። ከዩኒቨርስቲ በወርቅ ሜዳልያ አልተመረቃችሁም ይሆናል። የስዕል ሥራዎቻችሁ አድናቆትን አላስገኙላችሁ ይሆናል። ዋሽንት ስትጫወቱ ጎረቤት የምትረብሹ ልትሆኑም ትችላላችሁ! በእነዚህን መሰል ምክንያቶች የተነሳ ግን የፈጠራ ብቃት የለኝም የሚል እምነት አይኑራችሁ።

ሌሎችን ለመምሰል በመሞከራችሁ የተፈጠረ እምነት ሊሆን ይችላል። ሰዎች ለፈጠራ ችሎታ ያላቸው ግንዛቤ እጅግ ውሱን ነው። ፈጠራ ማለት ጊታር ወይም ዋሽንት መጫወቻ እስከዚያም ግጥም መፃፍ ይመስላቸዋል። በዚህ የተነሳ ሰዎች በግጥም ስም ግሳንግስ መጻፋቸውን ቀጥለዋል። ማድረግ የምትችሉትንና የማትችሉትን መለየትና ማወቅ ይኖርባችኋል። ሁሉም ሰው ሁሉን ነገር ማድረግ አይችልም! መድረሻችሁን ፈልጋችሁ ማግኘት ይኖርባችኋል። መክሊታችሁን ፈልጎ ማግኘት በጭለማ እንደመዳሰስ መሆኑን አውቃለሁ። የመክሊታችሁ ምንነት ግልጽና ቁርጥ ያለ አይደለም። ግን ሕይወትህ እንደዚያ ናት። ቢሆንም መክሊትን መፈለግ ይበጃል። ምክንያቱም በፍለጋው ውስጥ በቅሉ የሚለመልም ነገር ይኖራል።

ስትወለዱና ሕይወትን ሀ ብላችሁ ስትጀምሩ የሕይወታችሁ ፕሮግራም ዝርዝር ቢሰጣችሁ ኖሮስ? «ሕይወታችሁ ይህ ነው!» ወይ «አንተ ስታድግ ዋሽንት ነፊ ትሆናለህ።» ተብሎ ቢወሰንልህስ? ይህ ቢሆን ኖሮ ሕይወታችን አሰልቺ በሆነ ነበር። ልክ እንደማሽን። የማሽን እንጂ የሰው ዕጣ ፈንታ ሊታወቅ አይችልም። የሰው ልጅ ከዚህ ቅጽበት በኋላ የሚሆነው አይታወቅም። የሰው ልጅ ዘወትርም የእልፍ አእላፍ ብቃቶችንና የሕይወት አማራጮች ባለቤት ነው። በየእርምጃውና በየአዲሱ

ሰለት አዳዲስ በሮች ይከፈታሉ። ሥርክ ሕይወታችሁን በመምረጥ በውሳኔ የተሞላ ነው። በስሜት የሚፈተን ነው። ሕይወታችሁን የምትወዱ ከሆናችሁ ግን መከሊታችሁን ማግኘትም ትችላላችሁ።

የምትወዱት ሕይወታችሁን ሳይሆን ሌላ ነገርን ከሆነ ግን ችግር ይኖራል። ገንዘብ ወድዳችሁም የፈጠራ ብቃት እንዲኖራችሁ መፈለግ አትችሉም። የገንዘብ ጥማችሁ ብቻውን፣ ስሜቱ በራሱ የፈጠራ ስጦታችሁን ይሰልበዋል። ዝናን የምትፈልጉ ከሆናችሁም ፈጠራን እርሱት። ዝና ከፈጠራ ችሎታ ይልቅ ከማውደምና ከማጥፋት በቀላሉ ይገኛል። ዝና ለአዶልፍ ሂትለር ወይም ለሔንሪ ፎርድ የበለጠ ትቀርባለች። በፉክክር ላይ ካለች ዝናን በቀላሉ ታገኟታላችሁ። ሰዎችን መግደልና ማጥፋት ከቻላችሁ ዝናን ታገኛላችሁ።

ታሪክ በአጠቃላይ በነፍሰ-ገዳዮች ታሪክ የተሞላች ናት። እናንተም ነፍሰ ገዳይ መሆን ከፈለጋችሁ ዝናን ማግኘት አይከብዳችሁም። የጠቅላይ ሚኒስቴር ወይም የፕሬዚዳንት ሥልጣን ልታገኙ ትችሉ ይሆናል፣ እነዚህ ሁሉ ግን መሸሸጊያ መጋረጃ ናቸው። ከእነዚህ መጋረጃ ጭምብሉት በስተጀርባ ግን በፈገግታቸው የተደበቁ እጅግ ጫካኝና ነፍሰ-በላ ግለሰቦችን ታገኛላችሁ። ጭምብሉቹ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ባህሪ አላቸው። ጭምብሉች ቢወልቁ የምታገኙት ታላቁን አሌክሳንደርን፣ ሒትለርን፣ ወይም ናፖሊዮን ይሆናል።

የምትፈልጉት ታዋቂነትን ከሆነ ስለ ፈጠራ አትናገሩ። ታዋቂነት በፈጠራ ወደተካኑ ግለሰቦች ዘንድ ጨርሶ አትመጣም እያልኩ አይደለም። አንድ ጊዜ ትመጣለች። አመጣጧ፣ አጋጣሚ የሚያስብል ዐይነት ከመሆኑም በላይ የምትመጣ ከረጅም ጊዜ በኋላ ነው። ሁልጊዜ ማለት ይቻላል፣ ዝና እንድን የፈጠራ ሰው ልትጎበኘው ስትመጣ በሕይወት አታገኘውም። እሱ ተልእኮውን አጠናቅቆ ከዚህች ዓለም ከተሰናበተ በኋላ ዘግይታ ትደርሳለች።

ኢየሱስ በዘመኑ ዝነኛ አልነበረም። እንደውም መፅሐፍ ቅዱስ ባይኖር ኖሮ ማንነቱን በውል ማወቅ ባልተቻለ ነበር። ከአራቱ ደቀ-መዛሙርቱ ሌላ ስለ እሱ የፃፈ ማንም የለም። ዝና አልነበረም። በዓለማዊ ሕይወቱ ስኬታማ አልነበረም። ዳሩ ግን ቀስ በቀስ ጊዜ እየቆጠረ ሲመጣ ዝናው ከዓለም ዳር እስከ ዳር አስተጋባ። አዎ፣ ዝና ጊዜ ይወስዳል።

የሰው የታላቅነት ክብደት መጠን በጨመረ ቁጥር፣ ሌሎች ሰዎች ለዚህ ታላቅ ሰው እውቅና እስኪሰጡት የሚወስደው ጊዜም ይዘገያል። ምክንያቱም አንድ ታላቅ ሰው በሚወለድበት ጊዜ ማንነቱን የምናውቅበት እና የመጪ-ዘመን ሥራዎቹን የምንዳኝበት የሕይወቱ ፕሮግራም አብሮት አይወለድም። እነዚያ እሴቶች መፍጠር ያለበት እሱ ራሱ ነው። ፈጥሯቸው ከጨረሰ በኋላ ደግሞ ውጤታቸው መታወቅ ሲጀምር እሱ አይኖርም። አንድ የፈጠራ ሰው እስኪታወቅ መቶ ዓመታት ሊቆጠሩ

ይችላሉ። ከዚያን ጊዜ በኋላ መታወቁ አጠራጣሪ ነው። ከናካቴው ሳይታወቁ ያለፉ ብዙ የፈጠራ ታላላቅ ሰዎች አሉ። ስለዚህ አንድ የፈጠራ ሰው ዓለማዊ ስኬትን የሚያገኘው በአጋጣሚ ነው። ፈጠራን ለማያውቃት የውድመት ሰው ግን ዝናን ከዚህ ይልቅ በእርግጠኝነት ያገኛታል።

ስለዚህ፣ የፈጠራ ስም የምትፈልጉት ሌላ ነገር ከሆነ፣ የፈጠራ ሐሳብን ለቀቅ አድርጉት። ቢያንስ የምታደርጉትን እያወቃችሁ እና ነቅታችሁ፣ ማድረግ የምትፈልጉትን ማንኛውንም ነገር አድርጉ። እንጂ ከማስመሰያ ጭምብል በስተጀርባ አትደበቁ። በእውነት ከልባችሁ የፈጠራ ሰው መሆን ከሻታችሁ፣ የገንዘብ የስኬት፣ የሀብትና የመከበር ጥያቄ አያሳስባችሁም። ያን ጊዜ የምታደርጉትን ሁሉ ትወዱታላችሁ፣ እያንዳንዷ ተግባራችሁም ውድ ዋጋ ይኖራታል። የሚያደንቃችሁ ሰው ቢኖር መልካም፣ ከሌለ የሚያሳስባችሁ ምን ነገር ሊኖር አይገባም። በውስጣችሁ ተደስታችሁ ምልዓትን አግኝታችኋል።

ማንኛውም ዐይነት ፈጠራ-ቢስነት እምነት አደገኛ ሊሆን ስለሚችል አስወግዱት። ፈጠራ-ቢስ የሆነ ማንም የለም። ዛፎችና ድንጋዮች እንኳ ለፈጠራ የታደሉ ናቸው። ዛፎችን የሚያውቁና ለዛፎች ፍቅር ያላቸው ሰዎች፣ የትኛውም ዛፍ የራሱን ግዛት እንደሚፈጥር ያውቃሉ። ማንኛውም ድንጊያ የራሱን ግዛት ወይም ቦታ ይፈጥራል፣ ቦታው የእሱ እንጂ የሌላ ድንጊያ እንዳልሆነ ይታወቃል። ልቦናችሁን ከፍታችሁ በቅንነት ለመረዳት ብትችሉ፣ እጅግ ትጠቀማላችሁ። ማንኛውም ዛፍ የራሱ በሆነ መንገድ የፈጠራ ስጦታን መታደሉን ትገነዘባላችሁ። እያንዳንዱ ዛፍ መሳይ የለውም፣ የራሱ ግላዊ ተፈጥሮ አለው። እያንዳንዱ ቋጥኝም እንደዚያው። ዛፎች እንዲያው ዛፍ ብቻ አይደሉም፣ ሰዎች ናቸው። ቋጥኞችም እንዲያው ቋጥኞች ብቻ አይደሉም፣ ሰዎች ናቸው። አንድ ድንጋይ አጠገብ ሄዳችሁ ተቀመጡና በፍቅር ዐይን ተመልከቱት በፍቅር ዳብሱት፣ በፍቅር ስሜቱን አዳምጡት።

ግዙፍ ቋጥኞችን ማንከባለልና መፈንቀል እንደሚችል ይነገርለት የነበረ አንደ የዜን አስተማሪ ነበር። ይህ ሰው ግን በጣም ቀጭን ከመሆኑ የተነሳ እንኳን ቋጥኝ ድንጋይ ሰውም ማንሳት የሚችል አይመስልም። አካሉን በመመልከት ብቻ ለማመን አስቸጋሪ ነበር። ከእሱ እጅግ የጠነከሩ ሰዎች ማነቃነቅ ያልቻሉትን ቋጥኝ፣ በቀላሉ ፈንቅሉ ያነሳዋል።

ታዲያ ነገሩ ግራ ሲገባቸው ምስጢሩ ምን እንደሆነ ይጠይቁታል። እሱም ሲመልስ፣ «ምስጢር የለውም፣ ቋጥኟን ስለምወዳት ትተባበረኛለች። መጀመሪያ እንዲህ እላታለሁ፣ «እንግዲህ ዝናዬ እጅሽ ላይ ነው፣ እነዚህ ሰዎችም ይህንን ሊመለከቱ መጥተዋል። እስኪ ከራሱ ጋር ለመተባበር እርጂኝ። እሺ? እላታለሁ። ከዚያ በኋላ ድንጊያዋን በፍቅር ስሜት በእጆቼ እይዝና ፍንጭ እስክትሰጠኝ እጠብቃታለሁ። ቋጥኟ የምትሰጠን ፍንጭ እንደ እርግብግቢት ነው። ታዲያ ስርስሬ በሙሉ መርገፍገፍ ይጀምራል፣ ያን ጊዜ እንቀሳቀሳለሁ። እናንተ የምትንቀሳቀሱት

ከቋጥኟ በተቃራኒ እንጂ ከቋጥኟ ጋር አይደለም፣ ለዚያ ነው ያን ያህል ከፍተኛ ኃይል የሚወስድባችሁ። እኔ የምንቀሳቀሰው ከቋጥኟ ጋር ነው፣ የምፈስሰው ከቋጥኟ ጋር ነው። እንደውም ቋጥኟ ባለችበት ከመገኘቴ በስተቀር እንክባለልኳት ማለት በራሱ ስህተት ነው። ቋጥኟ ናት እራሷን ያንቀሳቀሰችው።»

አንድ አናጢ የዜን መምህር ነበር፣ ታዲያ በሙያው የሚሰራቸው ጠረጴዛዎችና ወንበሮች ሁሉ ከፍተኛ መስህብና ጥራት ነበራቸው። «እንዴት ብትሰራቸው ነው እንዲህ የሚያማምሩትን» ተብሎ ተጠየቀ።

ሲመልስም፣ «ኧረ እኔ አልሰራቸውም። እንዳውም ዝም ብዬ ወደ ጫካ እሄዳለሁ . . . መሠረታዊው ነገር ያለው፣ ወንበር ወይም ጠረጴዛ ለመሆን ዝግጁነቱ ያለው ዛፍ ይኖር እንዲሆን፣ ጫካውን እንዲሁም ዛፎቹን መጠየቁ ላይ ነው።»

እነዚህ ነገሮች ግራ አጋቢ መስለው የሚታዩን ካለማወቃችን የተነሳ ነው፣ ቋንቋውን አናውቀውም። ሦስት ቀናት ሙሉ ጫካ ውስጥ ገብቶ ይቆያል። እንደ አንዱ ዛፍ ሥር ከዚያ ሌላው ዛፍ ሥር እየተቀመጠ፣ እንደ እብድ ብቻውን ያወራል፡ ፡ እብድማ ነው! እንዳትሉ ደግሞ፣ አንድ ዛፍ የሚመዘነው በፍሬው እንደሆነ ሁሉ፣ ይህ መምህርም ሊመዘን የሚገባው በፈጠራ ሥራው ነው። እሱ ከሚሰራቸው ወንበሮች መካከል ጥቂቱ አሁንም ቻይና ውስጥ ይገኛሉ። ወንበሮቹን ለተመለከታቸው ሁሉ የመስህባቸው ማራኪነት ለመግለፅ ይቸግረዋል። በቃ ውበታቸው፣ ውስጡን ውስጡን የሚያስገኝ ነው። የሺህ ዓመታት ዕድሜ ቢኖራቸውም፣ አሁንም መስህባቸው ከየት እንደሚመነጭ ማወቅ አስቸጋሪ ነው። ምትሃታዊ ውበትን የተጎናፀፉ ነገሮች ናቸው።

እናም ይሄ አናጢ ሲናገር፣ «ወደ ጫካው እሄድና ወንበር መሆን የሚፈልግ ዛፍ እየፈለግሁ መሆኔን እናገራለሁ። ዛፎቹንም ሊተባበሩኝ ፈቃደኛ ይሆኑ እንደሆነና አብረውኝ ሊሄዱ ዝግጁነት ይኖራቸው እንዲሁ እጠይቃቸዋለሁ። ፈቃደኛ ካልሆኑ አልወስዳቸውም። አንዳንድ ጊዜ ወንበር ለመሆን የተዘጋጀ ዛፍ ስለማላገኝ፣ ባዶ እጄን እመለሳለሁ።» ይላል።

አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ፣ የቻይና ንጉሠ ነገስት ለመፀሐፍቶቻቸው መደርደሪያ እንዲሰራላቸው ይጠይቁታል። ይህ አስገራሚ አናጢም ጫካ ገብቶ ሦስት ቀን ከቆየ በኋላ ይመለስና፣ «ወደቤተ-መንግስቱ ለመምጣት ዝግጁ የሆነ አንድም ዛፍ ስላልተገኘ፣ ጥቂት ይታገሱ።» ይላቸዋል።

ከሦስት ወራት በኋላ ደግመው ሲጠይቁት፣ አሁንም «ወደ ጫካው እየተመላለስኩ ዛፎቹን በማግባባት ላይ ነኝ። በተለይ አንደኛው ዛፍ የመስማማት አዝማሚያ እያሳየ ነው።» ሲል ይመልሳል።

በመጨረሻ አንዲት ዛፍ ፈቃደኛ ትሆንለታለች፡፡ ‹‹ጥበቡ ሁሉ ያለው እዚህ ላይ ነው!›› ይላል፡፡ ‹ዛፊቷ በራሷ ፈቃድ ወደ ቤተ-መንግስቱ በምትመጣበት ጊዜ፣ የአናጢውን እርዳታ እንደምትጠይቅ ይቆጠራል፡፡››

እናንተም በፍቅር ከሆናችሁ ፍጥረተ-ዓለም ባጠቃላይ የራሱ የሆነ ልዩ ማንነት ወይም ባህሪይ እንዳለው ትመለከታላችሁ፡፡ ነገሮችን በኃይል ለመፈፀም አትነሱ፡፡ አስተውል፣ ከማንኛውም ጋር ተወያዩ ከዚያም የሚሰጧችሁን እርዳታ ተቀበሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ከኖራችሁ ብዙ ጉልበት ትቆጥባላችሁ፡፡

ድንጊያዎችና ዛፎች እንኳን የራሳቸው የፈጠራ ክህሎት አላቸው፡፡ አንተ ደግም የፍጥረታት ሁሉ ቁንጮ የሆነው የሰው ልጅ ነህ፡፡ የምታደርገውን የምታውቅ ፍጡር በመሆንህ፣ የፍጥረተ-ዓለም ፊት መሪ ነህ፡፡ የፈጠራ ብቃት እንደሌለህ ከሚነግሩህ እምነቶች ሁሉ ራቅ፡፡ በአእምሮህም የተሳሳቱ እምነቶችን በጭራሽ አታስገባ፡፡ ወላጅ አባትህ ወይም ወዳጅህ የፈጠራ ብቃት እንደሌለህ ተናግረውህ ሊሆን ይችላል፡፡ የፈጠራ ችሎታህን ከምታስመሰክርበት የተለየ መስመርና አቅጣጫ ስትባዝን ቆይተህም ሊሆን ይችላል፡፡ ዳሩ ግን ያለ ምንም ጥርጥር ያንተ የሆነ ትክክለኛ አቅጣጫ መኖሩ ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን የፈጠራ ብቃትህን መስመር እስከታገኘው ድረስ ፍለጋህን አታቋርጥ፣ ዕድሉ መጥቶ እንዳያጣህም ዘወትር በርህን ክፍት አድርገው፡፡

ማንኛውም ሰው ወደዚህች ምድር የሚመጣው የራሱን ልዩ እጣ-ፈንታ ታድሎ ነው፡፡ ሊያከናውነው የሚገባው አንድ ሥራ ሊያሟላው የሚገባ አንድ ነገር ወይም የሚያደርሰው አንድ መልዕክት አለ፡፡ የተፈጠርከው በአጋጣሚ ድንገት ሳይሆን በምክንያት ነው፡፡ ከበስተጀርባህ አንድ ዓላማ አለ፡፡ ምልዓተ-ዓለም ማለትም መላው ፍጥረተ-ዓለም አማካይነት ሊያደርገው ያቀደው አንድ ነገር አለ፡፡

## 4. የዝና ገበጣ

ሕይወታችንን በጠቅላላ የተዋቀረበት አንድ አመለካከት በዓለም ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ታዋቂና ዝነኛ ካልሆንን በስተቀር ተራና ዋጋ ቢስ እንደምንሆን እንድናስብ ተደርገን ተምረናል፡፡ በዚህ የተነሳም ትኩረታችንን የምንሰራው ሥራ ላይ ሳይሆን በስራው የምናገኘው እውቅና ላይ አነጣጥሯል፡፡ ይህ ግን መሆን ከነበረበት የተገላቢጦሽ ነው፡፡ ሥራው መቅደም ይኖርበታል፡፡ ሥራችን የደስታችን ምንጭ ሊሆን ይገባል፡፡ የምንሰራው ስራው ወይንም በስራችን ውስጥ የሚፈነጥቀው የፈጠራ ብቃታችን ብርሃን ስለሚያስደስተን እንጂ፣ ዝነኛ ለመሆን ብለን መሆን የለበትም፡፡ ሥራው ለሰራው ለራሱ፣ በስራነቱ እንውደደው፡፡

የምንሰራው ሥራውን ስለምንወደው እንጂ በሥራዬ ፈንታ እውቅናን አልጠይቅም፣ የሚል አቋም መያዝ አለብን፡፡ ዝነኝነትን ካገኛችሁ ቀለል አድርጋችሁ

ተቀብሏት፣ ባታገኛትም አትጨነቅላት፣ ከናካቴውም አታስባት። ደስታን ከሥራችሁ አግኙት። ይህንን ሥራን የማፍቀር ጥበብ እያንዳንዱ ሰው ተረድቶ ዝናን ባይፈልግ በሥራው ቢደሰት፣ ዓለማችንን ይበልጥ አስደሳችና ማራኪ በሆነች።

የማፊይቱ ዓለማችን በውስብስብ ችግሮቿና ኃዘኖቿ ተብትባ ይዛን ትገኛለች። ሰዎች ጥሩ ሥራ እየሰሩ መሆናቸውን የሚያስቡት፣ ለሥራው ካላቸው ፍቅር የተነሳ ሳይሆን ወይንም በጥራት ስለሚያከናውኑት ሳይሆን፣ እውቅና ሲያመጣላቸው፣ ሲያሸልማቸው፣ ትርፍ ሲያስገኝላቸውና የኖብል ሽልማት ሲያሸልማቸው ነው።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በዚህ አመለካከት የተነሳ ሕይወታቸው ተበላሽቷል። ምክንያቱም የኖብል ሽልማት ለሚሊዮኖች ማዳረስ አይቻልም። ይህ አመለካከት የፈጠራ ክህሎትን ውድ ዋጋ እራከሶታል። ዘመኑ ግን፣ በሁላችንም ውስጥ የመታወቅን ፍላጎት በመፍጠሩ፣ ሰዎች እያደረጉ ያሉትን ማንኛውም ነገር እየተደሰቱበት በሰላምና በፀጥታ ማከናወን እንዳይችሉ ሆነዋል። ሕይወት ደግሞ የትንንሽ ነገሮች ጥርቅም ናት። እነዚህ ጥቃቅን ነገሮች ሽልማት የላቸውም። የመንግስታት ሹመት ወይም ዩኒቨርስቲዎችን የክብር ዲግሪ አያገኙም።

በዚህ ክፍለ-ዘመን ታላላቅ ገጣሚዎች መካከል አንዱ የነበረው ራቢንድራናት ታጎር፣ በሕንዷ ከተማ በቤንጋል ይኖር ነበር። ግጥሞቹና ልብ-ወለድ መፅሐፎቹን በዚህች ከተማ ውስጥ ቢያሳትማቸውና ለንባብ ቢያበቃቸውም ታዋቂነትን ሳያገኝ ይቀራል። ከዚያም ጊታንጃሊ ወይንም ‹‹የዜማዎች መባዕ (Offering of Songs) የተሰኘች አነስተኛ መፅሐፍ ወደ እንግሊዝኛ ይተረጉማል። የቤንጋሊ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚጠቀሙበት አወቃቀርና አገላለፅ ከመለያየቱ የተነሳ፣ የትርጉም ሥራው የዋናውና ሥራ ያህል ለዛና ውበት እንደማይኖረው ጠንቅቆ ያውቅ ነበር። ቤንጋሊ ቅኝቱ የጣፈጠ ቋንቋ ነው። ባለመግባባት እና በፀብ ጊዜ እንኳን፣ የጠበኞች አነጋገር እጅግ በትህትና የተሞላ ከመሆኑ የተነሳ፣ ቋንቋውን ለማያውቅ ሰው እንኳን የሚጣሉ ቅር ያላቸውም አይመስሉም። ለጆሮ አስደሳችና እያንዳንዱ ቃል የሙዚቃ ያህል የሚማርክ ነው። እነዚህ ባህሪያቱ ታድያ እንግሊዝኛ ውስጥ የሉም። ተመጣጣኝ አገላለፆችም ሊገኙላቸው አይችልም። የሆነው ሆኖ መፅሐፉን ተረጎመው። ከዋናው ሥራ ጋር ሲወዳደር የማይረባ ሊባል የሚችለው የትርጉም ሥራ ግን የኖቤል ሽልማት አስገኘለት። መፅሐፉ በቤንጋሊ እና በሌሎች የሕንድ ቋንቋዎች ታትሞ ለዘመናት ገበያ ላይ የቆየ ቢሆንም፣ ከጉዳይ የጣፈው አልነበሩም። አሁን ግን ድንገት መላው ሕንድ አትኩሮት ሰጠው።

የክብር ዶክትሬት ሊሰጠው ያልፈለገ ዩኒቨርስቲ አልነበረም። ይኖርበት በነበረው የካልካታ ከተማ የነበረ ዩኒቨርስቲ፣ የክብር ዶክትሬት ሊሰጡ ጥያቄ ካቀረቡለት ዩኒቨርስቲዎች የመጀመሪያው እሱ ነበር። እሱ ግን አልተቀበለውም።

# አራት ቁልፎች

*በፈጠራ ውስጥ ሆናችሁ የፈጠራ ሥራ በምታከናውኑበት ወቅት፣ ሕይወትን ታጣጥሟታላችሁ። ይህም የሚወሰነው በስራው ውስጥ በሰመጣችሁበት ጥልቀትና በሁለንተናዊነታችሁ ይሆናል። ሕይወት በፍልስፍና ሳይሆን፣ በመንፈሳዊ ሕቡዓዊነት የሚፈታ እንቆቅልሽ ነው። ያን ጊዜ፣ እዚህ ግባ የማይባል፣ ወለል እንደማፅዳት ዓይነተኛ እለስተኛ ተግባር፣ ፈጠራ ሊሆን ይችላል። ማንኛውንም ተግባር በፈጠራ መንፈስ፣ በፍቅርና በሁለንተናዊነት ልታደርጉት ከቻላችሁ የሕይወትን ጣዕም መቅመስ ትችላላችሁ።*

## 1. ዳግመኛ ሕፃን ሆንኩኝ

ዳግም ሕፃናት ብትሆኑ የፈጠራ ብቃት ይኖራችኋል። ሕፃናት ሁሉ የፈጠራ ክህሎትን ታድለዋል። የፈጠራ ክህሎት ነጻነት ይሻላል። ከእእምሮ፣ ከዕውቀት እና ከእንቱ-እምነቶች ነፃ መሆንን ይጠይቃል። የፈጠራ ብቃት ያለው የሚባለው አዲስ ነገር መሞከር የሚችል ሰው ነው። የፈጠራ ክህሎት ያለው ሰው ሮቦት አይደለም። ሮቦቶች የተሞሉትን ብቻ ከመደጋገም ሌላ መፍጠር አይችሉም።

ስለዚህም ዳግመኛ ሕፃናት ሁኑ፣ እናም ሕፃናት ሁሉ ፈጣሪ መሆናቸውን እውቃችሁ ትደነቃላችሁ። በየትም ሥፍራ የተወለዱ ሁሉም ሕፃናት የፈጠራ ክህሎትን የታደሉ ቢሆንም እኛ ግን የፈጠራ ብቃታቸውን አንፈቅድላቸውም። ይህንን ክህሎት እንገድልባቸዋለን፣ የራሳችንን አመለካከቶች እናሰፍንባቸዋለን፣ እኛ ነገሮች ይደረጉበታል ብለን የምናስበውን መንገድ እናስተምራቸዋለን።

የፈጠራ ሰው ዘወትርም የተሳሳቱ በተባሉ መንገዶች ሙከራ እንደሚያደርግ አስታውሱ። አንድ ነገርን ለማድረግ የምትከተሉት መንገድ ዘወትርም ትክክለኛውን መንገድ ከሆነ በፍፁም የፈጠራ ብቃት አይኖራችሁም። ምክንያቱም ‹‹ትክክለኛው መንገድ›› ማለት በሌሎች የተደረሰበት መንገድ ማለት ነው። ማለትም ትክክለኛው መንገድ ማለት፣ አንድ ነገር መስራት የሚያስችልህ አምራች የሚያደርግህ ማለት አይደለም።

ታድያ በአምራችና በፈጣሪ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? አምራች ነገሮችን የሚያደርግበት ትክክለኛውን መንገድ ያውቃል። አንድን ነገር በትንሽ ወጪ ማድረግ የሚችልበትን ስልት ያውቃል። በጣም ትንሽ ጥረት ብዙ ውጤቶችን

ማምጣት ይቻላል፡፡ አምራች ነውና ወጪውን ይቀንሳል፡፡ ፈጣሪ ግን እዚያ ይጣዝናል፡ ፡ ነገሮችን የማከናወኛውን ትክክለኛ መንገድ ስለማያውቅ፣ እስኪፈለገው የተለያዩ መንገዶችን መሞከሩን ይቀጥላል፡፡ ብዙ ጊዜ በተሳሳቱ መንገዶች ላይ ራሱን ያገኘዋል፤ እናም ከዚያ ይማራል፡፡ የበለጠ እየበለፀገ ሐብትን እያገኘ ይሄዳል፡፡ ከእሱ በፊት ሌላ ማንም ሰው አድርጎት የማያውቀውን ነገር ያደርጋል፡፡ ትክክለኛ የተባለውን መንገድ ተከትሎ ቢሆን ኖሮ ይህን ማድረግ ባልቻለ ነበር፡፡

እስኪ ይህቺን ታሪክ ጀባ ልበላችሁ፡ -

አንዲት የሰንበት አስተማሪ ተማሪዎቿን የክርስቶስን ቤተሰብ የሚያሳይ ስዕል እንዲስሉ ትጠይቃቸዋለች፡፡ ተማሪዎቹ ስዕሎቻቸውን እንደየሐሳቦቻቸው እየሳሉ ያመጡላታል፡፡ አብዛኞቹ ስዕሎች የክርስቶስ ቤተሰብ ማለትም ሕፃኑ ኢየሱስ ከማርያም ከዮሴፍ ጋር በረት ውስጥ በቅሎ ላይ ተቀምጠው ወዘተ የሚያሳዩ ነበሩ፡፡

ለየት ያለ ስዕል የሳለ አንድ ተማሪ ስላጋጠማት ትጠራውና የሳለውን እንዲያብራራላት ትጠይቀዋለች፡፡ ስዕሉ ከአንድ አይሮፕላን መስኮቶች ብቅ ብቅ ያሉ አራት ጭንቅላቶች የሚያሳይ ነበር፡፡ አስተማሪዋም፣ ‹‹ሦስቱ ራሶች የኢየሱስ፣ የማርያም እና የዮሴፍ መሆናቸውን ተረድቼያለሁ፡፡ ግን አራተኛው ራስ የማነው?›› ብላ ትጠይቀዋለች፡፡

‹‹እንዴ፣›› ሲል ይመልሳል ልጁ፡፡ ‹‹ይህማ የአብራሪው የፓይለቱ ጭንቅላት ነው፡፡››

እንግዲህ ይህ ውብ ነገር ነው! ፈጠራ ማለትም ይኸው ነው፣ የደረሰበት ነገር አለ፡፡ ይህንን ማድረግ የሚችሉት ግን ሕፃናት ብቻ ናቸው፡፡ እናንተ ብትሆኑ ሰው ይስቅብናል ብላችሁ ትፈራላችሁ፡፡

ፈጣሪ ግን እንዲሳቅበትም መፍቀድ አለበት፡፡ ፈጣሪ ሰው ልክበር ብሎ እንደተከፈለ መኖር አይችልም፡፡ ለዚህ ነው፣ ዘወትርም ቢሆን ገጣሚያን፣ ሰዓሊያን አቀንቃኞች እጅግ የተከበረ ስም የማይኖራቸው፡፡ የኖብል ሽልማት አግኝተው

የሚከፍሉበት ወቅት ደግሞ የፈጠራ ክህሎታቸው ይከስማቸዋል። ከዚያን ጊዜ በኋላም ክህሎቱ አይኖራቸውም።

ምን ተፈጠረ? አንድ የሥነ-ጽሁፍ የኖቤል ሽልማት አሸናፊ፣ ከሽልማቱ በኋላ እዚህ ግባ የሚባል ነገር ፅፎ አይታችሁ ታውቃላችሁ? አንድ የተከበረ ሰው የፈጠራ ሥራ የሚባል ነገር ሲሰራ አጋጥሟችሁ ያውቃል? ይፈራል። አንድ ስህተት ቢሰራ ወይም አንድ ነገር ቢስተጓጎል ከክብሩ ይዋረዳል። ይህ እንዲሆን ደግሞ አይፈቅድም። ስለዚህ አንድ የሥነ-ጥበብ ሰው የተከበረ ሲሆን ይሞታል፣ ወይም የፈጠራ ክህሎቱ ይከስማል።

ክብራቸውን፣ ኩራታቸውንና ዝናቸውን በተደጋጋሚ አደጋ ላይ ለመጣል ዝግጁ የሆኑ ብቻ ናቸው፣ ማንም የማያስበው ሥራ ውስጥ ለመግባትና ለመፍጠር የታደሉ። ዘወትርም ቢሆን ፈጣሪዎች እብድ ተደርገው ይታሰባሉ። ዓለም ካለፉ በኋላ አድናቆቱን ይቸራቸዋል። አንድ ችግር እንዳለባቸው ማሰቡን አያቋርጥም። ፈጣሪዎች ጥራዝ-ነጠቅ ናቸው።

እያንዳንዱ ሕፃን የሚወለደው ፈጣሪ የሚያደርገውን ሙሉ ብቃት ይዞ መሆኑን ደግማችሁ አስታውሱ። ማንኛውም ሕፃን ፈጣሪ ለመሆን ይሞክራል፣ እኛ ግን አንፈቅድለትም። ከመቅጽበት ነገሮችን የሚያከናውኑበትን ትክክለኛ መንገድ ልናስተምራችሁ እንነሳለን፣ አንድን ነገር የሚያደርጉበት ትክክለኛ መንገድ ሲያውቁ ደግሞ እንደ ሮቦት ይሆናሉ። ከዚያም ትክክለኛው ነገር በተደጋጋሚ ማድረጋቸውን ይቀጥላሉ። ከድግግሞሽ ብዛትም ብቃታቸው እየጨመረ ይመጣል። ክብራቸውም ከፍ ከፍ እያለ ይሄዳል።

በአንድ ሕፃን በአራትና በሰባት ዓመት ዕድሜው ክልል ውስጥ አንድ ነጥብ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ይከሰታል። የሥነ-አእምሮ ጠበብት እዚህ ነጥብ ላይ ምን እንደሚከሰትና ለምን እንደሚከሰት ለማወቅ ከፍተኛ ጥናት አድርገዋል።

ሁላችንም በአንጎላችን ግራና ቀኝ ንፍቀ-ክበብ ውስጥ የሚገኙ ሁለት አእምሮዎች አሉን። በስተ-ግራው አእምሮ የፈጠራ ብቃት የለውም፣ ብስለት እና ክህሎት እንጂ ብቃቱ ከፍተኛ ቢሆንም ከፈጠራ አንፃር ግን ምንም ዐይነት ብቃት የለውም። አንድን ነገር አንድ ጊዜ ከተማረ በኋላ ያለ ስህተት በብቃት ሊያከናውነው ይችላል። ይህ የስተ-ግራው ንፍቅ፣ የምክንያታዊነት፣ የሎጂክ እና የሒሳብ ስሌት የአእምሯችን ክፍል ነው። የብልጠት፣ የስርዓት፣ የደንብ እና የስሌት ክፍል ነው።

የቀኙ ንፍቀ-ክበብ ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ነው። የውጥንቅጥ እንጂ የሥርዓት ንፍቅ አይደለም። የቅኔና የሥነ-ጥበብ እንጂ የስሌት ንፍቅ አይደለም። የፍቅር እንጂ የምክንያት ክፍል አይደለም። ለውበት ታላቅ ስሜት አለው። ለአንጋፋነት (originality) ታላቅ አመለካከት አለው። ግን ብቃት የለውም፣ በአንድ ነገር ላይ

የተለየ ብቃት ሊኖረው አይችልም:: ፈጣሪ ሰው ብቁ ሊሆን አይችልም፣ ዘወትር የሙከራ ሕይወት መኖር አለበት::

ፈጣሪ አንድ ሥራ ላይ መርጋት አይችልም:: ፈጣሪ ዱር አዳሪ ዘላን ነው:: አንድ ቦታ ላይ አንድ ቀን ማደር ቢችልም ሲነጋ ግን መኖሪያውን ተሸክሞ ይዞራል:: አንድ ቦታ ላይ አንድ ቀን ማደር ቢችልም ሲነጋ ግን ወደ ሌላ ሄዷል:: ለዚያ ነው ፈጣሪውን ዱር አዳሪ ያልኩት:: በአንድ መርጋት ስለማይችል አዲስ ነገር ፍለጋ ራሱን አደጋ ላይ ይጥላል:: አደጋ ውስጥ መግባት ነፍሱ ነው::

ይህ ግን የበስተቀኙ ንፍቅ ሥራ ነው:: ይህ የአእምሮ ክፍል ሕፃን ልጅ ሲወለድ የሚሰራው ክፍል ነው:: የበስተግራው ንፍቅ በዚያን ወቅት ግልጋሎት የለውም:: ከዚያ ግን ሕፃኑን ሳናውቅ በሳይንስ ያልተረጋገጡ ነገሮች እናስተምረዋለን:: ባለፉት ብዙ ዘመናት የበስተቀኙን ንፍቅ እንዴት እንደምናስቆምና እንዴት የበስተግራውን ክፍል እንደምናስጀምር ስንለማመድ ኖረናል:: ትምህርታችን ሁሉ ዓላማው ይህ ነበር:: ከመዕዋለ-ሕፃናት እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ የተማርነው ሁሉ የበስተቀኙን ክፍል በማውደም የበስተግራው ለማጎልበት የተደረገ ጥንት ነው:: በዕድሜያችን በሰባትና በአስራ አራት ዓመት ክልል አንድ ሥራ ላይ ውስጣችን የነበረው ሕፃን ይገድላል:: ሕልውናው ያበቃለታል::

ከዚያን ጊዜ በኋላ ልጅነት ቀርቶ ዜጎች እንሆናለን:: ከዚያ ደግሞ ሥርዓት፣ ቋንቋና ሎጂክን እንማራለን:: በትምህርት ቤት ውስጥ መፎካከር ራሱን ከፍ ለማድረግ መጣርና ማህበራዊ ኩነታት ውስጥ መሳተፍ ይጀምራል:: ይህ ወጣት ለኃይልና ለገንዘብ አትኩሮት ይኖረዋል:: ስለዚህም የበለጠ ኃይልን ለማግኘት እንዴት በትምህርት መጎልበት እንዳለበት ማሰብ ይጀምራል:: ይህን ጊዜ የበስተቀኙ አእምሮ ሥራውን እየተወ በመሄድ በሕልም ወቅት ብቻ እንቅልፍ ሥራ መስራት ይጀምራል:: ወይ ደግሞ አደንዛዥ ዕፅ ስትወስዱ ሥራውን ይጀምራል::

በምዕራቡ ዓለም አደንዛዥ ዕፅ ከፍተኛ መስህብ ይዞ የሚታየው፣ ምዕራባውያኑ በመሰረታዊ ትምህርት አማካይነት የቀኙን ንፍቅ ፈፅሞ ማውደሙ ስለተሳካላቸው ነው:: ምዕራቡ ዓለም ከመጠን በላይ ትምህርት ጠጥቷል፣ ማለትም ወደ ግራው የአእምሮ ክፍል ጠልቆ ገብቷል:: ስለዚህ በአንድ ዘዴ የቀኙን ንፍቅ የሚያንሰራራ ነገር በዩኒቨርስቲዎችና በሌሎች ትምህርት ተቋማት ተግባራዊ ካልተደረ በስተቀረ አደንዛዥ ዕፆችን ማስወገድ አይቻልም:: በሕግ ብቻ አደንዛዥ ዕፆችን መከልከል የማይቻል ነው:: የሰው ልጅ የአእምሮ ሚዛን ሥፍራው እስካልተመለሰ ድረስ ሕጉን ማስፈፀም አስቸጋሪ ሆኖ ይኖራል::

የአደንዛዥ ዕፅ ተግባርና አስደሳችነቱ ያለው ኃይልን ከግራው የአእምሮ ንፍቅ ከመቅፅበት ወደቀኙ የአእምሮ ክፍል በማሸጋገሩ ላይ ነው:: አንድ አደንዛዥ ዕፅ ከዚህ ሌላ የሚሰራው ምንም ነገር የለም:: አልኮልም ተመሳሳይ ሥራ እየሰራ

ለተወሰኑ ምዕተ-ዓመታት ቢቆይም አሁን ግን ከአልኮልና በኃይል የተሻሉ አደንዛዥ ዕፆች እየመጡ ነው፡፡ ኤል.ኤስ.ዲ፣ ማሪዋና እና ሲሎሳይ ቢን ለዚህ ተጠቃሽ ናቸው፡ ፡ መጪው ዘመን ደግሞ ከእነዚህ የተሻለ ኃይል ያላቸውን እፆች ይዞልን መምጣቱ አይቀርም፡፡

በዚህ የተነሳ፣ ወንጀለኛው ዕፅ ተጠቃሚው ሳይሆን ፓለቲከኛው እና ትምህርት ተቋማት ወይም አስተማሪዎች ናቸው፡፡ ጥፋተኞቹ እነሱ ናቸው እንጂ ሌሎች አይደሉም፡፡ የሰው ልጅን ሕሊና ወደ አንድ ጥግ ከፍተው የወሰዱት እነሱ ናቸው፡፡ ይህ የዝንባሌ መጠን እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ አመፅ አስፈላጊ ነው፡፡ የዚህ እምቢ ባይነትና አመፅ አስፈላጊነቱ እጅግ ከፍተኛ ነው! ቅኔ ከሰዎች ሕይወት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል፣ ውበትም የለም፣ ፍቅርም ተፈልጎ አይገኝም - ገንዘብ፣ ኃይል እና ተፅእኖ ክርን ብቸኞቹ አማልዕክት ሆነው የሚገኙበት ዓለም ላይ ነን፡፡

ታድያ ለብዓዊነት ያለ ፍቅር እና ያለ ሕብራዊ ቅኝት እንዲሁም ያለ ሐሴት እንዴት በሕልውና መቀጠል ይችላል? ለረዥም ጊዜ አይቀጥልም፡፡ ይህ በዓለም ዙሪያ የሚገኘው አዲሱ ትውልድም ትምህርት ብላችሁ የምትጠሩትን ቀስሞ በመተግበር ታላቁን ጥፋት እያፋጠነላችሁ ነው፡፡ አደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚዎች ዘወትር ከዩኒቨርስቲ አቋርጠው የሚወጡት በአጋጣሚ አይደለም፡፡ አጋጣሚ አይደለምም የአንድ ተመሳሳይ አመፅ አካል እንጂ፡፡

አንድ ሰው የአደንዛዥ ዕፆችን ደስታ ከቀመሰ በኋላ ሊተዋቸው ይከብደዋል፡፡ አደንዛዥ እፆችን መተው የሚቻለው፣ በውስጣችን የታመቀውን ቅኔ ወይም ሥነ-ጥበብ ማውጣት የምንችልባቸው መንገዶች ስናገኝ ብቻ ነው፡፡ ከዕፅ ይልቅ፣ አርምሞ (ምስጠት)፣ ከጉዳት አንፃር የተሻለ ነው፡፡ ጉዳቱ ከየትኛውም ንጥረ-ነገር ያነሰ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ምንም ዐይነት ጉዳት የለውም፣ ጥቅም እንጂ፡፡ ምስጠት ከአደንዛዥ ዕፅ የተለየ ውጤት የለውም፡፡ አእምሯችን ከግራው ወደ ቀኝ ያሸጋግረዋል፡፡ ውስጣዊ የፈጠራ ብቃትን ያወጣል፡፡

በአደንዛዥ ዕፅ ሳቢያ በዓለም ላይ ሊመጣ ያንዣበበው ትልቅ ጥፋት ሊወገድ የሚችለው በምስጠት (meditation) ብቻ ነው፡፡ ሌላ ምንም መንገድ የለም፡፡ ምስጠት እየተስፋፋ ሄዶ በበለጠ ወደ ሰዎች ሕይወት ሲገባ አደንዛዥ ዕፆች ይጠፋሉ፡፡

ትምህርትም ይህን ያህል ቀኙን አእምሮ እና ተግባሩን መቃረኑን መተው ሊጀምር ይገባዋል፡፡ ልጆች አእምሯቸው ሁለት ክፍሎች እንዳሉትና የትኛውን የትና መቼ እንደሚጠቀሙበት የሚያሳውቃቸው ትምህርት ያስፈልጋቸዋል፡፡ የግራው አእምሮ የሚያስፈልግባቸው ቦታዎች አሉ፣ ማስላት ሲያስፈልግ፣ በገበያና በሥራ (የንግድ) ላይ፣ ቀኙን ደግሞ በሌሎች ጊዜያት መጠቀም ያሻል፡፡

ቀኑ ንፍቀ ክበብ ፍፃሜው፣ ግራው ደግሞ ፍፃሜው የሚወሰደው መንገድ መሆኑን እናስታውስ። ግራው ንፍቅ ቀኙን ንፍቅ ማገልገል አለበት። ቀኑ ንፍቅ አሰታ ነው፣ ምክንያቱም ገንዘብ የምናገኘው በሕይወታችን ለመደሰትና ሐሴትን ለማድረግ ስለሆነ። ባንክ ውስጥ ተቀማጭ ገንዘብ የሚያስፈልጋችሁ ማፍቀርን እንድትችሉ ብቻ ነው። ሥራ የምትሰሩት መጫወት እንድትችሉ ብቻ ነው። ስለዚህ ዋናው ዓላማ አሁንም መጫወት ይሆናል። የምትሰሩ መዝናናት እንድትችሉ ብቻ ነው። ዓላማችሁ ሥራው ሲያልቅ መዝናናት እንጂ ሥራው አይደለም።

የሥራ ሥነ-ምግባር ካለፈው ጊዜ የዞረ ድምር በመሆኑ መቅረት አለበት። የትምህርት ተቋማት ሁሉም በከፍተኛ አብዮት ውስጥ ማለፍ አለባቸው። ሰዎች በተለይ ልጆች በተደጋጋሚ ሂደት ውስጥ ለማለፍ መገደድ የለባቸውም። እናንተስ? የተማራችሁት ምንድን ነው? አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? አስባችሁት ታውቃላችሁ? በቃ፣ የትውስታ ሥልጠና ነው። በትምህርታችሁ አስተዋይ አልሆናችሁም። እንደውም በተቃራኒው የማትረቡ ሆናችኋል። እያንዳንዱ ሕፃን ትምህርት ቤት ሲገባ አስተዋይነት ነበረው። ከዩኒቨርስቲ አስተዋይ ሆኖ የሚመረቅ ግን ከስንት አንድ ወጣት ነው። ሠርክ ዩኒቨርስቲ ይሳካለታል። አዎ፣ ዲግሪ ጭናችኋል፣ ግን እነዚህን ዲግሪዎች የሸመታችሁት በትልቅ ዋጋ ነው። አስተዋይነታችሁ፣ ደስታችሁን፣ ሕይወትን መስዋዕት አድርጋችሁ ነው። ዲግሪያችሁን ያገኛችሁት የቀኙን አእምሯችሁን አጥታችሁ ነው።

እሺ ታዲያ ምን አወቃችሁ? መረጃ። አእምሯችሁ በትውስታ ታጭቋል፣ የምታስታውሱትን መድገም እና ማባዛት ትችላላችሁ። መመዘኛ ፈተናዎቻችሁንም ይህንኑ ያረጋገጡ ነበሩ። አንድ ሰው ‹‹አስታይ›› የሚባለውን እንዲውጥ የተደረገው ሁሉ መትፋት ከቻለ ነው። መጀመሪያ በግድ እንዲውጥ ሲደረግ ይቆይና መጨረሻ ላይ በፈተና እንዲያስመልሰው ይደረጋል። በብቃት ማስመለስ የቻለ አስተዋይ ነው። የተጎሰጎሰበትን ሁሉ ምንም ሳይቀር በትክክል ማስመለስ የቻለ አስተዋይ ይባላል። ይህ ነው፣ የዓለማችን የትምህርት ሥርዓት።

እዚህ ላይ ግንዛቤ የሚያስፈልገው ነገር አለ። አንድ ሰው የበላውን ሁሉ ራሱን ማስመለስ የሚችለው ጨጓራው ሳይፈጨውና ሳያብላላው ከቀረ ብቻ መሆኑን አስታውሱ። ብታብላሉት ኖሮ ራሱን ማስመለስ አትችሉም። ሌላ ነገር ሊወጣ ይችላል፣ ደም ሊወጣ ይችላል፣ እንጂ የበላችሁትን ዳቦ ራሱ አይወጣም። ስለዚህ የበላችሁትን በፈተና ለማስመለስ ሳታብላሉ ጨጓራችሁ ውስጥ ማስቀመጥና ማቆየት ሊኖርባችሁ ነው። ከሁሉ የባሱ ስቱፒዶች፣ ከሁሉ የበለጡ አስተዋዮች ተደርገው የሚታዩት ለዚህ ነው። እጅግ አሳዛኝ ሁናቴ ነው።

በትክክል አስተዋዩ ሰው ከዚህ ስርዓት ጋር ላይጣጣም ይችላል። ዝነኛው የፊዚክስ ጠበብት አልበርት አንስታይን የማትሪክ ፈተናውን ሳያልፍ መቅረቱን

ታውቃላችሁ? ያን ያህል የፈጠራ ብቃት የተሰጠውን አስተዋይነት ቢይዝም፣ ሌሎች ሁሉ በሚከተሉት መንገድ መራመድ ተቸግሮ ነበር።

በየኮሌጁና በዩኒቨርስቲው የምታገኟቸው የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚዎች ሁሉ ይከስማሉ። በጭራሽ ምንም ጥቅም አይኖራቸውም። የድላቸው ፍጻሜ በወርቅ ሜዳሊያዎች ይበሰራል። ከዚያ በኋላ የትም ሥፍራ አይገኙም። ለሕይወት ያበረከቱላት ምንም ነገር ስለሌለ እሷም ምንም አትሰጣቸውም። እነዚህ ሰዎች ምን ነክቷቸው ነው? የምስክር ወረቀታቸውን ገዝተው ሁሉን ነገር አጥተዋል።

ይህንን መሰል ትምህርት ሙሉ በሙሉ መለወጥ አለበት። ወደ ትምህርት ክፍሉ የበለጠ ደስታ፣ የበለጠ ውጥንቅጥ፣ የበለጠ መዝሙርና ዜማ፣ የበለጠ ቅኔና ቅኝት፣ የበለጠ ፈጠራና የበለጠ አስተውሎት መግባት ይኖርበታል። በትውስታ ላይ ይህን ያህል ጥገኝነት መኖር የለበትም።

ሰዎች ክትትልን ማግኘትና አስተዋይ እንዲሆኑ መርዳት ይኖርባቸዋል። አንድ ሰው በአዲስ መንገድ ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ ዋጋ ሊያገኝ ይገባል። ትክክለኛ መልስ የሚባል ነገር መኖር የለበትም - የለምም። ያለው ወይ  መልስ አለዚያ ደግሞ አስተዋይ መልስ ነው። ነገሮችን ትክክለኛና ስህተተኛ አድርጎ መፈረጅ በራሱ ስህተት ነው። መልሱ ወይ ከመደጋገሙ የተነሳ ደካማ፣ ወይ ደግሞ በፈጠራ ከመታጀቡ የተነሳ አስተዋይ መልስ ብቻ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። አንድ ተደጋጋሚ መልስ ስለተለመደ ብቻ ትክክል ተደርጎ ቢታይ እንኳን፣ ተደጋጋሚነቱ በራሱ ዋጋ ሊያሳጣው ይገባል። ልክ እንዲሁ ሁሉ፣ አንድ አስተዋይ መልስ ሙሉ በሙሉ ትክክለኛ ባይሆን እንኳንና አርጌዎቹ የተለመዱ ሐሳቦች ጋር ባይገጥም እንኳን፣ አዲስ በመሆኑ ብቻ ውዳሴ ይገባዋል። ምክንያቱም አዲስነቱ አስተዋይነቱን ያሳያል።

የፈጠራ ብቃት እንዲኖራችሁ ከፈለጋችሁ፣ ምን ማድረግ ይኖርባችኋል? ወላጆቻችሁ ማህበረሰብ እናንተ ላይ ያደረሰባችሁን ሁሉ መፍታት ይኖርባችኋል። ፖሊሱ፣ ፖለቲከኛውና፣ ቄሱ እና አስተማሪዎቻችሁ ያስያዟችሁን ሁሉ መካድ። ብትችሉ፣የፈጠራ ያስተማሯችሁንና ያሳዩዋችሁን መንገዶች ሁሉ መካድ መለወጥ ብትችሉ፣የፈጠራ ብቃትና ስትፈጠሩ የነበራችሁን የመኖር ጉጉት ዳግመኛ ታገኙታላችሁ። አሁንም ሥራውን መጀመር ይችላል። ሥራውን ባለበት ተዳፍኖ ተጨቁኖ ይጠብቃል። ሥራውን ማለት የፈጠራ ክህሎት ሲጀምር ሃይማኖታዊ ትሆናላችሁ። ለእኔ ሃይማኖታዊ ሰው ማለት የፈጠራ ብቃትን ይዞ ያለው ሰው ማለት ነው። ማንኛውም ሰው የሚወለደው የፈጠራ ብቃትን ይዞ ነው። ማንኛውም ሰው የሚወለደው የፈጠራ ብቃትን ይዞ
ቢሆንም ይህንን ብቃት ይዘው የሚዘልቁት ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው።

ትችላላችሁም።

ከዚህ ወጥመድ ውስጥ መውጣት የእናንተ ፈንታ ነው። ምክንያቱም ማህበረሰቡ ያሰረባችሁን መፍታት በእርግጥ ታላቅ ወኔ ያስፈልጋችኋል። ምክንያቱም ማህበረሰቡ ያሰረባችሁን መፍታት በእርግጥ ታላቅ ወኔ ያስፈልጋችኋል። ሰዎች ስትጀምሩ ክብራችሁን ታጣላችሁ። የተከበራችሁ ተደርጋችሁ አትታሰቡም። ‹‹ምን ሆኖ ግራ-አጋቢና ባይተዋር ያደርጓችኋል። እንደ ቀውስ ይቆጥሯችኋል።

ነው፣ ምስኪን!›› እያሉ ያስባሉ። እንደቀውስ ወደምትቀጠሩበት ሕይወት ውስጥ መግባት ወኔን ይጠይቃል።

ዳሩ ግን ይህንን አደጋ ሕጋፊጥ ይጠበቅባችኋል። ካለበለዚያ የፈጠራ ብቃት ማግኘታችሁ ያጠራጥራል። ግን ውጤቱ አርኪ ነው። ትንሽ የፈጠራ ብቃት ከዚህች ዓለም ሁሉና ከግዛቷ የበለጠ ዋጋ አለው።

2. ለመማር ዝግጁ ሁን

ሥርዓት የሚለው ቃል ውብ ነው። ግን ባለፉት ጊዜያት እንደ ሌሎቹ ውብ ቃላት ሁሉ ይህም ቃል ያለአግባብ ጥቅም ላይ ሲውል የኖረ ነው። ሥርዓት (discipline) የሚለው ቃል የመጣው disciple (ሐዋርያ) ከሚለው ስርወ-ቃል ነው። (የግዕዝ የሐዋርያ (disciple) ስርወ-ትርጓሜው ‹‹የመማር ሂደት›› ማለት ነው። (የግዕዝ ትርጓሜውም፣ ‹‹ሐዋርያ / ሐዋሪ›› ማለት መንገደኛ ወይም መምህር ሲሆን፣ ሐ - ሂደ የቃሉ ሥር ነው።) ለመማር ዝግጁ የሆነ ሰው ሐዋርያ ሲሆን፣ ሥርዓት ደግሞ ለመማር ዝግጁ የመሆን ሂደት ይሆናል።

አዋቂ ሰው አውቃለሁ ብሎ ስለሚያስብ ፈፅሞ ለመማር ዝግጁ አይደለም። ዕውቀቱ በ‹‹ዕውቀቱ›› ወይም ዕውቀቴ ብሎ በሚጠራው ነገር እጅግ ይኩራራል። ሐዋርያ መሆን ለእኔነቱ እና ለትምክህቱ ማዳበሪያ እንጂ ምንም አይደለም። (ሕዋር - discipline) አይችልም። ትክክለኛ ሕዋር ውስጥ መግባት አይችልም።

‹‹አንድ ነገር ብቻ አውቃለሁ፣ ምንም አለማወቄን›› ብሎ ሶቅራጥስ ተናግሯል። የሕዋር / ሥርዓት መጀመሪያው ይህ ነው። ምንም የማናውቅ ስንሆን የመጠየቅ፣ የመመርመርና፣ የመፈተሽ ፍላጎት ይኖረናል። መማር ስንጀምር ደግሞ ይህን ተከትሎ የሚመጣ ሌላ ነገር አለ። የተማርነውን ሁሉ ዘወትር ወደ ኋላ እየተውን መሄድ ይከተላል። ካለበለዚያ ግን ትምህርቱ ወደ ዕውቀት ይለወጣል። ዕውቀት ደግሞ ቀጣይ ትምህርትን ይከለክላል።

እውነተኛው የሕዋር ሰው ዕውቀትን አያከማችም። በየቅጽበቱ ያወቀውን ሁሉ ከአእምሮው በማውጣት ዳግመኛ መሐይም ይሆናል። ይህ መሐይምነቱ እውነተኛ ብርሃን ነው። ዳዮኒሲየስ መሐይምነትን ብሩህ ብሎ መሰየሙ ላይ እኔም እስማማበታለሁ። በሕልውና ሁሉ ውስጥ እጅጉን ከተዋቡ ኩነታት አንዱ ባለማወቅ ብርሃን ውስጥ መሆን ነው። በዚያ ያለማወቅ ስሜት ስትሆኑ፣ ያለምንም ገደብ በክፍት ልቡና ለመመርመርና ለማወቅ ዝግጁ ትሆናላችሁ።

ሕዋር / ሥርዓት የተሳሳተ ትርጓሜ ሲሰጠው ኖሯል። ሰዎች ሌሎች ሰዎችን ሕይወታቸውን በሥርዓት እንዲመሩ፣ ይህንንና ያንን በሥርዓት እንዲያደርጉ ሲመክሩ ኖረዋል። በሰው ልጆች ይህን አድርግና አታድርግ እያሉ የሚናገሩ በሺህ

ሚቆጠሩ ሥርዓቶች ተጭነውበታል፡፡ ሰው በእነዚህ ሥርዓቶች ቀንበር ሥር የኖረ ሬጠሩ ብቃት ይኖረዋል ማለት ዘበት ነው፡፡ እስረኛ ነውና በሄደበት ሁሉ መሰናክል አያጣውም፡፡ በፈጠራ የተካነ ሰው ራሱን ከማህበረሰብ ድንጋጌዎች ሁሉ ማንጻት አለበት፡ ነፃነትና ሰፊ ቦታ ያሻዋል፡ ሰማዩ ሁሉ፡ ከዋክብቱ ሁሉ የእሱ ሲሆኑ በፈጠራ፡ በራሱ ጊዜ ተቀጣጣይ ውስጣዊ ማንነቱ ማደግ የሚጀምረው ያን ጊዜ ብቻ ይሆናል፡፡

ስለዚህም ለሥርዓት የሰጠሁት ፍቺ እንደ አስርቱ ትዕዛዛት የማይለወጥና ሱ ያለመሆኑን አስታውሱ፡፡ ይህን ተከለሱ እያልኩ ሥርዓት እያስያዝኳችሁ ወይም ሕዋር እያሳየኋችሁ አይደለም፡፡ በእንዴት ዐይነት መንገድ ዘወትር ትምህርት መቅሰማችሁን ሳታቋርጡ፣ ግን ፊፅሞ ዕውቀት የሚባል ነገር ሳይኖራችሁ መኖር የምትችሉበትን ዘዴ እያስቃኘኋቹ ነው፡፡ ሥርዓቶቹ ከራሳችሁ ልብ ውስጥ የመነጩ፣ የግላችሁ ሥርዓት መሆን አለበት፡፡ በራሳችንና ሌሎች በሚያስርፁብን ሕዋር መካከል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ ሌሎች የሚከተሉትን ሕዋር ስንከተል፣ ከእኛ ጋር አብሮ ሊሄድ አይችልም፣ ልክ የሌላ ሰው ልብስ እንደመልበስ ነው፡፡ ወይ ይሰፉናል ወይም ይጠብቡናል፣ ሊኮሰኩሱንም ይችላል፡፡

ነብዩ መሐመድ ለሐዋርያቱ የሚከተሉት ሕዋር ሰጥቷቸዋል፡፡ ለራሱ ቢስማማውም ለሌሎች ሰዎች ሁሉ ግን ሊስማማ አይችልም፡፡ ቡድሀም ለብዙ ሚሊዮን ሐዋርያቱ / ተከታዮቹ ያወረደላቸው ሕዋር ለራሱ መልካም ይሁን እንጂ ለሌላ ለማንም መልካም ሊሆን አይችልም፡፡ ሥርዓት የግል ነው፡፡ ከሌሎች ከተዋስነው ግን በተደነገጉ ደንቦች መሰረት መኖር እንጀምራለን፡፡ እነዚህ ደንቦች በእኛ ላይ ሙት ናቸው፣ ለእኛ የተዘጋጁ አይደሉም፣ ሕይወት ደግሞ በየቅፅበቱ ያለማቋረጥ የምትለዋወጥ እንጂ፣ ሙት አይደለችም፡፡

ፈላስፋው ሔራክሊተስስ አንድ ጊዜ የረገጥከውን ወንዝ ደግመህ አትረግጠውም፣ ብሎ የተናገረው ትክክል ነበር፡፡ እንደውም እኔ፣ ወንዙ በፍጥነት እየወረደ ከመሆኑ የተነሳ፣ እዚህ ወንዝ ውስጥ አንድ ጊዜ እንኳ መርገጥ አትችልም ብዬ ሐሳቡን ማጠናከር ይዳዳኛል! ማንም ሰው ቢሆን የሚገጥመውን እያንዳንዱን ሁኔታና የሁኔታውን አሉታዊና በጎ ገጽታ በንቃትና በጥንቃቄ መመልከት አለበት፡፡ ከዚያም እንደየቅፅበቱ ለሁኔታው ምላሽ መስጠት እንጂ በሌሎች የተሰጡ ምላሾችን ተመርኩዞ ምላሽ መስጠት አይችልም፡፡

የሰው ልጅን አይረቤነት አስተውላችኋል? ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ማኑ ለሒንዱ ተከታዮች የሰጣቸውን ሕዋር አሁንም ድረስ እየተከተሉት ይገኛሉ፡፡ ከሦስት መቶ ዓመታት በፊት ሙሴ ለአይሁዶች ያወረደላቸውን ሥርዓት አሁንም እየተከተሉት ነው፡፡ ከአምስት ሺህ ዓመታት በፊት አዲናታ ለጄናች የቀረፀውን ሕግጋት በአሁኑ ዘመንም ይከተሉታል፡፡ ዓለም በጠቅላላ በእነዚህ ሥርዓቶች የተነሳ አብደት ውስጥ በመዳከር ላይ ይገኛል! እነዚህ ሕግጋትና ሥርዓቶች ጊዜያቸው

ስለፈፃሚው ስለመሆናቸው ትዝታቸው-መፈታቸው መፈፀም የነበረበት ድር ገና ከሬደም በመኖት በፊት ነበር። የተሰጣችሁት በድን ፊሳቸውን ብቻ ነው። ከበድን ትሬታቸው የሚመጣው ሽታም ዓለምን እያበላሸት ይገኛል። በበድን ፊሳዎች ተከብባችሁ ስትኖሩስ ሕይወት ምን ዐይነት ሊሆን ይችላል?

እኔ የማስተምራችሁ፣ ስለዚህች ቅጽበትና ስለዚህች ቅጽበት ነፃነት፣ እንዲሁም ስለዚህች ቅጽበት ጋሻፊነት ነው። በዚህች ቅጽበት ትክክል የሆነ አንድ ነገር በሚቀጥለው ቅጽበት ስህተት ሆኖ ሊገኝ ይችላል። ዘወትር ተመሳሳይ ሕይወትን ለመኖር አትሞክሩ፣ ካለዚያ ሕያውነታችሁ የስም ብቻ ይሆናል። ዘወትር ተመሳሳይ ሕይወት የሚኖሩት ሙታን ብቻ ናቸው። ሕያው ለመሆን ሞክሩ። ሕያውነታችሁ በየቅጽበቱ ተለዋዋጭ ነው። እያንዳንዷን ቅጽበት እየኖራችሁ ሲታልፉትም ስላለፈው ወይም ስለመጪው ጊዜ ምንም ሳትጨነቁ ይሁን። ስለ ትናንት አትፀፀቱ ስለነገም አትጓጉ። ይህቺን ቅጽበት ከራሷ አኳያ ብቻ በምትኖሯት ጊዜ ምላሻችሁ ሁለንተናዊ ወይም ምሉዕ ይሆናል። ይህ ምሉዓዊነት በራሱ ውበት አለው። ፈጠራ ማለትም ይህ ሁለንተናዊነት ነው። ከዚህ ስጦታችሁ በኋላ የምታደርጉት ማንኛውም ነገር የራሱ የሆነ ውበትን ይጎናፀፋል።

3. ኒርቫናን በተራ ነገር ውስጥ አግኙ

ሕይወትን የሚፈጥር፣ ሕይወትን የሚያስውብ አትክልተኛ የኖቬል ሽልማት ተሰጠው ተብሎ ሰምታችኋል? ምድራቱም እርሶ ለሁላችሁም መፋፋትን የሚያመጣው ክበራውስ ተሸልሞ ያውቃል? በጭራሽ። ይህ ሰው ከመኖሩ እንኳን ሳይታወቅ ይሰፋል።

ይህ ሐቅ የዓለማችንን ደንቦች እስከፊ ገጽታ አሳይ ነው። ምንም ፈጠራ ምን፡ ማንኛውም ሰፈጠራ የበቃ ነፍስ፣ ሰፈጠራ ከብር ሲባል መከበርና መወደስ ሰበጉት፡ ዳሩ ግን ዓለማችን ከብልፕ ወንደሰዋች ሳልተሻሉት ሰፖሰቲከኞች እንኳን ግብዕ ትሸልማለች፡ እስከዛሬ በዚህች ዓለም የተፈጠረው የደም መፋሰስ ምክንያቶች እነዚሁ ፖለቲከኞች ናቸው። እሁንም ቢሆን ዓለም በገዛ እጇ ሕይወቷን እንድታጠፋ በሚገፋት መልክ የኒውክሊየር ጦር መሣሪያዎችን በገፍ እያዘጋጁ ነው።

በእውነት ለራሱ በታመነ ማህበረሰብ ዘንድ፣ የፈጠራ ተግባር ክብር አለው። ምክንያቱም ያ የፈጠራ ነፍስ በፈጣሪ እምላክም ፈቃድ በመፍጠር ተግባር ላይ እየተሳተፈ ነው።

ለውበት ያለን ግንዛቤና ስሜት እጅግ ውስን ነው።

ይህንን ሐሳብ ሳነሳ፣ አብራሃም ሊንከን ትዝ አለኝ። አብርሃም ሊንከን ጊላ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ለመሆን የበቃ፣ የአንድ ጫማ ሰፊ ልጅ ነበር። በጊዜው

በወቅት የንጉሳዊ ቤተሰብ ፊላጭ ቆራጭ አባላት በዚህ ጉዳይ ከመጠን በላ ተረበሹ፤ ተቆጡም፡፡ ብዙም ሳይቆይ አብርሃም ሊንከን በሰው እጅ መገደሉ፣ አስገራሚ ሊጋጣሚ አልነበረም፡፡ ታድያስ! የአንድ ጫማ ሰፊ ልጅ በፕሬዝዳንትነት ሀገር እየመራ መሆኑ አልተዋጠላቸውም፡፡

የሥልጣን ዘመኑን ሀ ብሎ በሚጀምርበት በቀዳሚዋ ዕለት ለምክር ቤቱ የመክፈቻ ንግግር ለማድረግ ከመቀመጫው ሊነሳ እየተዘጋጀ ሳለ፤ ድንገት አንድ መርዘኛ የዘውድ ሥርዓት አቀንቃኝ ቀድሞ ከመቀመጫው በመነሳት እንዲህ ይለዋል! ‹‹ሚስተር ሊንከን፣ አሁን በአንድ አጋጣሚ የሀገሪቷን ፕሬዝዳንት ብትሆንም፤ ለተከበረው ቤተሰባችን ጫማ ለመስፋት ከአባትህ ጋር እኔ መኖሪያ ቤት ትመጣ እንደነበር አትርሳ፡፡ እንደውም አባትህ የሰሩላቸውን ጫማዎች ያደረጉ የምክርት-ቤቱ አባላት እዚህ ይገኛሉ፣ ስለዚህ መነሻህን ፈፅሞ እንዳትረሳ፡፡››

ዘውደኛው ይህንን የተናገረው ፕሬዚዳንቱን ለማሳፈርና ለማሳቀቅ አስቦ ነበር፡፡ ዳሩ ግን አብርሃም ሊንከን ዐይነት ሰውን ማሳፈር አይቻልም፡፡ ለሚሳቀቁ የዝቅተኝነት መንፈስ የተጠናወታቸው መናኛ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ ታላላቆቹ የሰው ልጆች መሳቀቅን ተራምደው አልፈውታል፡፡

ታላቁ አብራሃም ሊንከንም ለተሰነዘረበት የሰጠው ምላሽ፣ በሰዎች ሁሉ ሊታወስ ይገባዋል፡፡ እንዲህ ሲል ነበር የመለሰለት ‹‹ለምክር ቤቱ የመጀመሪያ ንግግሬን ሳደርግ ስዘጋጅ ስለ አባቴ ስላስታወስከኝ በጣም ላመሰግንህ እወዳለሁ፡፡ አባቴ ውብ ተሰጥኦ የነበረው የፈጠራ ከያኒ ነበር፡፡ እንዚህ መሰል ውብ ጫማዎች ከእሱ ሌላ ሊሰራቸው የሚችል ሰው የለም፡፡ የትኛውንም ነገር ባደርግ፣ የእሱን ታላቅ ፈጣሪነት የሚስተካከል ታላቅነት በፕሬዝዳንትነቴ በጭራሽ ልቀዳጀው አልችልም፡፡ ከእሱ ልልቅ አይቻለኝም፡፡›› ብሎ ንግግሩን ቀጠለ፡፡

‹ብካራችን ላይ፣ እዚህ ለተገኛችሁ ንጉሣዊ ቤተሰብ አባላት ሁሉ ባስታውሳችሁ የምፈልገው ነገር ቢኖር፣ አባቴ የሰራላችሁ ጫማዎች ከጠበቧችሁ፤ እኔም የጫማ ሥራን ጥበብ ከአባቴ መማሬን እንድታውቁ ነው፡፡ የእሱን ያህል የተዋጣልኝ ጫማ ሰራተኛ ባልሆንም፣ ግን ቢያንስ ቢያንስ ጫማዎቻችሁን በልካችሁ ሳስተካክልላችሁ እችላለሁ፡፡ እናንተ አሳውቁኝ እንጂ፣ ወደየመኖሪያ ቤታችሁ እመጣለሁ፡፡››

ይህን ጊዜ ምክር-ቤቱ በታላቅ ፀጥታ ተዋጠ፡፡ የምክር-ቤቱ አባላትም ይህንን ሰው ማሳቀቅ እንደማይቻል ተገነዘቡ፡፡ ሊንከን በዚህ ምላሹ ለፈጠራ ያለውን ታላቅ አክብሮትም አሳይቷል፡፡

የፈጠራ ክህሎታችሁ በተሰማራችሁበት መስክ የሚወሰን አይደለም፡፡ ሰዓሊ፣ ቀራፂ፣ ጫማ ሰሪ፣ አትክልተኛ ወይ ገበሬ አለዚያ ደግሞ እናቂ መሆናችሁ ለውጥ

አያመጣም። ዋናው ነገር ነፍሰያችሁን ከምትፈጥሩት ውስጥ አዋህዳችሁ ነው ብዬ የሚለው ነጥብ ነው። ከሆነ፣ የፈጠራ ውጤቶቻችሁን ከመለኮታዊ ባህሪ የሚወርሱት አንድ መለያ ይኖራቸዋል።

ፈጠራ ከአንድ የተለየ የሥራ ዘርፍ ጋር ምንም ዝምድና የለውም። ፈጠራ የሚዛመደው ከንቃተ-ሕሊናችሁ ጥራትና ምጥቀት ጋር ነው። ፈጠራ ምን እንደሆነ ካወቃችሁ፣ የምታደርጉት ማንኛውንም ነገር የፈጠራ ድርጊትት የፈጠራ ተግባር ሊሆን ይችላል።

ፈጠራ ማለት የትኛውንም ዐይነት ሥራ የፀሎት ያህል በደስታ ማከናወን፣ ሥራ የተባለን ሁሉ በጥልቅ የፍቅር መንፈስ መሥራት ማለት ነው። በፍቅር ማለትም ወድዳችሁ መኘታ ክፍላችሁን ማፅዳት በራሱ ፈጠራ ነው። ሳትወደደ የግዳችሁን ካደረጋችሁት ግን ተግባራችሁ የግዳጅ እንጂ የፈጠራ አይሆንም። ይህ ከሆነ ደግሞ የፈጠራ ተግባራችሁን መራገፍ እንዳለበት ሸክም ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የፈጠራ ተግባራችሁን የምታከናውኑበት ሌላ ሰዓት ሌላ ጊዜ ያስፈልጋችኋል ማለት ይሆናል። ግን ለፈጠራ በመደባችሁት በዚያ ጊዜ ላይስ ምን ታደርጋላችሁ? ቤታችሁን ከማፅዳት የተሻለ ሥራ ልትሰሩ ትችላላችሁ? ስዕል ብትስሉ በተሻለ የፈጠራ መንፈስ ይኖረናል ብላችሁ እያሰባችሁ ይሆን እንዴ?

ግን እኮ ስዕል መሳል ወለሉን ከማፅዳት ያልተለየ ተራ ነገር ነው። ስትስሉ በሸራው ላይ ቀለማ ቀለም እየቀባችሁ ታስውቡታላችሁ፣ ወለሉን ስታፀዱ ደግሞ ልክ እንደመጀመሪያው በውሀ እየወለወላችሁ ታሳምሩታላችሁ። ልዩነቱ ምንድን ነው? የሥራ ሰዓት ብላችሁ በመደባችሁት ጊዜ ከጓደኞችሁ ጋር መነጋገር ጊዜ እንደማባከን ትቆጥሩታላችሁ። ግን አንድ ታላቅ መፅሐፍ ልትደርሱ ስትፈልጉ ያን ጊዜ በፈጠራ ውስጥ የገባችሁ ይመስላችኋል። ጓደኞችሁ እኮ የመጣው እናንተን ብሎ ነው! የእሱ መምጣት እንደምትደርሱት መፅሐፍ ታላቅ ነው። ጥቂት መጫዋወቱ ማንን ጎዳ? እንደውም ፍፁም ውብ ነገር ነው። ፈጣሪነት ይኑራችሁ!

አጫውቱት ወይ አጫውቷት። የምታውቁትንም ሰው በበጎ ማማት ትችላላችሁ። ምን አለበት፣ ታላላቅ የተባሉት ቅዱሳን መፅሐፍት እንኳን የፈጠራ ሰዎችን ከማማት በስተቀር ሌላ ምን ያጫቁ መሰላችሁ? እኔስ አሁን ምን እያደረግኩ ነው? ሰዎችን እያማሁ አይደለም እንዴ? አንድ ቀን ጊዜ ሲቆጠር ቅዱሳን መጻሕፍት ይሆናሉ እንጂ፣ መጀመሪያ ሁሉም የሐሜታዎች ስብስብ ነበሩ። እኔ ግን ማማትና ማውራት እወዳለሁ። የማማው በፍቅር ስለሆነ ዝንተ-ዓለም እያማሁ መኖር እችላለሁ። እናንተ ሁላችሁም (አንባቢዎች) አንድ ቀን ሊደክማችሁና እኔን ማደመጥ ሰልችቷችሁ ልትሄዱና፣ ብቻዬን ልቀር እችላለሁ። ግን እኔም ማውራቴን አላቋርጥም። አንድን ነገር ከልብ ከወደዳችሁት፣ ፈጠራ ማለት ይህ ነው። ፈጠራ ፍቅር ነው።

በማንኛውም ሰው ላይ የሚከሰት ነገር ነው:: ብዙ ሰዎች እኔ ዘንድ ይመጡና፣ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ከሆነ፣ ‹‹ማንኛውም ሥራ ይሆናል አሸ:: በቃ የትኛውም ዐይነት ሥራ፣ ማፅዳትም ቢሆን?›› ብለው ይጠይቁኛል:: ‹‹አዎ፣ ሥራችሁ ከሆነ የግድ ያስደስታችኋል›› እላቸዋለሁ:: ግን ከጥቂት ቀናት በኋላ ተመልሰው ይመጡና፣ ‹‹ፅዳት እያስደስትም፣ ታላቅ የፈጠራ ሥራ ቢኖረኝ ደስ ይለኛል::›› ይሉኛል::

አንድ እውነተኛ አጭር ታሪክ ልንገራችሁ፣

ወጣቷ ሚስት ለባለቤቷ ጋር ያላት ጎምዛዛ የወሲብ ሕይወት ስላሳሰባት፣ እንደምንም ብላ ወደ ሥነ-ልቦና ሐኪም እንዲሄድ ታሳምነውና ወደስፍራው ይሄዳል:: ሕክምናውን ለተወሰኑ ቀናት ከተከታተለ በኋላ የወሲብ ፍላጎቱ እንደገና ይቀጣጠላል:: ዳሩ ግን ዘወትር ግንኙነት እያደረጉ እያሉ እሱ ከመኝታ ቤቱ ድንገት ተፈናጥሮ በመውጣት መፀዳጃ ክፍለ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ቆይቶ ይመለሳል::

በድርጊቱ የምትገረመው ባለቤቱ፣ አንድ ምሽት ተከትላው ወደ መፀዳጃ ክፍል በመሄድ ተደብቃ የሚያደርገውን ስትመለከት፣ መስታወቱ ፊት ለፊት ቆሞ፣ ራሱን አፍጥጦ እየተመለከተ፣ ‹‹ሚስቴ አይደለችም . . . ሚስቴ አይደለችም::›› በማለት በተደጋጋሚ ሲናገር ደረሰችበት እላችኋለሁ::

ከአንዲት ሴት ጋር ፍቅር ከያዘህ፣ ያቺ ሴት ያለጥርጥር ሚስትህ አይደለችም ማለት ነው:: ፍቅር ትሰራላችሁ፣ ትደሰታላችሁ ከዚያ ግን ነገሮች ይሰክኑና ሚስትህ ትሆናለች:: ከዚያ ደግሞ ነገሮች ያረጃሉ፡ ከዚያ ደግሞ ፊቷን ትለምደዋለህ፣ አካሏን ትለምደዋለን፣ ሁለመናዋን ትለምደዋለህ:: ከዚያ ድብርት ይፈጠራል:: የሥነ-ልቦና ሐኪሙ ጥሩ ሥራ ሰርቷል:: ሐኪሙ፣ ለባልየው ‹‹ከሚስትህ ጋር አልጋ ላይ ጨዋታ ስትጀምሩ፣ ያለማቋረጥ ሚስቴ አይደለችም እያልክ አስብ::›› ከሚለው አስተያየት ሌላ ምንም መድኃኒት አልሰጠውም::

እናንተም እያፀዳችሁ ሳላችሁ፣ እየሳላችሁ መሆናችሁን ያለማቋረጥ አስቡ:: ‹‹ይህ ጽዳት ሳይሆን ታላቅ የፈጠራ ሥራ ነው!›› እያላችሁ ስታስቡ ሆኖ ታገኙታላችሁ! ጨዋታውን የሚጫወተው አእምሯችሁ ነው:: ከተረዳችሁት፣ ፈጠራን በምታከናውኑበት ነገር ሁሉ ላይ ትዋሀዱታላችሁ::

የማንዛቤ ሰው ዘወትር ፈጠራን ይከተላል:: ፈጣሪ ለመሆን እየሞከረ ሳይሆን፣ በቃ ሌላው ይቅርና አቀማመጡ እንኳን የፈጠራ ተግባር ነው:: ተቀምጦ ስትመለከቱት በእንቅስቃሴው ላይ የተወሰነ የዳንስ ባህሪ የተወሰን ክቡርነትን ማስተዋል ትችላላችሁ:: ባለፈው ጊዜ፣ መቃብር ውስጥ በታላቅ ክብር እንደቆመ ሞቶ ስለተቀበረው የዜን መምህር አንብበናል:: የዚህም ሰው ሞት የፈጠራ ተግባር

ነበር። ተግባሩን የፈፀመው ያለምንም እንከን በመሆኑ ሊያርሙለት አልፈለጉም፤ ሞቶ እንኳን በክብርና በግርማ እንደቆመ ነበር።

የምትረዱበት ወቅት የምታደርጉት ሁሉ፣ ምግብ ማብሰልም ሆነ ማፅዳት ፈጠራ ይሆንላችኋል። ሕይወትን ያዋቀሯት ጥቃቅን ነገሮች ናቸው። ሆኖ ግን እኔነታችንን ወይም ግላዊ-ማንነታችን እነዚህ ነገሮች ትናንሽ በመሆናቸው ታላላቅ ነገሮች እንደሚያስፈልጉን ሹክ ይለናል። ‹‹ታላቅ ግጥም ግጠም እንጂ፣ ልክ እንደ ሼክስፒርና እንደሚልተን ትሆናለህ›› ይልሃል። ግለ-ማንነትህን አለመገደድና የፈጠራ ብቃትን ታገኛለህ።

የሰማሁትን ልንገራችሁ፡-

አንዲት የቤት እመቤት በግርሰሪ ሽያጭ በወጣቱ ቅልጥፍና ተማርካ ስሙን ትጠይቀዋለች። ‹‹ሼክስፒር እባላለሁ፤›› ይላታል ወጣቱ።

‹‹ይህማ፣ እጅግ ዝነኛ ስም ነው።›› ትለዋለች።

‹‹መሆን አለበት። እዚህ መንደር ውስጥ ግልጋሎት ስሰጥ ሦስት ዓመት ሊሆነኝ ነው። አላት እላችኋለሁ።

ቀልዱን እወደዋለሁ! ሼክስፒር ለመሆን ምን አስጨነቀን። ሦስት ዓመት በመንደር ውስጥ ማገልገል፣ አንድን መፅሐፍ ከመድረስ ባልተናነሰ ውብ ነገር ነው።

ሕይወት የጥቃቅን ነገሮች ድምር ውጤት ናት። ፍቅር ካለን ያድጋሉ። ያን ጊዜ ሁሉ ነገር እጅግ ታላቅ ይሆናል። የማናፈቅር ከሆነ ግን እኔነታችን ማንኰሻኩን ይቀጥላል።

## አራት ጥያቄዎች

በልባችሁ ውስጥ የሚዘመር ዜማ፣ የሚጨፈር ዳንኪራ አለ። ዳንኪራው ግን ለዐይን አይታይም። ዜማውም ራሳችሁ እንኳን አድምጣችሁት አታውቁም። መገኛው በውስጠ ውስጥ ማንነታችሁ ---------- ጠልቆ የተቀመጠ ነው። ስለዚህ ከጥልቁ የሚያወጣው ይሻል፣ መገለጥ ይገባዋል። የself-actualization /ራስን እውን የማድረግ ምስጢሩ ይኸው ነው።

## 1. ትውስታ እና ዐይን-ሕሊና

በዚህች ቅጽበት ዓለም መኖር ከፈለጋችሁ ከትውስታ መለየት አለባችሁ በማለት ዘወትር ትወተውተናለህ፡፡ ግን ደግሞ ለምሳሌ እኔ ከትውስታዬ ከተለየሁ ወይም ማስታወስ ከተውኩ ከፈጠራ-ዐይን-ሕሊናዬ ጋር እለያያለሁ፤ ምክንያቱም ፀሐፊ እመሆኑ የተነሳ የምፅፈው ሁሉ የሚመነጨው ከማስታውሰው ነገር ነው፡፡

በዓለም ላይ ሥነ-ጥበብና ሥነ-ጥበብን እውን የሚያደርገው የፈጠራ-ዐይን-ሕሊና ባይኖሩ ኖሮ ዓለም ምን ትመስል ነበር? እያልኩ እደነቃለሁ፡፡ አንድ እንደ ፋልስቶይ ዐይነት ሰው ቡድሀን መሆን አይችልም፡፡ ግን ደግሞ አንድ ቡድሀ ፋልስቶይ የደረሰው ዐይነት መፅሐፍ መፃፍ ይቻለዋል?

መልስ፦ አልተረዳችሁኝም እንጂ ይህ ተፈጥሮአዊ ነገር ነው፡፡ በፍፁም ልትረዱኝ አትችሉም፡፡ ምክንያቱም እኔን መረዳት ከፈለጋችሁ ትውስታችሁን ወዲያ መጣል አለባችሁ፡፡ ትውስታችሁ ግንዛቤያችሁን ያዛባዋል፡፡ የምታዳምጡት ቃላቶቼን ብቻ በመሆኑ፤ ያዳመጣችሁት ቃል ከትውስታችሁ ወይም ካለፈ ታሪካችሁ እኳያ ፍቺ ልትሰጡት ትሞክራላችሁ፡፡ በዚህች ቅፅበትዓለም ውስጥ እስካልተገኛችሁ ድረስ ልትረዱኝ አትችሉም፡፡ ከእኔ ጋር የምትሆኑት በዚያን ወቅት (በቅፅበተ-ቦታ-ጊዜ) ብቻ ነው፤ ያለዚያ በአካል እንጂ በሕሊና ከእኔ ጋር መሆን አትችሉም፡፡

እኔ የምነግራችሁ፣ ስነግራችሁ የቆየሁት ሐቅን መዝግባችሁ ያኖራችሁበትን ትውስታ እንድትሰርዙ አይደለም፡፡ ይህም የማይመስል ይሆናል! በሕይወት ዘመናችሁ ያሳለፋችሁትንና የሆናችሁትን መሰረዝ አይቻልም፡፡ ስማችሁ፣ የእናትና የአባታችሁን ማንነት፣ የትዳር ጓደኞችሁንና ልጆቻችሁን ማንነት፣ አድራሻችሁን ማወቅ አለባችሁ፡፡ ወደቤታችሁ ወይም ወደሆቴላችሁ መመለስ ይኖርባችኋል፡፡ ስለዚህ እነዚህን ሐቆች መዘንጋት የለባችሁም፡፡ ልሰርዛቸው ብትሉም አይቻላችሁም፡፡ እኔ የምናገረው ስለ የመቼ-የት-ማን ትውስታ ሳይሆን ስለ ሥነ-ልቦናዊ ትውስታችሁ ነው፡፡ የመቼና የት ትውስት ችግር የለውም፡፡ ምንም ያልተቀላቀለበት ትውስታ ነው፡፡ ዳሩ ግን ይህ ትውስታ ሥነ-ልቦናዊ ተፅእኖ ካሳደረባችሁ ያን ጊዜ ችግር ይፈጠራል፡፡ ልዩነቱን ለመገንዘብ ሞክሩ፡፡

ትናንት አንድ ሰው በስድብ ወረፋችሁ እንበል፡፡ ከዚያ ይህንን ሰውዬ ዛሬ አገኛችሁት፡፡ የመቼ-የት ትውስታችሁን ‹‹ይህ ሰውዬ ትናንት ሰድቦኛል›› የሚል ብቻ ይሆናል፡፡ የክስተቱ ሥነ-ልቦናዊ ትውስታ ግን ሰውየውን ስታገኙት ከመናደዳችሁና እልህ ከመተናነቃችሁ ጋር ይገናኛል፡፡ ይሄን ጊዜ እኮ ሰውየው ወደእናንተ የመጣው ይቅርታን ፈልጎ ይሆናል፡፡ ስህተቱን ወይም ሳያስበው ያደረገው ታውቆት ፀፅቶት ይሆናል፡፡ የመጣው ወዳጅነታችሁን ለማደስ ቢሆንም እናንተ ግን እልህ አልበረደላችሁም፡፡ በዚያች ጊዜና ቦታ ላይ ትመለከቱት አልቻላችሁም፡፡ በትላንት ላይ ስለምትገኙ ብድራችሁን ለመመለስ ልትነሱበት ትችላላችሁ፡፡ ትናንት ግን አልፋለች!

ክትናንት እስከ ዛሬ በጋንጀስ ወንዝ ቁልቁል ምን ያህል ውሀ ተንቆርቁሯል? ይህ ሰው ትናንት የምታውቁት ሰው አይደለም፡፡ በሃያ-አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ሁለታችሁም ተቀይራችኋል፡፡

ሐቅን የመዘገባችሁበት የመች-የት ትውስታችሁ፣ ‹‹ይህ ሰው ትናንት እኔን ሰድቦኛል!›› ይላችኋል፣ ይህ እኔነቴ ግን ተለውጧል፡፡ ይህ ሰውዬም ተለውጧል፡፡ በዚህ የተነሳ ክስተቱ የተፈጠረው ከእናንተ ጋር ምንም ግንኙነት በሌላቸው ሁለት ሰዎች መካከል መሆኑን ትገነዘቡና ሥነ-ልቦናዊ ነፃነትን ታገኛላችሁ፡፡ ‹‹ዛሬም እንደተናደድኩ ነኝ›› አይባልም፡፡ ምንም ዐይነት ቅሪተ ንዴት የለም፡፡ የክስተቱ ትውስታ እንዳለ ቢሆንም የሥነ-ልቡናዊ ተፅእኖው ግን ተፍቷል፡፡ ያንን ሰው ዳግመኛ ስታገኙት አሁን / በወቅቱ በሚኖረው ማንነት አግኙት፣ እናንተም ባገኛችሁት በዚያች ቅፅበተ-ዓለም በያዛችሁት ማንነት ሆናችሁ አግኙት፡፡

በአንድ ወቅት አንድ ሰው ይመጣና ቡድሀን ፊቱ ላይ ይተፋበታል፡፡ ሰውዬው እጅግ ተናዷል፡፡ ይህ ሰው የቤተ-መቅደስ አገልጋይ / ብራሕሚን / በመሆኑ ቡድሀ የሚናገራቸው ነገሮች ሁሉ ያበሳጩዋል፡፡ ቡድሀም የረጠበ ፊቱን ጠረገና ‹‹ከዚህ ሌላ የምትናገረው አለህ?›› ሲል ጠየቀው፡፡

ይህን ጊዜ አናንዳ የተባለው ደቀ-መዝሙሩ በጣም ከመቆጣቱ የተነሳ ‹‹ይህን ሰው ልክ እንዳስገባው ፍቀድልኝ፡፡ ይህ ከልክ በላይ ነው፡፡ ልታገሰው አልቻልኩም፡፡›› ሲል ቡድሃን ይጠይቀዋል፡፡

ቡድሀም ሲመልስ፣ ‹‹ግን እኮ የተፋው አንተ ፊት ላይ አይደለም፡፡ ይሄ የእኔ ፊት ነው፡፡ ሁለተኛ ነገር እስኪ ይህንን ሰው ተመልከተው! ምን ያህል ከባድ ችግር ላይ እንደሚገኝ ተመልከት! ለዚህ ሰው ሐዘኔታ ይኑርህ፡፡ ሊነግረኝ የፈለገው ነገር ነበር፣ ግን ቃላት አጠረው፡፡ ይህ ችግሩ የእኔም ችግር ነው፣ ሕይወቴን ሙሉ የተፈታተነኝ ነገር ነው፡፡ ይህም ሰው ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ መግባቱ ይታየኛል! እኔ ያወቅኩትን ሁሉ ለእናንተ ማካፈል እፈልጋለሁ፣ ግን ለዚህ የሚሆን በቂ ቃል ስለማላገኝ ጥረቴ መና ይቀራል፡፡ ይህም ሰው ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ነው፣ እጅግ ከመናደዱ የተነሳ ንዴቱን የሚገልፅለት ምንም ዐይነት ቃል አላገኘም፡፡ እኔም የምገኝበትን የፍቅር ዓለም ለመግለፅ ምንም ዐይነት ቃላት አላገኘሁም፡፡ የዚህ ሰው ችግር ይታየኛል፡፡ እስኪ ተመልከት!›› ይለዋል፡፡

ቡድሀም ሆነ አናንዳ እየተመለከቱ ነው፡፡ ቡድሀ ከመች-የት ትውስታው በስተቀር የተረተረው ሌላ ትውስታ የለም፣ የአናንዳ ትውስታ ግን ሥነ-ልቦናዊ ትውስታ ነበር፡፡

ሰውዬው ቡድሀ እየተናገረው የነበረውን ፈፅሞ ማመን አልቻለም፡፡ ግራ ተጋባ ቡድሀ በቡጢ ቢነርተው ኖሮ ግራ ባልተጋባ ነበር፡፡ አናንዳ ዘሎ ጉብ ብሎበት

ቢሆን ኖሮም እንደዚያው። በተለምዶ የሚጠበቅ ነገር በመሆኑ ግራ የሚያጋባው ነገር አይኖርም። የሰው ልጆች ተፈጥሮአዊ ምላሽ ነዋ። ቡድሀ ግን የሰውዬው ድርጊት ለሰውየው እንዲያዝንለት፣ ችግሩን እንዲረዳለት ሲያደርገው . . . ያን ጊዜ ሰውዬው ተለይቷቸው ወደ ቤቱ ሄደ። ለሊቱን ሙሉ እንቅልፍ ሳይተኛ ሲያስብበት አደረ። ዘግማው ስሜቱን ይጎዳው ጀመር። ባደረገው ነገር ተፀፀተ። ልቡ ውስጥ ቁስል ተፈጠረ።

በነጋታው ጠዋት በቀጥታ ወደ ቡድሀ በመሄድ እግሩ ላይ ወደቀ፣ እግሩን እየሳመ ይቅርታ ጠየቀው። ይህን ጊዜ ቡድሀ ለአናንዳ እንዲህ ሲል ነገረው «አሁንም ይህንን ችግሩን ተመልከት! አሁን ደግሞ በጣም ስላዘነልኝ፣ ስሜቱን በቃላት መግለፅ አቅቶታል! ስሜቱን እግሬን በመሳም እየገለፀልኝ ነው። ይህ ሰው በጣም ምስኪን ሰው ነው። ከመጠን በላይ የሆነ ነገር ሁሉ በቃላት መግለፅ ይከብዳል። ስለዚህ ይህንን መሰል ስሜት ለመግለፅ አንድ ምልክት ያስፈልጋል። አየህ!»

ይህን ጊዜ ሰውየው ማልቀስ ጀመረ፣ «ይቅርታ አድርግልኝ ጌታዬ። በጣም አዝናለሁ። እንደአንተ ያለ ሰው ላይ መትፋቴ የማልረባ መሆኔን የሚያሳይ ነው።» ይለዋል።

ቡድሀም፣ «እርሳው! የተፋህበት ሰው አሁን የለም፣ ተፊውም አሁን የለም። አንተም እኔም አዲስ ሰዎች ነን! ተመልከት - ይህች ፀሐይ አዲስ ሆና ነው የወጣችው። ሁሉ ነገር አዲስ ነው። ትናንት አሁን የለም። አልፏል። ስለዚህ ሕልውና የለውም። ስለዚህ አንተም ተሰናበተው! እናማ እንዴት ይቅርታ አደርግልሃለው? ምንም ሳታደርገኝ? የተተፋው ሌላ ሰው ላይ ነበር፣ ተፊውም አሁን ከእኔ ጋር ያለኸው አንተ አይደለህም።»

ልቡና ማብቂያ የሌለው ወንዝ ነው።

ትውስታችሁን ወዲያ ጣሉት ብዬ ስል ሥነ-ልቦናዊ ትውስታን ማለቴ ነው። የመቸ-የት ትውስታን ማለቴ አይደለም። ትናንትና ይህ ሰው እንደተፋበት ቡድሀ ጠንቅቆ ያስታውሳል። ዳሩ ግን ይህ ሰውም ሆነ ራሱ አሁን እንደተለወጡ ያስታውሳል። ምዕራፉ ከተዘጋ ቆየ፣ ሕይወታችሁን ሙሉ ተሸከማችሁት መኖሩ አያዋጣም። እናንተ ግን ይዛችሁት ትዞራላችሁ። ከአስር ዓመታት በፊት አንድ ሰው ነግሯችሁ ያቺን እንጓደቡቱን ይዛችሁ እስከ አሁን ድረስ እየኖራችሁ ነው። በልጅነታቹ እናታችሁ ተናድዳባችሁ የነበረውን እስከአሁን ድረስ ተሸክማችሁታል። ገና ጨቅላ ሆናችሁ ሳለ አባታችሁ በጥፊ መትቷችኋል፣ ያንን እስከአሁን ድረስ ታስታውሱታላችሁ።

እነዚህ ሥነ-ልቦናዊ ትውስታዎች ያለማቋረጥ ጫና ያሳድሩባችኋል። ነፃነት ያሳጧችኋል፣ ሕያውነታችሁን ያጠፉባችኋል፣ ያስሯችኋል። የመች የት ትዝታ ግን፣ ስሜት ያልተቀላቀለበት ንፁህ ትዝታ ግን ምንም ዐይነት ችግር የለውም።

ግንዛቤ ማግኘት ያለበት ሌላው ተጨማሪ ነገር፣ ምንም ዐይነት ሥነ-ልቦናዊ ትውስታ በማይኖርበት ጊዜ የመች-የት / ሐቃዊ ትውስታችን ከስህተት ነፃ መሆኑ ነው። ምክንያቱም ሥነ-ልቦናዊ ትውስታ እውነታን ያዛባል። ሥነ-ልቦናችን ከመጠን በላይ በሚረበሽበት ወቅት እንዴት በትክክል እውነታውን ልናስታውስ እንችላለን? ይህ ፈፅሞ የማይቻል ነገር ነው! ስሜታችን እየናወጠ ነው። የመሬት መንቀጥቀጥ ዐይነት ክስተት ውስጥ ገብተን እንዴት በትክክል ማስታወስ እንችላለን? ወይ እናጋንነዋለን ወይም አንደኛውን ሁኔታ ከሁናቴዎች መካከል ሰርዘን እንደውም አዲስና ያልተፈጠረ ነገርን ፈልስፈን ጨምረንበት እናስታውሰው ይሆናል። አስተማማኝ የመረጃ ምንጭነታችን አጠያያቂ ይሆናል።

ምንም ዐይነት ሥነ-ልቦናዊ ትውስታ የሌለው ሰው ሊታመን ይችላል። ለዚህ ነው፣ ከሰዎች ይልቅ ኮምፒውተሮች በበለጠ አስተማማኝ የመረጃ ምንጭ የሚሆኑት ምክንያቱም ኮምፒውተሮች ምንም ዐይነት ሥነ-ልቦናዊ ትውስታ የሌላቸው ‹‹ፍጡራን›› ናቸው። በቃ ከንፁህ ሐቅ ከእርቃን እውነታ ሌላ ምንም የሚያስታውሱት ስሜታዊ ነገር የለም። ስለሐቅ ራሱ ስንነጋገር ሐቅ ማለትም እኛ ሰዎች ሐቅ የምንለው ነገር ብዙ ልብ-ወለድ የተቀላቀለበት ነገር ነው። የቆረጥነው፣ የቀነጠስነው፣ ያጣመምነውና ያዛባነውን ነው ሐቅ ብለን የምንጠራው። የየራሳችንን የተለያዩ ቀለማት ቀብተነዋል። ስለዚህ ሐቅነቱ አክትሞለታል! የሐቅን ምንነት ማወቅ የሚችለው ዐቡድ ወይንም ንዑድ / የበቃ ሰው ብቻ ነው። እናንተ ግን ብዙ ልብ-ወለዶችን ይዛችሁ ስለምትኖሩ ሐቁ ላይ አትደርሱም። ልክ አንድ ሐቅ ላይ ስትደርሱ የራሳችሁ ፈጠራ የሆኑ ልብ-ወለዶቻችሁን ትጨምሩበትና ሐቅነቱ ሳይታያችሁ ያልፋል። እናንተም እውነታን ማዛባት ትቀጥላላችሁ።

ንዑድ ሰው ማለት ልቦናው የነቃ፣ የበቃ ሰው ዘወትርም እውነተኛ ነው፣ ምክንያቱም የሚናገረው ከእውነታ ጋር አብሮ የሚሄድ ነገርን ብቻ ነው! ይላል ቡድሀ። ንዑድ ሰው ከእውነት በስተቀር የሚናገረው ሌላ የለውም። ንዑድ ሰው ማንነቱ ከገሃዳዊነት ጋር ይመሳሰላል። ምንም ይሁን ምንም ንዑድ ሰው እንደ መስታወት ሆኖ ያንፀባርቀዋል። እኔም የምለው ይህንን ነው - ሥነ-ልቦናዊ ትውስታዎችን ወደጎን ብተዉ እናንተም መስታወት ትሆናላችሁ።

‹‹እንዳናስታውስ፣ ትውስታችንን እንድንተወውና በዚህንና በአሁን ጊዜ ላይ እንድንኖር ትወተውተናለህ . . . ›› የሚል ጥያቄ ነበር የጠየቃችሁኝ። ይህ ማለት ግን ያለፈ ታሪኮች ይረሳል ማለት አይደለም። ያለፈው ጊዜ የዚህች ቅፅበት አንድ አካል ነው። ባለፈው ጊዜ ያደረጋችሁት ሁሉ፣ የሆናችሁት ሁሉ፣ የአሁኑ ማንነታችሁ አካለ ነው። ሕፃኑ ማንነታችሁ አሁንም አብሯችሁ አለ። አፍላ ወጣት

ማንነታችሁ አሁንም በውስጣችሁ አለ፡፡ እስከዚች ደቂቃ ድረስ የሆናችሁት ማንነት ሁሉ. . . ያደረጋችሁትን ሁሉ ከእናንተ ጋር አለ፡፡ ባለፉት ዘመናት የተመገባችሁት ምግብ ከደምና ከአጥንታችሁ ጋር ተዋህዷል፤ ያለፈ ታሪካችሁ ቢሆንም በዚህች ቅፅበት በደምስራችሁ ውስጥ እየተሯሯጠ ይገኛል፡፡ ያሳለፋችሁት ፍቅር አሁን ባታገኙትም ግን ለውጧችኋል፡፡ አዲስ ዐይነት የሕይወት እይታ እንዲኖራችሁ ምክንያት ሆኗችኋል፡፡ ዐይኖቻችሁን ገልጦላችኋል፡፡ ትናንትና ከእኔ ጋር ነበራችሁ - ያልፋል? አጋጣሚው ማንነታችሁን ለውጦታል፡፡ አዲስ ብልጭታ ወይንም የዕውቀት ብርሃን አግኝታችሁበታል፤ ይህ ብርሃንም የማንነታችሁ አካል ሆኗል፡፡

አሁን የምትገኙበት ቅፅበት ያለፈ ታሪካችሁን ሁሉ ጠቅልሎ ይዟል፡፡ ታዲያ ልትረዱኝ የምትችሉ ከሆነ ያላችሁበት ይህ ቅፅበት ከዚህ ሌላ መጪውን ታሪካችሁንም ጨምሮ ይዟል፡፡ ምክንያቱም ያለፈ ታሪካችሁ ለውጥን ደረጃ በደረጃ እየፈጠረባችሁ በሚሄድበት ወቅት ጎን ለጎን ለመጪው ጊዜም እያዘጋጃችሁ ነበር፡፡ መጪው ጊዜም አሁን በምትከተሉት ሕይወት ይወሰናል፡፡ በቅጽበተ-ዓለም የምትኖሩት አኗኗር በመጪው ሕይወታችሁ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ አለው፡፡

በዚህች በአሁኗ ቅፅበት ያለፈው ጊዜ ሁሉ ሰፍኖባት ይገኛል፡፡ በዚህች በአሁኗ ቅፅበት መጪው ጊዜ በአጠቃላይ ተጠቃልሏል፡፡ የመጪውን ጊዜ ዕጣ-ፈንታ የሚወስነው ይህ ያለንበት ቅፅበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ስለ መጪው ጊዜም የመንፈስ ጭንቀት ወይንም ሥነ-ልቦናዊ ስጋት / ሐሳብ ሊኖራችሁ አይገባም፡፡ መጪው ጊዜ በዚህች ቅፅበት እየተከናወነ ከሆነ እንዴ ለሆነ ነገር ምን አሳሰባችሁ! ለመንፈሳዊ ሽክም ልታደርጉት አይገባም፡፡ እየተረዳችሁኝ ከሆነ ቀድሞ ነገር በአሁኑ ጊዜ ላይ ተጠቃልሎ እየተከናወነ ነው . . . አንድ ዛፍ ትናንት ከምድር ስለመጠጠው ውሀ አያስብም፤ ድርጊቱ ግን ሆኗል፡፡ አሰበውም አላሰበውም፡፡ ትናንት ስላረፉበት የፀሐይ ጨረሮችም አያስብም፡፡ ዛፎች እንደሰዎች ቂል አይደሉም፡፡

ስለትናንት የብርሃን ጨረሮች ማሰብ ለምን አስፈለገ? እነዚያ ጨረር የዛፉ አካል ሆነዋል፤ የልምላሜው አካል ሆነዋል፡፡ ይህ ዛፍ የዛሬ ማለዳውን ፀሐይ ሲኮመኩም የነበረው ስለትናንቱ ምንም ዐይነት ስነ-አእምሯዊ ትውስታ ሳይኖረው ነው፡፡ ዱሩ ግን ትናንት ከግንዱ፤ ከቅርንጫፎቹ፤ ከቅጠሉቹና ከአበቦቹ ጋር ተዋህዷል፡፡ የዛሬ ማንነቱ አንድ አካል ሆኗል፡፡ መጪው ጊዜ እየመጣ ነው፡፡ ነገ አበቦች የሚያብቡት የሚሆኑት እምቡጦች ብቅ ብቅ እያሉ ነው፡፡ ነገ ምርት የሚሆኑት ፍሬዎች እያሸተቱ ነው፡፡ ሁሉም ዛሬ ላይ አሉ፡፡

ይህች የአሁኗ ቅፅበት ሁሉን ይዛለች፡፡ አሁን ዝንተ-ዓለም ዘላለም ናት፡፡ ስለዚህ ያለፉትን ጊዜያት ክስተቶች እንርሳ እያልኩ ሳይሆን በክስተቶቹ መረበሻችን ይብቃ እያልኩ ነው፡፡ ትውስታው ሥነ-አእምሮአዊ ወይም በየትኛውም መልኩ ስሜታዊ ሊሆን አይገባም፡፡ በቃ ክስተቶቹ ከታሪካዊ ሐቅነት ያለፈ ምንነት የላቸውም

ስለዚህ ሊታወሱ የሚገባቸውም በዚህ ሁናቴ ብቻ ነው። ሊታስታውሷቸው እንዳትችሉ ሁሉ እያልኩም አይደለም። አስፈላጊ ሆነው የሚገኙበት ጊዜና ቦታ ይኖራል! ይሁን እንጂ አስፈላጊ ሆኖ ሊገኝ የሚችለው በአንዲት ቅጽበታዊ ጊዜና ቦታ ላይ በመሆኑ በወቅቱ አስታውሳችሁ የሚጠበቅባችሁን ምላሽ መስጠት ነው። አንድ ሰው የስልክ ቁጥራቹሁን ቢጠይቃችሁ የስልክ ቁጥራችሁን የማስታወስ አስፈላጊነቱ የሚፈጠረው በዚያች በተጠየቃችሁበት ቅፅበት ብቻ ሆኖ ሳለ የስልክ ቁጥሬን ከየት አምጥቼ ልንገርህ? ያለፈ ታሪኬን እኮ ረስቼዋለሁ። ብላችሁ ብትመልሱ አላስፈላጊ እንካ-ሰላንቲያ ውስጥ ከመግባት ሌላ የሚያተርፉችሁ ነገር አይኖርም። በዚህ የተነሳ ይህ ሕይወታችሁን በደስታና በሐሴት ይሞላል ብላችሁ ያደረጋችሁት ነገር ከሰው እያጋጫ ሕይወታችሁን በተቃራኒው መንገድ ሊመራው ይችላል። ይህ አስፈላጊ አይደለም።

ልትረዱኝ ሞክሩ።

ከዚያስ፣ «ያለፈ ታሪካችንን በመርሳት የፈጠራ ዐይን-ሕሊናችንንም ልናጣ እንችላለን . . .» ብላችሁኝ ነበር። ትውስታ ዐይን-ሕሊና ጋር ምን አገናኘው? እንደእውነቱ ከሆነ በትውስታችሁ መጠን ብዛት የፈጠራ ብቃታችሁ ይቀንሳል ምክንያቱም ሠርከ እነዚያኑ ትዝታዎቻችሁን ከመደጋገም ሌላ አዲስ ነገር አይፈጥሩም። ፈጠራ ማለት ደግሞ ለአዲስ ነገር ሕልውና ቦታ መስጠት እንዲሆን መፍቀድ ማለት ነው። አዲስ ነገር እንዲሆን ለመፍቀድ ደግሞ ያለፈውን ትውስታ ገለል በማድረግ ለአዲሱ ቦታ መተውን ይጠይቃል።

አዲስ ነገር ዘልቆ ድል ሊነሳችሁ ፍቀዱ። አዲስ አመለካከት ወደልባችሁ ዘልቆ እንዲያስደስታችሁ ፍቀዱ። ያለፈው ታሪክ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ ይኖራል። ይህ ጊዜ ግን አሁን አይደለም። ያለፈ ታሪክ የሚያስፈልገው ይህንን አዲስ ሕይወት መኖር ስትጀምሩ ነው። ያን ጊዜ ያለፈው ታሪክ አስፈላጊ ይሆናል፣ ምክንያቱም ቋንቋ ያስፈልጋል፣ ቋንቋ የሚገኘው ባለፈ ታሪክ ውስጥ ነው። በዚህ በአሁን ጊዜ ላይ ቋንቋን መፍጠር አትችሉም። ብትፈጥሩ እንኳን ለብዙዎች የማይገባ ዐይነት ይሆናል። ትሩጉም አይኖረውም። መግባቢያ ሊሆንም አይችልም፣ ምላስን በማንቀሳቀስ ድምፅ እየፈጠሩ እንደ ሕፃን ልጅ ከመጫወት በስተቀር መልዕክት ያዘለ እንደበት አይሆንም። ከዚህ ቋንቋ ውስጥ እምብዛም ፈጠራ አይኖርበትም። ትርጉም የለሽ እንደበት ይሆንባችኋል።

ትርጉም ያለው ነገር ለመናገር ቋንቋ ያስፈልጋል። የቋንቋው መናሪያው ያለፈው ጊዜ ነው። ዳሩ ግን ቋንቋ መምጣት ያለበት ልምድ ከተወሰደ በኋላ ነው። ከዚያ ቀጥሎ በመሣሪያነት ተጠቀሙበት እንጂ ሊገድባችሁ አይገባም።

በማለዳው ፀሐይ ዕጌሬዳ እየፈካች ስትመለከቱ ልባችሁን ስጧት። በእናንተ ላይ ተፅእኖ ይኑራት፣ ጠልቃ ወደውስጣችሁ እንድትገባ ፍቀዱላት። ቀለሟ

ይግዛችሁ፣ ያሸንፋችሁ፣ ምንም ነገር አትናገሩ፣ ብቻ በትዕግስት ጠብቁ። ክፍት ሆናችሁ ጠብቁ። ተቀበሏት። ፅጌሬዳዋ እናንተ ዘንድ ትድረስ፣ እናንተም እርሷ ዘንድ ድረሱ። እንደሁለት ፍጡራን ሁናችሁ ውህደት ፍጠሩ፣ ፅጌሬዳዋና እናንተ።

ታዲያ እናንተ ፅጌሬዳዋ ውስጥ ዘልቃችሁ መግባት የምትችሉት ፅጌሬዳዋ እናንተ ውስጥ ዘልቃ በገባችበት መጠን መሆኑን ተረዱ። ከዚህ በኋላ ተመልካቹ ማን? ፅጌሬዳ ማን እንደሆነ ለመለየት የሚቸገርበት ጊዜ ይመጣል። እናንተ ፅጌሬዳዋን፣ ፅጌሬዳዋ ደግሞ እናንተን የምትሆኑበት ቅጽበት ይመጣል። ተመልካቹ ተዋናይ፣ ተዋናዩ ደግሞ ተመልካች ይሆናል። የሁለትዮሽ ዓለም ይጠፋል። በዚህች ቅፅበት እውነታው ይገለጥላችኋል። የፅጌሬዳዋ ህላዌ (suchness) ይታያችኋል። ከዚህ በኋላ ቋንቋችሁን መጠቀም፣ ወደኪነታችሁ መመለስ ነው። ሰዓሊ ከሆናችሁ ብሩሻና ቀለማችሁን ያዙና ሸራችሁን አቅልሙ። ገጣሚ ከሆናችሁ ወደ መቶየት ትውስታችሁ ተመለሱና ያሻችሁን ሐሳብ የምትገልፁባቸው ቃላት ፈልጋችሁ አግኙ።

ዳሩ ግን በዚህ ሂደት ውስጥ ሆናችሁ ከራሳችሁ ጋር መነጋገር የለባችሁም። የውስጣችሁ ጫጫታ ሥራችሁ ላይ ጣልቃ ይገባል። ፅጌሬዷን ባላት የምንነት ጥንካሬ ልክ ልታውቋት አትችሉም። የምታውቁት ከላይ የምታዩትን ቀለምና ቅርጿን ብቻ ይሆናል። የምታውቁት ከላይ ከላይ ያለውን ብቻ ከሆነ ደግሞ በፈጠራችሁ ላይም የምታንፀባርቁት ይህንኑ ከአንገት በላይ እይታ ብቻ ይሆናል። ፈጠራችሁ እምብዛም ቦታ አይኖረውም።

‹‹ማን እኮ ትውስታዬን ከዘነጋሁ የፈጠራ ዐይነ-ሕሊናዬንም በተመሳሳይ መርሳት ይኖርብኛል . . .›› ብላችሁ ስትናገሩ የፈጠራ ትርጉም ግቧችሁ አይደለም፡ ፡ ፈጠራ ማለት አዲስ ማለት ነው። ፈጠራ ከዚህ ቀደም ያልተዳሰሰና ልብ-የወለደው ማለት ነው። ፈጠራ ማለት ትኩስና ያልታወቀ ህብዕ ማለት ነው። ፈጠራ ላይ ለመድረስ ክፍት ሆናችሁ ራሳችሁን በነፃነት ልትሰጡት የግድ ነው።

ትውስታና ትዝታን ወደጎን ተውት። ኋላ ትደርሱበታላችሁ። አሁን ግን ጣልቃ ከመግባት ውጪ የሚፈይድላችሁ ምንም ነገር የለውም። እኔን በምታዳምጡበት ወቅት በውስጣችሁ ያለውን የሂሳብ ቀመር ደግማችሁ እያዳመጣችሁ ይመስላችኋል? የምታውቁትን መልክዓ-ምድር የምስልላችሁ ይመስላችኋል? የምታውቁትን ታሪክ እየደገማችሁት ነውን? አይደለም። ለቋንቋውም ቢሆን ተመሳሳይ ነገር ተጠቀሙ ልክ ለጆግራፊና ለታሪክ የተጠቀማችሁትን ማለት ነው። ለትውስታችሁም እንደዚያው - እርሱት! ረስታችኋቸዋል። ሕሊናችሁን አሳርፉት! አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ በሚመጣ ሰዓት ብቻ ተጠቀሙበት! ገለል አድርጉት!

ይህንን በማድረጋችሁ ሕሊናን እያጠፋችሁት ሳይሆን ፋታ እየሰጣችሁት ነው። አስፈላጊ አይደለም! ስለዚህ አሳርፉት፣ ለአእምሯችሁ! ‹‹ እስኪ ለአንድ ሰዓት

አሪፍ በልና እኔ ላለምንበት። አሳምጨው! አትናገዉ! በልቴ! ጠዋቴ! ስለፈርስ ያኔ እርዳታህን ከፈለግኩ እጠራሃለሁ። ያኔ የአንተ እርዳታ ቋንቋህ፣ ስውቶችህ፣ የተሸከምከው መረጃ ያስፈልገኛል። ከዚያ አንድ ስዕል እስላለሁ ወይ ግጥም አትምማለሁ አስቢያም መፅሐፍ እፅፋለሁ፣ አሁን ግን እረፍት አድርግ። ብላችሁ ልትነግሩት ትችላላችሁ። እረፍት ካደረገ በኋላ አእምሮ የበለጠ ትኩስ ኃይል ይዞ ይመጣል። አእምሯችሁ በወትሮ አልባሌ ነገሮች እንደለበ የሚያገረው እረፍት ስለማትሰጡት ነው።

እስኪ በኦሉምፒክ ለመሳተፍ ስላቀደ አንድ ሰው እናስብ። በኦሉምፒክ ለመሮጥ ብቃት ለማግኘት ሲል በቀን ሃያ አራት ሰዓታት ሙሉ ሲሮጥ ውሎ እያደረ እንበል። ግን በዚህ ሁኔታ ላይ ሆኖ ውድድሩ ላይ ቢሳተፍ በጣም ስለሚደክም እግሩን እንኳን ማንሳት አይችል ይሆናል። ከውድድሩ ቀደም ብላችሁ እናንተም እረፍት ማድረግ ይኖርባችኋል። እግራችሁ መልሶ እስኪያድርስና እስኪጠነክር ድረስ በቂ እረፍት ማድረግ ይኖርባችኋል።

ለአእምሯችሁም ተመሳሳዩን ማድረግ ይኖርባችኋል። ለፈጠራ የምትጠቀሙበት ዐይነ-ሕሊና ከትውስታ ጋር የሚገናኘው ምንም ነገር የለም። ሊፈጥር የሚችለውም በዚያን ወቅት ብቻ ነው። እየተረዳችሁኝ ከሆነ ሥነ-ልቦናዊ ትውስታችሁን በምትተውበት ወቅት የፈጠራ ክህሎት ይኖራችኋል። ይህ ባይሆን ኖሮ ፍጥረት ብላችሁ የምትጠሩት ነገር እውን ፍጥረት ሳይሆን ድርሰት በሆነ ነበር። በፍጥረትና በኪነት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። የምታውቋቸውን ነገሮች ራሳቸውን በአዲስ መልክ ብታቀናጇቸውና ብትደረድሯቸው ያው አሮጌ ናቸው፣ አቀማመጣቸው ተቀየረ እንጂ አዲስ ነገር አይደሉም።

የቤታችሁን እቃ አቀማመጥ ከመለዋወጥ የተለየ አይደለም። አዲስ ቁሳቁስ የለ፣ የግድግዳ ስዕሎቻችሁ፣ መጋረጃዎቻችሁ ያው ናቸው። ግን በአዲስ መልክ ልትደረድሯቸው ትችላላችሁ። አዲስ የፈጠራችሁት ነገር የለም። ዘጠና ዘጠኝ በመቶ ገጣሚያንና ደራሲያን የሚያደርጉት ይህንኑ ነው። የራሳቸው የሆነ ሥራ የላቸውም ስለዚህ የፈጠራ ሰዎች አይደሉም።

የፈጠራ ሰው ማለት አንድን ነገር ከማይታወቀው ዓለም ወደሚታወቀው ዓለም የሚያመጣ ነው። የሰማዮ-ሰማያት፣ የፍጥረታትን ምስጢር ወደዚህች ዓለም የሚያሻግር ነው። ፈጣሪ አምላክ እሱን ወይም እሷን ተጠቅሞ የፈለገውን እንዲናገር የሚፈቅድ ሰው ነው። ልክ እንደሽምበቆ ወይም እንደዋሽንት ይሆናል። ያን ጊዜ ፈጣሪ በውስጡ እንዲመላለስ ይፈቅድለታል። ታዲያ እንዴት እንደዋሽንት መሆን ይቻላል? የሕሊና / የአእምሮ እስረኞች ከሆናችሁ እንደዋሽንት መሆን አትችሉም። ፈጠራ ደግሞ ከእናንተ ወይም የእናንተ ሳይሆን የፈጣሪ ወይም ከፈጣሪ ነው። እናንተ ስትጠፉ ፈጠራ ይከሰታል። እናንተ ሳትሆኑ ፈጠራ ይሆናል። ይህ የሚሆነው ፈጣሪ በእናንተ በኩል መሥራት ሲችል ብቻ ነው።

እውነተኞቹ ፈጣሪያን ይህንን ጠንቅቀው ያውቃሉ። እንዲሆን። እነሱ ከመሣሪያነት የዘለለ አስተዋፅኦ እንደሌላቸው ያውቃሉ። ፈጣሪዎቹ እነሱ ሁሉ አንድ ነገር ተሰርቷል ግን አድራጊዎቹ እነሱ አልነበሩም። በእነሱ

በአንድ የቴክኒክ ባለሞያና በፈጠራ ሰው መካከል ያለውን ልዩነት አስታውሱ፡ ቴክኒሽያኑ አንድን ነገር እንዴት መስራት እንዳለበት ያውቃል። ምናልባትም ሙያው ወደር ላይኖረው ይችላል፣ ግን ጥልቅ አስተውሎት አይኖረውም። የፈጠራ ሰው ይህ ማስተዋል የጎደለው ነው። ከዚያ ቀደም ማንም ተመልክቷቸው የማያውቃቸውን ነገሮ መመልከት የሚችል ነው። ከእሱ ቀድሞ ማንም ሰው ያላመጣቸውን ነገሮች መመልከት የሚችል ነው። ይህንን ማድረግ ስትፈቅዱ ፈጠራ ትከሰታለች።

እስኪ ተመልከቱ . . . የኢየሱስ አባባሎች በፈጠራ የተሞሉ ናቸው፣ ከእሱ ቀድሞ ማንም ተናግሯቸው የሚያውቅ ሰው የለም። የቀለም ትምህርት የተማረ ሰው አይደለም። ስለንግግር ጥበብ የሚያውቀው ነገር የለም። ስለ እንደበተ ርዑትነቱ የሚያውቀው ነገር ባይኖርም ከእሱ በላይ አንደበተ ርዑት ሰዎች አልነበሩም። ታዲያ ምስጢሩ ምን ነበር? ማስተዋል ነበረው። ወደ እግዚአብሔር ተመልክቷል፣ ወደማይታየውና ወደማይታወቀው ዓለም ሄዶ ተመልሷል። ከማይታወቀውና ሊታወቅ ከማይችለው ጋር ተገናኝቷል። ከሄደበት ዓለምም ያገኘውን ይዞ ተመልሷል። ሊያመጣው የሚችለው ጥቂት ብቻ ቢሆንም ከማይታወቀው ዓለም ጥቂት ብቻ እንኳን ይዞ መመለስ ግን የሰው ልጆችን ልቦና ሙሉ በሙሉ የመለወጥ ኃይል አለው።

እሱ ፈጣሪ ነው። እኔ ‹‹አርቲስት›› ነው የምለው። ወይንም ቡድሀ፣ ክሪሽና፣ ነጋትዙ - እነዚህ ሁሉ አርቲስቶች ናቸው። የማይቻለውን ይከስታሉ፣ ያደርጋሉ። የማይቻለው ማለት፣ የሚታወቀውን ከማይታወቀው ጋር ማገናኘት ነው። አእምሮን አእምሮ ካልሆነው ማገናኘት የማይቻል ነገር ነው። የማይቻለው ይህ ነው። እነሱ ግን የማይቻለውን ያደርጉታል።

‹‹ግን እኮ ከትውስታችን ጋር ከተለያየን፣ ከፈጠራ ዐይኑ-ሕሊናችን ጋርም መለያየት ግድ ይሆንብናል . . .›› ብላችሁኛል። ተሳስታችኋል። ትውስታ ከፈጠራ ዐይኑ-ሕሊና ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም። እንደውም ከትውስታችሁ ጋር ብትለያዩ የበለጠ የፈጠራ ዐይኑ-ሕሊና ይኖራችኋል። አሁን ግን ባለቀ ትውስታዎቻችሁ ከመጠን በላይ ከመሸበባችሁ የተነሳ የፈጣሪ ዐይኑ-ሕሊና ሊኖራችሁ አይችልም።

‹‹. . . ፀሐፊ በመሆኔ የምፅፈው ነገር ሁሉ መሰረቱ ትውስታዬ ነው ትላላችሁ። እጅግም ፀሐፍት አይደላችሁ ማለት ነው። በዚህ የተነሳ ትዝታና ታሪክ ስትፅፉ ትኖራላችሁ። መጪውን ጊዜ ወደአሁን ስባችሁ አታመጡትም። ቢቃ ስለድር

በሬ ስትፅፉ መሽቶ ይነጋል። ስለዚህ እናንተ መዝገብ ቤት እንጂ ምንን ፀሀፊ ሆናችሁት! ፀሐፍት መሆን ትችላላችሁ። ያኔ ግን ከማይታወቀው ጋር መገናኘት የግድ ይሆንባችኋል። ትውስታ ቀድሞ ነገር የሞተ ክስተት ነው። ከሆነው (that which is) ነገር ጋር ግንኙነት መፍጠር አለባችሁ። ዙሪያችሁን ከብቦአችሁ ከሚገኘው (suchness) ጋር መገናኘት ይኖርባችኋል። ያለፈው ጊዜ ውስጥ ከተገለጠላችሁ እውነታ ጋር ለመገናኘት እንኳን፣ በዚህ በአሁኑ ቅጽበት ላይ መገኘት ይጠበቅባችኋል።

ትክክለኛው የፈጠራ ክህሎት የሚመነጨው ከትውስታ ሳይሆን ከልቦና (consciousness) ነው። ልቦናችሁ መጎልበት አለበት። ልቦናችሁ እየጠነከረ ሲመጣ የሚኖራችሁ እውነትን የማጥመድ ብቃትም የዚያኑ ያህል ያይላል።

‹‹ዓለም ያስፈጠራና ፈጠራን እውን ከሚያደርገው የፈጠራ-ዐይነ-ሕሊና ባይኖር ምን ገፅታ ይኖራት ይሆን?›› ብላችሁ ጠይቃችኋል። የምትመለከቱት የዓለማችን ሥነ-ጥበብ ሁሉ ዘጠና ዘጠኙ ከመቶው ሥነ-ጥበብ ሳይሆን ውዳቂ ነው። የፈጠራ ሥራ ብቅ የሚለው እጅግ አልፎ አልፎ ብቻ ነው። ብዙዎቹ የፈጠራ ሰው ተብዬዎች ቀጂዎች፣ የቴክኒክና የሙያ ባለቤቶች ወይም ብሩህ አእምሮ ያላቸው እንጂ የፈጠራ ባለቤቶች አይደሉም። ይህ ዘጠና ዘጠኙ ከመቶ ‹‹ሥነ-ጥበብ›› ከምድረ ገፅ ቢጠፋ ምድር የተሻለ በረከት ባገኘች ነበር። ምክንያቱም ይህ ፈጠራ አቆሽሾታል።

አንድ ትልቅ ትርጉም ያለው ነገር አለ። የሥነ-ጥበብ ሕክምና (ቴራፒ) ይባላል። ሰዎች የመንፈስ ጭንቀት ሲጠናወታቸው ሥነ-ጥበብ ታግዛቸዋለች፣ ትፈውሳቸዋለች። ሕመምተኛው ብሩሽና ቀለም ይሰጠውና መሳል የሚፈልገውን ነገር እንደ አዲስ ይስላል። እርግጥ ነው ይህ ሰው የሳለው ምንም ይሁን ምን የእብደት ስዕል ከመሆን ባይዘልም፣ የሚገርማችሁ ነገር፣ የተወሰነ ጊዜ የእብደት ሥዕሉቹን ሲስል ከቆየ በኋላ የአእምሮ ሕመምተኛው እያገገመና ወደ ጤንነት እየተመለሰ ይሄዳል። የሳለው ስዕል ከውስጡ እንደወጣ ደዌ ነው። እንደትሩት ዐይነት እንጂ የፈጠራ ሥራ አይደለም። ለሕሊና ሥርዓቱ አላስፈላጊ በመሆኑ ሕሊናው ያስመለሰውን ነገር ነው የሳለው።

እንግዲህ ይሄ ዘመናዊ ሥነ-ጥበብ የሚባለው ነገርም ከዚህ የተለየ ነገር አይደለም። የፒካሶ ስዕሎች ፒካሶን ከእብደት አድነውት ይሆናል እንጂ ከዚያ ያለፈ የያዙት ነገር የለም። ለእናንተም ቢሆን እነዚህን ስዕሎች እየተመለከታችሁ ብታብሰለስሉ የምታገኙት ነገር ቢኖር እብደትን ብቻ ነው። ራቋቸው! በመኝታ ክፍላችሁ ውስጥ የፒካሶን ስዕል በፍፁም እንዳትሰቅሉ። ካለዚያ የሚተርፋችሁ ትገኑት ነው።

እስኪ አንድ የፒካሶን ስዕል አፊታችሁ አኑሩና ለአስራ አምስት ደቂቃ ትክ ብላችሁ ተመልከቱት፣ መቅበጥበጥ፣ ምቾት ማጣት፣ ማቅለሽለሽ እየተሰማችሁ

ይመጣል። ምን እየሆነ ነው? የሌላ ሰው ትፋት ነው! እሱን ጠቅሞታል፣ ለእሱ ጥሩ ነበር፣ ለሌሎች ግን ጥሩ አይደለም።

ደግሞ እስኪ ማይክል አንጀሎን ተመልከቱ፣ ለብዙ ሰዓታት በሐሴት ማብሰልሰል ትችላላችሁ። በቆይታችሁ ቁጥር መንፈሳችሁ እየተረጋጋና ሰላም እያገኘ ይመጣል። የማይክል አንጀሎ ስዕል ትፋት ሳይሆን ከማይታወቀው ዓለም የመጣ ነው። ከአእምሮ ሥርዓቱ የተፋው ደዌ ሳይሆን ከረቂቁ ዓለም ያመጣው እፁብ ምስጢር ነው። ታሞ ሕይወቱን ለማዳን የሰራው ሳይሆን በተቃራኒው፣ እርግዞ የተገላገለው የፈጣሪ እምላክ ምስጢር ነው። በሕላዌው ውስጥ ስር ሰዶ የቆየውን አንድ ነገር ለሌሎች አካፍሏል። የፍሬያማነት እና የምልዓተ ነፀብራቅ ነው። ሕይወቱን በፈጠራ ኖሯል፣ ሕይወትን በፈጠራ መንገድ አፍቅሯል። ሕይወት ወደ ውስጡ መቅደስ እንድትዘልቅ ፈቀደላት፣ ሕይወትን አረገዘ። ወይንም ፈጣሪን አረገዘ፡ ፡ ያረገዘ ደግሞ መውለድ አለበት።

ፒካሶ እያስታወከ ሲሆን ማይክል አንጀሎ ግን እየወለደ ነው። ፍሬደሪክ ኒቼ እያስመሰለ ሲሆን ቡድሀ ግን እየወለደ ነው። በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ሰፊና ግልፅ ነው። ማስመሰል ሌላ መውለድ ሌላ። ቤቶቨን እየወለደ ነበር፣ እጅግ ከባድ ዋጋ ያለው ነገር በእሱ በኩል እየወረደ ነበር። የእሱን ሙዚቃ ስትሰሙ ሙሉ ለሙሉ ትቀየራላችሁ፣ ወደሌላ ዓለም ትሻገራላችሁ። ቤቶቨን የሌላን ዓለም የባህር ዳርቻ በጥቂቱ ያስቃኛችኋል።

በዓለማችን የምናየው ዘጠና ዘጠኝ በመቶ ሥነ-ጥበብ ከበሽታ የፈለቀ በመሆኑ ይህ ቢጠፋ ምድራችን ጤናማ ትሆናለች። የዘመናችንን ሥነ-ጥበብ ሙሉ በሙሉ ማጥፋት ጠቃሚ እንጂ ጎጂ አይደለም። ዘመናዊው አእምሮ በቁጣ የነደደ አእምሮ ነው። ራሱን ማግኘት ስላቃተው ለሕይወት ትርጉም ስላጣ ወይንም ጥቅም ያለው የሚባለው የትኛው እንደሆነ ካለማወቁ የተነሳ በንዴት የጦፈ ሕሊና ይበዛበታል። ከዦን ፓውል ሳርቴር ዝነኛ መፅሐፍት መሃል አንዱ «ቅልሽልሽ» (nausea) ነው። የዘመናዊ አእምሮህ ሁናቴም ተመሳሳይ ነው። ዘመናዊው አእምሮ እቅለሽልሾታል። በታላቅ ስቃይ ውስጥ ነው። ይህ ስቃይ የራሱ ፈጠራ ነው።

ፍሬደሪክ ኒቼ እግዚአብሔር ሞቷል ብሎ አውጇል። ይህንን ብሎ ባወጀ አለት እብደት ይጠናወተው ጀመር። ምክንያቱም አንድ ሰው እግዚአብሔር ሞቷል ብሎ ስላወጀ ብቻ አይሞትም፣ ኒቼ ግን መሞት ጀመረ። ዓለም ያለ እግዚአብሔር የእብደት ሞት ናት። ምክንያቱም ፈጣሪ የሌለባት ዓለም ሕልውናዋ ትርጉም የለውም።

እስኪ ተመልከቱ . . . አንድ ግጥም ስታነቡ የግጥሙ ቃላት ትርጉም የሚኖራቸው ከግጥሙ ይዘት አንፃር ብቻ ነው። አንዱን ቃል ከይዘቱ ብትነጥሉት ትርጉም አይኖረውም። ከይዘቱ አኳያ ግን ውብ ይሆናል። የአንድን ስዕል ቅዳጅ

ብትመለከቱት ትርጉም አይሰጥም። ትርጉሙ ያለው ዋናው ምሉው ስዕል ውስጥ ነው። በስዕሉ ውስጥ እያለ ብቻ ነበር ቅጻጼ ትርጉም ሊሰጥ የሚችለው።

አንድ ዐይኒን ከጉድጓዱ ብታወጡት የምታገኙት የሞተ ዐይን ነው። ሕያውነቱ የሚረጋገጠው ከአኔ ጋር ሲሆን ነው። አሁን የዐይኑን ውስጥ ብትመለከቱት፣ በውስጡ ታላቅ ትርጉም አገኙ.ል። ዐይኖቹ የአንድ ግጥም አካል ናቸው። የትልቅ ግጥም አንድ አካል ናቸው!! ትርጉም የምትሰጡት ዘወትርም ከእናንተ በላይ ከሚገኝ አካል ጋር አዋህዳችሁ ነው።

ኒቼም እግዚአብሔር ሞቷል ብሎ ባወጀ ዕለት ከትርጉሙ ወጣ። ያለእግዚአብሔር ሰው ትርጉም ሊኖረው አይችልም። ምክንያቱም ሰው የታላቁ የአምላክ ፍጥረት አንዱ አካል ነው። የአምላክ ሙዚቃ ቀመር አንዱ ኖታ ነው። ይህ አነስተኛ ነጠላ ኖታ ግን ከቅኝት ውጪ ሆኗል። ለጆሮም አይጥምም።

ኒቼ የገጠመውም ይኸው ነበር። ኒቼ በራሱ ቅኝት መዝፈን ፈለገ። በዚህ እምነቱ የተነሳም ወደ እብደት አለም ገባ። ከምሉዑ ትርጓሜ የወጣ ነገር ሁሉ እብደት ነው።

እናንተ ለምንድንነው ህያው የሆናችሁት? አታውቁትም። ያለማወቃችሁ ጥቅም የለውም። ድንገት የተፈጠራችሁ ያስመስላችኋል። ብትሆኑ ኖሮ ምንም ልዩ ነገር ባልታየ ነበር። ባትሆኑም እንደዚያው። አላስፈላጊዎች ናችሁ። እያሟላችሁና እየፈፀማችሁ ያላችሁት ምንም ነገር የለም። ብትኖሩም ባትኖሩም የሚመጣ ለውጥ የለም። እንዴት ደስ ሊላችሁ ይችላል። እንዴት ያለ እብደት ልትኖሩ ትችላላችሁ? የፈጠራችሁት ድንገት ነው? በቃ ድንገት? ከሆነማ ሁሉ ነገር ትክክል ነው። ከሆነማ፣ ነፍስ-ግድያም ትክክል ነው። ምክንያቱም ሁሉ ነገር የሆነው በአጋጣሚ ከሆን ምንስ ብታደርጉ ምን ልዩነት ይኖረዋል? የትኛውም እርምጃ የሚይዘው እሴት አይኖርም፣ ስለዚህ ራስን ማጥፋትና ነፍስ መግደል ምን ችግር አለበት?

ችግር ግን አለበት ምክንያቱም ደስታን የሚሰጧችሁ ጥቂት ነገሮች ሌሎች ጥቂት የሚያሳዝኗችሁ ነገሮች አሉ። ገሃነምን የሚፈጥሩባችሁ የተወሰኑ ነገሮች እንዲሁም ገነት የሚያስገቧችሁ የተወሰኑ ነገሮች ይኖራሉ በፍፁም ሁሉም ነገር ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም። ዳሩ ግን አንዴ እግዚአብሔር ሞቷል ከተባለ በኋላ፣ ከሁለንተናዊነት ጋር ከተለያያችሁ በኋላ ግን፣ ማዕበል ስለመጣበት ስለውቅያኖስ ከዘነጋ በኋላ ይህ ማዕበል ምንድን ነው? ያለውቅያኖስ ማዕበል ማዕበል አይሆንም።

አስታውሱ እውነተኛ ስነጥበብ የሚመጠው ከእውነተኛ መንፈሳዊነት ነው፣ ምክንያቱም መንፈሳዊነትና ሃይማኖተኝነት ማለት ከዕውቀት ጋር መተዋወቅ ማለት ነው። ከእውነታ ጋር ከተዋወቃችሁ በኋላ ትክክለኛዋ ሥነ-ጥበብ መገለጥ ትጀምራለች።

እውነተኛ ሥነ-ጥበብ ማለት ወደምስጠት ዓለም ለመግባት የሚረዳችሁ ነው፡ ፡ እስታውሱ የፈጠራ ክህሎት ማለት አርምሞአዊነት ማለት ነው፣ የፈጠራ ክህሎት ማለት አእምሮ የሌለበት ዓለም ማለት ነው፣ አእምሮ የሌለበት አካል ፈጣሪ አምላክ ወርዶ ይገባል፡፡ ከዚያም ፍቅር በውስጣችሁ ይፈስሳል፡፡ ያን ጊዜ ከመልካም ደህንነታችሁ ውስጥ የሚፈስስ ሕይወት ሰጪ ቡራኬ ይኖራል፡፡

## 2. የማጠናቀቅ ድብርት

የመፅሐፍ በምፅፍበት ወቅት በምሉዕ የማያቋርጥ ሀይልና ደስታ ተሞልቼ ነው። ፅፌው ሳበቃ ግን ከሚሠማኝ ባዶነትና ድብርት የተነሳ መጻፍ እንኳን ያስጠላኛል። አሁን መፅሃፉን መጀመሬ ነው። ግን ገና ከወራት በደላ ጨርሼው የሚሠማኝን ሳስበው ገና ካሁኑ በባዶነት ስጋት እሸነፋለሁ።

ይህ ጥያቄ ከአንድ ደራሲ የተሠነዘረ ነበር፡፡ መፅሐፍቶቿን አገላብጨ ስመለከት፣ ውብ ተደርገው የተፃፉ ሆነው አገኘኋቸው፡፡ ስጦታው አላት፣ ታሪክን በግሩምና ማራኪ ለዛ መተረክ ትችላለች፣ ታሪክን ማዋቀርና ማውጠንጠንም እንደዛው፡፡ ይህ ደግሞ የእሷ ንጠመኛ ብቻ አይደለም፡፡ የምትረበሽበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን ለነገሩ የሰጠችው ትርጓሜ ላይ ተሳስታለች፡፡ አንድን ነገር የምንመለከትበት ዓይን ብዙ ለውጥ ማምጣት ይችላል፡፡

አንዲት ሴት ነፍሰ-ጡር ስትሆን ሙሉ ናት፡፡ ከዚያ ደግሞ ልጁን ስትወልደው ባዶነት ይሰማታል፡፡ ምክንያቱም ተዋህዷት የነበረውን አዲስ ህይወት ከውስጧ አጥታዋለች፡፡ ይሁን እንጂ ያጣችው ተወስዶባት አይደለም፡፡ ልጅ የእሷ በመሆኑ ከወለደችውም በኋላ ለልጇ በምታበረክተው ፍቅር ባዶነቷን መሙላት ትችላለች፡፡ ለአንድ የጥበብ ሰው ግን ይህም የሚቻል አይደለም፡፡ ከዚያም በላይ አስቸጋሪ ነገር ነው፡፡ አንድ መፅሐፍ ተፅፎ ካለቀ በዲላ፣ በቃ አከተመ ፍቅርም እርዳታም አይፈልግም፡፡ እያድግም፡፡ የተወለደው እድገቱን አጠናቅቆ ነው፡፡ አርቲስቱ ወይም ሰዓሊው ግን ስራው ካለቀ በኋላ ባዶነት ይሰማዋል፡፡ ወደዚህ ባዶነት ውስጥ ጠልቆ ስመለከት ይገባዋል፡፡ ደከምኩ ከማለት ይልቅ ወጪ አወጣሁ ማለትን መልመድ ይገባል፡፡ ባዶ ሆንኩ ማለትም አይገባም፣ ምክንያቱም ባዶነቱ በውስጡ ያለለው ምሉዕነት አለ፡፡ ስህተቱ ያለው ምልከታችሁ ላይ ነው፡፡

አንድ ክፍል ውስጥ ስትገቡ ግድግዳው ላይ ስዕሎች ተሰቅለውበት በቁሳቁስ ተሞልቶ ታገኙታላችሁ፡፡ ከዚያ ደግሞ ውስጡ የነበሩት ቁሳቁስ ባጠቃላይ እንዲወጡ ከተደረጉ በኋላ ደግማችሁ ወደዚያ ቤት ቡትገቡ ምን ትላላችሁ? ባዶ ቤት ነው ወይንስ ሙሉ ቤት ነው የምትሉት? ቤት ወይም ክፍል ማለት "ባዶነት" ማለት ነው፣ ክፍል ማለት "ቦታ" ማለት ነው፡፡ ክፍሉ ቁሳቁሶቹ ከወጡ በኋላ ሙሉ ነው፡ ቁሳቁሱ ቦታው በነበሩበት ጊዜ ክፍሉ ሙሉ አልነበረም፡፡ በቁሳቁሱ የተነሳ አብዛኛው "ቦታው" ተይዞ ነበር፡፡ አሁን ይህ ክፍል ጥንቁቅ /ምሉዓ ሆኗል፡፡

ከሁለት አቅጣጫ መመልከት ትችላላችሁ። ቁሳቁስ - ተኮር ከሆናችሁና ከጠረጴዛ፣ ከወንበርና ከሶፋ ሌላ የክፍሉን ክፍልነት መመልከት የማትችሉ ከሆናችሁ፣ እውነትም ክፍሉ ባዶ ይሆናል። ይሁን እንጂ ባዶነትን ፊት ለፊት መመልከት እንደምትችሉ ብታውቁ ኖሮ ከፍተኛ ነፃነት ውስጥ መግባታችሁ ይሰማችኋል። ምክንያቱም ይህ ነፃነት ክፍሉ በቁሳቁስ በተሞላ ጊዜ በቦታው አልነበረም። ነፃነትን ልታስገቡት አትችሉም። እስኪ ቤታችሁን ነጋ ጠባ ቁሳቁስ እያመጣችሁ ድርድሩበት፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ቤታችሁ የእናንተ መሆኑ ያበቃል።

በአንድ ወቅት አንድ እጅግ ባለጠጋ የተባለ ሰው መኖሪያ ቤት ውስጥ አረፍኩ። ሰውየው ሃብታም ይሁን እንጂ ለዛ የሚያውቅ ሰው አልነበረም። መኖሪያ ቤቱ በቅራቅንቦ ከመሞላቱ የተነሳ ከነአካቴው ቤት ለማለትም ያስቸግራል። መንቀሳቀስ አትችሉም፣ ብትፈልጉ እንኳን ውድ ቅርሶቹን ላለመስበር በጥንቃቄ ነው። እሱ ራሱ እንኳን መንቀሳቀስ ያስፈራዋል። በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ካሉት ሁሉ እጅግ ውብ የተባለውን ለማረፊያነት ለቀቀልኝ።

"ይህ ክፍል አይደለም፣ ሙዚየም ነው።" አልኩት። "እባክህ እንደልቤ የምንቀሳቀስበት ሌላ ክፍል ስጠኝ። ይህ ክፍል ሲጠፋ ምንም አልቀረው!"

ክፍል ማለት ባዶ ስፍራ የሚሠጣችሁ ነፃነት ማለት ነው። በስራ እና በፈጠራ ላይ ስትሆኑ አእምሯችሁ በብዙ ነገሮች ይሞላል። አእምሮ ስፍራው ተይዟል። መፅሀፉ ስትፅፉ አእምሮ ተይዟል፣ ስትስሉ አእምሯችሁ ባዶነቱን አጥቷል። ውስጡ በብዙ ቁሳቁስ ታጭቋል። ቃላት፣ ስሜትና ሐሳብ ይተራመሱበታል። ከዚህ በኋላ መፅሐፉ ሲጠናቀቅ ቁሳቁሱ ተወገዱ ማለት ነው። ባዶነት ይሠማችኋል። ዳሩ ግን የምታዝኑበት ምክንያቱ የለም። በትክክል ከተመለከታችሁት፣ ከአንድ ከህሊና የማይወጣ ሐሳብ ወይንም ስራ ተገላግላችኋል። ቡድሃ "ትክክለኛ ዕይታ" ብሎ የሚጠራው ይህንን ነው። ዳግመኛ ንፅህና ከሸክም ነፃ የመሆን መንፈስ ይኖራችኋል። እነዚያ የመፅሐፉ ቃላት መተራመሳቸውን አብቅተዋል፣ እንግዶቹ ተስተናብረው ሔደው አስተናባሪው እፎይ ብሏል። በዚህ መደሰት ነው! ከተዛባ ዕይታችሁ የመነጨው ትርጓሜ ነው ሃዘንንና ፍርሃትን እየፈጠረባችሁ ያለው። አስተውላችሁ ከሆነ እንግዳ ቤታችሁ ሲመጣ ደስ ይላችኋል፣ ሲሄድ ደግሞ የበለጠ ደስ ይላችኋል። አሁን የራሳችሁ ብቻ የሆነ ቦታ አላችሁ።

መፅሐፍ መድረስ ግን የባሰ ነው፣ መክንያቱም ብዙ ገፀ-ባህሪያት በእንግድነት ይመጣሉ። ሁሉም እንግዳ የየራሱ ባህሪይ አለው። ፀሃፊው የሚለውን የሚሠማ ገፀ-ባህሪይ የሚገኘው አልፎ አልፎ ነው። ስለዚህ ይህን መሠል እንግዳ ፀሃፊውን ባልፈለገበት አቅጣጫ ይመራዋል። ከዚያ ፀሃፊው ፅሁፉን ይጀምራል እንጂ በፍፁም አይጨርሰውም። መፅሐፉን የሚያጠናቅቁት እነዚያ ገፀ-ባህሪያት በራሳቸው ነው።

ልክ ህፃን ልጅ እንደመውለድ ነው:: ልጅ መውለድ ይቻላል፣ ግን ልጅ በራሱ ጊዜ መንቀሳቀስ ይጀምራል:: እናቲቱ ልጄ ዶክተር ይሆንልኛል ብላ ታስብ ይሆናል፣ ልጁ ግን አድጐ እንባ ጠባቂ ከሆነ፣ ምን ይደረጋል?

ልብ-ወለድ ስትፅፉም የሚፈጠረው ይኸው ነው:: አንድ ገፀ-ባህሪይ ትፈጥሩና ቅዱስ አድርጋችሁ ልትስሉት ስትጀምሩ፣ እሱ ግን ነፍሰ-በላ ጨካኝ እየሆነባችሁ ይመጣል:: ልክ እናቲቱ እንደምትጨነቀው ደራሲውም ይጨነቃል:: ገፀባህሪው ባልቀደሳት መንገድ ሲሄድበት ማድረግ የሚችለው ነገር የለም:: የገፀ-ባህርያቱ መጠቀሚያ የሆነ ያህል ይሠማዋል:: በመጀመሪያ የዓይነ-ህሊናችን ውጤት ቢሆኑም በኋላ ግን አብረዋችሁ ሲቆዩ እውን እየሆኑ ይሄዳሉ:: ከህሊናችሁ ካላወጣችኋቸው በስተቀረ እረፍት አይሠጧችሁም:: ህሊናችሁ ውስጥ መፅሃፍ ካለ፣ ካልተፃፈ በስተቀር ልታስወግዱት አትችሉም::

ለዚህ ነው የፈጠራ ሰዎችን ብዙ ጊዜ ወደአብደት ሲያመሩ የምናያቸው:: ተራ ሰዎች በፍፁም አይቀውሱም:: የሚያስቀውሳቸው ነገር የለም:: እነቫንጐግ እና እነእቼ ግን ያብዳሉ:: ለምን? ህሊናቸው በብዙ ነገሮች ከመጠመዱ የተነሳ በውስጣቸው የራሳቸው የሆነ ቦታ የላቸውም:: ዘወትር በትራፊክ የተጨናነቀ አውራ-ጐዳና ላይ ከመቀመጥ የተናነሰ ህይወት የላቸውም:: እያንዳንዱ አርቲስት የዚህ አባዜ ሰለባ ነው::

መፅሐፍ ተደርሶ ሲያበቃ እና ልጅ ሲወለድ ደስ እንዲላችሁ አስታውሱ፣ በተፈጠረው ባዶ ስፍራ ተደሰቱ፣ ወደሌላ መፅሐፍ ልትሸጋገሩ በመሆኑ ደስ የበላችሁ:: ቅጠሎች ከዛፍ እንደሚወለዱ ሁሉ ግጥሞችም ከገጣሚ ስዕሎች ከሰዓሊያን ይወለዳሉ:: ተፈጥሮ በመሆኗ ሊደረግ የሚችል ነገር የለም::

ስለዚህ አንዳንዴ በበልግ ወቅት ዛፎች ቅጠሎቻቸውን እራግፈው እርቃናቸውን ቆመው ስትመለከቱ ደስ ይበላችሁ:: ባዶነት ብላችሁ አትሰይሙት፣ አዲስ አይነት ምልዐት ብላችሁ ጥረት:: ምይውም ተሞይውም እናንተ ናችሁ:: ጣልቃ የሚገባ ምንም የለም፣ በራሳችሁ ውስጥ እረፍት እየወሰዳችሁ ነው:: ይህ የእረፍት ጊዜ ለማንኛውም አርቲስት አስፈላጊ ነው:: ተፈጥሮአዊ ሂደት በመሆኑ ነው:: ዳግም ከመፀነስ በፊት የማንኛውም እንስት አካል እረፍት ይሻል:: ያለማቋረጥ ያለእረፍት ስትወልድ የኖረች ሴት ገና በሳሳ እመት እድሜዋ ታረጃለች:: ከመገላገል በኋላ እረፍት ያስፈልጋል:: ልጅየው አንበሳ የሚሆን ልጅ ከሆነ ደግሞ የበለጠ ረጅም እረፍት ያስፈልጋል:: አንበሳ የምትወልደው አንድ ብቻ ነው::

ምክንያቱም አንበሳን ለማርገዝ ሙሉ ማንነቷን ይጠይቃል:: ከወለደ በኋላ ሃይሏን ለማሰባሰብ ረጅም እረፍት ትወስዳለች:: እናንተም ጥሩ ነገር ከወለዳችሁ በኋላ ሌላ ጥሩ ነገር ለመውለድ በመካከሉ ረጅም እረፈት መውሰድ የኖርባችኋል::

የፈጠራው ጥልቀትና ረቂቅነት በጨመረ መጠን የሚሰማችሁ ባዶነትም የዚያኑ ያህል የሳቀ ነው፡፡ ልክ ከከባድ ዶፍ ዝናብ በኋላ እንደሚነግሰው ሃያል ፀጥታ፡፡ ይህንን ፀጥታ አጣጥሙት፡፡ ያለፈው ዶፍ ዝናብም ሆነ እሱን ተከትሎ የመጣው ፀጥታ መልካም ናቸው፡፡ ቀኑ በድርጊቶች የተሞላ ውበት አለው፣ ግን ደግሞ ለሊቱም እንደዚያው ውብ ባዶነትና ፀጥታ አለው፡፡

ስሜቱ ሊያስፈራችሁ አይገባም፡፡ ብዙዎቻችን ከንዋኔ የሌለበት ባዶ የለሊት ፀጥታ ያስፈራናል፡፡ ጭለማ፣ ሁሉን ተወት አድርጐ ዘና ማለት፣ እጅ ሰጥቶ ለሚሆነው ሁሉ መንበርከክ ያስፈራናል፡፡ ምሉዕና ጥንቁቅ ስንሆን የምንችለው ግን ምሽቱንም በእሙኔታ ስንቀበለው ነው፡፡ ስለዚህ በተሳሳተ ገፅታው ልንገነዘበው አይገባም፡፡ ባዶነት ውብ ነው፣ እንደውም ከፈጠራ ቀናቶቻችሁ ይልቅ ውብ ነው፡፡ ምክንያቱም ፈጠራ ራሱ የሚመጣው ከባዶነት ውስጥ ነው፣ እነዚያ አበቦች የፈኩት ከባዶነት ውስጥ ነው፡፡ በዚያ ባዶነት ተደሰቱ፣ ሱራኬውን ተቀበሉ፡፡ ያን ጊዜ ብዙም ሳትቆዩ በሌላ አዲስ ክንዋኔ ተጠምዳችሁ ራሳችሁን ታገኙታላችሁ፡፡ ሊያስጨንቃችሁ አይገባም፡፡ ለአንድ ውብ ክስተት የፈጠራችሁት የተሳሳተ ግንዛቤ ነው፡፡

የሰው ልጅ ግን የሚኖረው ቃላት ውስጥ ነው፡፡ አንድ ጊዜ አንድን ነገር የተሳሳተ ስም ከሰጣችሁት በኋላ ያስፈራችሁ ይጀምራል፡፡ ስትሰይሙ የነገርየውን ስርው-መሠረት አስባችሁ ይሁን፡፡ ዘወትርም የምትናገሩትን አስታውሱ፡፡ ምክንያቱም መናገር፣ መናገር ብቻ ሳይሆን ከማንነታችሁ ጋር ጥልቅ ቁርኝት ያለው ሃይል ነው፡፡ አንድን ኩነት ባዶነት ብላችሁ ባዶነትን አሉታዊ አድርጋችሁ በመሳል ከሰየማችሁት በኋላ፣ ቃሉ ራሱ ያስፈራችሁ ይጀምራል፡፡

ህንድ ውስጥ ለባዶነት የተሻለ ቃል አለን፡፡ "ሽንያ" ብለን እንጠራዋለን፡፡ ይህ ቃል በራሱ አዎንታዊ ቃል ነው፡፡ ገደብ የሌለበት ቦታ ማለት ነው፣ ውብ ቃል፡፡ ታድያ የሰው ልጅን መድረሻና ዋንኛ ግብ "ሹንያ" ብለን ሰይመነዋል፡፡ ቡድሃ እንደሚለው፣ ሹንያ ስትሆኑ፣ ፍፁም ባዶ፣ ባዶነትን ራሱን በምትሆኑበት ወቅት ያን ጊዜ ግባችሁ፣ ላይ ደርሳችኋል፡፡

ገጣሚው፣ ደራሲውና ሰዓሊው ወደመለኮታዊነት ዓለም ጉዞ ላይ ናቸው፡፡ ማንኛውም የአርቲስት ስራ ወደመንፈሳዊነት ጉዞ ላይ ነው፡፡ ገጥማችሁ፣ ደርሳችሁና ስላችሁ ከተገላገላችሁ በኋላ በሚመጣው ባዶነት ውስጥ እረፍት ስታደርጉ፣ ይህንን የባዶነት ቅፅበት ወደራሳችሁ ውስጥ የምትገቡበት ጊዜ አድርጋችሁ ተጠቀሙበት፡፡ ባዶነት ሳይሆን ምልዐት፣ ሁነት (being) ወደ እውነት ብላችሁ ጥሩት፡፡ ፈጣሪ ብላችሁ ጥሩት፡፡ ፈጣሪ ብላችሁ ጥሩት፡፡ ያን ጊዜ ቡራኬው ይደርሳችኋል፡፡

# 4. የገንዘብ ጥበብ

ስለገንዘብ ልትነግረን ትችላለህ? በገንዘብ ዙሪያ ያሉት እነዚህ ሁሉ ሰሜቶች ምንድን ናቸው? ሰዎች ህይወታቸውን እስከመሠዋት ድረስ የሚወስዳቸው ምን ዓይነት ሃይል ቢኖረው ነው?

ይህ በጣም ወሳኝ ጥያቄ ነው።

ሃይማኖቶች ሁሉ ለሃብት ያላቸው አቋም አሉታዊ ነው፣ ምክንያቱም ሃብት በህይወታችሁ ውስጥ በግዢ ልታገኙት የምትችሉትን ነገር ሁሉ ይሠጣችኋል ፍቅርን፣ ርህራሔን፣ ንፁድነትን ወይም ነፃነትን የመሳሰሉ መንፈሳዊ ነገሮችን ካልሆነ በስተቀር ገንዘብ የተቀረውን ሁሉ ማለት ይቻላል፣ ይገዛል። እነዚህ ጥቂት መንፈሳዊ ነገሮች ብቻ ናቸው ይህንን ህግ የሚያፈርሱት። ሃይማኖቶች ሁሉ የህይወት ተቃራኒና ተቃዋሚ የመሆናቸው ሃቅ የገንዘብም ተቃዋሚ ያደርጋቸዋል። የህይወት ህግ ግን፣ ህይወት ገንዘብ ያስፈልጋታል ይላል። ህይወት ምቾት፣ ጥሩ ምግብ ጥሩ አልባሳት እና ጥሩ መኖሪያ ቤቶች ትፈልጋለች። ህይወት ሰፊ ናት!

ታድያ ክላሲካል ሙዚቃ የማይገባው ሰው ደሃ ነው። ደንቆሮ ነው። ቢመረመር የመቅመስ፣ የማሽተት፣ የማየት፣ የመስማት ችግር አይኖርበት ይሆናል፣ ከቁስ ባሻገር ካለው ዓለም አንፃር ግን እውር ነው (metaphysically speaking)። የታላቁ ስነ-ፅሑፍና ስነ-ጥበብ ውበት ይታያችኋል። ካልታያችሁ በቃ ዓይነ-ስውራን ናችሁ። የታላላቅ ስነ-ጥበብን ውበት ለማየት ደግሞ የታረቀ ህይወት ያስፈልጋችኋል።

ክላሲካል ሙዚቃን ለመረዳት የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ ትምህርት ነው ትምህርት ረጅም ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ለመማር ከረሃብ ከጽህነትና ከተለየዩ ዓይነት ከንቱ አመለካከቶች ነፃ መሆን ይገባችኋል።

ለምሳሌ መሃመድ ሙዚቃን የሚከለክል ድንጋጌ አለው። እንግዲህ ሰውን ይህ ነው የማይባል ታላቅ ጣዕም እንዳይቀምስ ከልክለውታል ማለት ነው። ኒውደልሂ ውስጥ እንዲህ ሆነላችሁ ... እሱ ከተባሉት ታላላቅ የመሃመድ ተከታይ ንጉሠ ነገስት መካከል አንዱ የነበረው አውራንግዘብ ስልጣን ላይ የነበረበት ወቅት ነበር። አውራንግዘብ ሃያል ብቻ ሳይሆን ጨካኝም ነበር።

እሱ እስከነገሰበት ጊዜ ድረስ ሁሉም ነገስታት ሙዚቃ የእስልምና ጠላት ናት የበሉ እንጂ ኒውዶልሂ ግን በሙዚቃ እንደተጥለቀለቀች ኖራለች። አውራንግዘብ ግን በቀላሉ የሚያልፍበት ጨዋታነት አልፈጠረበትም። ዶልሂ ውስጥ ሙዚቃ የተባለ፣ ዘፈን የተባለ ነገር ቢሰማ ዘፋኙን ከመቅዕበት አንገቱን እንደሚቀላ አወጀ። ዶህሊ ደግሞ መዓከል ናት፣ ለብዙ አመታት ዋና ከተማ ሆና ቆይታለች። ስለዚህ ብዙ ሰሙጥር ጉብዛዝ የሚኖሩባት ስፍራ ናት።

ከአዋጁ በኋላ ሙዚቀኞች ተሰበሰቡና መከሩ፣ "ይህ ከመጠን ያለፈ ድንጋጌ ነው፣ አንድ ነገር መደረግ አለበት። "እሱ። "ከእስልምና ጋር አይጣጣም ማለት ይሁን። ግን ይህ ሰውዬ አደገኛ ነው፣ ሰው መግደል ይጀምራል።" ይህን ብለው ሲያበቁ፣ ተቃውሞቸውን ለመግለፅ ወደቤተ መንግስት አመሩ። በሺህ የሚቆጠር ብዛት ነበራቸው።

አውራንግዜብ ወደመስኮት ብቅ አለና ጠየቀ። "ማነው የሞተው" ስልፈኞቹ ልክ ህንድ ውስጥ ሰው ሲሞት እንደሚያደርገው ሬሳ ተሸክመዋል። በሬሳ ሳጥኑ ውስጥ ግን የሞተ ነገር የለም። ትራስ ምናምን ሰፍተው ሬሳ አስመስለውት ነበር። ለዚህ ነበር፣ "ማን ሞተ" ብሎ የጠየቀው።

ሰልፈኞቹም፣ "የሞተችው ሙዚቃ ናት። የገደልካትም አንተ ነህ! ይሉታል።

አውራንግዜብም ሲመልስ፣ "እሰዬያው እንኳን ሞተች። እንግዲህ አሁን፣ አንድ ውለታ ዋሉልኝ፣ የምትቀበርበትን መቃብር አርቃችሁ ቆፍሩልኝ፣ ዳግመኛ እንዳትንሰራራ አድርጋችሁ ወደታች ራቅ አድርጋችሁ ቅበሯት። አውራንግዘብ በራሱ ዓይን "ቅዱስ" ያለውን እያደረገ ስለነበር፣ ለዚያ ሁሉ ሰው እንባ ግድ አልነበረውም።

ሙዚቃ ለመሐመድ ተከታዬች ተካልክሏል፣ ለምን? ምክንያቱም ሙዚቃን መጀመሪያ ይጫወቱ የነበሩት የሩቅ ምስራቅ ቆንጆጅት ሴቶች ነበሩ። በምስራቁና በምዕራቡ "የሴተኛ አዳሪ" ትርጓሜ የተለያየ ነው። በምዕራቡ ዓለም "ሴተኛ አዳሪ" የምትሸጠው ገላዋን ነው። በምስራቁ ዓለም ግን የምትሸጠው ብልጠቷን፣ ውዝዋዜዋን፣ ሙዚቃዋንና ስንጥበቧን ነበር።

በጥንት ጊዜ እያንዳንዱ የህንድ ንጉስ፣ ወንበሩን የሚወርሱ ወንድ ልጆቹን ለጥቂት አመታት "ከሴተኛ አዳሪ" ጋር እንዲኖሩ ይልካቸው እንደነበር ብትሰሙ ትደነቃላችሁ። የሚልኳቸው፣ ሙዚቃን፣ ውዝዋዜን ርህራሔን እንዲለማመዱ በማለት ነበር። ምክንያቱም አንድ ንጉስ፣ በሁሉም ረገድ ሃብታም መሆን ይገባዋል። ውበትን፣ ምክንያታዊነትን፣ እና ደንበን መረዳት የኖርበታል። ጥንታዊው የህንድ ባህል ይህንን መስሎ ነበር የቆየው።

የመሐመድ ተከታዬች ይህንን ባህል አደፈረሱት። ሙዚቃ ከሃይማኖታቸው ጋር የማይጣጣም ሆነ። ለምን? ምክንያቱም ሙዚቃ መማር የፈለገ ወደ ሴተኛ አዳሪ መግባት ይኖርበታል። የመሐመድ ተከታዬች የሳቅና የደስታ ተቃዋሚዎች ናቸው። "የሴተኛ አዳሪ" ቤት ደግሞ በሳቅ፣ በሙዚቃ፣ በዜማና በፈንጠዚያ የተሞላ ነው።

ከተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ በሌሎች ሃይማኖቶች ውስጥም ይሄው ሀቅ ጉልቶ ይታያል። በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ ዋንኛው ትምህርት ገንዘብን ማከድ እንደሌለብን ይናገራል።

እሁን ምክንያቱ ታያችሁ? ገንዘብ ከሌላችሁ ሌላ ምንም ነገር ሊኖራችሁ አይችልም፡፡ በቅርንጫፎቹ ፋንታ ችግር ነው ያሉትን ግንድ ከስሩ ቆርጠው መጣላቸው ነው፡፡ ገንዘብ የሌለው ሰው ረሃብተኛና የሚለብሰው የሌለው ለማኝ ነው፡፡ የዶስቶቭስኪንና የአልበርት አንስታይን ስራዎች የሚያነብበት ጊዜ እንዲኖረው አትጠብቁ፡፡ የማይሆን ነገር!

ሃይማኖቶች ሁሉ ሰውን የቻሉትን ያህል እንዲደኸይ አድርገዋል፡፡ ገንዘብን እጅግ በማውገዝ ድህነትን አሞግሰዋል፡፡ እንደኔ እንደኔ በዓለም ላይ ከእነሱ በላይ ወንጀለኛ የለም፡፡

እስኪ እየሱስ የሚለውን እንስማ፡- ባለፀጋ ወደገነት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብትሾልክ ይቀልላታል፡፡ ይሄ ሰውዬ ጤነኛ ይመስላችኋል? ግመልን በመርፌ ቀዳዳ ሊያሾልክ ተዘጋጅቷል ፈፅሞ የማይቻል ነገር ግን ደግሞ ይህ የማይቻል ነገር ሲደረግ እንደሚችል እምኖ ይቀበላል፡፡ የባለፀጋ ገነት መግባትስ? ይህማ ከመጀሪያው የባሰ የማይቻለ ነገር ነው፡፡

ሃብት ይወገዛል፣ ገንዘብ ይወገዛል፡፡ ዓለም በሁለት ጐራ ተከፍላለች፡፡ የዓለም ዘጠና-ስምንት በመቶ ህዝቦች ተፅናንተው በድህነት ይኖራሉ፡፡ ምክንያቱም እነሱ ባለፀጐቹ የማይገቡበት መልዓክት በበገና "እንኳን ደህና መጣችሁ፡፡" እያሉ ወደሚዘምሩበት ስፍራ መግባት ይችላሉ! የተቀሩት ሁለት በመቶ ደግሞ በሃብታምነታቸው ዘወትር የጥፋተኝነት መንፈስ ተጠናውታቸው ይኖራሉ፡፡ በዚህ ጤናማ ያልሆነ ስሜት የተነሳ በሃብታቸው መደሰት አይችሉም፡፡ ገነት መግባት አይችሉማ፡፡ ምድር ላይ ይህን ሁሉ ነገር በማግኘታቸው ገነት የመግባት መብታቸው ተነፍጓል፡፡ ወደገሃነም ይወረወራሉ፡፡

በዚህ የተነሳ ሃብታሞች የሚኖሩት በስጋት ነው፡፡ በሃብታቸው ሲደሰቱ ቢሞክሩ እንኳን የጥፋተኝነት መንፈሳቸው ይመርዘዋል፡፡ ከውብ ቆንጆ ሴት ጋር እንሶላ ቢጋፈፉም የሚያገኙት ገላዋን ብቻ ይሆናል፡፡ ግመል የሚያስገባ የመርፌ ቀዳዳ በር ላይ ነዋ የቆሙት፣ እንዴት ብሰው ይገባሉ፡፡ ይህ ሰው እንዴት ህይወትን በውል ሊያጣጥማት ይችላል? እለ የተባለ ምግብ ቢመገቡም ሊያጣጥሙት አይችሉም፡፡ ከዚህች አጭር ህይወት በኋላ የሚጠብቃቸውን ጭለማና የገሃነም እሳት እያሰቡ እንዴት አይጨነቁ?

ደሃ ግን ቀድሞ ነገር የሚኖረው ገሃነም ውስጥ ቢሆንም መፅናኛ አለው፡፡ የሚገርማችሁ! ከሃብታም ሃገሮች ይልቅ በደሃ ሃገራት የሚኖሩ ህዝቦች የበለጠ ደስ ባሏቸው መኖራቸው ነው፡፡ አሜሪካኖች ግን አንድ የሆነ መንፈሳዊ ፋና ወደ ፍለጋ ሲባዝኑ ይታያሉ፡፡ በግመሉት መበለጥ አይፈልጉማ፣ እነሱም የገነትን በሮች አልፈው መግባት ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ መፅናኛ የሚሆናቸው መንፈሳዊ ነገር ይፈለጋሉ፡፡

ይህ ዓለም ሙሉ በሙሉ በራሱ ላይ እንዲነሳ ተደረገል።

ምናልባት ገንዘብ ያከበርኩ የመጀመሪያው ሰው እኔ እሆናለሁ።

ምክንያቱም ገንዘብ ብዝሀ-እውታራዊ ሃብትን ያጕናፅፋል።

አንድ ድሃ ሰው ሞዛርትን መረዳት አይችልም። ረሃብተኛ ማይክል አንጀሎን ማገናዘብ አይችልም። ለማኝ የቫን-ጉግን ስዕል ሲያደንቅ ይቅርና አይመለከተውም። በረሃብ የሚሠቃዩ ህዝቦች ጥበበኛ የሚያደርግ በቂ ሃይል እንኳን አይኖራቸውም። ጥበብ የምትመጣው ምልቶ ተርፎ የሚፈስስ ሃይል ሲኖረን ብቻ ነው። የድሆች ሃይል ዳቦ ለመግዛት በሚያደርጉት ጥረት ላይ ያልቃል። ጥበብ የላቸውም፣ መረዳት አይችሉም። እንጀራቸውን ትተው የጥበበኞችን ስነ-ጥበብ የሚመረምሩበት ጊዜውም ገንዘቡም ሃይሉም አይኖራቸውም። በየቤተመቅደሳቸው የየአይረቤ ደነዝ ቀሳውስቶቻቸውን ስበካ ከማዳመጥ ሌላ የሚያደርጉት ሌላ ነገር የለም። ቄሱም ራሱ የሚሰብከውን ነገር ምንነት አያውቀውም፣ ምዕመናኑም እንደዚያው። ብዙሃኑ ምዕመን ከስድስት ቀን የእለት ጉርስ ሩጫ በኋላ ደክመው ተኝተዋል። ቄሱ ደግሞ ምዕመናኑ ሁሉ ሲተኙላቸው ደስ ይላቸዋል። አዲስ የሰበካ ርዕስ ከማዘጋጀት ይተርፋሉ። የድሮውን የደገሙላቸዋል። ሁሉም እንቅልፍ ላይ በመሆናቸው እየሸወዷቸው መሆኑን የሚያውቅባቸው የለም።

ሃብት የሙዚቃንና የታላቅ ስነ-ጥበብን ያህል አስፈላጊ ነው። የሙዚቃ ስጦታን ታድለው የተወለዱ ሰዎች አሉ። ሞዛርት ሙዚቃ መጫወት የጀመረው ገና በስምንት አመቱ ነበር። እሱ በስምንት አመቱ ይቀምረው የነበረው ሙዚቃ ሌሎች በጊዜው ታላላቅ የነበሩ የሙዚቃ ቀማሪዎች ጥጉ አይደርሱበትም። እንግዲህ ይህ ሰው ከዚህ ስጦታ ጋር የተወለደ ሰው ነበር። የቪንሰንት ቫን ጉግ አባት በድንጋይ ከሰል ማዕድን ማውጫ ውስጥ የሚሠራ ያጣ የነጣ ድሃ ነበር። አልተማረም፣ የስነ-ጥበብ ትምህርት ቤትን አያውቀውም። ግን ቫን ጉግ የዓለማችን ታላቅ ሰዓሊ ለመሆን በቃ።

ከጥቂት ቀናት በፊት ከስዕሎቹ አንዱን ለማየት ችዬ ነበር። ሌሎች ሰዓሊዎች በዚህ ስዕሉ ተሳልቀውበታል። ለምን? ከዋክብትን ሌሎች ተመልክተውት በማያውቁት መልክ ያስማቋረጥ እየተሽከረከሩ የሚያሳይ ስዕል ነበር የሳለው። ማን እንደዚህ አይነት ስዕል አይቶ ያውቃል? የሚንቀሳቀስ ኮከብ ያለበት!

ሌሎች ሰዓሊዎች ምን አሉት? "አብደሃል እንዴ-እነዚህ ከዋክብት ናቸው ከዚያ ሌላ ደግሞ ከከዋክብቱ በታች የሳላቸው ዛፎች ከከዋክብቱ በላይ ቁመት ነበራቸው። እንዲህ አይነት ዛፍ የት አለ? እብደት ነው! አሉት።

ከቅርብ ጊዜ በፊት ግን ይህንን መሠል ፎቶግራፍ ተመልክ

ቿያለሁ። የፊዚክስ ሊቃውንት አሁን ቫንጎግ እንዳልተሳሳተ ደርሰውበታል። ከዋክብት እንደምንመለከታቸው ሳይሆኑ ልክ ቫን ጎግ እንደሳላቸው ናቸው። ምስኪን ቫን ጎግ! ይህ ሰው ምን ዓይነት ዓይኖች ቢኖረው ነው ሊቃውንት ግዙፍ ቤተ ሙከራዎቻቸውንና ቴክኖሎጂያቸውን ተጠቅመው ከአንድ መቶ አመታት በኋላ የደረሱበትን እውነት፣ ገና ያኔ ሲመለከት የቻለበት? ቪንሰንት ቫን ጎግ በዓይኖቹ ብቻ የከዋክበትን ትክክለኛ ቅርፅ ማወቅ ችሏል። ከዋክብት ባሉበት የቆሙ ነገሮች ሳይሆኑ የሚሽከረከሩ ነገሮች ናቸው።

ስለዛፎቹም፣ "እነዚህን ከከዋክብት ከፍታ በላይ የረዘሙ ዛፎች ከየት አገኘሃቸው?" ብለው ሲጠይቁት። "እነዚህን ዛፎች ያገኘኋቸው ከከዋክበቱ አጠገብ ናፍቆታቸውን ሲያዳምጡ ነው። እነዚህ ዛፎች የምድር ከዋክብቱ ላይ የመድረስ ናፍቆት መሆናቸውን ነግረውኛል።" ብሎ ነበር የመለሰላቸው።

ምናልባት ከተወሰኑ አመታት በኋላ ደግሞ ሊቃውንቱ የምድር ናፍቆት የሆኑ አንዳንድ ዛፎች መኖራቸውን የደርሱበት ይሆናል። ማን ያውቃል? ዛፎችን የመሬት ስበት እንደማይገድባቸው መቼስ ያደባባይ ምስጢር ነው። ምድር ራሷ ከስበቷ በተቃራኒ እንዲያድጉ አቅዳ ደግፋ ትንከባከባቸዋለች። ምድር ከከዋክብቱ ጋር የምትነጋገርበት እንደአንቴና ዓይነት ነገር አስፈልጓት ቢሆንስ? ማን ያውቃል? ምድር ህያው ናት፣ ህይወት ደግሞ ዘወትርም ሽቅብ መውጣት ትወዳለች። ሁሌም ወደላይ ከፍ ከፍ ማለት ደስ ይላታል። ታድያ ይህንን የወሰን የለሽነት ምስጢር ድሆች እንዴት ብለው ይረዱታል። ጥበብ የላቸው።

ልክ ሰዓሊና ገጣሚ ሆነው የሚወለዱ እንዳሉ ሁሉ ሃብት ፈጣሪ ሆነው የሚወለዱ እንዳሉም ልታስታውሱ እሻለሁ። እነዚህ አርቲስቶች አድናቆት ተነፍጓቸው ኖረዋል። ሁሉ ሰው ሔንሪ ፎርድን መሆን አይችልም።

ሔንሪ ፎርድ ድሃ ሆኖ የተወለደና በኋላ ላይ በዓለም ወደር የለሽ ሃብታም ለመሆን የበቃ ሰው ነበር። ገንዘብን መፍጠር ያስቻለው፣ ሃብትን መፍጠር ያስቻለው አንድ ጥበብ ቢኖረው ነው። ሃብትን የመፍጠር ጥበብ ከመድረስና ከመሳል የተናነሰ የፈጠራ ክህሎት አይደለም። ሃብትን መፍጠር ቀላል ስራ አይደለም። ሔንሪ ፎርድ ከአንድ ዝነኛ ሰዓሊ ወይም ሙዚቀኛ ያልተናነሰ ሙገሳ ያስፈልገዋል። እንደውም የበለጠ ሞገስን ይሻል ምክንያቱም በገንዘቡ ሁሉን ዓይነት የስነ-ጥበብ ጥሙን ማርካት ይችላል።

እኔ ለገንዘብ ክብር አለኝ። ገንዘብ ከሰው ልጅ የፈጠራ ውጤቶች መካከል ከዋንኞቹ ይመደባል። አድራጊ ነው። የሚኮንኑት ራሳቸው ፋይዳ የሌላቸው ሰዎች ናቸው።

ገንዘብ ነገሮችን የመለዋወጫ ሳይንሳዊ መንገድ ነው። ገንዘብ ከመፈጠሩ በፊት ሰዎች ትልቅ ችግር ውስጥ ነበሩ። በዓለም ባጠቃላይ ንግድ ልውውጥ የሚካሄደው ቁስን በቁስ በመቀየር ነበር። ለምሳሌ ፈረሱን ሸጦ ላም መግዛት የሚፈልግ ሰው ላሙን ሸጦ ፈረስ መግዛት የሚፈልግ ሰውን ፈልጐ ማግኘት ነበረበት። ይህ የህይወት ዘመንን ሊፈጅ የሚችል ፍለጋ ነው። ስለዚህ ሰዎች የግድ ድህነት ውስጥ ይገቡ ነበር። መግዛትና መሸጥ ያልቻለ ሰው ድሃ መሆኑ አይቀርም። ኋላ ገንዘብ መጣና ነገሮችን አቀለለላቸው።ላሙን መሸጥ የፈለገ ፈረስ የሚሸጥ ፍለጋ ከተማውን አያስስም። ቢቃ ገበያ ወጣ ብሎ ላሙን ሸጦ ይመለሳል።

ገንዘብ የመገበያያ መንስኤ ሆነ። ገንዘብ ለሰው የጠቀመውን ያህል ሌላ የጠቀመው ነገር የለም። የበለጠ ሃብታም እንዲሆን አድርጐታል። ይህን መረዳት የኖርብናል። ገንዘብ የበለጠ በተንቀሳከሰ መጠን የበለጠ ገንዘብ ያመጣል። ለምሳሌ አንድ ዶላር ቢኖረኝ፣ ለምሳሌ ነው እንኳን ዶላር ሳንቲም አልይዝም፣ ኪስ እንኳ የለኝም። ግን እንበልና ቢኖረኝ፣ አንዱን ዶላር ዝም ብዬ በኪሴ ባስቀምጠው ምንም አይጠቅመኝም። አንድ ነገር ብገዛበት ግን በገዛሁበት ነገር የማገኘው ደስታ ይኖራል። ብር አይበላም። ስለዚህ ገንዘብ ይዞ ቁጭ የማይል ሰው በጨመረ ቁጥር የአንድ ህዝብ ሀብት ከፍ ይላል። ገንዘቡ ቶሎ ቶሎ ይንቀሳቀሳል። ራሱን ያበዛል። ገንዘብን ይዛችሁ በመቀመጥ ጊዜውን አታጥፉበት እንዳገኛችሁት አውጡት፣ አንቀሳቅሱት። የበለጠ ይዞ ይመጣላችኋል።

ገንዘብ ዕፁብ ፈጠራ ነው። ሰዎችን የበለጠ ሃብታም ያደርጋል፣ የማያገኙትን ነገር እንዲያገኙ ዕድል ያመጣላቸዋል። ሃይማኖት ግን የገንዘብ ተፃራሪ ነው። የሰው ልጅ ሃብታም እንዲሆን አይፈልግም። ሃይማኖተኞች የሰው ልጅ የማስተዋል ዓይኑ እንዲበራ አይፈልጉም። ማን መፅሃፍ ቅዱስ ያነብላቸዋል?

እኔ ወደየትኛውም ሃይማኖታዊ ስፍራ አልሄድም። ለምን እሄዳለሁ? የቤተ መቅደሱ አስተዳዳሪዎች ሃይማኖታዊ ነገር ሊያስተምሩኝ ከፈለጉ ወደእኔ መምጣት አለባቸው። መካ አልሄድም፣ መካ ነው እኔ ዘንድ መምጣት ያለበት። እየሩሳሌም አልሄድም፣ አላበድኩም። ያለንበት ስፍራ ፍቅርንና ደስታን ማምጣት እንችላለን። እስራኤል ምን አለ? አዲሲቷን እስራኤል ፈጥረናታል።

ስለገንዘብ የጣሉባችሁን የተሳሳቱ አመለካከቶች ሁሉ ወዲያ ጣሉ። ገንዘብን አክብሩት። ሃብትን ፍጠሩ፣ ምክንያቱም ብዙ አውታሮች ሊከፈቱላችሁ የሚችሉት ገንዘብንና ሃብትን ከፈጠራችሁ በኋላ ብቻ ነው።

# ፍጥረት

## የፈጠራዎች ሁሉ ራስ - የሕይወት ትርጉም

ሕይወት በራሱ ምንም ትርጉም የለውም። ሕይወት ለሕይወታችን ትርጉም የመስበሻነትን የተሰጠን ዕድል ነው። የሕይወት ትርጉም ተፈልጎ የሚያረሰበት ሳይሆን የሚፈጠር ነው። ለሕይወታችሁ ትርጉም የምታገኙለት ስትፈጥሩት ብቻ ነው። የሕይወት ትርጉም ቀስ በቀስ ፈልጋችሁ እንደምታገኙት የተሸሸገ ነገር አይደለም። የሚገጠም ግጥምና የሚቃኝ ዜማ ነው። የሚዘመር መዝሙር የሚደነስ ዳንስ ነው።

ትርጉም ቅኔያዊ ውዝዋዜ እንጂ ቋጥኝ አይደለም። ትርጉም ሙዚቃ ነው። የምታገኙት ስትፈጥሩት ብቻ ነው። ስታስታውሱት።

በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ትርጉም የለሽ ሕይወት እየኖሩ ያሉት በዚሁ የሕይወት ትርጉም ተፈልጎ የሚገኝ ነው በሚለው የተሳሳተ አመለካከት የተነሳ ነው። ልክ ዕንድ ስፍራ ላይ ተቀምጦ የሚጠብቃቸው ይመስል። ከእናንተ የሚጠበቀው ነገር ቢኖር መጋረጃውን በመግለጥ ማስተዋል ብቻ ነው! ከዚያ ትርጉሙን እናገኘዋለን ብላችሁ ታስባላችሁ። ግን እንደዚያ አይደለም።

ስለዚህ አስታውሱ፣ ቡድሀ ትርጉምን ያገኘው ስለፈጠረው ነው። እኔም ያገኘሁት ስለፈጠርኩት ነው። ፈጣሪም ፍጥረት እንጂ አንድ ነገር አይደለም። በአንድ በተለየ ቦታ ቅርፅ ይዞ የሚገኝ ነገር አይደለም። የሚያገኙትም የሚፈጥሩ ብቻ ናቸው። ትርጉምም ቢሆን በተለየ ሥፍራ ላይ የተቀመጠ፣ የሚገኝ ነገር አይደለም። አለመሆኑም መልካም ነው፣ ቢሆን ኖሮ አንድ ሰው ፈልጎ ያገኘውና የሌሎቻችንን ፍለጋ ፍሬ አልባ ያደርገዋል።

በኃይማኖታዊ ትርጓሜ እና በሳይንሳዊ ትርጓሜ መካከል ያለው ልዩነት አይታያችሁም። የአንፃራዊነትን ፅንሰ ሀሳብ የደረሰበት አልበርት አንስታይን ነው፤ ታዲያ እናንተ ይህንን ጽንሰ ሀሳብ ደግማችሁ ደጋግማችሁ ልትደርሱበት ትችላላችሁ? አስፈላጊም አይደለም። አንድ ሰው ደርሶበት ካርታውን ሰጥቷችኋል። ለእርሱ ብዙ ዓመታት ፈጅቶበት ሊሆን ይችላል። እናንተ ግን በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ትደርሱበታላችሁ። ዩኒቨርስቲ ሄዳችሁ የአንድ ሰዓት የአንፃራዊነት ፅንሰ-ሀሳብ ትምህርተ በሚሰጥበት የፊዚክስ ክፍለ ጊዜ መገኘት ትችላላችሁ።

ቡድሃም የደረሰበት ነገር አለ። ዛራቱስትራም እንደዚያው የደረሰበት ነገር አለ። የእነሱ ግኝት ግን ከአልበርት አንስታይን ግኝት የተለየ ነው። ግን

የዛራቱስትራን የማኘት ካርታ በመከተል ብቻ ልትደርሱብ የምትችሉት ነገር አይደለም፡ ፡ የዛራቱስትራ ማኘት ላይ ለመድረስ ዛራቱስትራን መሆን ይጠበቅባችኋል፡፡ አሁንስ ልዩነቱ ታያችሁን!

የአንፃራዊነትን ፅንሰ-ሀሳብ ለመረዳት የግድ አልበርት አንስታይን መሆን የለባችሁም፡፡ በጭራሽ፡፡ በቃ መጠነኛ የመረዳት ብቃት ካላችሁ ፅንሰ-ሃሳቡን መረዳት አይከብድም፡፡ የመጨረሻ ደነዝ ካልሆናችሁ በስተቀር ይህንን መረዳት አይቸግራችሁም፡፡

ዳሩ ግን የዛራቱስትራን ትርጉም ለመረዳት ግን በቃ የግድ ዛራቱስትራን ሆናችሁ መገኘት ይኖርባችኋል፡፡ ዳግመኛ ልትፈጥሩት ግድ ይላችኋል፡፡ እያንዳንዱ ግለሰብም እምላክን መውለድ ይኖርበታል፡፡ እያንዳንዳችን በወሊድ ምጣችን ስቃይ ውስጥ ማለፍ ይጠበቅብናል፡፡ እያንዳንዳችን ፅንሱን በማህፀናችን ተሸክመን ከደማችን እየመገብን ልንከባከበው ይገባል፡፡ ማኘቱ ላይ የምንደርሰው ያን ጊዜ ብቻ ነው፡፡

በሕይወት ውስጥ ምንም ዓይነት ትርጉም ማየት የማትችሉ ከሆነ በቻልታ ተቀምጣችሁ ይህ ትርጉም እስኪመጣ ድረስ እየጠበቃችሁት ማለት ነውና መቼም አታገኙትም፡፡ ያለፉት ዘመናት ሃይማኖቶች ያነገቡት ይህንን ሀሳብ ነበር፡፡ ትርጉሙ ቀድሞ ነገር እዚሁ ነው የሚል፡፡ ግን እዚህ አይደለም! ነፃነት የሚመጣው ሲፈጠር ነው፡፡ ኃይል የሚመጣው ሲፈጠር ነው፡፡ ዘሩን ዘርተን ምርቱን የምንሰበስብበት መሬት ብቻ ነው ያለው፡፡ ፈረሱም ሜዳውም ተሰጥቶናል፡፡ ዳሩ ግን የሕይወት ትርጉም የሚመጣው ሲፈጠር ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ነው የሕይወትን ትርጉም መፍጠር ታላቅ ደስታን የሚያመጣው፡፡ ታላቅ ሐሴትን፡፡

ስለዚህም ከሁሉ በፊት ኃይማኖት የፈጠራ ውጤት መሆን ይገባዋል፡፡ እስከአሁን ድረስ ኃይማኖት እጅግ ቸልተኛ እና ምንም ፍሬ የሌለው ሆኖ ኖሯል፡፡ ከዚያ ሰው የሚጠበቀው መፆም! ዋሻ ውስጥ ተቀምጦ መዋል ማለዳ ተነስቶ ፀሎቱን ማድረስ እና እነዚህን የመሳሰሉ አይረቤ ፍሬ-ከርስኪ ነገሮችን ማድረግ ነው፡፡ እናንተም በዚህ ተግባሩ ተቃውሞ የላችሁም! ምን እያደረገ ነው? እናንተ ሰወራት በፆም ሲሰነብት አድናቆታችሁን ትለግሱታላችሁ፡፡ ምናልባት እኮ ይህ ሰው በራሱ ላይ ስቃይን በማድረግ የሚረካ ይሆናል፡፡ በቆፈን ውስጥ እርቃኑን ስለተቀመጠ ታደንቁታላችሁ፡፡

ዳሩ ግን ትርጉሙ ምንድነው? እንስሶች ሁሉ እርቃናቸውን በቀዝቃዛ በረዶ ላይ ይኖራሉ! ግን ፃድቃን አይሆኑም፡፡ ወይ ደግሞ በቃጠሉ ፀሀይ ንዳድ ውስጥ ተቀምጦ ስታገኙ ታደንቁታላችሁ፡፡ «እያችሁ! ታላቁ ፃድቅ ሰው ይሄውና» ትሉታላችሁ፡፡ ግን ምን እያደረገ ነው? ለዓለም ያደረገው አስተዋፅኦ ምንድን ነው? ለዓለም ምን ዓይነት ውበት አበርክቷል? ዓለምን ትንሽ ትንሽ እንኳን ለውጧታል?

ዓለምን ትንሽ የሚፈጠች፣ በተሻለ ውብና አንፀባራቂ አድርጓታል? አይ፣ እናንተ እነዚህን ጥያቄዎች አትጠይቁም።

አሁን ግን እኔ የምነግራችሁ እነዚህ ጥያቄዎች መጠየቅ እንዳለባቸው ነው። አንድ ሰው ውብ ሃውልት ሲቀርፅ አድንቁት አወድሱት። ውብ ሙዚቃን የቀመረን ሰው አድንቁት። ውብ ዋሽንትን ዜማን ሲጫወት ያዳመጣችሁትን ሰው አወድሱት። ከአሁን በኋላ ኃይማኖታዊ ባህሪያት የሚባሉት እነዚህ ሊሆኑ ይገባል። እንከል አልባ አፍቃሪያንን አወድሱ፣ ምክንያቱም ፍቅር ኃይማኖት ነው። በእሱ የተነሳ ዓለም በበለጠ ሞገስን አግኝታ ከሆነ፣ ይህንን ሰው አወድሱት፣ ያምን፣ ዋሻ ውስጥ ተደብቆ ራስን ማግለልን ወይንም የሾሉ ሚስማሮች በተንጠንጠቡበት አልጋ ላይ መተኛትን የመሳሰሉ ፍሬ-የለሽ ነገሮችን መርሳት አለብን። አበቦችን የሚያፀድቅን ሰው አምልኩት፣ ምክንያቱም ዓለም በዚህ ሰው የተነሳ በበለጠ አሸብርቃለች። ያን ጊዜ ለሕይወት ትርጉም ታገኙታላችሁ። ትርጉም የሚመነጨው ከፈጣሪነት ነው። ኃይማኖት አሁን ካለው በተሻለ ቅኔያዊ እና በበለጠ ተፈጥሮአዊ ውበትን የተጎናፀፈ ሊሆን ይገባል።

ሁለተኛው ጉዳይ አልፎ አልፎ እንደሚታየው የሕይወትን ትርጉም የምትፈልጉት ቀድሞ ነገር መደምደሚያ ላይ ከመድረሳችሁ የተነሳ ነው። ቀድሞ ነገር ምን ዓይነት ትርጓሜ እንደምትፈልጉ ወይንም የተደበቀውን የሕይወት ትርጉም ምንነት ወስናችሁ ተቀምጣችኋል። ከድምዳሜ በመነሳት የምትፈልጉትን ነገር ማግኘት ግን አትችሉም።

መጠይቃችሁ / መጠይቁ ንፁህ መሆን አለበት። መጠይቁ ንፁህ መሆን አለበት ስል ምን ማለቴ ነው? ከድምዳሜ ነፃ መሆን አለበት ማለቴ ነው። እንዲህ ቢሆን ነው የሚል ግምት ያዘለ መሆን የለበትም። የምትፈልጉት ምን ዓይነት ትርጉም ነው? አንድ የተወሰነ ትርጓሜን ለማግኘት በሚል ፍለጋ ውስጥ ገብታችሁ ከሆነ አታገኙትም። ምክንያቱም ገና ከመነሻው «የምፈልገው ምንድነው?» የሚለው ጥያቄያችሁ ተበክሏል፣ ንፁህ አልነበረም።

ለምሳሌ አንድ ሰው ወደእኔ መናፈሻ መጥቶ መናፈሻዬ ውስጥ እንቁ አገኛለሁ ብሎ ቢያስብ፣ መናፈሻዬ ውብ ሊሆን የሚችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው። ታዲያ እንዳሰበው ሳይሆን ቀርቶ እንቁ ሳያገኝ ቢቀር የመናፈሻው ትርጉም አይታየውም። መናፈሻዬ ውስጥ ብዙ ውብ አበቦች እና የሚዘምሩ አዕዋፍ አሉ። መናፈሻዬ በቀለማት ያሸበረቀ ውብ ከመሆኑ ሌላ የንፋሱ ሽውታና የተፈጥሮ መስህቡ ባጠቃላይ የመንፈስ ምግብ ነው። ይህ ሰው ግን በልቡ ያሰበው ነገር ስላለ መናፈሻዬ ትርጉም አይሰጠውም፣ ምክንያቱም እንቁውን ማግኘት አለበት። ለእሱ ትርጉም የሚሰጠው እንቁውን ማግኘቱ ብቻ ነው። ትርጉም ያጣለት ቀድሞ ሀሳቡ ተስፋ ያደረገው ነገር ስለነበረው ነው።

ጥያቄያችሁ ንፁህ ይሁን። ምንም ዓይነተ የተወሰነ ግምታዊ ሃሳብ አይኑራችሁ እርቃናችሁን በንፅህና ሁኑ። ክፍትና ባዶ ሁኑ። እንድ ሳይሆን እንድ ሺህ እንድ ትርጉም ታገኙለታላችሁ። ያን ጊዜ እያንዳንዱ ነገር ትርጉም ይሰጣችኋል፡ ፡ በፀሀይዋ ብርሃን ውስጥ የሚያንፀባርቅ ባለቀለም ድንጋይ ሊሆን ይችላል። ወይ ደግሞ ዙሪያው በቀስተ ደመና የሸበረቀ እንድ ዘለላ የጤዛ ጠብታ ይሆናል፣ ወይንም በንፋስ ሽውታ ጎንበስ ቀና የምትል ውብ አበባ … ምን ዓይነት ትርጉም ነው የምትፈልጉት?

መደምደሚያ ላይ ደርሳችሁ አትጀምሩ፣ ከጀመራችሁ ግን ጅምራችሁ በራሱ ስህተት ነው። ሳትደመድሙና ቀድማችሁ የምታገኙትን ሳትወስኑ ጀምሩ። እውነትን ማግኘት ከፈለጋችሁ ስለምታገኙት ሳታስቡ ሂዱ። የምታገኙትን ሳታውቁት ሂዱ።

ጎልድስቲን የተባለ ሰው በሕይወቱ ዝነኛ ቲያትር ቤት ረግጦ የማያውቅ ሰው ነበር። ለልደት በዓሉ ልጆቹ በስጦታ መልክ የቲያትር ቤት ትኬት ሰጡት።

በዝግጅቱ ማግስት ሊጠይቁት ይመጡና ‹‹እንዴት ነበር?›› ብለው ይጠይቁታል። ‹‹አይ ተውት እባካችሁ›› ሲል ይመልስላቸዋል።

‹‹የረባ ነገር የለውም። እሱ ፈቃደኛ ሲሆን እሷ ፈቃደኛ አትሆንም። እሷ ፈቃደኛ ስትሆን እሱ ፈቃደኛ አይሆንም። ልክ ሁለቱም ፈቃደኞች ሲሆኑ መጋረጃው ተዘጋ።››

እንግዲህ እንድ የተወሰነ ግጥም ካላችሁ ቤቃ እየፈለጋችሁት ነው ማለት ነው። ከዚህ የአእምሮ ጠባብነት የተነሳ ከምትፈልጉት ሌላ ልታገኙት የምትችሉት ነገር ሁሉ ታጡታላችሁ። ትርጉም መፈጠር ይኖርበታል። ትርጉም መፈለግ ያለበት ቀደም ተብሎ ምንም ዓይነት መደምደሚያ ላይ ሳይደርስ ነው። የምትፈልጉትን ቀድማችሁ መገመት ወይ ማወቅ በምታቆሙበት ጊዜ ሕይወት በድንገት ታሸበርቃለች፣ ህልም እውን የሚሆንበት ዓለምን ትፈጥርልናለች። ዳሩ ግን እናንተ ዘወትር የየቅዱስ መፅሐፎቻችሁን፣ የመፅሐፎቻችሁንን የፅንሰ ሀሳቦቻችሁን፣ የቀኖናዎቻችሁን፣ የፍልስፍናዎቻችሁን . . . ቅራቅንቦዎች እንደተሸከማችሁ እየኖራችሁ ነው። በእነዚህ ውስጥ ገብታችሁ ጠፍታችኋል። ሁሉም ነገር ተደበላልቆ ምን እንደሆነ እንኳን ማስታወስ አትችሉም።

አእምሯችሁ ውዥንብር ውስጥ ነው። ተዝረክርኳል። ስለዘህ ልታፀዱት ይገባል! ባዶ አድርጉት። ከባዶው አእምሮ የበለጠ አእምሮ የለም። ባዶው ህሊና የሰይጣን መናኸሪያ እንደሆነ የሚነግሯችሁ ሰዎች የራሳቸው የሰይጣን ሉሌዎች ናቸው። ከባዶ አእምሮ ይልቅ ለፈጣሪ የቀረበ ምንም የለም። ሰይጣን ያለሀሳብ ምንም ማድረግ አይችልም። ወደባዶነት የሚገባበት ምንም መንገድ የለውም።

በሕሊና ውስጥ የተደበላለቁ ብዙ ሀሳቦች ሲኖሩና ከተለያዩ ምንጮች ያደመጣችኋቸው ብዙ የተለያዩ ሀሳቦች ሲደበላለቁ፣ ግልፅ ነገር ይጠፋል። ለማስታወስ ትሞክራላችሁ፣ ምክንያቱም እንድታስታውሱ ተነግሯችኋል። «አትርሱ!» ተብላችኋል። እንደ እውነቱ ከሆነ ችግሩ ማስታወስ ያለመቻላችሁ ነው። ብዙ ነገሮችን ዘንግታችኋል። ብዙ ነገሮችን በራሳችሁ ማምት አክላችሁበታል፣ ሞልታችሁበታል።

አንድ አሜሪካን እየጎበኘ የነበረ እንግሊዛዊ በተገኘበት ግብዣ ላይ፣ የግብዣው አስተናባሪ በሚከተለው ሁኔታ መልካም ምኞቱን ሲገልፅ ያዳምጣል፡-

«የሌላ ወንድ ሚስት በሆንችው በእናቴ እቅፍ ውስጥ ላሳለፍኳቸው ጣፋጭ የሕይወቴ ጊዜያት ፅዋዬን አነሳለሁ።»

«የአምላክ ያለህ፣ ይህ እፁብ ድንቅ አነጋገር ነው!» ሲል እንግሊዛዊው ለራሱ ያስባል። «ሃገሬ ስገባ እኔም እጠቀምበታለሁ።»

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ወደ ኢንግላንድ ተመልሶ በአንድ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ምሳ ግብዣ ላይ ይገኛል። ከአሜሪካ ይዞት የመጣውን አባባል በኩራት ሙክ ብሎ በመናገር የመልካም ምኞት ፅዋውን ያነሳል።

የግብዣው እድምተኛም በዝምታ ተናጋሪውን በንቀት ሲመለከተው ጥቂት ሰከንዶች ያልፋሉ። ከተናጋሪው አጠገብ የተቀመጠ ወዳጁ ሁኔታውን በማስተዋል «ቶሎ ብለህ ማለት የፈለግከውን ብታብራራ ሳይሻል አይቀርም» ይልና ሹክ ይለዋል።

«የአምላክ ያለህ!» ይላል ይህን ጊዜ፣ ተናጋሪው። «ይቅርታ ልታደርጉልኝ ይገባል። የውቢቱን ሴት ስም ሳልጠቅስላችሁ ቀረሁ። ረሳሁት መሰል።» በማለት ራሱን ያርማል።

እየሆነ ያለው ይህ ነው። ይህን ታስታውሱታላችሁ፣ «ፕሌቶ ራስህን እወቅ» ማለቱን ላለትዙ የተናገረውን «ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን፣ መሀመድ ያለውን . . . ሁሉ ታስታውሱታላችሁ። ሌሎች ብዙ ነገሮችን ታስታውሳላችሁ። እነዚህ ሁሉ ተደበላልቀውባችኋል። በራሳችሁ የተናገራችሁት አንድም ነገር የለም። የራሳችሁ የሆነ የምትናገሩት ከሌላችሁ የሁሉም ትርጉም ሊገባችሁ አይችልም። ይህንን ሁሉ እውቀት ተውትና በበለጠ የፈጠራ ክህሎት ይኑራችሁ። አስታውሱት እውቀት የሚቃረም ነገር በመሆኑ ለእውቀት ፈጠራ አያሻውም። ክፍት መሆን ብቻ እንጂ ሌላ ምንም አያስፈልጋችሁም። የሰው ልጅ ግን ተመልካች ብቻ ሆኗል። ጋዜጣ ማንበብ፣ መፅሐፍ ቅዱስ ማንበብ፣ ፊልም ቤት ገብቶ ፊልም መመልከት ወይ በቀን ለሀያ ቴሌቪዥን ላይ ማፍጠጥ አለዚያ ደግሞ ሬዲዮ ማዳመጥ ወዘተ. . .

አራት ሰዓት ያለምንም ድርጊት ተመልካች ሆኖ ይውልና ያድራል። ሌሎች ያደርጋሉ የሰው ልጅ ግን፣ በቃ ማየት ብቻ።

በማየት ትርጉም አታገኙም። አንድ ሺህ አንድ ፍቅረኞች ፍቅር ሲሰሩ ስትመለከቱ ውላችሁ ብታድሩ የፍቅር ትርጉም አይገባችሁም። በማየት ብቻ ያንን የእርካታ ደስታ ወይም እፎይታ ትርጉሙን ልታውቁ አትችሉም። እንዲገባችሁ ያንን የእርካታ ደስታ ወይም እፎይታ ትርጉሙን ልታውቁት አትችሉም። እንዲገባችሁ ተሳታፊ መሆን ይኖርባችኋል። ትርጉም የሚገኘው ከተሳትፎ ነው። በሕይወት ውስጥ ተሳተፉ! የሕይወት ትርጉም በሕይወት ውስጥ ከመሳተፍ ይገኛል። የተቻላችሁን ያህል ሁሉ ጥልቅ የሕይወት ተሳትፎ ይኑራችሁ። ለተሳትፎ ስትሉ የራሳችሁ የሆነውን ሁሉ ለመሰዋት ወደኋላ አትበሉ። የጭፈራን ምንነት ለማወቅ ብትሹ ጭፈራ ለማየት አትሂዱ ከዚያ ይልቅ ጭፈራ ተማሩና ዳንሰኛ ሁኑ። የትኛውንም ነገር ቢሆን ለማወቅ ብትሹ ተሳትፎ አድርጉ!

አንድ ነገር ጠንቅቆ ለማወቅ እውነተኛው እና ትክክለኛው መንገድ ይህ ነው። ይህንን መንገድ ከተከተላችሁ ሕይወታችሁ ትርጉም ይኖረዋል። ያውም ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን ከብዙ አቅጣጫዎች። በትርጉሞች ትጥለቀለቃላችሁ።

ሕይወት ባለብዙ ዘርፍ መሆን ይኖርበታል። ከሕይወት ትርጉም የሚገኘው ያን ጊዜ ብቻ ነው። ሕይወትን ፈፅሞ አንድ አውታራዊ አታድርጓት። ይህም ቢሆን ሌላ ችግር ነው። አንድ ግለሰብ ተምሮ መሃንዲስ ይሆንና ከዚያ በኋላ ሁሉን ነገር የጨረሰ ይመስለዋል። በመሃንዲስነት ይታወቃል። ከዚያ ቀጣዩን ሕይወቱን በሙላ «መሃንዲሱ» እየተባለ ሲኖር ያሳልፋል። ሕይወቱን ሙሉ ከመሃንዲስነት ሌላ ምንም ዓይነት መታወቂያ አይኖረውም። ዳሩ ግን ሌሎች በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማራጮች ቢኖሩትም እሱ ግን አንድ መንገድ ብቻ ተከትሏል። ይደበታል፣ ይሰለቻል። የሚኖረው የግዱን ስለሚሆን ሞትን ከመጠበቅ ሌላ ዓላማ አይኖረውም። ታዲያ ይህን ከመሰለ ሕይወት ምን ትርጉም ይገኛል?

ለሕይወት አሁን ካላችሁ የበለጠ አትኩሮትና ጉጉት ልትሰጧት ይገባል። ዘወትር ሥራ ጉዳይ ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ አልፎ አልፎ መዝናናት ተገቢ ነው። ዶክተር ወይ መሃንዲስ፣ ርዕሰ መምህር ወይ ፕሮፌሰር ብቻ አትሁኑ። የተቻላችሁን ያህል ሁሉ ብዙ ነገሮችን ለመሆን ጣሩ። ቼዝ ተጫወቱ፣ ቫዮሊን ተጫወቱ፣ መዝሙር ዘምሩ፣ ቅኔ ተቀኙ፣ አማተር ፎቶግራፍ አንሺ ሁኑ፣ ወዘተ። በሕይወት ውስጥ ማድረግ የምትችሏቸውን ሁሉ እየፈለጋችሁ ተሳተፉ፣ አድርጉ። ያን ጊዜ ሀብትና ፀጋ ይሞላላችኋል። የሕይወት ትርጉምም ቢሆን የፀጋና የመንፈሳዊ ሃብት ውጤት ነው።

*ስለፈላስፋው ሶቅራጥስ ያደመጥኩትን ከፍተኛ ትርጉም ያለው አንድ ታሪክ ልንገራችሁ።*

*ሶቅራጥስ ወህኒ-ቤት ውስጥ ሞቱን እየተጠባበቀ ሳለ ዘወትር አንድ ሕልም ያልም ነበር፡፡ ሕልሙም ‹‹አንተ ሶቅራጥስ ሙዚቃ ቃምር!›› እያለ የሚወተውተው ድምፅ ይሰማል፡፡ ታዲያ ሶቅራጥስ ወትርም ቢሆን በፍልስፍናው ለሥነ-ጥበብ አስተዋፅኦ እያደረገ መሆኑ ይሰማው የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ከሕልሙ ውትወታ በመነሳት ተረቶችን ወደ ግጥም ለመቀየር፣ ለአፖሉ ክብር እንጉርጉሮን ለመድረስ እና ዋሽንት ለመጫወት ቢቃ፡፡*

*ሰው ከሞት ጋር በሚጋፈጥበት ወቅት ፍልስፍና እና ሙዚቃ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ይሆናሉ፡፡ ሶቅራጥስም በሞቱ ጊዜ እንኳን ፀጋን ሳይነፈግ በሃሴት ኖሮ ያለፈ ሰው ሆነ፡፡*

ሶቅራጥስ ከዚያ ቀደም ዋሽንት ተጫውቶ አያውቅም፡፡ ከውስጡ ‹‹አንተ ሶቅራጥስ ሙዚቃ ተጫወት! የሚል ድምፅ ባይወተውተው ኖሮም ሶቅራጥስና ሙዚቃ ሳይተዋወቁ በቀሩ፡፡ በሞት ጥላ ሥር ግን ተገናኙ፡፡ ይደንቃል! የማንነት አንድ አካል ገና ከተኛበት አልነቃም ነበር፡፡ ሶቅራጥስን የመሰለ ሰው እንኳን አንድ አውታራዊ ሆኖ ሊቆይ ይችላል፡፡ ቆይቷልም፡፡ ሌሎች የሕይወት አውታሮችን የተነፈገው ማንነቱ ግን፣ ‹‹ሉጂክን ተወት አድርገው! ደሞ ወደሙዚቃው ግባና ሞክረው፣ ትወደዋለህ፡፡ ሙዚቃ ሕይወትህን ሚዛናዊ ያደርግልሃል፡፡ እስቲ አገባውን ተወውና ዋሽንት ተጫወት፡፡›› እያለ ይወተውተዋል፡፡ ታዲያ ይህ ከራሱ ውስጥ የሚያዳምጠው ድምፅ እያየለና እየፀና ከመቆየቱ የተነሳ፣ ሶቅራጥስ ለድምፁ እጁን መስጠት ግድ ሆነበት፡፡

ተከታዮቹ ሁኔታውን እንቆቅልሽ ሳይሆንባቸው አልቀረም፣ ‹‹ሕበደ እንዴ? ሶቅራጠስ ከመቼ ወዲህ ነው ዋሽንት መጫወት የጀመረው? ሳይሉ አልቀረም ይሆንም ይሆናል፡፡ ለእኔ ግን ድርጊቱ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ የተጫወተው ሙዚቃ ዕፁብ ድንቅ የሚባል ላይሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ከዚህ ቀደም ሙዚቃ ተጫውቶ ስለማያውቅ ልምድ አይኖረውም፡፡ ሙዚቃው ጥዑም ባይሆንም የተደፈነ መንፈሱን አብርቶለታል፡፡ የአንድ አቅጣጫ ጉዞ ብቻ ያለው ሰው መሆኑም እዚህ ላይ አከትሟል፡፡ ምናልባትም በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የልቡን ፍላጎት እውን አድርጓል፡፡ በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ለምን እንዳደረገው ምክንያት ሊያቀርብለት የማይችለውን ነገር አደረገ፡፡ በሌላው ጊዜማ ያለምክንያት የሚኖር ሰው አልነበረም፡፡

ባለፈው ምሽት ባልሺ ስለተባለው ታላቅ መንፈሳዊ ሰው ታሪክ እያነበብሁ ነበር፡፡

ቀኑ ዓውደአመት ነበር፡፡ ታዲያ በሐሲድ እምነት መሠረት በዕለቱ ምዕመናን ከመንፈሣዊ መሪያቸው ጋር በአንድ ላይ ተሰብስበው ፀሎት ያደርሳሉ፡፡ ከምዕመናን አንዱ ወደ እምነት ሥርዓቱ የመጣው የአእምሮ ዝግመት ካለበት ወንድ ልጁ ጋር

በመሆን ነበር። ልጁ በሰዎች መሃል ያልተገባ ነገር እንዳያደርግ በሚል ያለማቋረጥ በዓይናቹ ይቆጣጠረዋል። የፀሎት ክፍለ-ጊዜው እንዳበቃ ልጁ አባቱን፣ ‹‹ፊሽካ አለኝ፤ በፊሽካዬ መጫወት እችላለሁ?›› ሲል ይጠይቀዋል።

አባቱም ሲመልስለት፣ ‹‹በፍፁም አይቻልም - ፊሽካህ ያለው የት ነው?›› ሲል መልሶ ይጠይቀዋል። ይህን ያለው፣ ልጁ ያለእሱ ፈቃድ ፊሽካውን አውጥቶ እንዳይነፋው ሰግቶ ነበር። ልጁም ፊሽካውን የያዘበትን ኪሱን ያሳየዋል። አሁን አባቱ ዓይኑን ፊሽካ ያለበት ኪስ ላይ አሳርፎ ቁጥጥሩን ይቀጥላል። ትንሽ ቆይቶ ክብረ በዓሉ በዳንስና በሙዚቃ ሲምንሸነሸ አባትዬው መቆጣጠሩን ዘንግቶ የፈንጠዝያው ተካፋይ ይሆናል። ሐሲዲሞች ጭፈራ የሚወዱ ደስተኛ ሰዎች ናቸው። የአይሁድ እምነት መስህብ እና ውስጣዊ ፍሬ-ነገር ያለውም እሱው ጋር ነው።

ሰዎች ሁሉ በዙሪያው ሲደሰቱና ሲፈነጥዙ ሲመለከት፣ ልጁ ራሱን መቆጣጠር ስላልቻለ ፊሽካውን ያወጣና ይነፋዋል። ይህን ጊዜ ሁሉም ተደናግጠው ፀጥ ረጭ ይላሉ። ባል ሼም ግን ልጁ ወዳለበት በመምጣት ልጁን እቅፍ አድርጎ፣ ‹‹ፀሎታችን ተሰምቷል! ይህ ፊሽካ ባይኖር ኖሮ ሌላው ነገር ሁሉ ፋይዳቢስ ነበር። እዚያ ስፍራ ላይ በራሱ ጊዜ ያለማንም ጥረት የተከሰተ ነገር ቢኖር ይህ የፊሽካ ድምፅ ብቻ ነው፣ ሌላው ነገር ሁሉ የተለመደ የክብረ-በዓላችን አካል ነው።›› ሲል ተናገረ እላችኋለሁ።

የእናንተ ሕይወትም ከሙት ብሄል ያልዘለለ እንዲሆን አትፍቀዱ። በዚህ ምክንያት ተፈጠሩ ተብለው ለመዝለኢያቸው ማብራሪያ ማግኘት የማይቻልባቸው ቅፅበታት የሞሉበት ይሁን። ምክንያት ሊታቀርቡላቸው የማትችሉባቸው ጥቂት ምስጢራዊ ነገሮች ይኑሯችሁ። አንዳንዴም ‹‹ትንሽ ያመዋል እንዴ?›› ወይም ‹‹ነካ አእምሮ ያለው ሰው ካለ፣ ይህ ሰው ሞቷል ማለት ነው። በጥቂቱ ግራ የሚጋባ ወጣ ያለ ተፈጥሮ መያዝ ወይንም በሌላ አነጋገር ያለ ይሉኝታ ራስን ሆኖ መገኘት ደስተኝነትን ያመጣል። እስኪ አንዳንዴ ‹‹እብድ›› የሚያስብሉ ነገሮችን አድርጉና የሕይወትን ጣዕም ሞክሩት፣ ያን ጊዜ ሕይወት ትርጉም ይኖራታል።



እብድ ማለት መላውን ዓለም በራሱ ውስጥ ማግኘ
የሚችል ማለት ነው። ተናጋሪ እሱ ነው፣ አድማጪ
እሱ ነው፣ ተዋናዩ እሱ ነው፣ ተመልካቹ እሱ ነው
በቃ ሁሉም እሱ ነው፣ ዓለምን ሁሉ በውስ
ያገኛታል። ራሱን ብዙ ቦታ ከፋፍሎታል። በዚህ የተነ
ሁሉ ነገር ሽርፍራፊ ሆኗል። ሰዎች ዝምታ
የሚፈሩት ለዚህ ነው - ሳያስቡት ሊለፈል
እንደሚችሉ ይታወቃቸዋል። ስለዚህ አንተም ዝም
የሚያስፈራህ ከሆነ፣ ዘወትር ያለማቋረጥ በክንዋ
እንድትጠመድ የሚወተውትህ ቅብጥብጥና ጤ
ያልሆነ አእምሮ አለህ ማለት ነው።

ተቀምጦ ማስቲካ የሚያላምጥ ሰው፣ ምን እያደ
ነው? አንድ ሰው እየገደለ!? በአእምሮው የተሸ
የመግደልና የማጥፋት ፍላጎት አለ፡ ስለዚህ በራ
ምንም ስህተት የማይባል ነገር ያደርጋል፣ ማስ
ያላምጣል። ሌላ ሰውን እየጎዳህ አይደለም፣ ተግባሩ
ለአንተ በጣም አደገኛ ነው። ምክንያቱም የምታደርገው
አውቀህ እያደረግከው አይደለም። ሲጋራ የሚያጠ
ሰው ምን እያደረገ ነው? በትክክል ምን እያደረገ እን
ሳያውቅ፣ ግን ጢሱን እያስገባ ያስወጣል። ተግ
ከሐሰተኛ የእርምሞ ተግባር ጋር ጥብቅ ቁር
አለው። መንፈሳዊ ሰው መቁጠሪያ ይዞ ዶቃዎቹን
በተራ በተመሳሳይ መልኩ እንደሚዳስሳቸው ሁሉ
አጫሽም ጢሱን እንዲ እያስገባ መልሶ በማስወጣ
ተደጋጋሚ ግን ተመሳሳይ ተግባር ይፈጽማ
በማጤሱ ቅኝታዊ ተደጋጋሚነት ያለውና በዚ
ምሕጠት ውስጥ የሚያስገባውን ድርጊት ያከናው
ይህም የውስጡን ቅብጥብጥነት ያበርድለታል።